ስነ ስብከት

ግልጽ እና ቀላል

Preacing: **Pure and Simple**

By Stuart J. Olyott

Translated and Printed by MERF Ethiopia

ማውጫ

መግቢያ

ክፍል አንድ

ስብከት ምንድነው?

ክፍል ሁለት፡- አንድንስብከትን ጥሩ የሚያደርጉት ምንድናቸው?

1. ሥነ-ፍታቴያዊ ትክክለኝነት
2. አስተምህሯዊ ፍሬ-ነገር
3. ግልጽ የሆነ መዋቅር
4. ግልጽ የሆነ አስረጅ ምሳሌ
5. በነጥብ የሚቀመጥ ተዛምዶ
6. ጠቃሚ የሆነ የስብከት አቀራረብ
7. ልዕለ-ተፈጥሯዊ ሥልጣን

ክፍል ሦስት

1. ጥቆማ የተሰጠበት የስብከት አዘገጃጀት ዘዴ
2. በፍቅር የሚታወስ
   ኸግ ዴቪድ ሞርጋን (1928-1992)

መግቢያ

ዩሐንስ በሃያዎቹ የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ እና ጃክ ደግሞ ወደ ኃምሳዎቹ እየተጠጋ ያለ ሰው ቢሆንም ጥሩ ጓደኛማቾች ሆነዋል። በአጎራባች ባለው ከተማ ውስጥ ይሰጡ በነበሩት ወርሃዊ የአሰባበክ ዐውደ-ጥናቶች ላይ እስከተገናኙበት ጊዜ ድረስ አንዳቸው ከሌላቸው ጋር አይተዋወቁም ነበር። እነዚህ ወርሃዊ ስብሰባዎች ለእያንዳንዳቸው አዲስ ጓደኝነትን ጀባ ያሏቸው መሆኑ ብቻ ሳይሆን ለዘላለሙም ለውጠዋቸዋል።

ዐውደ-ጥናቶቹንከመካፈሉ በፊት፣ ጆን መቼም ሰብኮ አያውቅም ነበር። ለረጅም ጊዜ ስለ መስበክ ያስብ የነበረ ቢሆንም እንዴት መጀመር እንደሚችል ግን በእርግጥ ዐያውቅም ነበር። እንደው የሆነ ሆኖ፣ ስብከት ማለት በእርግጥ ምንድነው? በስብከት እና 'በንግግር' መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው? አንዳንድ ስብከት ቀልብን የሚገዙ እና ኃያል ሆነው ሌሎቹ ደግሞ አሰልቺ እና ደረቅ የሚሆኑት ለምንድነው? የጥሩ ስብከት መሠረታዊ ባህርያት ምንድናቸው? ዐውደ-ጥናቶቹ የዩሃንስን ጥያቄዎች ስለመለሱለት በትክክለኛው መስመር ውስጥ አስገቡት። ዛሬ መደበኛ ሊባል በሚችል ድግግሞሽ ይሰብካል፣ ደግሞም ጥሩ መጠን ያለው መንፈሳዊ ሥራ በእርሱ አገልግሎት ውስጥ ተከናውኗል።

የጃክ ታሪክ ከዚህ በእጅጉ የተለየ ነው። ወደ ዐውደ-ጥናቶቹ ከመሄዱ በፊት ከሃያ ዓመታት በላይ ለሚሆን ጊዜ ሲሰብክ የነበረ ሲሆን ከእስከዛሬዎቹ የተሻለ አድርጎ ሊሰብክ እንደሚገባው ይሰማው ነበር። በስብከት ላይ የተጻፉ ጥቂት መጽሐፍትን አንብቦ ያውቃል። የተወሰኑ ሰዎችንም ምክር ጠይቋቸዋል። እንግዲያው ስብከቶቹ የትኛውንም ሰው የማይመግቡ መስለው የሚታዩት ለምንድነው? ገና ጥቂት ደቂቃዎችን ከመስበኩ ሰዎች ዝግ የሚሆኑበት ለምንድነው? ከሁሉ በላይ ደግሞ፣ ከስብከቶቹ በየትኛውም በእርግጥ እንደተለወጡ የሚያውቃቸው ሰዎች በጣም ጥቂት የሆኑት ለምንድነው? ጠሊቅ እፎይታ የሰጠው ነገር ዐውደ-ጥናቶቹ የእርሱን ችግር ነቅሰው የሚዳስሱ በመሆናቸው ነበር። በርካታ ሰዎች አሁን ላይ ጃክ ስለሚሰብከው ኃያል የሆነ የእግዚአብሔር ቃል ጌታን ያመሰግናሉ።

ዐውደ-ጥናቶቹ በእጅጉ መልካም የሚባሉ ርእሰ-ጉዳዮችን ያነሣሉ። እያንዳንዳቸው አንድም አዲስ ነገር የማይናገር የመግቢያ ንግግር ያላቸው ሲሆን፣ ለሌሎች በርካታ ማስተዋሎችን የሰጡ ነበሩ። ይህም ከቤቱ በቀረቡ ጥያቄዎች የታጀበ እና ምሪት የሚደረግበት የግማሽ ሰዓት ውይይት የነበረው ነበር። ይሁን እንጂ እነዚያን ስብሰባዎች የታደሙት እነ ዩሐንስና ጃክ በተደጋጋሚ መለስ ብለው ያመሳክሯቸው እና እራሳቸውን ብቻ ሳይሆን ነገር ግን አንዳቸው ሌላኛቸውን ለመገምገም ይጠቀሙባቸው ነበር። የሰሟቸው ነገሮች ፍሬ-አሳቦች አነስ ባለች መጽሐፍ ውስጥ ሊቀመጥ እንደሚገባው ጠይቀዋል። ስለዚህም ከዚህ በኋላ የቀረበላችሁ እነርሱ ናቸው።

ስቱዋርት ኦሌዮት
ኢቫንጀሊካል ሙቭመንት ኡቭ ዌልስ፣ ብራይንትሪየን፣ ብሪጀንድ
ኖቬምበር 2004

ክፍል አንድ

ስብከት ምንድነው?

አንድ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ አንድ ሣምንት ቢያሳልፍ፣ እና ተጨማሪ አንድ ሣምንት ደግሞ የቤተክርስቲያን ታሪክ ዋና ዋና ክስተቶችን ቢቃኝ ምን ያስተውላል? የሚያስተውለው እግዚአብሔር በዓለም ውስጥ እያከናወነ ያለውን ሥራውን እና ስብከትም በጥልቅ ሁኔታ የሚወደድ መሆኑን ነው። እግዚአብሔር በሥራ ላይ ያለው የትም ቢሆን የት፣ ስብከት የሚያብብ ነገር ነው። ስብከት ዋጋ ባጣበት እና በሚቀርበት ሁኔታ ውስጥ የእግዚአብሔር ጉዳይ ጠባብ በሆነ ጊዜ ውስጥ እንኳን መሄዱ አይቀርም። የእግዚአብሔር መንግሥት እና ስብከት ሲነሡም ሆነ ሲወድቁ አብረው እንደሆኑ ሊለያዩ እንደማይችሉ የተጣበቁ መንትዮች ያክል ናቸው።

ይህ ለእኛ ምን ማለት ነው? እግዚአብሔር እስካሁን ከተደረገለት በላይ ሲመለክ እና ሲወደድ የማየት ከፍተኛ የሆነ መሻት ካለን፣ ስብከት በሚባለው ርእስ ላይ ጥልቅ የሆነ ፍላጎት ይኖረናል። እኛ ራሳችን ብንሰብክም ባንሰብክም እውነት የሚሆን ነገር ነው። የምንሰብክ ከሆንን፣ የተሻለ ልንሰብከው እንፈልጋለን። የማንሰብክ ከሆንን፣ የሚሰብኩትን ለመርዳት እና ለማበረታታት የትኛውንም ነገር ማድረግ እንፈልጋለን።

ስለዚህ ስብከት ምንድነው? ለዚህ ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ መስጠት የሚችሉት በጣም ጥቂት ሰዎች መሆናቸውን ማወቁ ያስደንቃል። ይህም ደግሞ ለአመታት ሲሰብኩ በነበሩት ላይ እንኳን እውነት ሆኖ የሚታይ ነገር ነው። ችግሩ ሰፊ ቍጥር ያላቸው ሰዎች ስለ ስብከት ያላቸውን አሳብ የገነቡት መጽሐፍ ቅዱስን በቅርበት ከማጥናታቸው ሳይሆን ከሰሙት እና ካነበቡት ነገር መሆኑ ነው።

ስብከትን የሚገልጹ አራት የአዲስ ኪዳን ቃላት

አዲስ ኪዳን ስብከትን የሚገልጸው ከስድሳ በሚበልጡ የተለያዩ መንገዶች ሲሆን፣ ነገር ግን ለአራቱ ታላላቄቹ[1] የተለየ ቦታ ይሰጣቸዋል። ስለ እነርሱ በምጽፍበት ወቅት ግሣዊ ቅርጻቸውን እጠቀማለሁ፣ ነገር ግን እንዲሁም ደግሞ በተመሳሳይ የቃሎቹ ቤተሰቦች ውስጥ ያሉ ሌሎች ቃላትንም ታሳቢ አደርጋለሁ። ለምሳሌ፣ *ኬሩሶ*፣ 'መስበክ' የሚለውን ቃል በምጠቀምበት ጊዜ፣ ታሳቢ የማደርገው *ኬሪግማ* 'የተሰበከው መልእክት' የሚለውን ቃል እና *ኬሪክስ* 'ብስራት' የሚሉት ናቸው። ስለዚህ እነዚህን አራት ታላላቅ ቃላትን እንመልከትና ስብከት ምን እንደሆነ እንድንነዘብ ሊረዱን የሚችሉት እንዴት እንደሆነ እንመልከት። ደግሞም ምናልባት አንዳንዶቻችን ራሳችንን ለመደነቅ ማዘጋጀት አለብን!

(ነ) ኬሩሶ

*ኬሩሶ*ከሚለው ቃል በላይ በጣም ጠቃሚ የሆነ ስብከትን የሚገልጥ ቃል የለም። ስብከት የሚለው ቃል በተገለጸ ቀጥር በድንገት ብቅ የሚል እና ከስድሳ ጊዜያት በላይ ጥቅም ላይ የዋለ ነው። ትርጉሙም 'የብስራትን ያክል ማወጅ' እንደማለት ነው። የንጉሥን መልእክት ያመላክታል። ሉዓላዊ የሆነው ለተገዢዎቹ መልእክት በሚኖረው ጊዜ፣ አዋጅን ለሚያውጁት ይሰጣቸዋል። እነዚህ አዋጅ ነጋሪዎች ነገሩን በየትኛውም መንገድ ሳይቀለብሱት ወይም ሳያሻሽሉት እንዳለው አድርገው ያውጁታል። የተሰጣቸውን መልእክት በቀላሉ ያስተላልፋሉ። አድማጮቻቸው እየተቀበሉት ያሉት ይፋዊ የሆነ አዋጅን እንደሆነ ያውቃሉ።

አዲስ ኪዳን ይህንን ግሥ የሚጠቀመው ሰባኪው የገዛ ራሱን ቃሎች እያስታወቀ እንዳልሆነ ትኩረት ሰጥቶ ለማሳወቅ ነው። የሚናገረው ለሌላኛው ሰው ነው። ትኩረቱ በመልእክቱ የተሰጠ መሆኑ ላይ ነው። ሰባኪው በገዛ ራሱ ሥልጣን አይመጣም። እርሱ *ተልኳል* ደግሞም የሚናገረው በላከው አካል ሥልጣን ነው። *ኬሩሶ* ከሚለው ቃል የተገኙት የቃሉ ተወላጆች ጥቅም ላይ

[1]መጀመሪያ ለእነዚህ አራት ቃላት የተሳብኩት የዶ/ር ኤድመንድ ፒ. ክሎውኔ ሥራ ከሆነው *ፕሪቺንግ ኤንድ ቢብሊካል ቲዎሎጂ* (ለንደን፣ ዚ ቲንዳል ፕሬስ፣ 1962)፣ ገጽ 54-9።

የዋሉት የዮናስን ስብከት (ማቴ. 12፡41)፣ የመጥምቁ ዩሐንስን (ማቴ. 3፡1)፣ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን (‘ማወጅ’፣ ሉቃ. 4፡18ለ-19) እንዲሁም የሐዋርያቱን (‘ሰባኪ’፣ 1 ጢሞ. 2፡7፤ 2 ጢሞ. 1፡11)።

(2) ኢዮንጌሊዞ

‘ቱ ኢቫንጀላይዝ’ (በወንጌል መድረስ) የሚለውን የእንግሊዘኛውን ግሥ ያገኘነው ከዚህኛው ቃል ነው። ግሪክኛው ቃል ‘መልካም የምሥራችን ማምጣት’ ወይም ‘መልካሙን የምሥራች ማወጅ’ ማለት ነው። በሉቃስ 2፡10 ውስጥ መልአኩ ‘. . . ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና. . .’ ብሎ ሲናገር፣ የተጠቀመበት ግሥ ይሄኛው ነበር። ነገር ግን ኢዮንጌሊዞ የሚለው ቃል በጣም የተለየ ሌላ ነገር ሆኖ ሳለ ኬሩሶ የሚለው ቃል አንድ ነገር እንዳልሆነ ወዲያውኑ ማስተዋሉ ወሳኝ ነገር ነው። እነዚህ ሁለት ግሦች ስለ ሁለት የተለያዩ ተግባራት የሚናገሩ እንደሆኑ የሚያደርጉበትን አሳብ ብዙ ሰዎች ወስደዋል። በርእሰ-ጉዳዩ ላይ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ሳያጠኑ ይህንን አሳብ ያንጸባርቃሉ። በዚህም መልኩ ስብከትን በተመለከተ በእጅጉ የተሳሳቱ አመለካከቶችን እያዳበሩ ይሄዳሉ።

ሉቃስ 4፡18-19ን በቅርበት ማየት ይኖርብናል። በዚህ ጥቅስ ውስጥ ጌታችን እየተናገረ የነበረው የገሊላ ከተማ በነበረችውና ባደገባት የናዝሬት ምኩራብ ውስጥ ነበር። መልእክቱን የጀመረው ከነብዩ ኢሳይያስ መጽሐፍ በማንበብ ነበር። በመቶዎች ለሚቆጠሩ ዓመታት ስለ አገልግሎቱ ተንብየው የነበሩትን ምንባባት ነበር የመረጠው። በሕዝቡ ፊት ያነበበው በእብራይስጥኛ ስለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለም። ነገር ግን ሉቃስ ነገሩን የመሰከረበት አተራረክ በግሪክኛ የተጻፈ ነበር። በቁጥር 18ሀ ላይ ‘ወንጌልን እሰብክ ዘንድ’ የሚለው አሳብ ኢዮንጌሊዞ በሚለው የግሥ ቅርጽ የተቀመጠ ሲሆን በቁ. 18 ለ እና 19 ላይ ‘እሰብክ’ የሚለው ቃል የተቀመጠው ኬሩሶ በሚለው የግሥ ቅርጽ ነው። ጌታችን አገልግሎቱን ለመግለጽ ሁለቱንም ግሦች ተጠቅሟል። አንደኛውን በማድረጉ ውስጥ፣ ሌላኛውን እያደረገ ነበር። ‘ማወጅ’ የሚለው ቃል ‘ወንጌልን መስበክ’ የሚል ሲሆን፣ ደግሞም ‘ወንጌልን መስበክ’ የሚለው ደግሞ ‘ማወጅ’ ማለት ነው።

‘ወንጌልን መስበክ’ የሚለው ለክርስቲያኖች እንኳን ሳይቀር ሊደረግ ለሚችል ነገር ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል! ለምሳሌ ይህ በሮሜ 1፡15 ላይ ሊታይ ይችላል። አንባቢዎችን ቁጥር 7 ላይ እንደ አማኝ ሰላምታ ከሰጣቸው በኋላ፣ እና

ከቊጥር 8-14 ሌላ አንዳንድ መረጃዎችን ከሰጣቸው በኋላ፣ ጳውሎስ ቀጥሎ ‘ስለዚህም በሚቻለኝ መጠን በሮሜ ላላችሁ ለእናንተ ደግሞ ወንጌልን ልሰብክ ተዘጋጅቼአለሁ’ በማለት ይቀጥላል። ‘ወንጌልን ልሰብክ’ የሚለው መግለጫ ኢዮንጌሊዞ ከሚለው ግሥ የተተረጎመ ነው። ጳውሎስ ወደ ሮም የመጣው ቀድሞውኑም በጌታ ለሆኑት ወንጌልን ለመስበክ ነው! ስብከት ለሚለው ያሉትን የተለያዩ ቃላቶቻችንን እንዴት እንደምንጠቀምባቸው በድጋሚ ለማሰብ ጊዜው አሁን መሆኑ ግልጽ ነው።

(3) *ማርቱሪዎ*

ይህ ግሥ ‘ስለ እውነታዎች መመስከር’ ማለት ነው። ነገር ግን ዛሬ ላይ ክርስቲያን ሰዎች ‘*መመስከርን*’ ሲናገሩ፣ አብዛኛውን ጊዜ ለማለት የፈለጉት ምንድነው? ከጌታ ጋር በተያያዘ ያላቸውን ግላዊ ተሞክሮ በተመለከተ ለሌሎች የተናገሩበትን እነዚያን አጋጣሚዎች ለመግለጥ ቃሉን በተደጋጋሚ ይጠቀሙበታል። *ማርቱሪዎ* የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለው በጭራሽ በዚያ መልኩ አይደለም። በጣም ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውለው በፍርድ ቤት ምስክርነትን መስጠት በሚለው መልኩ ነው። በሌሎች አጋጣሚዎች ደግሞ ጥቅም ላይ የዋለው ስለ አንዳች ነገር ምስክርነትን ለመስጠት የእግዚአብሔርን ስም በመጥራት (ወይም እንደውም ድንጋዮችንም በመጥራት) ነው።ይህ በጥቅሉስለ ግላዊ ስሜት (Subjectivity) ሳይሆን ገሃዳዊነት (Objectivity) ነው፤ ይህም ለሰዎች ስለ እውነታዎች እና ክስተቶች እንጂ ስለ *እኔ* ስሜቶች፣ ወይም *እኔ* ላይ ደርሶብኝ ስለነበረው ነገር የመናገር ጉዳይ አይደለም።

የሰብዐ-ሊቃናት ትርጉም በሚባለው ላይ (ወደ ጥንታዊው ግሪክኛ የተተረጎመው ብሉይ ኪዳን) ጊዜውን ያሳለፈ ማንኛውም ሰው አሁን ያልኩት ነገር እውነት መሆኑን ያውቃል። የአዲስ ኪዳን ጥናት ተመሳሳይ ወደሆነው ድምዳሜ የመጣው በጣም በፍጥነት ነበር። በዩሐ. 4፡39 ላይ ሳምራዊቷ ሴት *ማርቱሪዎ* (‘መመስከር’) የሚለውን ቃል ስትጠቀም፣ የውይይታቸውን ይዘት እየዘገበች ነበር። ሐዋርያው ዩሐንስ *ማርቱሪዎ* የሚለውን ቃል (‘ምስክርነትን መስጠት’) በ1 ዩሐ. 1፡2 ላይ ሲጠቀም ያየውን እና የሰማውን ነገር እየዘገበ ነበር። ጳውሎስ በሐዋ. ሥራ 26፡5 ላይ *ማርቱሪዎ* የሚለውን ቃል (‘መመስከር’) በፍርድ ቤት ውስጥ ምስክርነት እንዲኖርይግባኝ በማለቱ ነበር።

ነገር ግን ይህንን ቃል በማጥናት ውስጥ በተለየ መልኩ ጠቃሚ የሆነ አንድ ምንባብ አለ። ያም ሉቃ. 24፡44-48 ነው። በዚህ ጥቅስ ውስጥ ከሙታን የተነሣው ጌታችን አሁን ማድረግ ያለባቸውን ለደቀመዛሙርቱ እየነገራቸው ነው። በዓለም ዙሪያ ሁሉ እየሄዱ የንስሃ እና የኃጢአት ስርየት ይሰብካሉ (*ኬሩሶ*) ቁ. 47፣ ‘ይሰበካል’)፣ ደግሞም በሚሄዱ ጊዜ ታላላቅ የወንጌል እውነታዎችን ይመሰክራሉ (*ማርቱሪዎ* በሚለው ቃል ተዋረድ ውስጥ የሚገኝ ቃል) (ቁ. 48)። የሚያውጁ፣ የሚመሰክሩ እና ምስክርነትን የሚሰጡ፣ ያውጃሉ። ደግሞም ማቴዎስ 28፡20ን ስንመለከት፣ ይሄኛው ታላቅ ተልእኮ የተሰጣቸው እነዚሁ ሰዎች *እንዲያስተምሩ* (*ዲዳስኮ*) ጭምር ተነግሯቸዋል።

ይህ ሁሉ የሚያመራን ወደየት ነው? *ኬሩሶ* የሚለው ቃል *ኢዮንጌሊዞ* ከሚለው የተለየ እንዳልሆነ ተምረናል። *ኬሩሶ* የሚለው ቃል *ማርቱሪዎ* ከሚለው የተነጠለ እንዳልሆነም ተምረናል። አሁን ደግሞ *ኬሩሶም* ሆነ *ማርቱሪዎ* የሚሉት ቃላት *ዲዳስኮ* ከሚለው አሁን ልንማረው ካለው አራተኛው ታላቅ ቃል የተነጠሉ እንዳልሆኑ ተምረናል።

እነዚህ ቃሎች *በተለዋዋጭነት የሚሠሩ* ናቸው እያልኩኝ እንዳልሆነ እባካችሁን አስተውሉ። እያሳየሁ ያለሁት ከእነዚህ ነገሮች አንደኛቸውን ስንጠቀም ሌሎቹንም እየተጠቀማችሁ እንደሆነ ነው፣ ምክንያቱ ደግሞ ስብከት ማለት እነዚህን ነገሮች ሁሉ ማለት ስለሆነ! ተቻኩለን የማንደርስበት ጠንካራ ድምዳሜ ይህ ነው። ኋላ ላይም በድጋሚ እናሰምርበታለን። በአሁኑ ጊዜ ወደ አራተኛው ቃል እንመጣ ዘንድ ይገባናል።

(4) ዲዳስኮ

ይህ ቃል ‘ሕያዋን እስካሉ ድረስ መልእክቱ ያለውን ትርጉም ተጨባጭ በሆኑ ቃላት *መተርጎም*’ ማለት ነው። *ኬሪግማ* የሚለውን (*ኬሩሶ* በሚለው ቃል ዝርያ ውስጥ ያለውን) *ዲዳኬ* ከሚለው (*ዲዳስኮ* ከሚለው ቃል ዝርያ ውስጥ ካለው) መለየቱ አደገኛ የሆነ ስህተት ነው። ‘በወንጌል መልእክት’ እና ‘በትምህርት መልእክት’ መካከል ግልጽ የሆነ ልዩነት የሚያደርጉ ስፍር ቁጥር የሌላቸው አማኞች በቤተክርስቲያናችን ውስጥ ስላሉ ይህንን ለማድረግ የሞከሩት የነገረ-

መለኮት ትምህርት ዐዋቂዎች ብቻ አይደሉም። ይህንን በተመለከተ በጥቂት ጊዜ ውስጥ የበለጠ ብዙ ነገር እንነጋገራለን።

‘ሕያዋን እስካሉ ድረስ መልእክቱ ያለውን ትርጉም ተጨባጭ በሆኑ ቃላት መተርጎም’ የሚለው እንዲያው ዝም ብሎ በእወጃችን ላይ የምንለጥፈው መፈክር ሳይሆን የምናውጀው የመልእክታችን አንድ አካል እና ጥቅል ነው። ይህ ደግሞ በቀላሉ ሊረጋገጥ የሚችል የሚሆነው የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍን በማንበብ ነው። በሐዋ. ሥራ 5፡42 ላይ ሐዋርያት ኢየሱስ መሲህ እንደሆነ ‘ማስተማር እና መስበካቸውን’ (*ዲዳስኮ* እና *ኢዮንጌሊዞ*) እንዳላቋረጡ እናነብባለን። በሐዋ. ሥራ 15፡35 ላይ ጳውሎስ እና በርናባስ አንዖኪያ ውስጥ የጌታን ቃል ‘ሲያስተምሩ እና ሲሰብኩ’ (*ዲዳስኮ* እና *ኢዮንጌሊዞ*) እንደነበረ እናነብባለን። በሐዋ. ሥራ 28፡31 ላይ ጳውሎስ በሮም የነበረውን ቤቱን ‘ለመስበክ. . . እና ለማስተማር’ (*ዲዳስኮ* እና *ኢዮንጌሊዞ*) እንደተጠቀመበት እናነብባለን። ከግሦቻችን መካከል አንድ ሰው አንደኛውን ሲጠቀም፣ በተመሳሳይ ጊዜ ሌላኛቸውን እየተጠቀመ በሚሆንበት ጊዜ በእስትንፋሰ እግዚአብሔር ለተዘገበው የቃል አጠቃቀም እንስፍስፎች ልንሆን ይገባናል!

ከዚያ በላይ ሊባል የሚገባ ብዙ ነገር አለ። ሐዋ. ሥራ 19፡13ን ከ19፡8 ጋር ካነፃፀርን ጳውሎስ (*ሄሩሶ*) ኤፌሶን ውስጥ ሲሰብክ በነበረ ጊዜ፣ ‘በድፍረት እየተናገረ’፣ ‘አመክንዮታዊነት’ እና ‘ማሳመኛ’ ሲጠቀም እንደነበረ እናያለን። አንድ ሰው በሚያውጅበት ጊዜ፣ ከገለጽናቸው ሌሎች ሦስት ግሦች በእጅጉ በሚልቅ መልኩ እየተጠቀሙባቸው እንደሆነ ሉቃስ በዚህ መንገድ አሳይቷል። ይህንን ሰደድነት ያለውን አሳብ መከተሉ እንዲህ ካለው አነስተኛ መጽሐፍ ያለፈ ጥናት እንድናደርግ ይመራናል። ነገር ግን የሐዋ. ሥራ መጽሐፍን ከመሰናበታችን በፊት ምናልባትም ሐዋ. ሥራ 20፡24-25ን ልንመለከት ይገባናል። እዚህ ጋር ጳውሎስ ለኤፌሶን ሽማግሌዎች የሚያብራራላቸው ወንጌልን በጠንካራ ሁኔታ መመስከሩ (እዚህ ጋር የተጠቀመበት ቃል *ማርቱሪዎ* በሚለው ቃል ዝርያ ውስጥ ያለ ነው) ‘ሲሰብክ’ (*ሄሩሶ*) ሳለ በመከናወን ላይ የነበረ ነገር እንደነበር ነው።

ይህ ለእኛ ምን ማለት ነው

የዛፎቹን እንጨት ባለማየት አደጋ ውስጥ ነን። ለማስቀመጥ እየሞከርን ያለነው እውነተኛ ነጥብ ምንድነው? ይህ ነው፡- አንድ ሰው በሚሰብክበት ጊዜ፣ የሚሰብኩት የትም ሆነ የት፣ የሚናገሩት ለማንም ቢሆን ለማን፣ እነዚህ የጠቀስናቸውን *ሉራቱን ሁሉ* እያደረጉ ናቸው። የጠፉ ለሚባሉት በአዲስ ኪዳን ውስጥ አንድ ቃል ኖሮን ለዳኑት ደግሞ የምንሰብክበት ሌላ ቃል የለም። ሌሎቹ 'የወንጌል መልእክቶች' ተብለው በሚታወቁበት 'የማስተማር መልእክቶች' በማለት የምናውቃቸውን መልእክቶች አናገኝም። አንዳንድ አንባቢዎች ይህንን እውነታ ምኞች የማይሰጥ ሆኖ ያገኙት ይሆናል፣ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ነገር ልንቀለብስ አንችልም። ስብከት፣ *ሁሉም* ስብከት አራቱንም ነገሮች በአንድ ላይ ማድረግን የሚያካትት ነገር ነው።

ይህንን ልናይ ከቻልን፣ በርካታ የእግዚአብሔር ቃል ምንባባት አዲስ በሆነ መንገድ የሚነኩን ናቸው። ለዚህ ጥሩ የሚሆነው ምሳሌ 2 ጢሞ. 4፡1-5 ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ ቀድሞውኑም ጠቃሚ ለሆነ ወጣት ክርስቲያን መሪ ጳውሎስ የመጨረሻውን ቃሎቹን እየጻፈለት ነው። እርሱ ከበድ ሊድርጎ 'ቃሉን ስበክ!' በማለት ያዝዘዋል። ይህንን ሲል እየተጠቀመ የነበረው ቃል *ኬሩሶ* የሚለውን ነበር። ነገር ግን ጢሞቴዎስ ይህንን ማድረግ የነበረበት ለምን ነበር? ምክንያቱ ሊመጣ ያለው ጊዜ ሰዎች ጠንካራ 'ትምህርትን' (*ዲዳስኮ* በሚለው ቃል ዝርያ ውስጥ ያለ ቃል) የሚቃወሙበት እና ለራሳቸው 'አስተማሪዎችን' (*ኩዲዳስኮ* ዝርያ ውስጥ ሌላኛው ቃል) የሚያከማቹበት ስለሚሆን ነው። ግልጽ በሆነ መልኩ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ እየነገረው ያለው ነገር እንዲሰብክ (*ኬሩሶ*) ሲሆን እርሱም ቤተክርስቲያንን የማስተማሪያ (*ዲዳስኮ*) እና ከስህተት የመጠበቂያ አንዱ መንገድ ነው።

ነገሩ ግን ይህ ብቻ አይደለም። ጳውሎስ እንዲሁም ደግሞ ለጢሞቴዎስ የሚነግረው 'ወንጌል ሰባኪነትን' (*ኢዮንጌሊዞ* ከሚለው ቃል ዝርያ የተገኘ ቃል) ሥራው እንዲያደርግ ነው። በእርግጥ ለማለት የፈለገው ጢሞቴዎስ ሲሰብክ (*ኬሩሶ*) ከዚያም የተነሣ ሲያስተምር (*ዲዳስኮ*)፣ እውነተኛው ወንጌል (*ኢዮንጌሊዞ*) ግንባር ቀደም ሆኖ መከናወኑን ማረጋገጥ ያለበት መሆኑን ነው። ስለዚህ በአንድ አንቀጽ ውስጥ የጢሞቴዎስን ተግባር ከሚገልጹት አራት ቃላት ሦስቱን አይተናል። እርሱ እውነተኛ ሰባኪ ከሆነ ከእነዚህ ነገሮች ውስጥ

አንዳቸውን ብቻ አያደርግም፣ ሁሉንም እንጂ። እውነተኛ ስብከት በሚገኝበት ቦታ ሁሉ፣ በአንድ ጊዜ በርከት ያሉ ነገሮች ይከሰታሉ።

ይህንን እውነታ ካልተቀበልን መቼም እውነተኛ ሰባኪዎች አንሆንም። ሁለት ዓይነት የስብከት ዝርያዎች እንዳሉ እናስብ የነበረበትን ሁኔታ ማስወገድ አለብን። እነዚህም የስብከት ዝርያዎች አንደኛው ጌታን ላልተቀበሉ የሚደረግ የወንጌል ስብከት እና ሌላኛው ደግሞ ጌታን ለሚያውቁት ብለን የከፋፈልናቸው ናቸው። ከአሁን ጀምሮ ለጠፉት መስበክ እና ለዳኑት መስበክ ሁለት የተለያዩ ነገሮች እንደሆኑ አድርገን ማሰብን ማቆም አለብን። በስብከት እና በስብከት መካከል ሽብልቅ ልናስገባ አይገባንም። ሁሉም ስብከት ለወንዶች እና ለሴቶች፣ ለወጣት ወንዶች እና ሴቶች የደንነት ዐዋጅ ነው (ቃሉ ካለው የተሟላ ትርጉም አኳያ)። መልእክቱን የሚቀበሉት አድማጮች በስፋት የተለያዩ ሊሆኑ መቻሉ እውነት ነው። ጌታን የማያውቁ አድማጮች እና የዳኑት ተመሳሳይ ፍላጎቶች የሌሏቸው መሆኑም የማይካድ ኃቅ ነው። ስለዚህም ቃሉ ተግባራዊ የሚደረግበት መንገድ ሊለያይ እንዲችል መደረግ ያለበት መሆኑም እውነት የሆነ ነገር ነው። ነገር ግን ላልዳኑት አድማጮች የሚደረገው ስብከት ለዳኑት አድማጮች ከሚደረገው ጋር ሲተያይ የተለየ ባህርይ ያለው ነው። ሁለት የተለያዩ የስብከት ዓይነቶች እንዳሉ መታሰቡ (ደግሞም አንዳንድ ሰዎች በአንደኛው ዓይነት ስብከት ላይ ሊቆች፣ ሌሎቹ ደግሞ በሌላኛው ላይ ሊቆች እንደሆኑ መታሰቡ) በሁሉ ቦታ ያሉት ሰዎች እውነተኛ ስብከት ምን እንደሆነ እንዳይገነዘቡ እያደረጋቸው ነው።

ጥያቄያችን መልስ ሲያገኝ

ስለዚህ ስብከት ምንድነው? ስብከት፣ ሁሉም ስብከት ማለት አራት ነገሮች ማለት ነው፡-

1. ስብከት የሚባለው በንጉሡ የተሰጠውን መልእክት ማወጅ (*ኬሩሶ*) ነው፡- ይህ የሚነግረን ስለ መልእክቱ *ምንጭ* እና ከእርሱም *ጋር* ተያይዞ ስለሚመጣው *ሥልጣን* ነው።
2. ስብከት መልካሙን የምሥራች (*ኢዮንጌሊዞ*) ማስታወቅ ነው፡- ይህ የሚነግረን ስለ መልእክቱ *ጥራት* እና ስለ ተሰጠበት *መንፈስ* ነው።
3. ስብከት ለእውነታዎች ምስክርነትን መስጠት (*ማርቱሪዎ*) ነው፡- ይህ የሚነግረን ስለ መልእክቱ *ተፈጥሮ* እና ስለተገነባበት *መሠረት* ነው።
4. ስብከት ስለ መልእክቱ አንደምታዎች በግልጽ መናገር ነው፡- ይህ የሚነግረን ስለ መልእክቱ *ታላሚዎች* (የሰሚው ጎሊና) እና የስኬቱ *መለኪያ* (የማንኛውንም ሰው ሕይወት ለውጧልን?) የሚለውን ነው።

ይህንን በተመለከተ ነገሩ እስኪገባን ድረስ፣ በጭራሽ ልንሰብክ አይገባንም። ስለዚህም፣ ነገሮችን በተቻለ መጠን ግልጽ ለማድረግ ወደ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ከእኔ *ጋር* ትመጣላችሁን? አንድ ሰው መናገር እስከሚችለው ድረስ፣ በዚያ ብዙ ሰዎች የሉም እነርሱ በሙሉ እውነተኛ አማኞች ናቸው። ለእነርሱ ለመስበክ በምቆምበት ጊዜ፣ ምንድነው የማደርገው?

ከሁሉ አስቀድሞ፣ ለእነርሱ ያለኝን መልእክት ሙሉ ለሙሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ አገኛለሁ። አላሻሽለውም። በቃሉ ውስጥ ንጉሡ የሚለውን አገኛና *ያንን* ለእነርሱ እሰጣቸዋለሁ። *ኬሩሶ* ማለት ያ ነው።

ስለ ኃጢአታቸው ፍርጥ አድርጌ እነግራቸው ይሆናል። ያ መጥፎ ዜና ይሆናል። ነገር ግን በትካዜ እና ተስፋ መቁረጥ ውስጥ አልተዋቸውም። ምንባቡ ወደ ክርስቶስ የሚመራቸው እንዴት እንደሆነ አሳያቸዋለሁ፣ ደግሞም እርሱ ማን እንደሆነ እና ለኃጢአተኞችም ምን እንዳደረገ እነግራቸዋለሁ። ሁሉም ነገር የተባለበትን መንፈስ ይህ የሚነካው ይሆናል። አምልኮ ከማለቁ በፊት፣ ስለ

እግዚአብሔር ጸጋ መልካሙን የምሥራች ይሰማሉ። ኢዮንጌሊዞ ማለት ይህ ማለት ነው።

መልእክቴ እያቀረብኩት ካለው የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ ቀን እና ጊዜያት ይነግራቸዋል፣ ደግሞም በርከት ያለ እውነታ ላይ የተመሠረተን መረጃ ይነግራቸዋል። ይህም መረጃ ስለ ክስተቶች፣ ስለ መልክአ-ምድር፣ ባህል ወይም ማንኛውም ነገር ሊሆን ይችላል። ከሁሉ የሚሻለው ደግሞ በድጋሚ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስጋ ለብሶ መምጣት፣ ስለ ሕይወትና ሞቱ፣ ስለ ትንሣኤውና እርገቱ ታላላቅ እውነታዎችን ቢሰሙ ነው። ውስብስብ በሆነ ዓለም ውስጥ እንዲደነጋገሩ አልተዋቸውም። ይህ *ማርቱሪዎ* ነው።

ደግሞም በቀጥታ ለጎሊናቸው እናገራለሁ። ምንባቡ ምን ማለት እንደሆነ አሳያቸዋለሁ፣ ነገር ግን እዚያ ጋር አልቆምም፤ *ለእነርሱ* ምን ማለት እንደሆነ እነግራቸዋለሁ። ይህ ምንባብ በሕይወታቸው ለውጥ እንዲደረግ እየጠየቀ ያለው በምን መልኩ እንደሆነ ያውቃሉ። በክርስቶስ ስም፣ ንስሃ እንዲደረግ እጎተጉታለሁ። መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ ተግባራዊ መመሪያዎችን እሰጣቸዋለሁ። በስተመጨረሻም፣ ለራሱ ለእግዚአብሔር እንዴት እንደሚመልሱ አስታውሳቸዋለሁ። ይህ *ዲዳሰኮ* ነው።

እሰብካለሁ፣ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል ከእኔ የሚጠይቀውን አራቱንም ነገሮች ሁሉ ማድረግ ስላለብን። ከዚያም ወደ ቤቴ እሄዳለሁ። ነገር ግን ወደ ቤቴ ስሄድ፣ ላይሆን ቢችልም አንድ ጥግ ላይ ሰብስብ ያሉ ታዳጊ ወጣቶችን አያለሁ። እርስዎ ከእኔ ጋር መሆንዎን በማስተዋል፣ ልጆቹን ለማነጋገር እቆማለሁ። መሰላቸታቸውን የሚያሳዩበትን ጋጠወጥነት በጥቂት ደቂቃዎች እንደምንከናነብ ሁለታችንም እናውቃለን። በስተመጨረሻ ልንለው ላለው ነገር ሊሰሙን እንደሚስማሙም ጨምረን እናውቃለን። ስለዚህ ከየት እንጀምራለን?

ለእነርሱ ልንላቸው ያለውን ነገር አንፈለስፍም። በዐይኖቻቸው ፊት የተከፈተ የታተመ መጽሐፍ ቅዱሶች ላይኖሩን ቢችሉም፣ የምንለው ነገር በሙሉ የሚመጣው ከመጽሐፉ ነው። እንደነዚህ ላሉት ወጣት ሰዎች ንጉሡ ሊለው ያለውን ነገር በታማኝነት እናስተላልፋለን። ይህ *ኬሩሶ* ነው።

በእርግጥም ልናተኩርበት የሚገባው በወንጌል ታላላቅ እውነታዎች ላይ ነው። ለእነዚህ ወጣት ሰዎች ስለ እግዚአብሔር፣ ስለሚጠብቅባቸው ነገር፣ ስለ

ልጁ፣ እና ተናዝዘው ሊያምኑ የሚገባቸው ስለመሆኑ እንነግራቸዋለን። ስለ እግዚአብሔር ቍጣ እንነግራቸዋለን። ደስ እያለን ስለ ፍቅሩ፣ ደግሞም በመስቀል ላይ ስላደረገው ነገር እንነግራቸዋለን። እነዚህን ወጣቶች በምናነጋግራቸው ጊዜ እንወድዳቸዋለን። መልእክታችን መልካም የምሥራች መሆኑን ሁሉም ያውቃሉ። *ኢዮንጌሊዞ* ማለት ይህ ነው።

ልንሠራ ከሚገባን ነገር መስመር ለቀን አንወጣም። ስለ እግዚአብሔር መኖር፣ ስለ ኃጢአታቸው፣ ሊመጣ ስላለው ከርስቶስ እና ስለማስታረቁና ትንሣኤው፣ ስለ ዓለም ፍጻሜ እና ወደ እርሱ ለሚመለሱት እግዚአብሔር ቃል ስለገባላቸው ነገሮች እውነታዎችን ሁሉ እንነግራቸዋለን። ይህ *ማርቱሪዎ* ነው።

ልንጠቀም በምንችለው ኃይል ሁሉ መልእክታችንን ከስፍራው እናደርሳለን። አሁን እንዳሉት ሆነው ቢቀሩ ለዘላለም እንደሚጠፉ እናብራራላቸዋለን። ኃጢአታቸውን እንዲናዘዙ እና ወደ ከርስቶስ እንዲመለሱ እናዛቸዋለን፣ እንመክራቸዋለን። ከዚያ በላይ ጠቃሚ የሆነ ምንም ነገር እንደሌለ እንነግራቸዋለን። አሁኑኑ እንዲያደርጉት እንጎተጉታቸዋለን። ይህ *ዲዳሰኮ* ነው።

ስለዚህም በቤተክርስቲያንም ሆነ በአደባባዮች ላይ እነዚህኑ አራት ነገሮች እናደርጋለን - *ኬሩሶ፣ ኢዮንጌሊዞ፣ ማርቱሪዎ* እና *ዲዳሰኮ*። የሰበክነው አንድ ስብከት ብቻ ነው፣ ነገር ግን*ሁለት* ጊዜ እንሰብከዋለን! በሁለት የተለያዩ ሰፋፊ ሁኔታዎች ውስጥ የምንሆን ሲሆን እርሱም አንደኛውን በቤተኞቹ ዘንድ ሆኖ መጫወት እና ሌላኛውን በውጭ። አንዳቸው ለሌላቸው በጣም የተለዩ ለሆኑ፣ ነገር ግን ውስጣዊ የጠለቀ ስሜታቸው አንዳይነት ለሆኑ ሰዎች እንናገራለን። የተለያዩ የተዛምዶ አሳቦችን እናበጃለን። የተለያዩ ውጤቶች ይኖሩን ይሆናል። ነገር ግን የምናደርገው ነገር ሁለት የተለያዩ ነገሮችን *ሉይደለም*። በሁኔታዎቹ ላይ ግዙፍ ልዩነቶች ቢኖሩም ቅሉ፣ በሁለቱም አጋጣሚዎች ላይ *እየሰበክን ነበር*!

የአዲስ ኪዳን ስብከት አንዳንድ ቀጭልፍ ገጽታዎች

እንግዲህ ስብከት ምን እንደሆነ ግልጽ ሆኗል። የምር እየሰበከን መሆን አለመሆናችንን ማወቅ እንድንችል በሚያበቃ መልኩ ስለ ስብከት በቂ ነገር አውቀናል። እንዲሁም ደግሞ ስብከት ሊከናወን ስለሚገባበትም መንፈስ አሁን ላይ አውቀናል። ነገር ግን አዲስ ኪዳን የእውነተኛ ስብከት ሦስት የተለዩ ገጽታዎች አድርጎ የሚያተኩርባቸውን ሳያሳዩ እንዲህ ያለውን የመግቢያ ምእራፍ መዝጋቱ ስህተት ይሆናል።

(ነ) ግዳጅ

የመጀመሪያው ግዳጅ ነው። በሰባኪው ውስጥ ይህንን ሥራ እንዲፈጽም የግድ በማለት የሚያነሣሣው አንዳች ነገር አለ። ከእርሱ ይልቅ ትልቅ የሆነ ውስጣዊ አስገዳጅ ነገር አለ። ሊወጣ የማይፈቅድ በውስጡ ያለ እሳት በልቡ ውስጥ አለ። ያንን በተመለከተ ምንም ሊያደርግ አይችልም። መስበክ ይኖርበታል። 'ወንጌልን ባልሰብክ ወዮልኝ!' በማለት ይጮኻል (ነ ቆሮ. 9፡16)። እንዲያቆም በሚታዘዝ ጊዜ፣ እንደ ሐዋርያቱ ሁሉ 'እኛስ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር ዝም ማለት አንችልም አሉአቸው' ተብሎ እንደተጻፈው ይላል (ሐዋ. ሥራ 4፡20)። 'እርሱም። በዚያ ደግሞ ልሰብክ ወደ ሌላ ስፍራ በቅርብ ወዳሉ መንደሮች እንሂድ ስለዚህ ወጥቻለሁና አላቸው።' (ማር. ነ፡38) በሚልበት ጊዜ ጌታው ምን ማለቱ እንደሆነ ለመገንዘብ የማይቸገርበት መዳረሻውን ለይቶ የሚያውቅ ሰባኪ ነው።

ውስጣዊ ንዝነዛው በማይኖርበት ጊዜ፣ እውነተኛ የሚሆን ስብከት አይኖርም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ የሚያውጅ፣ እውነታዎች ላይ የሚመሰከር እና ኅሊና ላይ የሚያተኩር ሰው *በመኑዳት* የሚሰብክ ሰው ነው። በነፍሱ ጥልቀት ውስጥ እንዲህ ያለው ሰው እግዚአብሔር አሸንፎታል፣ ስለዚህም እያንዳንዱን የንቀሥነቱን ሰዓታት የሚመላለሰው *ጸንደተላከ* በመሆን ነው። ይህ ልምምዱ ጥልቅ ከመሆኑ የተነሣ የሚገልጽበት ቃል እንኳን የለውም። ሊያደርግ የሚችለው የተሻለ ነገር ምንም እንኳን ድምጽ ሰምቶ ወይም ራእይን አይቶ የማያውቅ ቢሆንም ስለ 'ጥሪው' መናገር ነው።

በሁሉም የተለመዱ ሁኔታዎች ውስጥ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን የሰባኪን 'ጥሪ' በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ የምታወቀው በስተመጨረሻ ላይ ነው። ይህኛው እውቅና አብዛኛውን ጊዜ 'ውጫዊው ጥሪ'

በሚል የሚመላከት ነው። ለየትኛውም ሰው ያለዚህ መስበክ ያልተለመደ ነገር ይሆናል። ነገር ግን እንዳንድ ጊዜ ተናጋሪ የሆነችው ቤተክርስቲያን ከሰማይ የተላከውን ሰው መለየት እስከማትችል ድረስ ይህንን መለየት ያቅታታል፣ በእጅጉ ያልበሰለች ትሆናለች፣ በጣም አለማዊነት ያላት እና በጣም ኃጢአተኛ ትሆናለች። በእውነት የተጠራ ሰው በዚህ ምክንያት አይዘገይም። እግዚአብሔር የሰጠው እሳት ከመቼውም ጊዜ በላይ ብሩህ እየሆነ ይቀጣጠላል። ውስጣዊው ጉልበቱ የሚነዳው ይሆናል። ይሰብካል፣ ደግሞም ይሰብካል፣ ከዚያም እንደገና ይሰብካል፣ ምክንያቱም በውስጡ ያለው ግዳጅ አይበገርለትም ደግሞም ሌላ ምርጫ አይተውለትም።

(2) ግልጽነት

ሁለተኛው ቁልፍ ገጽታው *ግልጽነት* ነው። በእርግጥም ይኸው ነው! አዋጆች ሁልጊዜ የሚናገሩት እፊት ለፊታቸው ባለው ሰው ቋንቋ ነው። አስቸጋሪ በሆኑ ቃላት እና ሐረጎች የተጠቀለለ የምሥራች የምሥራች አይደለም። እውነታዎች በግልጽነት የማይቀርቡ ከሆነ፣ ልብ-ወለድ ሊመስሉ ይችላሉ። ደግሞም የትኛውም ነገር ሊገነዘቡት የማይችሉት ከሆነ ጎሊናን ሊነካ የሚችለው እንዴት ነው?

እውነተኛ ሰባኪዎች በግልጽነት የሚሰብኩ ናቸው። የንጉሡን ቃል ያውጃሉ፣ ደግሞም ትኩረቱን ወደ ራሳቸው አይስቡም። የመስቀሉን መልእክት የትኛውም ነገር እንዲያደበዝዘው ወይም እንዲጋርደው አይፈቅዱም። እያንዳንዱ አድማጭ እውነታዎችን መመዝገቡን እና በሚቀርቡበት መንገድ ላይ ምንም የሚረብሽ ነገር አለመኖሩን በማሰብ ይጨነቃሉ። ቀጥሎ ስለሚጠበቅባቸው ነገር ማንም ሰው ጥርጣሬ ውስጥ እንዳይገባ ለማድረግ ቀኖርጠኞች ናቸው።

እውነትን በተመለከተ ግልጽ የሆነ ነገር እንደሚናገር በማድረግ ስብከቱን ሲገልጸው ሐዋርያው ጳውሎስ እየተናገረ የነበረው በዓለም ላይ ለሚገኙ እውነተኛ ሰባኪዎች በሙሉ ነበር (2 ቆሮ. 4፡2)። ‘ለማጥመቅ ክርስቶስ አልላከኝምና፥ ወንጌልን ልሰብክ እንጂ፤ የክርስቶስ መስቀል ከንቱ እንዳይሆን በቃል ጥበብ አይደለም’ (1ቆሮ.1፡17) ባለ ጊዜ ዐቋሙን አስተካክሎ ነበር። አገልግሎቱን የሚገልጽበት ማብራሪያ የሚከተለውን ይመስላል፡-

> እኔም፥ ወንድሞች ሆይ፥ ወደ እናንተ በመጣሁ ጊዜ በቃልና በጥበብ ብልጫ ለእግዚአብሔር ምስክርነቴን ለእናንተ እየነገርሁ አልመጣሁም። በመካከላችሁ ሳለሁ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር እርሱም እንደተሰቀለ ሌላ ነገር እንዳላውቅ ቆርጬ ነበርና። እኔም በድካምና በፍርሃት በብዙ መንቀጥቀጥም በእናንተ ዘንድ ነበርሁ፤ እምነታችሁም በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ጥበብ እንዳይሆን፥ ቃሌም ስብከቴም መንፈስንና ኃይልን በመግለጥ ነበረ እንጂ፥ በሚያባብል በጥበብ ቃል አልነበረም።
>
> (1 ቆሮ. 2፡1-5)

(3) ክርስቶስ-ተኮርነት

ሦስተኛው ቁልፍ ገጽታው ክርስቶስ-ተኮር መሆኑ ነው። እንደዚህ ሊሆን ይገባል። ይህም ሊሆን የሚገባው ሰባኪዎች የቃለ እግዚአብሔር ዐዋጅ ነጋሪዎች ስለሆኑ እና ሁሉም ቅዱሳት መጻሕፍት ደግሞ ስለ ክርስቶስ በመሆናቸው ነው። ግልጽ በሆነ መልኩም ሆነ ባልሆነ መልኩ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ እያንዳንዱ ክፍል የሚጠቁመው ወደ እርሱ ነው። ሊተው የሚችል አንድም ምንባብ በመላው መጽሐፍ ውስጥ የለም።

እያንዳንዳቸውን የብሉይ ኪዳን ጸሐፊያን የጻፉትን ነገር እንዲጽፉ ያንቀሳቀሳቸው ነገር የክርስቶስ መንፈስ ነበር (1 ጴጥ. 1፡10-12)። የብሉይ ኪዳን መጽሐፍትን ለደቀመዛሙርቱ የከፈተው እና በሁሉ ቦታ ላይ የተጻፈው ስለ እርሱ እንደነበረ ያብራራላቸው ራሱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነበር (ሉቃ 24፡25-27፣ 44-48)። አራቱ ወንጌላት እና ሐዋርያት ሥራ፣ ሁሉም መልእክታት እና ራእይ መጽሐፍ፣ እንደ ዋና ርእሰ-ጉዳያቸው የያዙት እርሱን ነበር። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን ስለሚከፍት እና ፊት ለፊቱ ካለው ምንባብ ስለ ክርስቶስ የማይሰብከው ሰባኪን ምን እንለዋለን? እንዲህ ያለው ሰባኪ መጽሐፉን አልተረዳውም፣ ደግሞም መጽሐፉን ካልተረዳው ደግሞ ሊሰብክ አይገባውም!

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ ለገለጣቸው ነገሮች በሙሉ ድምድማቱ እና ማዕከሉ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ የታሪክ ሂደት ሁሉ ትኩረቱ እርሱ ነው። ራሱን ለአእምሯቸው እየገለጠና ከዚያም የተነሣ እንዲጽፉ እየመራቸው በእያንዳንዱ ጸሐፊ ልብ ውስጥ ነበረ። እርሱ በግል ለመስበክ የተላከ

እንደሆነ ለእያንዳንዱ ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ ገጾች በኩል ራሱን ገልጧል። እርሱ አልተሰበከ እንደሆነ በጭራሽ ስብከት የሚባል ነገር አልነበረም ማለት ነው።

ይህ መጽሐፍ እንደዚህ እንዲሆን የተቆረጠው ለምንድነው

ይህን ሁሉ ነገር በአእምሯችን እንደያዝን፣ አሁን ይህ መጽሐፍ ለምን እንደዚህ እንዲሆን እንደተፈለገ ወደምንረዳበት እንሂድ። አሁን ስብከት ምን እንደሆነ አውቀናል። ሦስቱን ቁልፍ ገጽታዎቹን አይተናል። ስለዚህ ይህንን የምናደርገው እንዴት ነው? ደግሞስ ይህንን በጥሩ ሁኔታ እንደምናደርገው እርግጠኞች የምንሆነው እንዴት ነው?

እነዚህን ጥያቄዎች መመለሱ አስቸጋሪ አይደለም። እኛ የንጉሡ ዐዋጅ እና በመጽሐፉ ውስጥ ሊለው ያለው ነገር በሙሉ ነጋሪዎች መሆናችንን ስንመለከት፣ ትርጉሙ ትክክል እንዲሆን ከማድረግ የሚበልጥ ጠቃሚ የሆነ ምንም ነገር ሊኖር አይችልም። ደግሞም ክርስቶስን በዚያ ካላየን ትርጉሙን በትክክል አላገኘነውም ማለት ነው። ስብከት *የሥነ-ፍታቴ (አፈታት) ትክክለኝነት* እንዲኖር ይጠይቃል።

ይሁን እንጂ፣ መጽሐፍ ቅዱስ የተሟላ መጽሐፍ ነው። አሁን ላይ ምንም ነገር በእርሱ ላይ ሊጨመርበት አይችልም። ይህ እውነት ሆኖ እንዳለ፣ ገጾቹን ልናጠና እና ተለይቶ በሚታወቅ ርእሰ-ጉዳይ ላይ የሚለውንም ነገር ለመተግበር እንችላለን። ይህንንም ስናደርግ መላውን የአስተምህሮ ሥርዓቶች እያስተማረ እንደሆነ እናገኘዋለን። የምሰብከው የትኛውም ምንባብ የዚያን ሥርዓት አንድ አካል ይገልጣል፣ ስለዚህም ያ ምን እንደሆነ ለሕዝቡ ልነግራቸው ይገባኛል። ስብከት *ኦሰተምህሯዊ ፍሬ-ነገር* እንዲኖር ይጠይቃል።

ነገር ግን ግልጽነት የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ስብከት ቁልፍ ገጽታ እንደሆነ አልተማርንምን? ልንከተለው አስቸጋሪ ከሆነ እና ለማስታወስም የማይቻል ከሆነ መልእክቱ ግልጽ ነበር ተብሎ ሊጠራ ይችላልን? ስብከት *ግልጽ የሆነ መዋቅር* እንዲኖረው ይጠይቃል። ደግሞም፣ በዚሁ ምክንያት *ግልጽ የሆነ ኦሰረጅ-ምሳሌ* እንዲኖር ይጠይቃል።

በእውነታዎች ላይ የተመሠረተው መልካም የምሥራች የሆነው የንጉሡ ቃል፣ ለጎሊና ሊነገር እንደሚገባው መዘንጋት አይኖርብንም (*ዲዳስኮ*)። እያንዳንዱ ሰሚ ሕይወታቸውን ሊያስተካክሉ እንደሚገባ የሚጎተጉት ነው። ስብከት *የሚጠቅም ተዛምዶ* እንዲኖር ይጠይቃል።

መለኮታዊው መልእክት ወደየት ሊደርስ እንደሚገባው አይታወቅም። በዚህ መንገዱ ላይ ምንም ነገር እንዲገባ ሊፈቀድ አይገባም። ሰባኪው የሚናገርበት ወይም የሚንቀሳቀስበት መንገድ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል ወይም የሚያሰናክል። ስብከት *ሉጋሹ የሆነ አቀራረብን* ይጠይቃል።

ሊዳፈን ከማይፈልገው ውስጣዊ እሳት የተነሣ፣ ሰባኪው በሚሰብክበት ጊዜ በእርግጥም በስሜታዊ ሁኔታ ያቀርበዋል። የንጉሡን ቃል በንጉሡ ስም ይናገራል፣ ነገር ግን ይህንን የንጉሡ ህልውና እና በረከት ሳይኖር ማድረግ አይፈልግም። በእውነተኛ ስብከት ውስጥ ችላ ልንለው የማንደፍረው ገጽታ አለ። ስብከት *ልዕለ-ተፈጥሯዊ ሥልጣንን* ይጠይቃል።

እውነተኛ ስብከትን እውነተኛ የሚያደርጉት ባህርያት እነዚህ ናቸው። አብዛኞቹን ማካተቱ በቂ አይደለም፤ ሁሉም ያስፈልጉናል። እንዲሁም ደግሞ በተቻለ መጠን ይህ መሟላቱን የሚያረጋግጥ ስብከቶችን የመስበኪያ ዘዴ ሊኖረን ይገባል። ስለዚህም መጽሐፉችን የሚያበቃው ለስብከት ለመዘጋጀት የተጠቆሙ ዘዴዎችን በሚዘረዝር ክፍል ይሆናል። ይህም ደግሞ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተዘረዘሩትን መርኾዎች በምሳሌነት ለሚፈጽም ተከትሎ በሚመጣ የአድናቆት መግለጫ የሚዘጋ ነው።

ክፍል ሁለት፡-

አንድንስብከትን ጥሩ የሚያደርጉት ምንድናቸው?

1

ሥነ-ፍታቴያዊ ትክክለኝነት

እንግዲያው ተግባራችን ግልጽ ነው፡- የእግዚአብሔርን ቃል ለማብራራት እና ለማወጅ አፋችንን እንጠቀማለን ደግሞም በፊት ለፊታችን ባሉት ሰዎች ኅሊና እና ሕይወት ላይ እናዛምደዋለን።

ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል የሚገኘው የት ነው? እግዚአብሔር ለወንዶች እና ሴቶች ሊለው ያለው ሁሉ *መጽሐፍ ቅዱስ* እንዲኖር ባደረጉት ቃሎች እና ዐረፍተ-ነገሮች ውስጥ ተጽፏል። እነዚያ ቃሎች እና ዐረፍተ-ነገሮች የታለመ ትርጉም አላቸው። እንግዲያው፣ ምንም ነገር በጭራሽ! ያንን ትርጉም ትክክለኛ አድርጎ የማግኘትን ያክል የበለጠ ጠቃሚ ሊሆን አይችልም። የቃሎቹን እና ዐረፍተ-ነገሮቹን የታቀደ ትርጉም የሚያወጣ ጥናት *ሥነ-ፍታቴ* ተብሎ ይጠራል። የተባለው ነገር በሙሉ *በሥነ-ፍታቴያዊ ትክክለኝነት* ላይ መሠረት ያደረገ ካልሆነ በቀር የትኛውም ስብከት እውነተኛ ስብከት አይደለም።

ከታቀደው ትርጉሙ ይልቅ ቃለ እግዚአብሔር እያለ ያለው የሚመስለንን ነገር መስበክ ኃጢአት ነው። ቃሉ በእርግጥ እያወጀው ካለው ይልቅ ያው ቃል በገዛ አእምሯችን ውስጥ የሚፈጥራቸውን አሳቦች መስበክም የዚያኑ ያክል ኃጢአት ነው። ንጉሡ እያለው ያለውን ነገር *በትክክል* ካላስተላለፈ ዐዋጅ ነጋሪው ባንዳ የሆነ ከሃዲ ነው ማለት ነው።በማኅበረ-ምእመናኑ ፊት ቆሞ "ጌታ እንዲህ ይላል!" ለማለት እና በጌታ ስም እርሱ *ያላለውን* ነገር ለማለት የሚደፍር ሰው ማነው? በስብከት ውስጥ ከሥነ-ፍታቴያዊ ትክክለኝነት በላይ ጠቃሚ የሆነ ነገር ምንም፣ በጭራሽ ምንም! እንደሌለ አሁንም አሁንም ጠበቅ ተደርጎ ሊነገር ይገባዋል።

'ሥነ-ፍታቴ' ሥነ-ፍታቴ የማይሆነው መቼ ነው?

ይሁን እንጂ፣ መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናት ረጅም ጊዜ የሚያሳልፉ ሰባኪዎች ሁሉ ጥሩ የሥነ-ፍታቴ ችሎታ አላቸው ማለት አይደለም። ለአተረጓጎም ትክክለኛ መርኾዎች ጸሎት፣ ጊዜ እና ጥረት አብረው የሚኖሩ መሆን ይኖርባቸዋል። በርካታ እውነተኛ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ሙሉ ለሙሉ በተሳሳተ መልኩ ይገነዘቡታል። ከዚያም ይቆሙና ሰሚዎቻቸውን ወደ ስህተት ይመራሉ። ይህ አይሠራም[2]።

(ሀ) አጉል እምነት (ሱፐርስቲሽን)

ለምሳሌ አንዳንድ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን የሚያጠኑት *በአጉል እምነት* ውስጥ ሆነው ነው። ገጹ ላይ ካሉት ግልጽ የሆኑ የቃሎቹ እና ዐረፍተ-ነገሮቹ ስሜቶች ላይ ትኩረት ከማድረግ ይልቅ፣ ያለማቋረጥ የሚመለከቱት ድብቅ የሆኑ ትርጉሞችን ነው። በእግዚአብሔር ቃል ገጽታ ላይ የተጻፈው ነገር በተለየ ሁኔታ አያንቀሳቅሳቸውም፣ ነገር ግን በዚያ ቦታ ላይ ተራ ሰዎች ሊያዩት የማይችሉትን ጥቂቱን ነገር ሲያገኙ ይደነቃሉ! ለእነርሱ ይህ የእግዚአብሔር ቃል 'መንፈሳዊ' ትርጉም ነው፣ ደግሞም ግልጽ ከሆነው ትርጉሙ ይልቅ የበለጠ ጠቃሚ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስን እንደዚህ አድርገው ከሚያጠኑት መካከል አንዳንዶቹ ለዕብራይስጡ ፊደላት የቍጥር አቻቸውን ለመስጠት ትኩረት የሚያደርጉት ይገኙበታል። አብዛኛው ብሉይ ኪዳን የተጻፈው በእብራይስጥ ቋንቋ ነው። እያንዳንዱ የእብራይስጥ ሆሄያት እንደ ፊደል ብቻ ሳይሆን፣ እንደ ቍጥርም ጭምር ያገለግላሉ። በቃሉ ፊደላት የሚወከሉትን ቍጥሮች እየጨመራችሁ ልታካትቱ እና ለቃሉም ቍጥራዊ ዋጋውን/አቻውን ልትሰጡት ትችላላችሁ። በዐረፍተ-ነገሮችም እንዲሁ ያለ ተመሳሳይ ነገር ማድረግ ትችላላችሁ። ከዚያም በተመሳሳይ የቍጥር ዋጋዎቹ ላይ ሌሎች ፊደላትን ወይም ዐረፍተ-ነገሮችን ልታገኙ እና በዚሁ ልትቀጥሉ ትችላላችሁ። እነዚህ ሁሉ ቍጥሮች በፊት ለፊታችሁ ሆነው እና ጥቂት ምናባዊነት ኖሯችሁ ስታጠኑት ሁሉም ዓይነት ድምዳሜ ሊኖራችሁ ይችላል! 666 የሚል የቍጥር ዋጋ ያላቸውን ቃላት እና ዐረፍተነገሮች ሁሉ ካጠናችሁ በኋላ ለሰዎች ልትሉ የምትችሉትን አስቡ!

---

[2]የዚህ ከፍል አንዳንዶቹ አሳቦች *መሠረት* ያደረጉት የነገረ-መለኮት ተማሪ በነበርኩበት ጊዜ ከዶ/ር ኸርነስት ኤፍ. ኬቫን ከሰማኋቸው ላይ ነው። ከዚያ ገለጻ በከፊል የተወሰዱት ቀደም ሲል የታተሙት ኬቫን፣ ኸርነስት ኤፍ. 'ዚ ፕሪንሲፕልስ ኦቭ ኢንተርፕሪቴትሽን'፣ ኢን ካርል ኤፍ. ሔነሪ (ኤዲተር)፣ *ሬቭሌሽን ኤንድ ዚ ባይብል* (ለንደን፣ ዚ ቲንዳል ፕሬስ፣ 1959)፣ ገጽ 283-98።

ሌሎች ሰዎች ደግሞ የዚህን ያክል ገፍተው አይሄዱም፣ ነገር ግን ተመሳሳይ በሆነ የአስተሳሰብ ሁኔታ ቀጥጥር ሥር የወደቁ ናቸው። በእብራይስጥ ፊደላት ላይ ካልተሳቡ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ የቦታ ስሞች የሚኖሯቸው ትርጉሞች ላይ የሚደነቁ ይሆኑና አብዛኛወንኢ ትምህርታቸውን በዚያ ላይ ይመሠርታሉ። ለእነርሱ፣ ያ ጠቃሚ የሆነና ተራ ሰዎች ሊያዩት ያልቻሉት ትርጉም ነው። 'የሆነ ሆኖ፣ ነ ቆሮንቶስ 2፡14 መንፈሳዊ ነገርን የምንረዳው በመንፈስ ነው' በማለት ይሞግቱናል።

ያህንን ጥቅስ በዚያ መልኩ መጠቀም መቻላቸው የሚያሳየው ምን ያክል ብልሹ የቃሉ ፈቺዎች መሆናቸውን ነው! በዚያ ጥቅስ ውስጥ ጳውሎስ እየተናገረ ያለው ስላልዳኑ ሰዎች ነው። መንፈሳዊ ነገሮችን እንደማይቀበሉ እያስተማረ ነው። ከእነርሱ ጋር በተያያዘ የትኛውንም ነገር አይፈልጉም። መንፈሳዊ ነገሮች ሞኝነት እና የማይመለከታቸው እንደሆነ አድርገው ያስባሉ። ይህም የሆነበት ምክንያት የትኛውም መንፈሳዊ ስሜት ስለሌላቸው ነው። መንፈሳዊ ነገሮችን ማድነቅ ከመቻላችሁ በፊት፣ የባህርይ ለውጥ ሊኖራችሁ ይገባል፣ አዲስ ልብ ልትቀበሉ ይገባል።

ገጾቹን መገንዘብ የሚቻለው በመንፈሳዊ ቁንጮዎች ብቻ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ አያስተምረንም፣ እንዲሁም ደግሞ እውነተኛ ትርጉሙ አብዛኞቹ ሰዎች ሊያገኙት የማይችሉት እንደሆነ ጨርሶ አይናገርም! እውነተኛ የቃሉ ሰባኪዎች አጉል እምነቶች ያሉባቸውን የሥነ-አፈታት አካሄዶች ሁሉ አይቀበሉም።

(ለ) ተለዋጭ ትርጓሜ (አሊጎሪ)

አንዳንድ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን *በተለዋጭትርጓሜው* ያጠኑታል። የአስተሳሰብ መንገዳቸው ቀደም ሲል ካስረዳነው ጋር አንዳንድ ተመሳሳይነት ይኑረው እንጂ ፍጹም አንዳይነት አይደለም። እንደነዚህ አይነት ሰዎች በእውነት የተሳቡት የእግዚአብሔር ቃል ላለው ግልጽ ሥነ-ጽሑፋዊ ስሜት ይሁን እንጂ ሆኖም ግን ከዚያ በተጨማሪነት ፈልገው ሊደርሱበት የተገባ *ተጨማሪ* የሆነ አንድ ነገር አለ ብለው ያምናሉ።

ከቀደምት የክርስትና ቤተክርስቲያን ክፍለ-ዘመናት ጀምሮ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን የሚያጠኑት በተለዋጭ የአተረጓጎም ዘይቤ ነው። ምልክት የሚያደርጉት እንዴት እንደሆነ ለመገንዘብ ምናልባትም *ዮመናኙ ጉዞ* የሚለውን የጆን ቡንያንን ታላቅ መጽሐፍ ማሰብ ይኖርብናል። በዚያ መጽሐፍ ውስጥ ከተለመደው በላይ ትልልቅ ጀብድ የሚያደርጉትን የተለያየ ዓይነት ሚና ያላቸውን ገጸ-ባሕርያት እናገኛለን። ያለ እነርሱ ህልውናውን ስለማያገኝ ገጸ-ባሕርያቱ እና ጀብዶቹ ጠቃሚዎች ናቸው። ይሁን እንጂ፣ በእርግጥም ዋጋ ያለው ነገር የታሪኩ ዝርዝር ሳይሆን ቡንያን ታሪኩን በሚነግረን ጊዜ ያደርሰን የነበረው ነገር ነው። እርሱ የሚያስተምረው እውነቶች ነበሩት። የምንማራቸውን ትምህርቶች አስቀምጦልናል። ዋጋ ያላቸው የሚቆጠሩ ነገሮች እነዚህ ናቸውእንጂ ገጸ-ባህርያቱ እና እነርሱን ለማስተወን ጥቅም ላይ የዋሉት ጀብዱዎቹ አይደሉም።

መጽሐፍ ቅዱስን በተለዋጭ አተረጓጎም መንገድ የሚያጠኑትም ሰዎች የሚያነብቡት በተመሳሳይ መልኩ ነው። የቃላቱ እና ዐረፍተ-ነገሮቹ ግልጽ ትርጉም ጠቃሚዎች ናቸው፣ ነገር ግን ከበስተጀርባው የሚገኙትን እውነታዎች እና ትምህርቶች ያክል ጠቃሚዎች አይደሉም። መጽሐፍ ቅዱስ በትርጉሞች የተሞላ ሲሆን ግልጽ የሆነው ትርጉም የሚገኘው ትንሽ ዋጋ ብቻ ከሚሰጣቸው መካከል ውስጥ ነው።

ይህ አካሄድ የሚያመራው ገደብ ወደማይኖረው ቅዠት እና ዋልጌ ወደሚሆን አተረጓጎሞች ነው። በተለይ ብሉይ ኪዳን ሰባኪው ሊለው የፈለገውን የትኛውንም ነገር እንዲል ተደርጎ የሚሰበክ ክፍል ነው። ይኼኛው የ ‘ሥነ-ፍታቴ’ ዘዴ ኮስታራ የሆነ ጥናትን የሚገድል ነገር ነው። ኃቀኛ አለመሆንን የሚያበረታታ ይሆናል። ኮስታራ የሆነው የሥነ-አፈታት ሂደት የሚጠይቀው አስቸጋሪ የሆነው የትጋት ሥራ ከእይታ እየጠፋ ይሄድና ስብከት የአንድ ሰባኪ የፈጠራ ኃይል የሚታይበት ይሆናል።

አንድ ወቅት ላይ ዘፍጥረት 24 ላይ አስደናቂ የሆነ ስብከት ሰማሁ። ለልጁ ለይስሐቅ ሚስት እንዲያገኝ አብረሃም የታመነውን አገልጋዩን ወደ ሜሶፖታሚያ የላከው እንዴት እንደነበረ ያለውን ታሪክ ሰባኪው ሲናገር በሙሉ መደነቅ ውስጥ ሆኜ የሰማሁት አንደኛው ጥግ ላይ ለሰባ አምስት ደቂቃዎች ቀጭ ባልኩበት ነበር። የስብከቱ ዓላማ አባት ሙሽራይቱን ለልጁ ያመጣት እንዴት እንደሆነ ለእኛ ማሳየት ነበር። በስብከቱ ውስጥ አብረሃም የተካከለው ከእግዚአብሔር ጋር ሲሆን፣ ይስሐቅ ደግሞ ከእግዚአብሔር ልጅ ጋር፣ አገልጋዩ

ደግሞ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር፣ ርቢቃ የተካከለችው ደግሞ ከቤተክርስቲያን ጋር ሲሆን ግመሎቹ የተካከሉት በመንፈስ የምትመራው ቤተክርስቲያን በደህና ወደ መንግሥተ-ሰማይ እንድትደርስ የሚሸከሟት መለኮታዊ ተስፋ ቃሎች በመሆን ነው!

ያንን ስብከት ከሰማሁ አሁን አርባ ዓመታት ሊሞላው ሲሆን ከሞላ ጎደል ስብከቱን ቃል በቃል አስታውሰዋለሁ ማለት እችላለሁ። ልገልጠው ከምችለው በላይ በዋለልኝ የእግዚአብሔር ሰው የተሰበከ ስብከት ነበር። ወደ ጌታው ከሄደ አመታት የተቆጠሩ ቢሆኑም ትዝታውን በጭራሽ ለማደብዘዝ አስቤ አላውቅም። ዘፍጥረት 24ን እያስተማረው ለነበረው አስተምህሮ እንደ አስረጅ ምሳሌ አድርጎ በቀላሉ ተጠቅሞበት ቢሆን ኖሮ ስብከቱ ትክክል በሆነ ነበር። ነገር ግን እንደዚያ አላደረገም። ፈጽሞ የሰጠው ገለጻ ዘፍጥረት 24 *የታሰበው* እግዚአብሔር አብ ሙሽራይቱን ለልጁ ያመጣት እንዴት እንደሆነ ለማስተማር እንደሆነ አድርጎ ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር ያሰበው ትርጉም በጭራሽ እንደዚያ አልነበረም። ደግሞም በመደነቅ መናገር እንዳልችል አድርጎኝ የነበረው ስብከት መጥፎ ስብከት ነበር ብዬ ስናገር በጣም እያዘንኩ ነው።

እውነተኛ ስብከት እየሰበክነው ያለውን ምንባብ *የታለመ ትርጉም* እንድናወጣ ይጠይቃል። ያንን ለማድረጋችን ብቸኛው ምክንያታችን አንድን ነጥብ በምሳሌነት ለማስረዳት አስበን እንደሆነ ለሰዎች በግልጽ ካልነገርን በስተቀር ለተለዋጭ ትርጓሜ ቦታ አይኖርም። ይህም ነጥብ ደግሞ ተገቢ በሆነ የሥነ-አፈታት ዙር ቀድሞውኑ ያደርገነው ነገር መሆን ይኖርበታል። ተለዋጭ አተረጓጎም አንዳንድ ጊዜ የተፈቀደ መሆኑን ለማሳመን እንደ ገላትያ 4፡21-31 ያሉ ምንባባትን መሞገቻ ማድረግ ጥቅም የለውም። አንዳንድ ሰዎች እንዲሁም ነ ቆሮንቶስ 10፡1-3 እና ዕብራዊያን 7፡1-3ን ለዚህ አቋም ድጋፍ እንዲሆኑ ይጠቅሷቸዋል። እነዚህ ምንባባት ላይ በቅርበት ከተመለከትን፣ ምንም እንኳን መጀመሪያ ላይ ሲታዩ መስለው የሚታዩት እንደዚያ ቢሆኑም፣ በጭራሽ ተለዋጭ ትርጓሜዎች እንዳልሆኑ እናያለን። እነዚያ ምንባባት በአስረጅ ምሳሌነት ብሉይ ኪዳን እንዴት ጥቅም ላይ ሊውል እንደሚችል የሚያሳዩ ምሳሌዎች ናቸው። ከእነዚህ ምንባባት መካከል ማናቸውም የትኛውንም ዓይነት አስተምህሮ ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ እንዳልዋሉ ማስተዋሉም ጠቃሚ ነገር ነው።

በተለዋጭ የአተረጓጎም ዘይቤ ላይ ጀርባችንን ለመስጠት ጊዜው አሁን ነው። አንድን ምንባብ የምንተረጉምበት መንገድ ተለዋጭ ትርጓሜ ይሁን አሊያም

አስረጅ ምሳሌ እንደሆን እንድንለይ የሚነግረን አንድ ቀላል የሆነ ጥያቄ አለ፦ ምንባቤን በማጥናቴ ውስጥ የቃሎቹ እና ዐረፍተ-ነገሮቹ *ይታለመ ትርጉም* ወደ መድረክ ፊት ይመጣሉ፣ ወይስ ከበስተጀርባ የሚሸሸግ ነገር ይሆናል? የታለመው መልእክት ወደ ግንባር የሚመጣ ካልሆነ፣ ተለዋጭ አተረጓጎም የሚባለው አደገኛ በሆነ መልኩ አንድ የሆነ ቦታ ላይ እያደባ ነው ማለት ነው - ደግሞም ወዲያውኑ ሊገደል ይገባዋል!

(ሐ) ትምህርተ-ኃይማኖት

መጽሐፍ ቅዱስን *በትምህርተ-ኃይማኖታዊመልኩ* የሚያጠኑ የሌሎች ሰዎች ቡድንም አለ። ምን እንደሆነ እስከተረዳነው ድረስ ትምህርተ-ኃይማኖት ስህተት አይደለም። ቃሉ ፋሽኑ ያለፈበት በመሆኑ እና ሰዎች እስከሚያውቁት ድረስ ተቀባይነት የማይሰጠው ምልክቶችን የሚልክ ነገር በመሆኑ፣ ያን ያክል የምወድደው ቃል አይደለም። ትምህርተ-ኃይማኖት የሚባለው ቃል አስተምህሮ ለሚለው ቃል ጊዜው ያለፈበት መግለጫ ነው። '*ሥልታዊ ነገረ-መለኮት*' የሚለው ቃል የሚገለጽበት ሌላኛው መንገድ 'የትምህርተ-ኃይማኖት ነገረ-መለኮት' የሚል ነው። ነገር ግን፣ ለመሆኑ ያ ምንድነው? ያ ማለት ራሱ መጽሐፍ ቅዱስ ከሚሰጠው በተነጠለ መልኩ የትኛውንም መረጃ ሳይጠቀም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ትምህርት የተሰጠበት የዚያ አስተምህሮ ሥርዓት መግለጫ ነው።

እጅግ ኃያላን የየዘመናቱ ሰባኪዎች የሆኑት በትምህርተ-ኃይማኖት ነገረ-መለኮት ላይ ብርቱዎች የነበሩት ናቸው። እነርሱ ሙሉ ለሙሉ የሚቆጣጠሯቸውን ደንቦች የያዙ ናቸው። ያም ደንብ እምነታቸውን ይወስናል፣ ባህርያቸውንም ይገዛል። በጸሎቶቻቸው ውስጥ ይስተጋባል፣ ደግሞም በስብከታቸው ውስጥ ግልጽ ሆኖ ይመጣል። እነርሱ የአቋም ሰዎች ናቸው፣ ደግሞም በአደጋ ውስጥ የሚወድቁበት ምክንያትም በትክክል ይህ ነው።

የትኛውንም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በሚያጠኑበት ጊዜ፣ ለእነዚህ ሰዎች የዚያ ሥርዓት ምንጩ ራሱ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሆነ ከማስታወስ ይልቅ ባስቀመጡት ሥርዓት አተያይ መተርጎማቸው የሚቀልላቸው ነገር ነው። እውነታው ግን አንዳንዶቹ የእግዚአብሔር ቃል ምንባባት ለመገንዘብ በጣም አስቸጋሪ መሆናቸው ነው። ጊዜ እና አስፈላጊ የሚሆነውን ችግር ወስዶ ወደ

አንዳች አይነት ጠንካራ ሥነ-አፈታት ከመግባት ይልቅ እነዚያን በእኛ ሥርዓት ውስጥ 'የሚገጥሙ' እንዲሆኑ ለማድረግ እንፈተናለን። በትምህርተ-ኃይማኖት ነገረ-መለኮት ብርቱ የሆኑ በርካታ ሰባኪዎች እዚህኛው ወጥመድ ውስጥ ይገባሉ። በተደጋጋሚ እዚህ ውስጥ ይወድቃሉ ማለት እንኳን እንችላለን። አንዳንድ ክፍሎችን እና ምንባባትን በእርግጥም ክፍሎቹ *የማይሉትን* ነገሮች የሚሉ እንዲመስሉ ያደርጓቸዋል!

ዕብራዊያን 6፡4-8ን እንደ ምሳሌ መውሰድ እንችላለን። ቁጥር ስፍር የሌላቸው ሰባኪዎች እና አስተያየት ሰጪዎች እነዚህን ክፍሎች በእነርሱ ሥርዓት እይታ ውስጥ ተርጉመዋቸው ከዚያም የተነሣ በትክክል ሳይገነዘቧቸው ቀርተዋል። እውነተኛ ክርስቲያኖች ሊጠፉ እንደሚችሉ የሚያስተምር ሥርዓት ያላቸው ሰዎች ነጥባቸው ላይ ማረጋገጫ ለመስጠት ይህንን ጥቅስ ይጠቀማሉ። የያዙት ሥርዓት እውነተኛ ክርስቲያን መቼም ሊጠፋ እንደማይችል የሚያስተምርላቸው ሰዎች ደግሞ በዚህ ጥቅስ ውስጥ የተሰጠው ማስጠንቀቂያ መላምታዊ ነው ይላሉ። ይህም ማለት ጸሐፊው አስፈሪ የሆነ ስዕልን እያሳየ ነው እንጂ ስለ እውነታው እያወራ አይደለም ማለታቸው ነው።

ይህም ሆነ ያ መጽሐፍ ቅዱስን በትምህርተ-ኃይማኖት ዘዴ መተርጎም ተከታዮቹን ወደ ስህተት የሚያመራ ይሆናል። ከእነዚህ ከሁለቱ ማናቸውም ቢሰበኩ ሰባኪው የሥነ-ፍታቴያዊ *ስህተታኝነት* ጥፋተኛ ይሆናል። ምንባቡ ክርስቲያኖች ይጠፋሉ ወይም አይጠፉም እያለ አስተያየት በመስጠት ላይ አይደለም። ዓላማው ያ አይደለም። ነገር ግን የሚናገርለት ሁኔታ ደግሞ ቁጥር 9 ግልጽ እንደሚያደርገው በእርግጥም መላምታዊ አይደለም። ይህ ምንባብ በዕብራዊያን መልእክት ውስጥ የግድ *ይድኑት* ተሞክሮ ሳይኖር ከመንፈስ ቅዱስ *ጋር ሕውነተኛ* የሆነ ተሞክሮ ሊኖር የሚቻል ነገር እንደሆነ ከሚናገሩት በርካታ ክፍሎች አንደኛው ነው። የመንፈስ ቅዱስ የሚያድን ተሞክሮ የነበራችሁ የመሆኑ ማረጋገጫ አንዳች ነገር እንዲሰማችሁ አይደለም፣ ነገር ግን በእምነት እና ፍሬን በማፍራት እንድትቀጥሉ ነው። ያ የማይሆን ከሆነ፣ ትጠፋላችሁ - ስለዚህም ተግባራችሁን ማሰባሰብ እና መንፈሳዊ የእድገት ሂደታችሁ የተረጋገጠ እንዲሆን የጸኑ እርከኖችን መውሰድ ይኖርባችኋል።

የምንባቡን የታለመ ትርጉም ሊሰብክ የሚችለው ጥልቅ ለሆነ ሥነ-አፈታት የሚኖረው መሰጠት ብቻ ነው። እናስ ዕብራዊያን 6፡4-8ን በተመለከተ እውነት የሆነው ነገር ለሌሎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችም እውነት ነው።

ትምህርተ-ኃይማኖታዊ ነገረ-መለኮት መልካም ነው፣ ነገር ግን በቦታው አድርጎ መጠበቅን ልንማር ይገባል። ስብከታችንን ያበላሸዋል።

(መ) ሰብአዊ አመክንዮ

ይህንን ክፍል መዝጋት የምፈልገው መጽሐፍ ቅዱስን *በአመክንዮታዊ* መልኩ የሚያጠኑ ሰዎች እንዳሉ በመጥቀስ ነው። ለእነርሱ ትልቁ አንድ ነገር ሰብዓዊ አመክንዮ ሲሆን ያንን የሚያስቀይመውን የትኛውንም ነገር አይቀበሉም። በእርግጥ ይህ ማለት በተዓምራቶች ወይም በየትኛውም ዓይነት ልዕለ-ተፈጥሯዊ ክስተት አያምኑም ማለት ነው። እነዚህ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እውነት ለመኖሩ እርግጠኞች ናቸው፣ ነገር ግን እያንዳንዱ ክፍል እውነት እንደሆነ ወደማመን ራሳቸውን አያመጡም። ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው ፍጹም ባልሆኑ ሰዎች አልነበረምን?

እንዲህ ያለው አካሄድ መጽሐፍ ቅዱስ በሚተረጎምበት አኳኋን ላይ ከፍተኛ ውጤት አለው። ሙሴ እና እሥራኤላዊያን ዘፀአት በሚገልጸው መልኩ ቀይ ባህርን ሊሻገሩ አይችሉም፣ ምክንያቱም ውሆች በቀኝና ግራቸው እንደግድግዳ ቆሙ የሚለውን ማን ሊያምን ይችላል? ኢሳይያስ የቂሮስን መነሣት ከመወለዱ ረጅም፣ ረጅም ጊዜ በፊት ተንብዮ በሰሙ እንደነበረ በእውነት ልናምን እንችላለን? የአምስት ሺዎቹ እንጀራ ተመግበው መጥገብ ልክ እንደ ጌታችን ኢየሱስ ከርስቶስ አካላዊ ትንሣኤ ሁሉ በአንዳች ሌላ መንገድ ሊብራራ ይገባል።

በሰብአዊ አመክንዮ ላይ እምነት መጣሉ በቅርብ ዓመታት ውስጥ ራሱን ያሳየበት መንገዶች መካከል አንደኛው የተገለጠው መጽሐፍ ቅዱስን፣ እና በተናጠልም ወንጌላትን 'ተዓምራዊ ከሆኑት ታሪኮቻቸው ማነጣጠል' ነው። አራቱ ጸሐፊያን ወንጌላቶቻቸውን በመጀመሪያው ክፍለ-ዘመን ላይ በሚጽፉበት ጊዜ፣ ሊያስቡ ይችሉ የነበረው የመጀመሪያው ክፍለ-ዘመን ሰዎች ሊያስቡ በሚችሉበት ደረጃ ብቻ ነው የሚለው መከራከሪያ አሳባቸው ነው። እያዘገሙበት ያለበትን አቅጣጫ ለመገንዘብ፣ ነገሮችን የሚመለከቱበትን የመጀመሪያውን ክፍለ-ዘመን ሁኔታ ማወላለቅ እና የተደበቀኑትን እውነታዎች በሃያ አንደኛው ክፍለ-ዘመን አኳኋን ልንመለከታቸው ይገባናል። ለምሳሌ፣ ኢየሱስ በአካላዊ ሁኔታ መነሣቱን ልናምን አይገባንም፤ በኢየሱስ ተሞክሮ ውስጥ ወንዶች እና ሴቶች እውነተኛ

ሕይወት ሊኖራቸው የሚችሉ መሆናቸውን ማመኑ በቂ ነው። የእርገቱ ታሪክ በቀጥተኛ አተረጓጎም ባይወሰድ እንኳን፣ እየሆነ ያለው ነገር የወንጌል ጸሐፊያኑ የኢየሱስን ‘ልዩ መሆን’ እየጠቆሙን ናቸው።

ስለዚህ ሁሉ ነገር ምን እንላለን? ይህንን አካሄድ አልተቀበልንም ማለት፣ ሁሉንም ነገር ጠቅልለን አልተቀበልነውም ማለት ነው። ምንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው ፍጹም ባልነበሩ ሰዎች ቢሆንም የእግዚአብሔር ቃል ነው። እርሱ እስትንፋሰ መለኮቱን አድርጎበታል ደግሞም ሰብዓዊ ጸሐፊያኑ በትክክል የጻፉት ለመሆኑ ማስተማመኛ የሰጠበት በየትኛውም መንገድ ስብዕናቸውን ወይም ልዩ የሆኑ ዘይቤዎቻቸውን ሳይጨፈልቅ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ከመገኛው አንጻር ልዕለ-ተፈጥሯዊ ነው። ከውስጡ የተገኘውን ነገር ሁሉ ልዕለ-ተፈጥሯዊ አድርገን ከወሰድነው፣ ምንም መልእክት አይኖረውም። ብሉይ ኪዳንን ልንረዳው የሚገባን ጌታችን እንደተረዳው አድርገን መሆን ይኖርበታል፤ ደግሞም አዲስ ኪዳንን ልናምነው እና ልንገዛለት የሚገባን የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ አድርገን እና ሐዋርያቱን እንዲጽፉት እንደላካቸው አድርገን ሊሆን ይገባል።

የሰብአዊ አመክንዮን የሚያደናቅፈውን ሁሉ አውጥተን ከጣልን ለሥነ-ፍታቴያዊ መበላሸት ጥፋተኞች እንሆናለን። የገዛ ራሳችንን አሳቦች ብቻ እንጂ ከዚያ ያለፈ ነገር የማንሰብክ ሆነን እናርፈዋለን። ልዕለ-ተፈጥሯዊ የሆኑትን አለመቀበል መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም የማይሰጥ ወደመሆን እንዲወርድ ያደርገዋል፣ ደግሞም ሰባኪው እንዲልለት የፈለገውን ሁሉ እንዲል ያደርገዋል። ሙሉ ለሙሉ ሰው-ተኮር የሆኑ የአተረጓጎም መርኾዎች የእግዚአብሔር መጽሐፍ የሆነውን በመገንዘብ ረገድ ምንም ስኬት አይኖረውም። የትኛውም እውነተኛ ሥነ-አፈታት እንዲሁም ከዚህ የተነሣ የትኛውም እውነተኛ ስብከት ከአመክንዮታዊው ሠፈር ሊወጣ አይችልም።

ሥነ-አፈታት የሚያደርገውን ሰው መግዘት የሚኖርባቸው መርኾዎች ምንድናቸው?

እንግዲያው በፊት ለፊቴ ያለው ምንባብ በእርግጥ እያለ ላለው ነገር ልወስዳቸው የሚገቡኝ መርኾዎች ምንድናቸው? የታለመውን መልእክት ላገኘው እና ከዚያም የተነሣ ልሰብከው የምችለውን ነገር የማወጣው እንዴት ነው?

በርካታ መጽሐፍት በዚህ ርእሰ-ጉዳይ ላይ ተጽፈዋል፣ ደግሞም ረጃጅም የሆኑት የግድ የተሻሉ ተደርገው መቆጠር የለባቸውም። ከእነርሱ ውስጥ የትኛቸውም ላሉት ነገር ይህ በስብከት ላይ የተዘጋጀ ትንሽ መጽሐፍ ሊያጠቃልል አይችልም። ሊያደርግ የሚችለው ግን አንዳንዶቹን ነጥቦች አጽንዖት ሰጥቶ ማለፍ ነው። ትኩረታችሁን መሠረታዊ ለሆኑት ነገሮች ሊስበው ይችላል። ወደ ሥነ-አፈታታዊ የጥፋት ባህር እንዳትገቡ ሊያስቆማችሁ እና እግሮቻችሁን አስተማማኝና እርግጠኛ በሆነ ወለል ላይ ሊያቆማችሁ ይችላል።

በየትኛውም የእግዚአብሔር ቃል ምንባብ ላይ ከመስበካችሁ በፊት፣ ራሳችሁን እና ሰሚዎቻችሁን ማጥፋት እንዳይሆንባችሁ ሰባት ጥያቄዎችን መጠየቅና መመለስ አለባችሁ። ጊዜ ውሰዱ! ስብከት ለማግኘት ስትሉ ጥናት አታድርጉ - በፍጹም! በፍጹም! - ነገር ግን የምታጠኑት ምንባቡን ለመገንዘብ ይሁን። *ሰባኪዎች ሊያከብሩት የሚገባው ኪደንቦች ሁሉ በላይ ያለው ደንብ ይህ ነው።* በሚስጢራዊው ስፍራ ካከናወናችሁት ታላቅ ሥራ አኳያ ሲነፃፀር በስተመጨረሻ የምትሰብኩት ነገር በጣም ትንሽ ነገር መሆን አለበት።

(1) ይህንን ሥራ ሳከናውን እግዚአብሔር ከእኔ ምን ይጠብቃል?

እያጠናሁት ያለሁት መጽሐፍ የእርሱ ቅዱስ ቃል እንደሆነ እንዳስታውስ ይጠብቃል። በመደነቅ እንድመለከተው እና በመገረም *'እዚህ ጋር* እግዚአብሔር ተናግሯል!. . . እግዚአብሔር *እዚህ ጋር* እየተናገረ ነው!' ብዬ እንዳንሾካሹክ ይጠብቃል። በአምልኮ፣ በመደነቅ፣ በምስጋና እና በፍርሃት እንድከፍተው ይጠብቅብኛል። ትልቁ የነፍሴ ጥልቀቷ በመለኮታዊ መገለጥ መገኘት ውስጥ ነኝ በሚለው የአሳብ ስሜት ውስጥ ሊሞላ ይገባል። ይህ ቅዱስ የሆነ ቅጽበት ነው። የእምባ ዘለላዎች መጉረፍ ያጋጥማል። የደስታ ለቅሶም ቢሆን እንደዚሁ።

የማነብበውን ሁሉ እንዳምን እርሱ ይጠብቅብኛል። ያንን ንባብ በማደርግበት ጊዜ እንዳነጋግረው ይጠብቅብኛል። ሁሉንም ነገር ከማር ይልቅ የጣፈጠ እና ከወርቅ ይልቅ ውድ እንደሆነ ነገር አድርጌ በልቤ ውስጥ ትልቅ ቦታ እንድሰጠው ይጠብቅብኛል። መሃላዎቼን ሁሉ ወደ ተግባር እንድቀይራቸው አድሳቸው ዘንድ ይጠብቅብኛል።

ይህንን መጽሐፍ የሰጠው መገለጥ እንዲሆን በማሰብ እንደሆነ እንዳስታውስ ይጠብቅብኛል። ስለዚህም ትርጉም አለው። አዎን፣ እያነበብኩት

ያለሁት ምንባብ ትርጉም አለው። ይሁን እንጂ፣ ሰብዓዊው ጸሐፊ ያሰበው ትርጉም ብቻ ሳይሆን (እኔ ላገኘው የሚገባኝ)፣ ነገር ግን የእርሱም ቃሎች እርሱ ራሱ ሊገነዘበው ከሚችለው በላይ የበለጠ ሙሉ ትርጉም እንደተሸከመ አስተውሎ ነበር። የተለየ ሁኔታን አስመልክቶ እየጻፈ እንደነበረ ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን የእርሱ ቃሎች በመላው ትውልዶች በኩል በመላው ዓለማቀፍ ክበብ ላለችው የክርስቶስ ቤተክርስቲያን እንደሆነም ያስተውላል። ይህንን እንዴት ዐውቃለሁ? ምክንያቱም ነ ጴጥሮስ ነ፡10-12 ይህንን ስለሚያስተምር ነው። ጌታ ይህንንም ቢሆን እንዳስታውስ ይጠብቅብኛል።

ሊለው *ስለሚገባው* ነገር አስቀድሜ ያሰብኩት ነገር ሳይኖር፣ ነገር ግን በእርግጥ *የሚለውን* ነገር ለማግኘት በትህትና እና በመታዘዝ ወደ ቃሉ እንድመጣ ይጠብቅብኛል። ማስተዋሌ በጣም የተወሰነ ፍጥረት እንደሆንኩ፣ ይህም ብቻ ሳይሆን ለማስተዋል ያለኝ ችሎታ በከፍተኛ ሁኔታ የተበላሸብኝ ኃጢአተኛ እንደሆንኩ ጭምር እንዳስታውስ ይፈልጋል። የእርሱን መጽሐፍ ያለ እርሱ ግላዊ እገዛ ልረዳው እንደማልችል አምኜ እንድቀበል ይጠብቅብኛል። ይህንንም ከእርሱ እንድጠይቅ ይጠብቅብኛል።

መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ሰው በጠረጴዛው ላይ አድርጎ ሊያጠናው የሚችለው ነው። ነገር ግን ያ ሰው እያጠናው ያለው የልቡ ጉልበቶች በተንበረከኩበት እስካልሆነ ድረስ እውነተኛ የሥነ-አፈታት ሰው እና እውነተኛ ሰባኪ ሊሆን አይችልም። ሥነ-አፈታት ብርቱ ሥራ ነው። ሥራው ራስን የማስገደድ ትምህርታዊ ዘርፍ ነው። ነገር ግን ከዚያ ሁሉ በፊት፣ የአምልኮ ተግባርም ነው።

(2) የቃሉ ሰዋሰዋዊ ትርጉም ምንድነው?

የእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል የተቀናበረው ከቃላት ነው። ከእነዚያ ቃሎች አንዳንዶቹ ስሞች፣ ሌሎቹ ግሶች፣ እንዲሁም አንዳንዶቹ መስተአምሮች፣ ቅጽሎች፣ ተውሳከ ግሶች፣ ቁጥሮች፣ ተውላጠ ስሞች፣ መስተዋድዶች፣ መስተፃምሮች፣ ቃል አጋኖች እና ከዚህም ባለፈ ጥሩ መደራደሪያን የያዘ ነው። ስሞቹ ነጠላ፣ ጥንድ ወይም ብዙ ቁጥር ሊሆኑ ይችላሉ። ግሶቹ በተለያዩ ብርታቶች፣ የሰዋሰው ጊዜ-አዘል፣ ግስ ገላጭ፣ እና ድምጸቶች ውስጥ ያሉ ሊሆኑ ይችላሉ። ደግሞም እነዚህ ቃሎች በሙሉ ወደ ዐረፍተ-ነገሮች ሊቀናጁና የሚቀናጁበትም መንገድ ለዚያ ዐረፍተ-ነገር *ትርጉም* የሚሰጡ ናቸው!

በዚህ ልንፈራ አይገባንም። ከተወሰኑ ጊዜያት ጀምሮ ስታነብቡት የነበረ መጽሐፍ በእጃችሁ አላችሁ። ያም ጭምር ከተለያዩ ዓይነት ቃላት የተዋቀረ፣ በዐረፍተ-ነገሮች የተቀናጀና ከእኔ አእምሮ ወደ እናንተ አእምሮ አንዳችን ነገር የማቀበል ራእይ ያለው ነው። የተለዩ ቃሎችን ተጠቅሜ ቢሆን፣ ወይም ተመሳሳይ የሆኑትን በሌላ መንገድ ባቀናጅ፣ የተለየ ትርጉምን ትመርጡ ነበር። ስለዚህም ሰዋሰው ጠቃሚ ነገር ነው። ያለ ሰዋሰው መጽሐፍን መጻፍ አይታሰብም።

በተመሳሳይ መንገድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ እያንዳንዳቸው ዐረፍተ-ነገሮች ትርጉም አላቸው። ቃሎቹ የተለዩ ቢሆኑ ኖሮ፣ ወይም ሰዋሰዉ ቢለወጥ ኖሮ፣ የተለየ ትርጉም በኖረው ነበር። ስለዚህም ወደድንም ጠላን፣ ለተናጠላዊ ቃላት እና ወደ ዐረፍተ-ነገርነት ለሚቀየሩበት መንገድ ጠንቃቃ ትኩረት ካልሰጠን ሥነ-አፈታታዊ ትክክለኝነት ሊኖረን አይችልም። ሥነ-አፈታት የሚባለው ይህ ነው።

ሰባኪዎች ሰዋሰውን እንዴት መውደድ እንዳለባቸው ሊማሩ ይገባቸዋል! ቋንቋ የሚሠራው እንዴት እንደሆነ ለመገንዘብ ጥረት ማድረግ አለባቸው። ካላደረጉ ግን፣ ሥራቸውን ለመሥራት አይቻላቸውም። መጽሐፍ ቅዱስ በመለኮታዊ ሁኔታ እስትንፋሰ-መለኮት ያለበት መጽሐፍ መሆኑ እውነት ነው። ነገር ግን እንደዚያም ሆኖ መጽሐፍ ነው። ሊነበብም የሚገባው እንደ መጽሐፍ ነው። የቃሎቹን እና የሐረጎቹን ሰዋሰዋዊ ስሜት ልናከብር ይገባናል። በእርግጥ ይህ እነዚያ ቃሎች እና ሐረጎች በሚገኙባቸው የሥነ-ጽሑፍ አይነቶች ይወሰኑ ይሆናል - ደግሞም ከጥቂት ጊዜ በኋላ ልንዳስሰው የሚገባን ነጥብ ይህ ነው። ነገር ግን የሚከተለውን እውነታ ልንጋፈጥ ይገባል፦ ሥነ-አፈታት ሊደረግ የሚችለው መጽሐፍ ቅዱስን ባለው ዋጋ ልክ በሚወስዱ እና ቃሎቹን እንዲሁም ዐረፍተ-ነገሮቹን መደበኛ በሆነው ትርጉማቸው በሚቀበሉት ነው።

በዚህኛው የሕይወቴ እርከን ላይ በሰፊው መጓዜ እና በርካታ ሰባኪዎችን መተዋወቄ ካገኘኋቸው እድሎች አንደኛው ነው። ከእነርሱ ውስጥ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሰባኪዎች ዓለማቀፍ ወረርሽኝ በሆነው የሰዋሰዋዊ ግድየለሽነት በሽታ የተለከፉ መሆናቸውን ስነግራችሁ አዝናለሁ። ስለ ሰዋሰው ዐያውቁም፣ ስለእርሱም ግድ የላቸውም፣ ሊሰብኩበት ካለው ክፍል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባብን በሚያጠኑበት ጊዜ ብዙም ትኩረት ለሰዋሰው አይሰጡም። ይሁን እንጂ ከሞላ ጎደል ሁሉም የማውቃቸው ሰባኪዎች የመጽሐፍ ቅዱስ መለኮታዊ እስትንፋሳዊነት እስከ እያንዳንዱ ነጠላ ቃል ድረስ የሚሄድ ነው!

በከፍተኛ ሁኔታ የተሳሳተ የሆነ አንዳች ነገር ያለ ሲሆን ያንን ለማስተካከል ዋናው ጊዜ አሁን ነው።

(3) እነዚህ ቃሎች የሚገኙት በምን ዓይነት ሥነ-ጽሑፋዊ ዘይቤ ነው?

ቃሎች በገዛ ራሳቸው ዝም ብለው አይገኙም። ሌላው ቢቀር ቀላል የሚመስለው 'አይሆንም!' የሚለው ቃል ቀደም ብሎ ተነግሮ ለነበረ አንዳች ነገር ምላሽ ነው። እያንዳንዱ ቃል ዐውድ አለው። አንዳች ቃል ከእርሱ በፊት ነበረ፣ ደግሞም ሌላ ቃል ይከተለዋል። እየተነጋገርን ያለነው ስለ ሐረጎች እና ዐረፍተ-ነገሮች አይደለም፣ ነገር ግን እነዚያ ሐረጎች እና ዐረፍተ-ነገሮች ስለሚገኙባቸው የሥነ-ጽሑፍ ዓይነቶችም ጭምር እንጂ። ይህም እንዲሁ የየትኛውንም የእግዚአብሔር ቃል ክፍል የታለመ ትርጉም ለማግኘት ስንፈልግ ጠንቃቃ ትኩረት ልንሰጠው የሚገባን አንዳች ነገር ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በርካታ ህግጋት አሉ፣ በተለይ ቀደም ባለው የብሉይ ኪዳን ክፍል ውስጥ። ህግጋት የሚጻፉት ግልጽ በሆነ ስድ-ነባብ ነው። ታሪካዊ ዘገባዎችም ልክ እንዲሁ። ነገር ግን ለእያንዳንዶቹ ሌሎች ስንናገር የምንጠቀመው ዘይቤ በእርግጥም በጣም የተለዩ ናቸው። የምናደርገውን ውይይት በሁሉም ዓይነት የቃላት-ስዕሎች ጋር እናደምቀዋለን - 'መብረቅ የመሰለ ፊት ነበራት'፣ 'ራሱን ወደ ላይ የጎተተው በቦቴ ጫማው ማሰሪያ ነው'፣ 'መድረኩን መቱት'፣ 'እርሱ አውሬ ነው'። እነዚህ መግለጫዎች ቃል በቃል መወሰድ እንደማይኖርባቸው ሁላችንም እናውቃለን (*በእውነት* እርሱ የጫማ ማሰሪያዎቹን ጎትቶ መንሳፈፍ ይችላልን?)፣ ነገር ግን የዛኑ ያክል ትርጉማቸውንም ማጣት አይኖርብንም። ስለዚህም ህጋዊ ስድ-ነባብ እና ግላዊ ውይይት በተመሳሳይ መልኩ መተርጎም እንደሌለባቸው፣ ደግሞም ይህ መጽሐፍ ቅዱስ በምናነብበትም ጊዜ ተግባራዊ መሆን እንዳለበት ግልጽ ነው።

ሁሉንም ዓይነት ሥነ-ጽሑፍ በተመሳሳይ መልኩ ልንተረጉም አንችልም። ከጠቀስናቸው ህጋዊ እና ታሪካዊ ስድ-ነባብ ጎን ለጎን፣ በርከት ያሉ ቅኔያዊ ጽሑፎችም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሉ። አንዳንዶቹ የሚገኙት በኢዮብ፣ *መዝሙራት* ወይም በመጎልየ *መጎልይ* መጽሐፍ ውስጥ ሲሆን አንዳንዶቹ ደግሞ በነብያት ውስጥ እና አንዳንዶቹም ደግሞ የሚገኙት ቢረዝሙም ቢያጥሩ በሌሎች መጽሐፍት ክፍሎች ውስጥ ነው። በተጨማሪም ደግሞ የጥበብ ሥነ-ጽሑፎችንም፣ ወንጌላት እና መልእክታትንም እናገኛለን።

ራእይ ነክ የሆነ ቋንቋዎችንም የምናገኝ ሲሆን እነርሱም የተጋነነ ቋንቋን፣ ቍጥሮችን፣ የጭራቅ ስዕሎችን እና ያልተለመዱ ራእዮችን በመጠቀም ነጥባቸውን የሚያሳዩ ናቸው። እነዚህን ሁሉ ዓይነት ሥነ-ጽሑፎችን በተመሳሳይ መንገድ ማንበብ ካለብን በእርግጥም በእጅጉ የሚምታታብን እንሆናለን!

በፊት ለፊታችን ያለው የትኛውም ዓይነት ሥነ-ጽሑፍ ቢሆን፣ ግልጽ ለሆነው ለእያንዳንዱ የምናነብበው ሰዋሰዋዊ ስሜት ትኩረት መስጠት ያለብን መሆናችንን መርሳት የለብንም። ነገር ግን ይህንን በምናደርግበት ጊዜ የአንድ ምንባብ *ቀጥታኛ* ትርጓሜ የግድ *የታለመው* ትርጉሙ ሊሆን እንደማይችል እና የምንፈልገው ደግሞ *ታልም* ያለውን ትርጉሙን እንደሆነ ልናስታውስ ይገባናል።

ለምሳሌ ኢሳይያስ ስለተነበየው ያልተለመደ ጊዜ ደስታ የተጻፈውን እንመልከት፤ “እናንተም በደስታ ትወጣላችሁ በሰላምም ትሸኛላችሁ፤ ተራሮችና ኮረብቶች በፊታችሁ እልልታ ያደርጋሉ፥ የሜዳም ዛፎች ሁሉ ያጨበጭባሉ” (ኢሳ.55፡12)። ምን ማለቱ ነው? በመጪው ክፍለ-ዘመን ውስጥ ዛፎች አንዳች ዓይነት አስደናቂ የሆነ አዲስ ባህርያትን ያዳብራሉ ማለቱ እንዳልሆነ እርግጥ ነው! በተመሳሳይ መልኩ፣ “ጻድቅ እንደ ዘንባባ ያፈራል፥ እንደ ሊባኖስ ዝግባም ያድጋል” (መዝ.92፡12)። የሚለው እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሽማግሌዎች ያቆጠቆጣሉ ማለት አይደለም። በተመሳሳይ “የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውሥጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኵላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ” (ማቴ. 7፡15) የሚለው ሹራብ ስለሚለብሱ ሰባኪዎች የተነገረ ማስጠንቀቂያ አይደለም! የቃሎቻቸውን ሰዋሰዋዊ ስሜት ሳንቀስም እነዚህን ንግግሮች ልንረዳቸው አንችልም። ነገር ግን ማናችንም ብንሆን ቀጥተኛው ትርጉማቸው *የታለመው* ትርጉማቸው ነው በማለት የምናስብበት ገራገርነት የለንም - ደግሞም የሥነ-ፍታቴ ሰዎቻችን ሊያገኙት እና እኛም በሕዝብ ፊት ልንሰብከው የሚገባው ያኛው የታለመ ትርጉም ነው።

(4) ዙሪያ-ገብ እና ሰፊው ዐውድ ምንድነው?

ቃሎች የሚገኙት በሐረጎች እና ዐረፍተ-ነገሮች ውስጥ ሲሆን ዐረፍተ-ነገሮች ደግሞ የሚገኙት በአንቀጾች ውስጥ ነው። እነዚህ አንቀጾች በተራቸው የአንድ ትልቅ የሆነ ነገር አካል ናቸው። ይህም ትልቅ የሆነው ነገር ምእራፍ እና የመጽሐፉ አካል የሆኑት ምእራፎች ናቸው። ራሳችንን ለሥነ-ፍታቴያችን ስናስገዛ ይህንንም እንዲሁ ልናስታውስ ይገባናል።

ዙሪያ-ገብ የሆነውን እና ሰፊውን ዐውድ ችላ ካልን፣ መጽሐፍ ቅዱስ እኛ የፈለግነውን ሁሉ እንዲል እናደርገዋለን። ስብከት ላይ ይህን መጽሐፍ መጽሐፍ ያደረጉት ነገሮች በዋናነት የተሰጡት በንግግር መልክ ነበር። ሁሉም መዳረሻዎች የተመዘገቡ ነበሩ። አሁን አንድን ካሴት ወይም ሲዲ የሚገዛን እና ያንን በአርታዒነት የሚሠራን ሰው እናስብ። ይህ ሰው እያንዳንዱን ዐረፍተ-ነገር ያልተነዱ አድርጎ ጠብቋቸዋል እንበል፣ ነገር ግን እነዚያን ዐረፍተ-ነገሮች በተለየ ቅደም-ተከተል ለማስቀመጥ ኤሌክትሪካዊ መሣሪያውን ተጠቅሟል። ያንን ካደረገ በኋላ፣ በክርስቲያናዊ ጋዜጣ ላይ ማስታወቂያ አስለጥፎ ካሴት እና ሲዲዎቹን መሸጥ ጀመረ።

በተቀዱት ላይ ያለው ድምጽ የእኔ ነው። እያንዳንዱ ዐረፍተ-ነገር ልክ እኔ እንደተናገርኩት የእኔ ነው። ነገር ግን የተነገረው አድራሻ ሙሉ ለሙሉ የተለየ ነው። እርስ በርሳቸው የማይስማሙና ያለ ሥርዓት የተደበላለቀ ዐረፍተ-ነገሮች ይመስል ይሆናል፣ ወይም በቀዳሚነት ካሰብኩት ፈጽሞ የተለየ ትርጉም ያለው ሊመስል ይችላል።

ዙሪያ-ገብ እና ሰፊ የሆነው ዐውድ ግልጽ ሳይሆንልን በየትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ሐረግ ወይም ዐረፍተ-ነገር ላይ ስንሰብክ የሚከሰተው ልክ እንዲህ ያለ ነገር ነው። “ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል” (ዩሐ. 3፡7) የሚለውን *ትእዛዝ* እንደሆነ ተደርጎ የተሰበካችሁት ምን ያክል ጊዜ ነው? ይህ ትርጉሙን ሙሉ ለሙሉ ማበላሸት ነው። እነዚያን ቃሎች እንደ ትእዛዝ አድርጎ መስበክ ማለት እያደመጡ ያሉትን እያንዳንዳቸውን ጎልማሶች እና ልጆች ማሳት ነው። አዲሱ ልደት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የትም ቦታ ላይ ትእዛዝ ሆኖ አልተነገረም። ትእዛዝ የተሰጠበት ንስሃ መግባት ነው። በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ትእዛዝ ነው። ነገር ግን አዲሱ ልደት ሙሉ ለሙሉ የእግዚአብሔር ሥራ ስለሆነ ትእዛዝ አይደለም (ሊሆንም አይችልም)። ጌታችን ለኒቆዲሞስ “ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል” ሲል፣ የእውነታን ጎልዳፋ ንግግር እያደረገ ነው። ዛሬ ላይ እነዚያን ቃሎች የሚሰማ የትኛውም ማኅበረ-ምእመን አጽንዖት ልንሰጥበት የሚገባው ነጥብ ያ ነው። ሌላ የትኛውንም ትርጉም መስበክ የሥነ-ፍታቴያዊ ትክክለኝነት እጦት ብቻ አይደለም፤ ኃጢአት ነው።

በበርካታ አጋጣሚዎች ስብከቶች ፣ ቆሮንቶስ 2፡9 ጳውሎስ ከኢሳይያስ 64፡4 ያጣቀሰው እንደሆነ ተደርጎ ሲሰበክ ሰምቻለሁ። የምንባቡ ዋና ክፍል እንዲህ ይነበባል፦ ‘ነገር ግን። ዓይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ

ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው ተብሎ እንድተጻፈ፥ እንዲህ እንናገራለን።' የሰማኋቸው እያንዳንዳቸው ሰባኪዎች እነዚህ ቃሎች ስለ መንግስተ-ሰማይ እንደሚናገሩ አድርገው ሰብከዋል። ይህንን ያደረጉት ቃሎቹን ከዐውዳቸው ውጪ ስለወሰዷቸው ነው። 1 ቆሮንቶስ ምእራፍ 2 ስለ መንግሥተ ሰማይ አይደለም፤ ከፍሉ ግን የጌታ ልጆች ካላመኑት ሰዎች ተደብቀው ያሉትን ነገሮች ይልቅ ማየት እና ማድነቅ እንደሚችሉ የሚናገር ነው። እንዴት ያለ ከተለመደው ውጪ የሆነ እድል አለን! እንዴት ያሉ አስደናቂ ነገሮችን እናያለን! በጌታ ያልተለወጠ ልብ ሊያስባቸው መጀመር እንኳን አይችልም፣ ይሁን እንጂ እኛን ከጫፍ እስከ ጫፍ የሚያስፈነድቁን ነገሮች ናቸው። ጥቅሱ የሚናገረው *ስለዚህ* ነው። ስለዚህም መለኮታዊው ጸሐፊ እንዲኖረው ያላሰበውን ትርጉም መስጠቱ ፈሪሃ እግዚሐር የሌለበት መሆን ብቻ ሳይሆን ስህተትም ጭምር ነው።

ሥነ-ፍታቴያዊ ስህተቶችን ልናስወግድ የምንችልበት ብቸኛው መንገድ በርካታ ተጨማሪ ሥራዎችን በመሥራት ነው። በየትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ *ክፍል* ላይ ከመስበካችን በፊት ከመላው ክፍል ጋር ጥሩ የሚባል ትውውቅ ሊኖረን ይገባል። ያ ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን ያንን የጻፈው ማን እንደሆነ፣ ለማን፣ ለምን እና መቼ እንደጻፈው የምናውቅበት ብቁ የሆነ ግንዛቤ ሊኖረን ይገባል። በተለይ ጠቃሚ የሆነው *መቼ* የሚለው ጉዳይ ሲሆን ቀጥሎ ያለውን ጥያቄያችንን የምንጠይቅበትም ምክንያት እርሱ ነው።

(5) *ታሪካዊ መቼት* ምንድነው?

መጽሐፍ ቅዱስ በሺዎች የሚቆጠሩ ቀጥተኛ ትርጉም ያላቸውን ክስተቶችን የሚገለጽ ሲሆን ሁሉም በተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ አልተከሰቱም። በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን የሚገልጽ ሲሆን ሁሉም በተመሳሳይ ጊዜ ላይ አልኖሩም። በሺዎች የሚቆጠሩ እውነታዎችን ያስተምራል፣ ነገር ግን ሁሉም በተመሳሳይ ጊዜ ላይ የተገለጡ አይደሉም። እያንዳንዱ ሰባኪ በአስተዋጽዖ ደረጃም ሆነ በዝርዝር ሊያውቋቸው የሚገባቸው በርካታ የታሪክ ሂደቶች አሉ። *መቼ* ምን እንደሆነ ግልጽ ሊሆንለት ይገባል። ደግሞም በታሪኩ ሂደት የትኛውም ቦታ ላይ ምልክት ሊያደርግ እና እስከዚያ ነጥብ ድረስ የተገለጠው ነገር እና ኋላ ላይ የሚገለጠው ነገር ምን እንደሆነ መናገር መቻል አለበት።

ይህንን በቀላሉ ማድረግ ካልቻለ በሥነ-ፍታቴያዊ አኳኋን ወደጥፋት ያቀናል፣ ደግሞም በሌሎች ላይ የሚኖረው የአገልግሎቱ ውጤት አውዳሚ

ይሆናል። እግዚአብሔር በጸጋ የተሞላ ነው፣ ነገር ግን የእርሱ ጸጋ ለወንዶች እና ሴቶች ሁልጊዜ በተመሳሳይ መንገድ አይታደልም። አስተዋጽዖ ሲወጣ፣ የተሟላ ንድፍ፣ የተሳለ ምስል፣ እና የባለቀለም ፊልም መካከል አስደናቂ የሆኑ ተመሳሳይነቶች እንዲሁም ሰፋፊ ልዩነቶች አሉ፣ ነገር ግን በክፍለ-ዘመናት መካከል እግዚአብሔር ትልቁን የመዋጀት እቅዱን የገለጠው እንደዚያ ነው። የብሉይ ኪዳን ታሪክ ጅማሬ እንደ መካከለኛው ወይም እንደ መጨረሻው ተመሳሳይ የሆነ አይደለም። ብሉይ ኪዳን አዲስ አይደለም። ጥላው አካል አይደለም። በወንጌላት ውስጥ ያለው ሁኔታ የሚቀድመውን ወይም የሚከተለውን ዓይነት አይደለም። ከጴንጤቆስጤ በፊት የነበሩ አማኞች ከዚያ በኋላ ካሉት ጋር ተመሳሳይ አይደሉም። በሐዋርያት ሥራ መጀመሪአ ላይ የነበረችው ቤተክርስቲያን በስተመጨረሻ ላይ ያለችውን ያክል የበሰለች ወይም አለማቀፋዊት አልነበረችም። በምድር ላይ የነበረችው ቤተክርስቲያን ከክርስቶስ ዳግመኛ መምጣት በኋላ ተድላ የምታደርገውን ገና ተድላ አላደረገችውም።

በኢዮብ 19:25-27 ፍዳን ተቀባዩ የተቀደሰ ሰው እንዲህ ብሏል፦ ‘እኔን ግን የሚቤዠኝ ሕያው እንደ ሆነ፥በመጨረሻም ዘመን በምድር ላይ እንዲቆም፥ይህ ቁርበቴም ከጠፋ በኋላ፥በዚያን ጊዜ ከሥጋዬ ተለይቼ እግዚአብሔርን እንዳይ አውቃለሁ።’ በታላቁ የታሪክ ሂደት ውስጥ ኢዮብ የሚገጥመው የት ቦታ ላይ እንደሆነ ብናውቅ፣ ይህ ንግግሩ እንዴት ያለ ያልተለመደ ንግግር እንደሆነ በማሰብ ማድነቅ እንጀምራለን። ነገር ግን ኢዮብ ይህንን ያለው ጳውሎስ 1 ቆሮንቶስ ምእራፍ 15ን ከጻፈ በኋላ ቢሆን ግን፣ ንግግሩን በተመለከተ ምንም የተለየ የሚሆን ነገር ባልኖረ ነበር። ይህ ብቻ አይደለም፣ በርካቶቹ ባህርያቱ አስደንጋጭ ናቸው ብለን ለመናገር እንገደድ ነበር።

በሐዋርያት ሥራ 19:2 ላይ ዐሥራ ሁለት ኃይማኖተኛ ሰዎች እንዲህ አሉ፦ ‘እነርሱም። አልተቀበልንም መንፈስ ቅዱስ እንዳለ ስንኳ አልሰማንም አሉት።’እነዚህ ሰዎች ይኖሩ የነበረው በአብረሃም ጊዜ ላይ ቢሆን ኖሮ በንግግራቸው ውስጥ ያልተለመደ የሚባል አንድም ነገር ባልኖረ ነበር። ነገር ግን እንደተባለው ይህንን የተናገሩት ከጴንጤቆስጤ በኋላ እና የክርስቲያኖች ቤተክርስቲያን ከተመሰረተች በርካታ አመታት ከሆናት በኋላ ነው። ከዚህ የተነሣ፣ የእነርሱ አለማወቅ ያለመለወጣቸው ማረጋገጫ ሲሆን ይህም ጳውሎስ በዚያ መልኩ እንዲያገለግላቸው ያስገደደው ነገር ነበር።

በዘኍልቁ 15፡32-36 ላይ ቅዳሜ ላይ የማገዶ እንጨት ሲለቅም የተገኘው ሰው እንዲገደል እግዚአብሔር አዘዘ። በታላቁ የታሪክ ሂደት ውስጥ ይህ ገጠመኝ ጥሩውን ቦታውን የሚያገኘው የቱ ጋር እንደሆነ በጣም እርግጠኞች መሆን ያለብን ይመስለኛል። አለዚያ ዛሬ ላይ ላሉት ሕዝቡ የጌታን ትእዛዝ ስናዛምድ እና ያም ደግሞ በርካታ የሆኑ ሰዎች ከቤተክርስቲያኖቻችን ውስጥ እንዲወገዱ ስናስደርግ እንገኝ ይሆናል! ከዚህ በላይ ማለት ያስፈልገናል? ነጥቡ ግልጽ ነው፡- ማንም ሰው ሊሰብክ ያለውን ምንባብ ታሪካዊ መቼት በተመለከተ በእጅጉ ግልጽ ሳይሆንለት፣ ኃላፊነት ያለበት የሥነ-ፍታቴ ሰው እና ከዚያም የተነሣ የቃሉ እውነተኛ ሰባኪ መሆን አይችልም።

(6) ሌሎች የቃለ እግዚአብሔር ክፍሎች በዚህ ምንባብ ላይ የሚሰጡት ፍንጭ ምንድነው?

ከስድሳ ስድስት መጽሐፍት የተውጣጣው መጽሐፍ ቅዱስ ራሱን በራሱ መተርጎም የሚችል ነጠላ መጽሐፍ ነው። የትኛውም ክፍሉ ግልጽ ሳይሆንልን ቀርቶ ብናገኘው፣ ሌሎቹ ክፍሎች እንድንገነዘበው ይረዱናል። የአንድ ነጠላ ምንባብ ትርጉም ትክክል እንደሆነ በልበ-ሙሉነት እርግጠኞች ስንሆን፣ ሌሎች ምንባባት አብዛኛውን ጊዜ ያርሙንና ትሁታን ያደርጉናል። ጥሩ የሥነ-ፍታቴ ሰዎች መሆን ካለብን፣ መላውን መጽሐፍ ቅዱስ ከጫፍ እስከ ጫፍ ማወቃችን ወሳኝ ነገር ነው።

የኢሳይያስን መጽሐፍ እየሰበክሁ ቢሆን፣ በስተመጨረሻ የምመጣው ምእራፍ 42 ላይ ነው። ምእራፉ የሚጀምረው ‘እነሆ ደግፌ የያዝሁት ባሪያዬ፤ ነፍሴ ደስ የተሰኘችበት ምርጤ. . .’ በማለት ነው። ነገር ግን እየተናገረ ያለው ስለማን ነው? መገመት አያስፈልገኝም። በአንዳንዶቹ ማብራሪያ ሰጪ መጽሐፍት የተቀመጡትን በስፊው የሚለያዩ ንድፈ-አሳቦች እንዲያደናግሩኝ አያስፈልገኝም። ይህ ምንባብ ፍጻሜውን ያገኘው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያ አመታት አገልግሎት ውስጥ እንደሆነ ማቴዎስ 12፡15-21 ይነግረኛል። አላስፈላጊ የሆነ ግጭት ከጠላቶቹ ጋር ማነሳሣት እስከማያስፈልገው ድረስ የእርሱ ባህርይ እንዲህ ያለው ነበር። በሌላኛው የቃለ እግዚአብሔር ክፍል ውስጥ ከተሰጠው ፍንጭ የተነሣ ኢሳይያስ ላይ ግልጽ የሆነ መልእክትን መስበክ እችላለሁ።

እየሰበክሁ ያለሁት በአሞጽ 9፡11-15 ላይ ቢሆን፣ ነብዩ እያለው ያለው አይሁድ አንድ ቀን ላይ የዳዊት ንጉሣዊ የቤተሰብ ዘር ይመለስላቸዋል፣ ደግሞም በእነዚያ ቀናት የእስራኤል ምድር የታደሰ ተጽዕኖ ፈጣሪነት እና ብልጽግና ይኖራታል እያለ ነው በማለት ለአድማጮቼ ለመንገር እፈተን ይሆናል። መጀመሪያ ላይ የሚኖረን እይታ፣ ማለትም ቃሎቹ የሚሉት የሚመስለው እንደዚያ ነው። ነገር ግን መጀመሪያ ባየነው ላይ መታመን የለብንም። ደግሞም ስድሰተኛውን ጥያቄ ሳንጠይቅ የትኛውንም ምንባብ በእርግጠኝነት መተርጎም የለብንም። ይህ በሚሆንበት ጊዜ፣ ሐዋ. ሥራ 1515-17 አሞጽ እያለው ባለው ላይ አስደናቂ የሆነ ፍንጭን ይሰጣል። ይህ ትንቢያ ፍጻሜውን ያገኘው አህዛብ ወደ እግዚአብሔር በመምጣታቸው ውስጥ እና የክርስቲያኖች ቤተክርስቲያን አካል በመሆናቸው ውስጥ እንደሆነ ያሳየናል። ይህም በመሆኑ፣ ብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኙ በርካታ ተመሳሳይ ትንቢቶች የሚኖራቸውን ትርጉም ልናገኝ የምንችልበትን ቁልፍም ይሰጡናል። ቃለ እግዚአብሔርን በቃለ እግዚአብሔር መተርጎም ባልቻልንበት ሁኔታ ውስጥ ምንም አይነት የሥነ-ፍታቴ ትክክለኝነት ሊኖር አይችልም።

ዕብራዊያን 5፡5-11 እና 7፡1-28ን ሳያመሳክር በፊት ከዘፍጥረት 14፡18-24 ያለውን የመልከጸዴቅ ታሪክ መስበክ የሚደፍር ማነው? ዘፀአት 16 ላይ ያለውን የመና ታሪክ ዩሐንስ 6ን አስቀድሞ ሳያጠና የሚናገር ማነው? በብሉይ ኪዳን ውስጥ የዚያን ነገድ ታሪክ መለስ ብሎ ሳያጠና በፊት የዳን ነገድ ከራእይ 7፡4-8 ዝርዝር ውስጥ ያልተካተተው ለምን እንደሆነ ያብራራ ዘንድ የሚሞክረው ማነው? ተመሳሳይ ርእሰ-ጉዳዮችን የሚያነሡትን ሌሎች ምንባባት ሳያገናዝብ በየትኛውም አስተምህሯዊ መግለጫዎች ላይ ለመናገር ደፋር የሚሆነው ማነው? ቃለ እግዚአብሔርን በቃለ እግዚአብሔር ማነፃፀሩ እጅግ ወሳኝ ነገር ነው። ይህንን ካላደረግን፣ በመደናበር፣ በግራ መጋባት፣ ኢሚዛናዊነት እና የስህተት ሸርተቴ ውስጥ ቆመን እንሰጥማለን።

(7) ይህ ምንባብ ወደ ክርስቶስ የሚጠቁመው በምን መልኩ ነው?

ስለዚህ ነገር በክፍል አንድ ውስጥ ያልነው ነገር አለ፣ ነገር ግን ሲበዛ ልናከርረው የማንችለው ነጥብ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ክርስቶስ ነው። ትልቁ የመጽሐፍ ቅዱስ ጭብጥ ክርስቶስ ነው። እያንዳንዱ ክፍል ወደ እርሱ ይጠቁማል። አንድ

ምንባብ ወደ እርሱ የሚጠቁመው እንዴት እንደሆነ ማየት ካልቻልኩኝ፣ ያንን ምንባብ ልረዳው እንደሚገባኝ ያክል ስላልተረዳሁት ነው። ክርስቶስ ማዕከል ባልሆነበት ውስጥ የሥነ-ፍታቴ ትክክለኝነት የለም።

አሁን ስለ ጻፍኩት ነገር ይቅርታ ልጠይቅ አልችልም። በዙሪያዬ ሁሉ አንዳች የተለየ ነገርን የሚሉ ድምጾች አሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቶስ ማዕከል የሆነበት ነው ብሎ መጎትጎት ስህተት ነው ብለው ይናገራሉ። ያ ብዙ አልፎ መሄድ ነው ብለውም ይናገራሉ። እነርሱ እንደሚሉት ከሆነ ከዚያ ይልቅ መጽሐፍ ቅዱስ *እግዚአብሔር ተኮር* ነው ልንል ይገባል። *እግዚአብሔር* ተኮር የሆነውን ያክል አብዝቶ *ክርስቶስ*-ተኮር አይደለም።

በዚህ እስማማለሁ - ነገር ግን ሙሉ ለሙሉ አልስማማም! አዎን በእርግጥ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር የሆነ መጽሐፍ መሆኑን እና በእግዚአብሔር አብ፣ በእግዚአብሔር ወልድ እና በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ላይ ትምህርት እንዳለውም እስማማለሁ። ነገር ግን ይኸው እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ካልሆነ በቀር ከእኛ *ጋር* ምንም ጉዳይ የለውም። ያለው ብቸኛ እግዚአብሔር የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ነው። በክርስቶስ ካልሆነ በቀር ራሱን መቼም አይገልጥልንም። በክርስቶስ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ እርሱ የሚያደርስ መንገድ የለም። በእኛ ውስጥ የሚሠራው መንፈስ የክርስቶስ መንፈስ ነው። ወደ መንግሥተ ሰማይ ስንሄድ ልናየው የምንችለው ብቸኛው እግዚአ ብሔር ክርስቶስ ነው። ክርስቶስ ተኮር ካልሆነ በስተቀር ምንም ነገር፣ ጨርሶ ምንም ነገር እግዚአብሔር ተኮር ሊሆን አይችልም። አንድ ነገር ክርስቶስ ተኮር ሳይሆን እግዚአብሔር ተኮር ሊሆን ይችላል ብሎ ማሰብ ከባድ ስህተት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር የሆነ መጽሐፍ መሆኑን ማመን ስለ ክርስቶስ የሆነ መጽሐፍ መሆኑን ማመን ነው!

ነገር ግን እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እቅጩን ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ወደ ክርስቶስ አይጠቁምም። ለምሳሌ፣ በመክብብ መጽሐፍ ውስጥ ክርስቶስ ያለው የቱ *ጋር* ነው? መጽሐፉ የሚነግረን ከሚታየው ነገር ውስጥ እግዚአብሔርን ካጎደልነው፣ ሕይወት ምንም ትርጉም እንደሌላት፣ ነገር ግን እርሱን የምንወድድ እና የምናመልክ ከሆነ ደግሞ ሙሉው ትርጉም እርሱ እንደሆነ ይነግረናል። ነገር ግን እግዚአብሔርን ልናውቅ የምንችለው *እንዴት* ነው? የመክብብ መጽሐፍ ይህንን ጥያቄ በአእምሯችን ውስጥ ይቀሰቅሳል፣ ነገር ግን መልሱን አይሰጠንም። እግዚአብሔርን ለማወቅ ረሃብተኞች አድርጎ

ያስቀረናል፣ ነገር ግን ወደ እርሱ የሚያደርሰውን መንገድ አያሳየንም። ወደ ክርስቶስ የሚጠቁመን በዚህ መልኩ ነው። ብቸኛው መልስ ክርስቶስ ስለመሆኑ ጥያቄን ያነሣል። ስለዚህ *ግልጽ ባልሆነ* መልኩ ወደ እርሱ ይጠቁማል።

ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍት *ግልጽ በሆነ መልኩ* ወደ እርሱ ይጠቁማሉ። ይህ በእያንዳንዱ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍት ላይ የሚታይ እውነት የሆነ ነገር ነው። በእያንዳንዳቸው ውስጥ በስም ተጠቅሷል። እንግዲያው እነዚህ መጽሐፍት *በቀጥታ* ወደ እርሱ ይጠቁማሉ ልንል እንችላለን። ነገር ግን ወደ እርሱ በቀጥታ የሚጠቁሙ ነገር ግን በስም የማይገልጹት ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍት ደግሞ አሉ። ኢሳይያስ እና የመዝሙር መጽሐፍት የዚህ ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው። እንደ መጀመሪያዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ አምስት መጽሐፍት ያሉ ሌሎች መጽሐፍት ደግሞ ወደ እርሱ የሚጠቁሙት እንደ ትንቢያ፣ ስዕላዊ፣ ተምሳሌታዊ እና ከብረ-በዓላት ባሉ ሁኔታዎች ነው። እነዚህ መጽሐፍት ስለ እርሱ *ቀጥተኛ ባልሆነ መልኩ* የሚናገሩ ናቸው ልንል እንችላለን።

አሁን አጽንዖት የሰጠሁባቸው እነዚህ ቃላት ላይ አንዳንድ አንባቢዎች ምቾት ላይሰማቸው ይችላል። ነገር ግን እያንዳንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊ በእስትንፋሳዊነት እንዲጽፉ የረዳቸው መንፈስ የክርስቶስ መንፈስ እንደሆነ እንደሚስማሙ ግን አምናለሁ። የእርሱ አገልግሎት ሁልጊዜ ወደ *እርሱ* የሚጠቁም እንደሆነ እንደሚያስታውሱ አምናለሁ። ለዚህም ነው ጌታችን 'አባታችሁ አብርሃም ቀኔን ያይ ዘንድ ሐሤት አደረገ፥ አየም ደስም አለው።' (ዩሐ. 8፡56)፣ '. . . ሙሴ ስለ እኔ ጽፏልና' (ዩሐ. 5፡46) እና ዳዊት "ጌታዬ" ብሎኛል' (ማቴ. 22፡45) ማለት የቻለው። እያንዳንዱ ጸሐፊ ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጽፏል። የእነዚያ ጸሐፊያን እያንዳንዱ ሰባኪ ከዚህ የተነሣ የሰበከው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ነበር። የስብከቱ ማጠቃለያ እና ንጥረ-ነገር ክርስቶስ ካልሆነ፣ የሥነ-ፍታቴያዊ ትክክለኛ አለመሆን ተጠያቂ ነው።

የተሻሉ የሥነ-ፍታቴ ሰዎች ለመሆን ራሳችንን መርዳት የምንችለው እንዴት ነው?

ይህ ሁሉ እንዲህ ባለበት፣ ራሳችንን አጣዳፊ የሆነ ጥያቄ ልንጠይቅ ይገባናል፡- የተሻሉ የሥነ-ፍታቴ ሰዎች ለመሆን ራሳችንን ለመርዳት *በትክክል* ልናደርገው የምንችለው ምንድነው? የዚህን ጥያቄ ጠቀሜታ ማንም ሰው ሊያጋንነው

አይችልም። ትክክለኛ ሥነ-ፍታቴ ሲሞት፣ ስብከት ይሞታል፣ ደግሞም ያ እንዲሆን የሚፈልግ ይህንን መጽሐፍ የሚያነብ ማንም አይኖርም።

ልናደርግ የምንችለው ሦስት ነገሮች አሉ። እነዚያን ለማድረግ ፈቃደኞች ካልሆንን፣ መስበክን ማቆም አለብን። እኩል ለኩል ማድረግ የምንችለው ሁላችንም አይደለንም። ነገር ግን የምናስቀረው ሳይኖር ሁላችንም በእነዚህ ክልሎች ላይ አንዳንድ መሻሻሎችን ልናደርግ እንችላለን።

(1) የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀታችንን ልናሻሽል እንችላለን

ልናደርግ የምንችለው የመጀመሪያው ነገር የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀታችንን ማሻሻል ነው። ይህ ምእራፍ ከእያንዳንዱ የተጻፈ የእግዚአብሔር መገለጥ ጋር ጥብቅ እና ጥልቅ የሆነ ትውውቅ ማድረግ ምን ያክል ጠቃሚ እንደሆነ አጽንዖት ሰጥቶበታል። በአሁኑ ሰዓት እያደረግን ካለው ስለምናነብበው ነገር ብዙ ጥያቄዎችን ከመጠየቅ፣ ተጨማሪ ቍልፍ የጥናት ጥቅሶችን እና ምንባቦችን ከማሰላሰል እና በቀኑ ውስጥ ባሉት የተለያዩ አጋጣሚዎቹ የእግዚአብሔርን ቃል ለማሰላሰል ተጨማሪ ጊዜ ከመውሰድ ይልቅ እያንዳንዳችን መጽሐፍ ቅዱስን የበለጠ ማንበብ እንችላለን።

ዊንስተን ቸርቺል የሆነ የላቲን ቃላት ማብቂያ ላይ ያለውን ማስታወስ ባለመቻላቸው ከትምህርት ቤት ጓደኞቻቸው በአንደኛው ተመትተው ነበር። ኋላ ላይ በነበራቸው ሕይወት ልጁን የሚገርፉበት ብቸኛው ቅይማት የአፍ መፍቻ ቋንቋውን ባለማወቁ እንደሆነ ተናግረዋል።በተመሳሳይ ሁኔታ፣ በሁሉም ዓይነት ክልሎች ውስጥ ለሰባኪ ልዝቦች ልንሆን እንችላለን። ነገር ግን በአፍ መፍቻ ቋንቋው መጽሐፍ ቅዱስን የተዋጣለት በሚባል መልኩ የሚያውቅ እንዳልሆነ ከገባን ጥልቅ የሆነ ቅሬታችንን መግለጻችን ትክክል ነው።

(2) ማንበብ እንችላለን

እኛ ያለንን ያክል በርካታ መጽሐፍት ለማግኘት እድል የነበረው አንድም የሰባኪዎች ትውልድ አልነበረም! ዕውቀታችንን ልናዳብር እንችላለን፣ ያንን በማድረጋችንም በጎደለን በየትኛውም ክልል ላይ *መሠረታዊ* በሆነ መልኩ ልናሻሽለው እንችላለን። ስለ የትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ገጸ-ባህርይ፣ ስለ ተገለጠው የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፣ ስለ መጽሐፍ ቅዱሳዊው ነገረ-መለኮት፣ ስለ

ሥልታዊው ነገረ-መለኮት፣ ወይም የእግዚአብሔርን ቃል ለማወጅ ጠቃሚ ስለሚሆን የትኛውም የዕውቀት ዘርፍ ያለማወቅ ሰበብ የትኛውም ሰባኪ አይኖረውም።

በመጽሐፍት አማካኝነት የተነሣው ክርስቶስ ወደ ቤተክርስቲያኑ የላካቸው በሕይወት ያሉ ቢሆኑ የሞቱ ታላላቅ አስተማሪዎች እግር ስር ቁጭ ልንል እንችላለን። በተጨማሪም፣ በተለይ በምእራባዊው ዓለም ውስጥ ያለነው በርካታ ልዩ ልዩ ጥሪቶችን ለማግኘት እድሉ ያለን ሲሆን እነዚህም ጥሪቶች የተቀዱ፣ ኮምፕዩተር ፕሮግራም የሆነ፣ እና በድረ-ገጽ መልኩ የቀረቡ ናቸው። ጌታችን እንዲህ ብሏል 'ብዙም ከተሰጠው ሰው ሁሉ ከእርሱ ብዙ ይፈለግበታል፥ ብዙ አደራም ከተሰጠው ከእርሱ አብዝተው ይሹበታል፤'(ሉቃ12:48)።

ማንበብ በማይችል እና በማያነበብ መካከል ምንም እውነተኛ ልዩነት ተብሎ ብዙ ጊዜ ይነገራል። የምንኖረው ባተሌ በሆነ ዓለም ውስጥ ነው። አብዛኞቻችን በጫናዎች ውስጥ ነን። በርካታ ሰባኪዎች በአንድ ተጨማሪ ነገር ውስጥ የሚጨመቀሩበትን ነገር ማሰባ እስከማይችሉ ድረስ በርካታ የተሰጡላቸው ጉዳዮች አሏቸው። ነገር ግን ከሞላ ጎደል ሁላችንም፣ ከአንዳች አሳብ እና ቅድሚያ የምንሰጣቸው ነገሮች ቅንጅት ጋር ለማንበብ ጊዜ ልናገኝ እንችላለን - በእውነትም እንችላለን! ራሳችንን በእጅ ውስጥ ለማስገባት ጊዜው ነው። ጠቃሚነታችን ጥገኛ የሚሆነው በዚያ ላይ ነው። የወንጌል ጉዳይ አንባቢነታችንን የሚጠይቅ ነገር ነው።

(3) ምንባቡን ለመገንዘብ የሚረዱን ክህሎቶችን ልናዳብር እንችላለን

ዕብራይስጥኛ፣ አረማይክ እና የግሪክ ቋንቋዎችን ብቁ በሆነ ደረጃ መማር የሚችሉ ብዙ ሰባኪዎች የሉም፣ ነገር ግን አንዳንዶች ይችላሉ ደግሞም እያንዳንዱ የቃሉ ሰባኪ እነዚህን ቋንቋዎች ለመማር መሄድ እንዲኖርበት የማስበው ለዚህም ነው። ችሎታቸው መጠነኛ እንደሆነ ብዙዎቹ የሚደርሱበት በጣም በፍጥነት ነው። ነገር ግን ቢያንስ በማብራሪያ መጽሐፍት ውስጥ፣ በጥንታዊ ቋንቋዎች መፍቻ እና ሙያዊ መጽሐፍት ውስጥ ያሉ ቃላትን ለማወቅ በቂ የሆነ ያክል ሊማሩ ይገባል። ያንግ ወይም ስትሮንግ የሚባሉትን የጥቅስ ማውጫ አይነቶች፣ ፍታቴያዊ ማብራሪያዎች፣ የጥቅሶች መሃል መጽሐፍ ቅዱስን እና ሌሎች አሁን

ላይ በደንብ የሚገኙ ስፍር ቁጥር የሌላቸውን የቃላት መፍቻ ኢጋዦችን መጠቀምን ሁሉም መማር አለበት። ከዚህ ዝርዝር ውስጥ አስደናቂ የሆኑ የኮምፕዩተር ፕሮግራሞችን እና በየትኛውም ኮስታራ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ ጥቅም ላይ ለመዋል ዝግጁ የሆኑ የበይነ-መረብ ድረ-ገጾችን መጠቀምን አልረሳንም።

በሃያ አንደኛው ክፍለ-ዘመን ላይ መኖር አስደናቂ ነው። የቀደሙት አባቶቻችን ሊያልሙት እንኳን የማይችሏቸው ጥሪቶችን እናገኛለን። ሌላው ቢቀር ለአብዛኛው ተራ ሰባኪ እንኳን የእያንዳንዱን የቃለ እግዚአብሔር ክፍል ሰዋሰዋዊ ትርጉም እርግጠኛ መሆን የሚቻል ነገር ሆኗል። በማኅበረ-ምእመናኑ ፊት ቆሞ ከከፈተው ምንባብ ሥልጣን በድፍረት መናገር ይችላል። ነገር ግን የሚያሳዝነው ነገር በበርካታ ቦታዎች ላይ ይህ እየሆነ አይደለም። ይህ የሆነው ለምንድነው? አብዛኛውን ጊዜ ሰባኪው ሰነፍ ስለሆነ፣ ወይም በቀላሉ የሥነ-ፍታቴ ትክክለኝነትን ጠቀሜታ ስላልተገነዘበ ነው። የዚህ ምእራፍ ዓላማ ያንን ማስተካከል ነው።

* * *

የመወያያ ጥያቄዎች

1. በሥነ-ፍታቴ (exegesis)፣ ሥነ-አፈታት (hermeneutics) እና ሥነ-ማብራሪያ (exposition) መካከል ያሉትን ልዩነቶች እና በመካከላቸውም ያለው ጥብቅ ግንኙነትን በተመለከተ አንድ አንቀጽ ጻፉ።
2. ደካማ ሥነ-አፈታት ያላቸው አቶ ሽመልስ ቤተክርስቲያናቸውን ለሃያ አመታት በመጋቢነት አገልግለዋል፣ ከዚያም ጎበዝ የሥነ-ፍታቴ ሰው በሆኑት እና በዚያም ለሃያ አመታት በመጋቢነት ባገለገሉት በአቶ ደጀኔ ተተኩ። በእነዚያ አርባ አመታት ውስጥ የሆነውን የቤተክርስቲያኒቱን ታሪክ ተናገሩ።
3. ወጣት ለሆነ አገልጋይ ሥነ-ፍታቴያዊ ክህሎቶቹን እንዴት ሊስል እና ሊጠብቅ እንደሚገባው በመምከር ደብዳቤ ጻፉለት።

2

አስተምህሯዊ ፍሬ-ነገር

ስብከት ምን እንደሆነ፣ እንዲሁም ደግሞ ለሥነ-ፍታቴ ትክክለኝነት ራሱን እስካልሰጠ ድረስ ማንም ሰው እውነተኛ ሰባኪ እንዳልሆነ አይተናል። ምንም ነገር ከዚህ የሚበልጥ ጠቃሚ ነገር ሊሆን አይችልም። ይሁን እንጂ በጠቀሜታ ደረጃ ሁለተኛ የሆነ፣ ነገር ግን ዛሬ ላይ ችላ የተባለ ነገር በስብከት ውስጥ አለ። ያም *አስተምህሯዊ ፍሬ-ነገር* ነው።

ምን ማለታችን ነው?

ይህንን ቃል ስንጠቀም ምን ማለታችን ነው? እያልን ያለነው የምንሰብከው እያንዳንዱ ስብከት በአስተምህሮዎች የተሞላ መሆን አለበት የሚለውን ነው። ስብከታችን በነገረ-መለኮት የተሞላ መሆን አለበት። እንደውም፣ መጽሐፍ ቅዱስ መለኮታዊ መገለጥ ነው። ስለ እርሱ ልናምን የሚገባንን ደግሞም በአጭሯ ሕይወታችን ወቅት እርሱ የሚጠብቅብንን ይገልጥልናል። መጽሐፍ ቅዱስ በተሰበከበት በእያንዳንዱ አጋጣሚ የሚሰሙት ሰዎች በአስተምህሮው እና በተግባር ግንዛቤያቸው ሊያድጉ ይገባቸዋል።

የበርካቶቻችን የሕይወት ዘመን ቆይታ በሰባ እና ሰማንያ ዓመታት መካከል ያለ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን ለበርካታ ጠርቀም ያሉ ጊዜያት ለማንበብ ያ በቂ የሆነ ብዙ ጊዜ ነው። ከሠላሳ እስከ አርባ አመታት የሚሰብክ የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ሁሉንም ሥነ-ፍታቴ ይሠራባቸው ዘንድ በቂ ጊዜ ይኖረዋል። ደግሞስ የመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢ፣ በተለይም ሥነ-ፍታቴ የሚሠራ ምን አዲስ ግኝት ያገኛል? ቃለ እግዚአብሔር የአስተምህሮ ሥርዓትን የያዘ መሆኑን በአዲስ ግኝትነት ይደርስበታል። መላው መጽሐፍ ቅዱስ በአእምሮ ውስጥ እንዳለ፣ ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ ድንጋጌዎቹ፣ እና ስለ ፍጥረት፣ ስለ መግቦት፣ መዋጀት፣ ነፃ ፈቃድ፣ መጽደቅ፣ ፍርድ፣ መንግሥተ-ሰማይና ሲዖል፣ እንዲሁም ስፍር-ቁጥር ስለሌላቸው ሌሎች ርእሰ-ጉዳዮች የሚያስተምረውን መግለጽ ይቻላል። በሥልታዊ ነገረ-መለኮት ደካማ የሆኑ ሰዎች ያለ ምንም ማቅማማት በመጽሐፍ ቅዱስ እውቀትም እንዲሁ ደካማዎች ናቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ የአስተምህሮ ሥርዓት ያለው የመሆኑ እውነታ በስብከታችን ላይ ቀላል የማይባል ውጤት አለው። ምንም ያክል ትንሽ ብትሆን የምሰብክበት እያንዳንዱ ምንባብ የዚያ ሥርዓት አንድ አካል ሲሆን ለዚያም አንዳችን ነገር የሚያበረክት ነው። ይህ በስብከት ወቅት ሊወጣ የሚገባው ነው። ይሁን እንጂ፣ ያ ምንባብ የሥርዓቱን ሁለንተና የያዘ አይደለም፣ ደግሞም በምሰብክበት ጊዜ መላውን ሥርዓት የማገናዝብ ካልሆንኩ ልስትበት እችላለሁ። እንግዲያው ክፍሉ ሥርዓቱን ግልጽ እንዲያደርግ ምንባቡ ያስፈልገኛል፣ እንዲሁም ምንባቡን ግልጽ እንዲያደርግ ሥርዓቱን ላወጣ ያስፈልገኛል! ዝረቱ በሁለቱም አቅጣጫዎች መፍሰስ ይኖርበታል። ካልሆነ ግን፣ ስብከቴ ሚዛኑን ያልጠበቀ ይሆናል። የተዛባ ስብከትን ማን መስማት ይፈልጋል? ሰዎችን ወደ ስህተትስ የሚመራ ስብከትን ማን መስበክ ይፈልጋል?

መጽሐፍ ቅዱስ በእንቁላዎች የተሞላ ትልቅ ሣጥን ነው። እያንዳንዱን እንቁላ መልቀም፣ በቅርበት መመርመር እና በውበቱ መነካት አስደናቂ ነገር ነው። ነገር ግን እነዚያ የከበሩ እንቁላዎች በአክሊሉ ላይ ለእያንዳንዳቸው ቦታ እንዲኖራቸው ያደረገው የንጉሡ እንደሆኑ ለሰዎች የማንነግራቸው ለምንድነው? እንቁላዎቹ በሙሉ የንጉሡን ራስ ለማስጌጥ እርስ በርስ የሚገጣጠሙ የሚሆኑት እንዴት እንደሆነ ይዩ። ያዩትን ነገር መቼም አይረሱትም። ደግሞም እያንዳንዳቸውን እንቁላዎች ከዚህ ቀደም ያዩዋቸው እንደነበረው አድርገው ከእንግዲህ አይመለከቷቸውም።

መጽሐፍ ቅዱስ ከስድሳ ስድስት የአበባ መደቦች እንደተሠራ ክብር የመላበት የአትክልት ሥፍራ ነው። እንደሰባኪ እናንተ ሥራችሁ እንደ አስጎብኚ ሰዎችን ዙሪያውን ማስጎበኘት ነው። አንዳንድ አስጎብኚዎች አንዱን የአበባ መደብ ብቻ ለማሳየት ጎብኚዎችን ያስተናግዳሉ። ያ መልካም ነው፣ ነገር ግን አትክልት ሥፍራው ከዚያ የበለጠ የሚታይ ነገር አለው። ሌሎች አስጎብኚዎች ከአንዱ ይልቅ በብዙዎቹ መደቦች ላይ የተለዩ የሆኑ ቀለማት እና ተጨማሪ ዝርያዎች እንደሚገኙ ያስረዱና ጎብኚዎቻቸው ሁሉንም ቀያይ አበቦች ወይም በዚያ የጽጌረዳ ዝርያ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም አትክልቶች እንዲያዩ ይወስዷቸዋል። ያም መልካም ነው፣ ነገር ግን እንደዚያ ያለ የአትክልት ሥፍራን ከማየት ያለፈ ነገርም አለ። የእያንዳንዱን የአበባ መደብ ሥፍራ መለኮታዊ እቅድ የወሰነው መሆኑን እና የተከላውን ጊዜ፣ እንዲሁም እያንዳንዱን ቀለም እና እያንዳንዱ የአበባ ክፍል ያለውን ትልቅ እና አስደናቂ ንድፍ ጭምር የማያሳዩት

ለምንድነው? በአትክልት ሥፍራው ውስጥ ያለው ነገር ሁሉ በአትክልት ሥፍራው ካሉት ሌሎች ነገሮች ሁሉ ጋር በቀጥታ የሚገናኘው እንዴት እንደሆነ ቆም ብለው እንዲያዩ ለምን አይጠይቋቸውም? እያንዳንዱ ዝርዝር የባለቤቱን እንከን-አልባ ንድፍ ለመሥራት በጋራ የሚጣመርበትን እውነታ ከእነርሱ የሚደብቀኑት ለምንድነው?

ስዕላዊ ቋንቋችንን ለጊዜው ተወት እናድርገውና ወደ ስብከት ርእሰ-ጉዳይ በቀጥታ እንመለስ። ይህ የእኔ ጠንካራ እምነቴ ነው፡- በስብከቴ ማብቂያ ላይ አድማጮቼ የተሰበከውን ምንባብ ከተገነዘቡ፣ ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ትምህርት የተሰጠበትን *የእውነታ ሥርዓት* በተሻለ ካልረዱት፣ ያኔ ስብከቴ ከንቱ ነው ማለት ነው።

ከዚያም አልፌ እሄዳለሁ፣ በመደበኛነት የሚያደምጡኝ ሰዎች የአስተምህሮ ሥርዓትን መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምር ማየት ካልቻሉ እና ሥርዓቱን መገንዘብ ካልጀመሩ፣ ቃሉ የሚናገረውን ‘እንደዚያ ዓይነቱን ትምህርት’ (ሮሜ 6፡17) እና ‘ጤናማ ትምህርት’ (2 ጢሞ. 1፡13) እንድሰብክ የቤተክርስቲያን ራስ ልኮኝ እንደሆን እና እንዳልሆነ የምርጥ ልጠራጠር ይገባኛል።አዎን፣ ስብከቶቻቸው አስተምህሯዊ ፍሬ-ነገር የማይኖርባቸው ሰባኪዎች መስበክ ማቆም አለባቸው። ጌታ አልላካቸውም።

ስብከት አስተምህሯዊ ፍሬ-ነገር ከሌለው ምን ይሆናል?

እስካሁን ስለው የነረውን ነገር ጠቀሜታ ለማጉላት ያክል፣ ስብከት አስተምህሯዊ ፍሬ-ነገር የሌለው በሚሆንበት ጊዜ ምን እንደሚሆን አሁን ላሳያችሁ።

(ነ) እግዚአብሔር የሚገባውን ያክል አይመለከም ወይም አይወደድም

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ የአስተምህሮ ሥርዓት ያልገባቸው ሰዎች እግዚአብሔር ምን እንደሆነ አላወቁም። ለእርሱ *መንፈስ* መሆን ማለት ምን ማለት እንደሆነ አልተገነዘቡም። ስለ ሌላ ማንኛውም አካል ሊባል የማይችል ስለ

እርሱ ሊባሉ የሚችሉ ነገሮች እንዳሉ አይገነዘቡም። ለምሳሌ፣ እርሱ አይወሰንም፣ ዘላለማዊ እና የማይለወጥ ነው። እርሱ በማንነቱ ብቻ ሳይሆን በሁሉም ነገሩ የማይወሰን፣ ዘላለማዊ እና የማይለወጥ ነው። በውጤቱም፣ በመደነቅ የሚሸነፉ አይሆኑም። በፍቅር በሆነ ፍርሃትና መንቀጥቀጥ በመንፈሳቸው ወደ እርሱ መሄድ ማለት ምን እንደሆነ አያውቁም። ሕይወታቸውን በመደነቅ አያሳልፉም። ከመንፈሳዊ ተሞክሯቸው ውስጥ በጥቅሉ የሚጎድል ነገር አለ።

ሌላ አምላክ የለም። እርሱ ሕያው ስለሆነ እግዚአብሔር እውነተኛ እግዚአብሔር ነው። ደግሞም፣ አንድ እግዚአብሔር ብቻ ያለ ቢሆንም ቅሉ፣ እግዚአብሔር የሆኑ እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድ እና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሦስት አካላት አንድ አምላክ አለ። እነዚህ እያንዳንዳቸው በገዛ ራሳቸው መብት እግዚአብሔር ናቸው፣ ደግሞም እግዚአብሔርነታቸው አንዳቸው ከሌላኛቸው ተመሳሳይ ነው። በሥልጣንና ክብር የተለዩ፣ ደግሞም እኩል ናቸው። ነገር ግን ሦስት አማልክት አይደሉም። ይህንን ሁሉ የሚያውቅ ሰው ግራ ተጋብቷል። በመደነቅ የሚሆን ግራ መጋባት ይገጥመዋል። እግዚአብሔር ስለ ራሱ ያወጀውን ነገር ያምናል፣ ደግሞም በሚስጢሩ ፊት ይሰግዳል። ይህም እንዲሁ አስተምህሮ ላይ ደካማ ከሆኑ ሰዎች የሚሰወርባቸው ነገር ነው።

እግዚአብሔር በራሱ ውስጥ ከወሰነው ነገር በስተቀር በምንም ነገር ላይ ጥገኛ ያልሆነ ዘላለማዊ ዓላማ አለው። እግዚአብሔር፣ እግዚአብሔር እንደመሆኑ በየትኛውም ቦታ ላይ የሚሆኑትን ነገሮች የሚያዝዘው ዓላማውን በሚያስፈጽሙበት እና ክብርን ለስሙ በሚያመጡበት መልኩ ነው። መላውን አጥናፈ-ዓለም በቃሉ ብቻ ከምንም ነገር ውስጥ የፈጠረው ለእነዚህ ክስተቶች መድረክ እንዲሆን ሲሆን በዚያ መድረክ ላይ ያሉትን እያንዳንዱን ነገር እና እያንዳንዱን ሰው በግሉ ይቆጣጠራል። እንደዚያ በመሆኑ አስተምህሮዎችን የተማሩት ሰዎች ታሪክን ያጠናሉ፣ ጋዜጣ ያነብባሉ፣ ደግሞም ደስታዎችንና የሕይወት ስብራቶችን ሁሉ የሚያሳልፉት አስተምህሮዎችን ካልተማሩት ይልቅ እጅግ የተለየ በሆነ መልኩ ነው። እነርሱ ወደ ሰማይ ይመለከቱና በሁሉ ነገር ምስጋናን ይሰጣሉ።

(2) የድነት ሥላሴያዊ ባህርይ አይደነቅም

የእግዚአብሔር ትልቁ እና ምርጡ ፍጥረት የሰው ልጆች ናቸው። እኛን ልዩ የሚያደርገን በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠራችን ነው። ስብከቶችን በመደበኛነት የሚያደምጡ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ወንዶችና ሴቶች ይህ ምን ማለት እንደሆነ ፍንጩን እንኳን አለማወቃቸው የሚያሳዝን ነው።ከተለመደው ውጪ ሆኖ ስላላቸው ክብር እና በዚህ ዓለም ውስጥ ሊመላለሱበት ስለሚገባበት ትህትና የሚያውቁት ጥቂት ነው ወይም ምንም አያውቁም።

መላው ዝርያችን የተገኘው ብቻቸውን ከነበሩት ጥንዶች ሲሆን በእነዚያ ጥንዶች ምክንያትነት እግዚአብሔር ከሁላችን ጋር ወደ ኪዳን ገባ። እርሱን ለሚታዘዙት ሕይወትን ለማይታዘዙት ደግሞ ሞትን በተስፋ ቃልነት ሰጠ። የመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን ከህግ ውጭ በሆነ መልኩ አለመታዘዝን መረጡ፣ እኛ ሁላችንም እንደዚያው። በውጤቱም በእኛ ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር መልክ ተበላሸ፣ ተፈጥሯችን ሊመለስ በማይችል መልኩ ቆሸሸ ተቀለበሰ።ደግሞም እኛ እያንዳንዱን ቀን የምንኖረው ፈሪሃ-እግዚአብሔር በሌለው መልኩ መሆን ጀመረ። ከዚያ በኋላ እግዚአብሔርን ተድላ አናደርግም፣ ደግሞም ከእርሱ ጋር የመጓዝን የልብ-ለልብ ጣፋጭነት በጭራሽ አናውቀውም። ከዚያ ይልቅ፣ የምንኖረው ቀጣ ውስጥ እና በቀጣው መግለጫዎች ውስጥ ነው። በሕይወት ውስጥ ያሉ የትኛቸውም መሰናከል ይህንን እንዲያስታውሱን የታሰቡ ናቸው። በዚህ ጊዜ ሞት እኛን ለማጨድ እየጠበቀ ሲሆን ሲያል እኛን ለማቃጠል ይጠብቃል።

በአስተምህሯዊ ደረጃ ያልበሰሉት በሰው ዘር ጥፋት ላይ አያለቅሱም። ያለንበት ሁኔታ የእውነት መጥፎ የሆነውን ያክል ማየት አይቻላቸውም። ይህም ደግሞ ኮስታራ ኃጢአት የሆነ ውድቀት ነው። የተፋረሰ የሕይወትኪዳንን እና ሁላችንንም የሚነኩት አስጨናቂ ክትያዎቻቸውን የሚያስቡት እምብዛም ነው። የጸጋ ኪዳንን ሲሰሙ እፎይታን ሊያገኙበት አይለምኑም። በእርግጥ፣ አብዛኖቻቸው የጸጋ ኪዳን ምን እንደሆነ እንኳን አያውቁም! የዚህን አስተምህሮ ሙዚቃ ዘምረውም ሆነ አሸብሽበውበት አያውቁም።

እግዚአብሔር እግዚአብሔር የሆነውን ያክል በተለየ የወደዳቸው በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኃጢአተኞች አሉ። የራሱ በሆነ ምክንያት ከተበከለው ነገርና ከማይታዘዙበት የሕይወት ጥፋት ሊታደጋቸው እና ሞገሱን እንዲሁም

የዘላለምን ሕይወት ሊሰጣቸው ወሰነ። ይህንን ለማድረግ ያቀደው በሚዋጅ ሰው በኩል ነበር። ቤዛ የሆነው ይህ ዋጂ ሰው የሆነው እና እግዚአብሔር-ሰው እንደሆነ የቀረው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ዘላለማዊው የእግዚአብሔር ልጅ ነው።

ቍጥር ስፍር የሌላቸው ኃጢአተኞች ይኖራሉ ደግሞም ይሞታሉ፣ ደግሞም ተኮንነዋል፣ ነገር ግን ለመዳን መንገዱን የተገነዘቡ አንዳንዶችም አሉ። ይህ የሆነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የእነርሱ *ሃብይ* ስለሆነና በቃሉና በመንፈሱ ይህንን ለእነርሱ ስለሚገልጥላቸው ነው። እነርሱ በኃጢአት ተሞልተዋል፣ ነገር ግን ክርስቶስ ስለ እነርሱ ፍጹም የሆነን ኑሮ ኖሯል፤ እነርሱ ሊሞቱ ይገባቸው ነበር፣ ነገር ግን እርሱ ስለ እነርሱ ሞተ፤ ወደ እግዚአብሔር ሊመጡ አይችሉም ነበር፣ ነገር ግን እርሱ ስለ እነርሱ ማለደ፤ ይህ ሁሉ ደግሞ የሆነው እርሱ *ካህናቸው* ስለሆነ ነው። ሊያምኑ አይችሉም ነበር፣ ነገር ግን እርሱ እምነትን ሰጣቸው፤ እንዳመኑ መቆየት አይችሉም ነበር፣ ነገር ግን እርሱ ኃይልን ሰጣቸው፤ ይህ ሊሆን የቻለው እርሱ *ንጉሣቸው* ስለሆነ ነው።

ከከፍተኛ ክብሩ ክርስቶስ ወደዚህች ምድር የመጣው በመስቀል ላይ ለመሞት እና ወደ መቃብር ለመሄድ ነው። አሁን ድረስ እግዚአብሔር፣ ግን ደግሞ ሰውም ጭምር በመሆን ከሁሉ ወደሚበልጠው ከፍታ የተመለሰው ከዚህ *ሥፍራ* ነው። መንፈስ ቅዱስን ወዳዳናቸው በሚሊዮን ወደሚቆጠሩ ሰዎች ልቦች ልኳል፣ ደግሞም በዚህ እነርሱ በእርግጥም ወደ ድነት ልምምድ ውስጥ በእርግጥ ይገባሉ። ኃጢአታቸውን እና መጥፋታቸውን ያያሉ፣ ክርስቶስ ያደረገውንም ይገነዘባሉ፣ ከዚያም ሙሉ ለሙሉ ራሳቸውን ለእርሱ ዐደራ አሳልፈው ይሰጣሉ።

ክርስቲያናዊ አስተምህሮን የተገነዘቡ እነርሱ አብ ሁልጊዜ ለእነርሱ የተለየ ፍቅር እንዳለው እና ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደሰጣቸው ለማወቅ ትሁታን ናቸው። 'የእግዚአብሔር ልጅ ወደደኝ ደግሞም ራሱን ለእኔ ሰጠ' (ገላ. 2:20) ብለው ሲያንሾካሹኩ ትኩስ እንባዎች ፊታቸውን ያርሱታል። መንፈስ በሕይወታቸው ውስጥ የሚሠራው እና በግላቸው በእርሱ ሕይወት፣ ሞት እና ትንሣኤ ላይ ተጠቃሚዎች ለመሆን በክርስቶስ ላይ እንዲታመኑ ያመጣቸው እንዴት እንደሆነ በሚያስገርም አመስጋኝነት ይናገራሉ። ለእነርሱ፣ እግዚአብሔር አብ አዳኛቸው ነው፣ እግዚአብሔር ወልድ አዳኛቸው ነው፣ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አዳኛቸው ነው። ነገሮች ከዚህ በተለየ በማንኛውም መልኩ አይመለከቱም፣ ይህም ደግሞ በአስተምህሯዊ ሁኔታ ፍሬ-ነገር ያለው ስብከትን ሰምተው የማያውቁት የሚገለሉበት ነው።

(3) አማኞች ያሏቸውን እድሎች የማያውቁ ይሆናሉ

አብዛኛውን ጊዜ በክርስቲያናዊ ስብሰባዎችና ሌሎች ቦታዎች ላይ ወንዶች እና ሴቶች ምስክርነቶቻቸውን ይሰጣሉ። ወደ ጌታ ከመምጣታቸው በፊት ምን ይመስሉ እንደነበረ፣ እንዴት እንደዳኑ፣ እና ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ምን እንደተፈጠረ ይናገራሉ። ከአንድ ሰው ታሪክ ብዙ ልትናገሩ ትችላላችሁ። ለምሳሌ በአስተምህሮ ፍሬ-ነገር የዳበረ ወይም ያልዳበረ ስብከት ሰምተው እንደሆነና እንዳልሆነ ልትናገሩ ትችላላችሁ።

ሰዎች ወደ ክርስቶስ በሚመጡ ጊዜ ወዲያውኑ ሁሉም ስፋት ያላቸውን በረከቶች ወዲያውኑ ይቀበላሉ። በሞት ጊዜ እና በትንሣኤ ጊዜ እንኳን የበለጠ በረከቶችን በእርግጠኝነት ይቀበላሉ። ወዲያውኑ ከሚቀበሏቸው ውስጥ አንዳንዶቹ በረከቶች ቀዳሚ በረከቶች ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ቀዳሚዎቹን የሚያጅቡ ወይም ከእነርሱ ውስጥ የሚፈስሱ ተከታይ/ሁለተኛ/ በረከቶች ናቸው። ከቀዳሚዎቹ በረከቶች መካከል ሁለቱ የሚደርሷቸው በሙልዐታቸው ሲሆን አንደኛው የሚደርሳቸው እለት በእለት የሚጨመር ቢሆንም በከፊል ሆኖ ነው።

የክርስቲያን ሕይወት በረከቶች *ምንድናቸው?* አሁን የሚመጡት የትኞቹ ናቸው፣ የትኞቹስ ኋለኛ ሆነው ይመጣሉ? በዚያ ያሉት ቀዳሚ በረከቶች ምን ያክል ናቸው? ምን ያክሎቹ ሁለተኛ በረከቶች ናቸው? ቀዳሚ ከሆኑት መካከል የትኞቹ እንደ *ተግባር፣* ደግሞስ የትኞቹ እንደ *ሥራ* ይገለጻሉ? አስተምህሮታዊ በሆነ መልኩ የበለጸገ ስብከት የሰሙ ሰዎች እነዚህን ጥያቄዎች ይመልሷቸዋል፣ ደግሞም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለሚገኘው የክርስትና ዓይነት እውነተኛ ነፀብራቅ የሆነ ምስክርነት ሊሰጡም ይችላሉ። አስተምህሮታዊ ረሃብ ውስጥ ያሉት የትኛቸውንም ማድረግ አይችሉም፣ ደግሞም ክርስቲያናዊ ሕይወታቸው ከዚህ የተነሣ ደካማ ነው።

የክርስቲያን ሕይወት የመጀመሪያው በረከት *መጽደቅ* ነው። ይህ ከፍተኛው በረከት አይደለም፣ ነገር ግን ሌሎቹ በረከቶች ሁሉ ጥገኛ የሚሆኑበት አንደኛው በረከት ነው። ያ እግዚአብሔር ሊያደርገው የሚችለው ነገር ነው። ያ ከቸርነቱ ውስጥ የሚፈስ ተግባር ነው። እርሱ ኃጢአታችንን ሁሉ ይቅር ይላል፣ ደግሞም እርሱ የሆነውን ያክል ጻድቃን እንደሆንን አድርጎ የሚያስብበት ነው! ይህ የሆነው ኃጢአታችን በሙሉ በክርስቶስ ሂሳብ ላይ ስለተጣለ እና የእርሱ

እንከን አልባ ጽድቅ ወደ እኛ ሂሳብ ስለተላለፈ ነው። እኛ የጸደቅነው ባደረግነው በየትኛውም ነገራችን አይደለም፣ ነገር ግን ሙሉ ለሙሉ ክርስቶስ ለእኛ ባደረገው ነገር ላይ ነው። ራሳችንን ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አሳልፈን የሰጠንበት በዚያው ቅጽበት ላይ ጸድቀናል።

ክርስቲያኖች የሚለማመዷቸው ከሞላ ጎደል እያንዳንዳቸው የሚባሉት ውስጣዊ ችግሮች የሚመጡት መጽደቃቸውን ከመርሳታቸው ወይም ካለመገንዘባቸው ነው። መጽደቅ በተሰበከበት እና ሰዎች ያንን በተገነዘቡበት ቦታ ሁሉ ደስተኛ እና ደፋር የሆኑ አማኞችን ታገኛላችሁ። ነገር ግን ባልተሰበከበት እና ሰዎች ያንን ባልተገነዘቡበት ቦታ ሁሉ ሰዎች ድንጉጥ ሲሆኑ እና አላስፈላጊ በሆኑ ፍርሃቶች ሲጠመዱ ታገኟቸዋላችሁ። መጽደቅ ምን እንደሆነ ሰዎች ቢገባቸው በቤተክርስቲያናችን ውስጥ ያሉት አብዛኞቹ ችግሮች የተገባቸውን ያክል በተነኑ ነበር። ይህ ታላቅ እውነት ችላ የተባለባት ወይም የተጣመመባት ቤተክርስቲያን ምንኛ ታሳዝናለች!

ሁለተኛው የክርስትና ሕይወት ታላቅ በረከት *ልጅ መደረጋችን* ነው። ወንጌል የሚነግረን ከፍተኛው እድል ይህ ነው። ይህ እግዚአብሔር የሚያደርገው ነገር ነው። ይህ ከቸርነቱ የሚፈልቅ ተግባር ነው። እርሱ አባታችን እና እኛም የእርሱ ልጆች እና ወራሾች ሆነን ከመብቶች እና ከልዩ እድሎች ጋር የተባረክን ነን። የእርሱ ዘላለማዊ ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ የእኛ ታላቅ ወንድም ነው። ሌላው ክርስቲያን በሙሉ፣ ወንድም ቢሆኑ ሴት ወንድማችን ወይም እህታችን ናቸው። በመንፈስ ቅዱስ የሚሰጠን የቤተሰባዊነት ስሜት ሁላችንንም ያስተሳስረናል። የቤተሰብ ተግባራት የእኛ ናቸው፤ ነገር ግን አባት ለእኛ የሚያሳየው እንክብካቤ፣ ደግሞም በጸሎት ውስጥ ያለን ነፃነት እንዴት ታላቅ ነው! መደበኛ የሆኑ አስተምህሯዊ ስብከቶችን የማይሰሙ ክርስቲያኖች ልጅ ስለመሆን ብዙም አያውቁም፣ ደግሞም ደስታቢስ ወደመሆን እና ወደሁሉም ዓይነት ህግ-አጥባቂነት በቀላሉ ይወድቃሉ ብዬ ስናገር እያዘንኩ ነው።

ሦስተኛው ታላቅ የክርስትና ሕይወት በረከት *መቀደሰ* ነው። ይህም እንዲሁ እግዚአብሔር የሚያደርገው ነገር ሲሆን፣ ነገር ግን ይህ ሥራ እንጂ ተግባር አይደለም። በሌላ አነጋገር፣ እነዚህን ሁሉ በረከቶች ወዲያውኑ አንቀበልም። እግዚአብሔር ውስጣችንን ይለውጠውና የእርሱ መልክ በውስጣችን ይታደሳል። ይህ ውስጣዊ ለውጥ ማለት ባህርያችንም ጭምር መለወጥ ይጀምራል ማለት ነው። ቀስ በቀስ፣ በዝግታ ነገር ግን በእርግጥ፣ ኃጢአት መሥራታችን

እየቀነሰ ይሄድና እየጨመረ በሚሄድ መልኩ እግዚአብሔርን መፍራት ይኖረናል። እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ በመሥራት ላይ ስለሆነ ልክ እንደዚህ መሆን ላይ ልንሠራ ይገባናል። አስተምህሯዊ ስብከት እንዲህ ያለውን አስደናቂ በረከት የሚነግረን ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን ክርስቲያናዊ ሕይወትን ለመኖር የእግዚአብሔርን መመሪያዎች ጭምር ይነግረናል።

ሁሉም ዓይነት ሌሎች በረከቶች ሦስቱን ቀዳሚ በረከቶች ያጅባሉ፣ ከእነርሱም ውስጥ ይፈስሳሉ። ለምሳሌ፣ እግዚአብሔር እንደሚወድደን የግል የሆነ ማረጋገጫ ወደማግኘት እንመጣለን። ኅሊናችንን ሰላም ይሞላዋል። ምንም ነገር የማይወስደውን ደስታ መንፈስ ቅዱስ ይሰጠናል። በመንፈሳዊ ሕይወታችን ብርቱዎች እየሆንን እንሄዳለን። ሁሉም ዓይነት እንቅፋት እና ፈተና እያለም ቢሆን፣ እስከምንሞት ድረስ ማመናችንን እንቀጥላለን።

ነገር ግን በሞት ጊዜ ምን ይሆናል? በርካታ ክርስቲያኖች የዚህን ጥያቄ መልስ ስለማያውቁ በጭንቀት ይሞታሉ። አስተምህሯዊ ፍሬ-ነገር ያለው ስብከት እንዲህ ካለው እርግጠኛ ያለመሆን ያድናቸው ነበር። በስብከት ውስጥ አስተምህሮ ያለውን ሥፍራ እንደነገሩ ማለፍ በመጋቢያዊ አገልግሎት ውስጥ ስሜት የለሽ እና ደግ ያለመሆን ነው።

ሞት የነፍስ እና የአካል መለያየት ነው። አካሉ የክርስቶስ ንብረት ሆኖ ትንሣኤን በሚጠብቅበት ወቅት የአማኙ ነፍስ፣ አሁን ላይ ኃጢአት አልባ በመሆን ወዲያውኑ እና በንቁኑ ኅሊና ወደ ክርስቶስ ህልውና ይሄዳል። ትንሣኤ ለእያንዳንዱ ክርስቲያን የክብር ቀን ይሆናል። ልክ እንደ ክርስቶስ የትንሣኤ አካል የራሱም አካል ይኖረዋል። በመጨረሻው ፍርድ ወቅት ነፃ ነህ ይባልለትና ወደ መንግሥተ ሰማይ እንዲገባ አቀባበል ይደረግለታል። እግዚአብሔርን ሙሉ ለሙሉ፣ ፍጹም በሆነ መልኩ እና ለዘላለም ያጣጥማል። መሆን የሚቻለውን ያክል ደስተኛ ይሆናል። አዎን፣ ክርስቲያን አስደናቂ የሆነ መጪ ጊዜ አለው። የትኛውም እውነተኛ ሰባኪ ስለዚህ ነገር ዝም ማለት አይችልም።

(4) አማኞች እንዴት መኖር እንዳለባቸው ግራ ይጋባሉ

ሰማይን እንናፍቃለን፣ ነገር ግን አሁን ድረስ ያለነው በዚህ ምድር ላይ ነው። እንደ ክርስቲያን ወንዶችና ሴቶች፣ ቅድሚያ ልንሰጣቸው የሚገቡን ነገሮች ምን

ሊሆኑ ይገባቸዋል? እለታዊ ባህርያችንን ሊገዟቸው የሚገቡ መርኾዎች ምንድናቸው? አስተምህሯዊ ስብከት የማይሰሙ ሰዎች መልሱን አያውቁትም።

የጌታ ሰዎች እንደመሆናችን፣ አንድ ቀላል የሆነ ግዴታ አለብን፡- እግዚአብሔርን መታዘዝ። ይኸው ነው። ይህን ያክል በቀጥታ የቀረበ ነው። እንዳለመታደል ሆኖ፣ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ አማኝ ወንዶች እና ሴቶች በየእለቱ ሲነቁ እግዚአብሔር ከእነርሱ ስለሚጠብቅባቸው ነገር በጥልቀት ግራ የሚገባቸው ናቸው። በቀኑ ውስጥ የሚመራቸው ግልጽ የሆነ መርኾ የላቸውም፣ በውጤቱም ጎዳናቸው ብልኅ እና ጠቃሚ ባልሆኑ ውሳኔዎች የተሞሉ ናቸው። ማድረግ ያለባቸውን የማያውቁት አሁንም አሁንም ነው። ራሳቸው ተሰቃይተው ወደ ሌሎች ሰዎች ሕይወት ውስጥ በተደጋጋሚ ስቃይን ያመጣሉ።

እግዚአብሔር የሚፈልገው አጠቃላዩ ነገር እንድንታዘዘው ብቻ ነው። ያ በዔድን የአትክልት ሥፍራ እውነት እንደነበረው ሁሉ ዛሬም እንዲሁ እውነት ነው። ማንም ብንሆን ማን፣ የትም ብንሆን የት፣ ያለንበት ሁኔታ ምንም ቢሆን ምን፣ በሕይወት ውስጥ አስተማማኝ በሆነ መልኩ ሊመራን በቂ የሚሆነው መርኽ አንድ ብቻ ነው፡- እግዚአብሔርን ልንታዘዝ ይገባናል።

እናስ እግዚአብሔር የሚፈልገውን የምናገኘው እንዴት ነው? ህጉ ይነግረናል። ያ ህግ የሚያካትተው የብሉይ እና አዲስ ኪዳን ስድሳ ስድስት መጽሐፍትን ነው - ከዚያ የሚጨመርም ሆነ የሚቀነስ የለም። እግዚአብሔር ከእኛ የሚጠብቀው እንድናምን እና እንድናደርግ የሚጠብቅብንን ሁሉ እንድናደርግ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። መላው መጽሐፍ ቅዱስ ያስፈልገናል፣ ነገር ግን ለመጽሐፍ ቅዱስ ተጨማሪ የሆነ ምንም ነገር አያስፈልገንም። እርሱ በቂ ነው።

ነገር ግን አንድ ችግር አለብን። በአማካኝ ያለው የታተመው መጽሐፍ ቅዱስ ወደ 1200 ገጾች ያሉት ሲሆን በርካቶቻችን በደንብ አናውቀውም ወይም በቀላሉ አናስተውሰውም። እንግዲያው ለእለታዊ ሕይወታችን ተጨባጭ እውነታ ልንተገብረው የምንችለው እንዴት ነው?

እግዚአብሔር የሰማይ አባታችን ሲሆን እርሱ በገርነት የተሞላ ነው። ከእኛ የሚጠብቀው ምን እንደሆነ ማጠቃለያውን ሰጥቶናል። ይህ ማጠቃለያ ዐሥርቱ ትእዛዛት ተብሎ ይጠራል። እነዚህም የተቀናበሩት እግዚአብሔር

በብሉይ ኪዳን ጊዜያት ላይ ለሕዝቡ የሰጣቸው ዐሥር ዐረፍተ-ነገሮች ናቸው። እነርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሁሉም ሌሎች ጊዜያት ላይ ለሁሉም ሰዎች አጽንዖት የሰጠባቸው ናቸው። ጌታችን የማጠቃለያውን ማጠቃለያ ይሰጠን ዘንድ የበለጠ ደግ ነው! እንዲህ ይላል፦

> ኢየሱስም እንዲህ አለው፦ ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ።ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት።ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች፥ እርስዋም፦ ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት።
>
> (ማቴ. 22፡37-40)

ዐሥርቱ ትእዛዛት አስደናቂዎች ናቸው። አምላካችን እግዚአብሔር ማን እንደሆነ፣ ለምን ልንወድደው እንደሚገባን፣ እና ያንን ፍቅር እንዴት ልንገልጥ እንደምንችል ይነግሩናል። በልባችን ውስጥ ምን ሊካሄድ እንደሚገባ፣ እንዴት ልናመልክ እንደሚገባ፣ ምላሳችንን እንዴት ልንጠቀም እንደሚገባን እና ጊዜያችንን እንዴት ልንጠቀም እንደሚገባ ይነግሩናል። በቤተሰባችን እና በማኅበረሰባችን መካከል እግዚአብሔርን እንዴት እንደምናከብር ይነግሩናል። ሕይወትን፣ ትዳርን፣ ንብረትን እና እውነትን ዋጋ እንድንሰጠው ያስተምሩናል። በዚህኛው ሕይወት እንዴት ኑሮዬ ይበቃኛል እንደምንል እና ለሚቀጥለው እንዴት የተሻለ እንደምንዘጋጅ ያሳዩናል። ከሞላ ጎደል የትኛውም ሰው ሊያስታውሳቸው በሚችላቸው መልኩ በጣም ቀላል ናቸው። ሕይወት ዘመናቸውን እነርሱን ሲያጠኑ የኖሩ ሰዎች እንኳን ሳይቀሩ ከዚያ በሚያገኙት ጥበብ መደነቃቸው የሚቀጥሉበት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በአንድ መንገድ ወይም በሌላ የሚገኙ እና በክርስቶስ ሕይወት ውስጥ ውብ በሆነ መልኩ ስጋ ለብሰው የታዩ ናቸው። እርሱ እንደሚያስፈልገን ያሳዩናል፣ ተፈጻሚነታቸውም በእርሱ ያገኛሉ።

አስተምህሯዊ ስብከት የሚሰሙ ክርስቲያኖች በሕይወት ውስጥ እንደ እውር ሆነው መመላለስ አያስፈልጋቸውም። መንገዱን በግልጽ ያዩና ከጌታቸው ጋር በዚያ ይጓዛሉ። ይህንን የሚያደርጉት በደስታ እንጂ እያጉረመረሙ አይደለም። ደግሞም እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ በግልጽ ከሚጠይቀው ነገር በስተቀር የትኛውንም ነገር ለማድረግ እንደማይገደዱ በጎሊናቸው ስለሚሰማቸው፣ አስደናቂ የሆነ ነፃነትን ያጣጥማሉ። ደስተኝነታቸው እና

ቅድስናቸው በእርግጠኝነት ፍጹም የሆነ የሚባል አይደለም፣ ነገር ግን በሰማይ የሚጠብቃቸው ነገር እውነተኛ ቀዳሚ ቅምሻ ናቸው።

(5) የግል ምስክርነታቸው ይመናመናል

አስተምህሯዊ ስብከትን አማኞች በማይሰሙበት ጊዜ፣ ግራ የሚገባቸው እንዴት መኖር እንዳለባቸው ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ለማያምኑት ማለት ስላለባቸው ነገር ጭምር ነው። በውጤቱም፣ ነፍሳትን የመማረክ ደስታን በተመለከተ የትኛውንም ነገር የሚያውቁት ብዙ ክርስቲያኖች አይደሉም። በዓለም ዙሪያ ሁሉ ባልዳኑት ሰዎች ዙሪያ የሚኖሩ፣ በተመሳሳይ መጓጓዣ ይጓዛሉ፣ በፋብሪካ፣ ቢሮዎች፣ እርሻዎች፣ ዩኒቨርስቲዎች እና ትምህርት ቤቶች ውስጥ አብረዋቸው የሚሠሩ ሕዝቦቹን ጌታ አስቀምጧል። አብዛኞቹ ክርስቲያኖች የሥራ ሕይወታቸውን የሚያሳልፉት መጋቢ ወይም ሚስዮናዊ ሄዶበት በማያውቅበት ቦታዎች ላይ ነው። ወንጌል ለማሰራጨት ያለው እድል እንዴት ግሩም ነው! ነገር ግን አማኞች ማለት ያለባቸውን ስለማያውቁ አሁንም አሁንም እድሉን እያጡ ናቸው።

ልክ እንደ ማንኛውም ሌላ ክርስቲያን፣ በአስተምህሯዊ ስብከት የተማሩት ፍርሃት ይገጥማቸዋል። መናገር ይፈራሉ። ነገር ግን አንዴ ሲናገሩ፣ ቃላት አያጥሯቸውም። የሚያስተላልፉት መልእክት ምን እንደሆነ ያውቃሉ። ይህ የሆነው ያላመኑ ሰዎች ሊያውቁት የተገባውን አስተምህሯዊ ስብከት ስላስተማራቸው ነው።

ያልዳኑ ሰዎች ምንም እንኳን እንደ አባት እና ጓደኛ የማያውቁት ቢሆኑም፣ እግዚአብሔርን እንደሚያውቁ ሊነገራቸው ይገባል። ይህ እውነት እንዳልሆነ በማቅማማት ይቃወሙ ይሆናል፣ ነገር ግን ጉዳዩ ይህ እንደሆነ አማኙ መጎትጎቱን ሊገፋበት ይገባል። ደግሞም የእነርሱ ማቅማማት እና መቃወም ወንዶች እና ሴቶች እውነትን የሚጫኑት እንዴት እንደሆነ ምሳሌ ነው። እውነታ እንደሆነ ውስጣቸው የሚነግራቸውን ነገር በግልጽ እየካዱ ናቸው። ሐቀኞች አይደሉም። የማታለል ተጠያቂዎች ናቸው። አፎቻቸው እና ልቦቻቸው እርስ በርስ ይቃረናሉ።

ያልዳኑ ሰዎች በደላቸው ከዚህም በላይ መሆኑ ሊነገራቸው ይገባል። በልባቸው ውስጥ የትክክል እና ስህተት ስሜት አላቸው። የእግዚአብሔር ህግ ትክክል እንደሆነ ያውቃሉ፣ ይሁን እንጂ ያንን በአሳብ፣ በቃል እና በተግባር

ይጥሳሉ። ይህንን የሚያደርጉት በየቀኑ ሲሆን በዚህም በየቀኑ የፈጠራቸውን እና መልስ ሊሰጡት በፊቱ የሚቆሙለትን እግዚአብሔር ያስቆጡታል። ሕይወት አጭር ናት፣ ሞት እርግጠኛ የሆነ ነገር ነው፣ ደግሞም በመጨረሻው ፍርድ ወቅት ተጠያቂዎች ያደርጋቸዋል። በእግዚአብሔር ላይ ማመጻቸውን ከቀጠሉ፣ በመላው ማንነታቸው ሊወድዱት የማይፈልጉ ከሆኑ፣ ተከትሎ የሚመጣውን ነገር ሊቀበሉ ይገባቸዋል። እርሱ የማይገደብ እና ዘላለማዊ ነው። የሚያስቆጡት እንዲህ ያለውን አካል ነው። ከዚህ የተነሣ ፍትህ የሚጠይቀው የቅጣት ዓይነት እንዲሁ የማይገደብ እና ዘላለማዊ ይሆናል።

የአስተምህሯዊ ስብከት ትምህርት የተሰጣቸው አማኞች ስለዚህ ሁሉ ነገር ግልጽ ይሆንላቸዋል። ይህ መልእክት ክርስቶስን የሚመስል ሕይወት ካላቸው ሰዎች በሚመነጭ ፍቅር እና ቀኑብ ሊቀርብ እንደሚገባ ግልጽ ሆኖላቸዋል። ነገር ግን ያ ሊሸረሸር አይገባውም። ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ላልዳኑት መናገር እንዳለባቸውም ግልጽ ሆኖላቸዋል። የትኛውም ኃጢአተኛ እንዲጠፋ እግዚአብሔር አይፈልግም። ኃጢአተኞች ያለፈውን ጊዜ ሊያሻሽሉ አይችሉም፣ እንዲሁም ራሳቸውን ሊያድኑ አይችሉም። ስለዚህ በሕይወቱ፣ ሞቱ እና ትንሣኤው ኃጢአተኞችን የታደገውን አዳኝ እግዚአብሔር ላከ። አስተምህሯዊ ስብከቶችን የተማሩ አማኞች ይህንን አዳኝ እንዳይገፉት ይጋብዛሉ፣ ይመክራሉ እና ያዝዟቸዋል። ነገር ግን ራሳቸውን ለእርሱ እንክብካቤ እንዲጥሉ፣ ራሳቸውን ለእርሱ ዐደራ እንዲሰጡ፣ እና ከእርሱ አገዛዝና እንክብካቤ በታች እንዲኖሩ ይነግሯቸዋል።

ያልዳኑ ሰዎች ንስሃ ሊገቡ ይገባል። ኃጢአታቸውን ሊያዩ፣ ጥፋታቸውን ሊያምኑበት፣ ከዚያ የተነሣ ሊያፍሩ እና መንገዳቸውን ሊቀይሩበት ይገባቸዋል። ስለ እግዚአብሔር ደግነት እና ምህረት አመስጋኞች ሊሆኑ፣ እና ወደ ክርስቶስ ሊመጡ፣ እርሱን ለመውደድ እና ለመከተል አእምሯቸውን ሊያዘጋጁ ይገባቸዋል። እርሱን መከተል ማለት በእርሱ ቃል መኖር፣ ከእርሱ ሰዎች ጋር ወንጌልን በምትወድድ ቤተክርስቲያን ውስጥ በግልጥ ጎብረት ማድረግ እና በጸሎት ከእርሱ ጋር መጓዝ ማለት ነው።

ስለዚህ አስተምህሯዊ ስብከት የተማረ ክርስቲያን ምንም እንኳን እውነተኛ ወዳጅነት የግል ሕይወቱ አንድ ክፍል ቢሆንም፣ የወንጌል መልእክትን ‘ለተጠቃሚው የሚያመች’ አያደርገውም። እርሱ ስለ ኃጢአት፣ ጥፋተኝነት፣ ስለ እግዚአብሔር ቀኖጣ እና ሲያል ይናገራል። ስለ እግዚአብሔር ደግነት፣ ስለ ልጁ

እና ሊያድን ፈቃደኛ ስለመሆኑም ይናገራል። ንስሃ ሳይገባ የዳነ ማንም ሰው ያለመኖሩን እውነታ አይደብቅም። ሰዎች ወደ ክርስቶስ እንዲመጡ ይለምናል። ወደ ክርስቶስ መምጣት በስም ብቻ የሚሆን ነገር ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን ለቃለ እግዚአብሔር መታዘዝን፣ በቤተክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ንቁ ሆኖ መሳተፍን እና ለጸሎት የተሰጡ መሆንን የሚያካትት ነው።

በአስተምህሮ ደካማ የሆኑት ሁልጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት እውነተኛ ንጽብራቁ ያልሆነ ነገርን በማምጣት የሚያበቁ ናቸው። መልእክታቸው አብዛኛውን ጊዜ ከእግዚአብሔር አይጀምርም። ከበደለኝነታቸው ይልቅ በሰዎች ፍላጎት ላይ አጽንዖት የመስጠት አዝማሚያ አላቸው። ንስሃ የመግባትን ርእሰ-ጉዳይ በተደጋጋሚ በማቃለል ይጥላሉ። የወንጌልን ታላቅ የማዳን እውነታዎች የሚያቀርቡት አብዛኛውን ጊዜ ግራ አጋቢ በሆነ መልኩ ነው። ወደ ክርስቶስ መምጣት ማለት ሕዝቦቹ ለሚሰባሰቡበት ማኅበረ-ምእመን የተሰጡ መሆን ማለት እንደሆነ ማሳየት የሚያቅታቸው ከሞላ ጎደል ሁልጊዜ ነው። በአጭሩ፣ መልእክታቸው ጠንካራ፣ አስገዳጅ፣ ክብር የሞላው እና የሚያስደስት ከመሆን ይልቅ በጠቅላላው አቅመ-ቢስ እና ኃይል የሌለው ነው። የእግዚአብሔር እውነተኛው ወንጌል በዓለም ውስጥ በጣም በመንቀራፈፍ እየተሠራጨ መሆኑ ብዙም አያስደንቅም!

(6) የቅድስና መንገድ ግልጽ ያልሆነ ይሆናል

አስተምህሮን ያልተማሩ አማኞች በሌሎች ክልሎችም ላይ ደካሞች ናቸው። የእግዚአብሔር ሰው ወይም ሴት የሚሆኑት እንዴት መሆኑን በተመለከተ አብዛኛውን ጊዜ በጣም ግልጽ አይሆንላቸውም። ክርስቲያኖች የሚያድጉት እንዴት እንደሆነ አይገነዘቡም። በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ብርቱዎች የሚሆኑት እንዴት እንደሆነ አያውቁም።

በዚህ የሃያ አንደኛ ክፍለ ዘመን ላይ የዚህን ምሳሌ ከሞላ ጎደል በየቦታው ልናይ እንችላለን። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዘመናዊ አማኞች ቅድስና ማለት *የምትቀሰሙት* አንዳች ነገር እንደሆነ አድርገው የሚቆጥሩበትን ግንዛቤ ወስደዋል። ራሳቸውን እንዲህ ባለው አካባቢ ወይም ድባብ ውስጥ ብታስከብቡ፣ ያኔ አንዳች ነገር ይደርስባችኋል። ጌታ ወደ እናንተ ይቀርባል፣ ራሳችሁ ስትበረቱ

ይሰማችኋል፣ ደግሞም በአንዳች መንፈሳዊ ጥንካሬና ሃይል ወደ ትክክለኛው ሕይወት መመለስ የምትችሉ ትሆናላችሁ።

ነገሮችን እንዲህ ባለ መልኩ መመልከት ሙዚቃ በበርካታ የክርስቲያኖች ስብሰባዎች እና የዘመኑ ቤተክርስቲያናት ውስጥ እንዲህ ያለ ጠቃሚ ቦታ ያገኘው ለምን እንደሆነ በሰፊው ያብራራል። አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያኖች በጋራ የሚያሳልፉት ከግማሽ በላይ የሚሆነው ጊዜ የሚሰጠው ለዝማሬ ነው። ዝማሬው ሲቀጥል፣ ሰዎች በሚጨምር መልኩ የተዘዋወሩ እና ከፍ የተደረጉ መስሎ ይሰማቸዋል፡፡ መንፈሳዊ ነገሮች ለእነርሱ ውድ ነገሮች እንደሆኑ እና ጌታም ከእነርሱ ጋር እንደተገናኘ መስሎ ይሰማቸዋል። መንፈስ ቅዱስ በመካከላቸው እየሠራ መስሎ ይሰማቸዋል፣ ዓለም የማትሰብ፣ እና በመንግሥተ-ሰማይ መሆን አስደናቂ ነገር እንደሆነ ይሰማቸዋል።

ይህንን እየጻፍኩ ያለሁት እንደ አከራሪ ሙዚቀኛ እና የጥንት፣ እንዲሁም ጥንታዊም ሆነ ዘመናዊ መልካም የሆኑትን የትኛቸውንም ዝማሬዎችን መዘመር እንደሚወድድ ሰው ሆኜ ነው። ነገር ግን እውነታዎች እውነታዎች ናቸው፣ እኛም ልንክዳቸው አንችልም። የአዲስ ኪዳኗ ቤተክርስቲያን በተለየ ሁኔታ ሙዚቃ-ተኮር እንዳልሆነች እና በጋራ መዘመር የሕይወቷ አንድ ትልቅ አካል አለመሆኑ የማይካድ ሃቅ ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን የሕይወቷን የመጀመሪያዎቹን ስድስት መቶ አመታት ያሳለፈችው የሙዚቃ መሣሪያዎችን ሳትጠቀም ነው። የጌታችን ሐዋርያት እና የመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን ክርስቲያኖች ዛሬ ላይ የክርስቲያኖችን ስብሰባ ቢካፈሉ ለሙዚቃ በተሰጠው ስፍራ በእጅጉ ግራ የሚጋቡ መሆናቸው የማያከራክር እውነታ ነው።

አስተምህሮን የተማሩ አማኞች በእርጥም የሙዚቃ አፍቃሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ፣ ነገር ግን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ውስጥ ለሙዚቃ አስፈላጊ የሆነ ቦታን እንዳይሰጡ ጠንቃቆች ናቸው። ይህ የሚሆነው መንፈሳዊ እድገት የሚከናወነው እንዴት እንደሆነ ስለሚያውቁ ነው። መንፈሳዊ እድገት እናንተ የምትቀስሙት ወይም የምትመጥጡት ነገር አይደለም። ካላችሁበት ድባብየተነሣ በእናንተ ላይ የሚሆንባችሁ አንዳች ነገር አይደለም። በስሜቶች በጥሩ ሁኔታ ሊገለጽ ይጽላል፣ ነገር ግን በስሜቶች አማካኝነት ወደ እናንተ ⸗ይመጣም። ወደ እናንተ የሚመጣው የእግዚአብሔር ቃል በ⸗⸗ምሯችሁ ውስጥ ውጤት እንዲፈጥር መንፈስ ቅዱስ ሲያደርግ ነው።

ቅዱሳት መጽሐፍት የእግዚአብሔር ቃል ናቸው። የትኛውንም ትኩረት ብንሰጣቸው ወይም ባንሰጣቸው ይህ እውነት የሆነ ነገር ነው። አንዳንድ ጊዜ በሚነበቡ ጊዜ፣ አእምሯችን ወደሌላ ቦታ ይሄዳል። በእነዚያ ቅጽበቶች ላይ ቅዱሳት መጽሐፍት በእኛ ላይ ምንም ውጤት ስለማይኖራቸው ምንም ዓይነት መንፈሳዊ እድገት አይከናወንም። ነገር ግን በሌላ አጋጣሚዎች ላይ ቅዱሳት መጽሐፍት ያስደነግጡናል። እያሉት ያለውን ነገር በተመለከተ አንዳች ግንዛቤ አለን፣ በተመሳሳይ ደግሞ፣ ይቆሰቁሱናል ደግሞም ያንቀሳቅሱናል። ይህ ብቻ አይደለም፤ እነዚያንም ልንተገብራቸው እንደሚገባን ጨምረን እናያለን። *ይህ* የሚሆነው በመንፈሳዊ ሁኔታ ስንበረታ ነው።

ሕዝቦቹ በጋራ ሲሰባሰቡ ቃለ እግዚአብሔር በሕዝባዊ ሁኔታ ይነበብ ዘንድ የጌታ ፈቃድ ነው። ይህ እንደውም መጽሐፍ ቅዱስን በራሳችን ብቻ ከማንበብም በላይ በጣም ጠቃሚ ነገር ነው። እንዲህ ያለውን ነገር እንዴት ልናገር ቻልኩ? ይህ የተባለበት ምክንያት እግዚአብሔር ቃሉን ለግለሰቦች ስላልሰጠ፣ ነገር ግን *ለቤተክርስቲያኑ* ስለሰጠ ነው፤ ደግሞም መጽሐፍ ቅዱስ በእጅጉ የሚባረከው እና የተሻለ የሚገነዘቡት የሚሆነው ሕዝቦቹ በጋራ ሲሰባሰቡ ነው።

ይሁን እንጂ፣ ቃለ እግዚአብሔርን በሕዝባዊ ሁኔታ ማንበብ ብቻውን በቂ አይደለም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአባቱ ቀኝ ተቀምጧል፣ መጽሐፍ ቅዱስን ለሕዝቡ እንዲያስተምሩ የታጠቁ በርካታ ሰዎችን ወደ ቤተክርስቲያኑ ልኳል። ኃጢአተኞች በወንጌል እውነት አምነው የሚድኑበት ዋናው መንገድ ስብከት የመሆኑን ያክል፣ በተመሳሳይ መንገድ ሕዝቦቹን በቅድስና ለማነጽ፣ እነርሱን ለማጽናናት፣ እና እስከ ሕይወታቸው መጨረሻ ድረስ እንዳመኑ እንዲቆዩ ለማድረግ የእግዚአብሔር ዋናው መንገድ ስብከት ነው። በርካታ ስብከቶችን ሳያደምጥ የሚገባውን ያክል ሊያድግ የሚችል አንድም ክርስቲያን አይኖርም። ይህ የማይቻል ነገር ነው። በእርግጥ ሥራቸውን በጥሩ ሁኔታ እንዲፈጽሙት ሰባኪዎችን የሚጠይቀው ይህ እውነታ መሆኑ አይካድም - በስብከት ላይ የተጻፈችው ይህች ትንሽ መጽሐፍ አንዳንድ ሰዎች ከሚገምቱት በላይ የበለጠ ጠቃሚ የሆነችው ለዚህ ነው።

አስተምህሮን የተማሩ ክርስቲያኖች ይህንን ሁሉ ያውቃሉ፣ ደግሞም ስብከት እንዲህ ባለው መንገድ ሊደመጥ እንደሚገባውም ያውቃሉ። መደበኛ በሆነ መልኩ ልንሰማው የምንችለውን ሁሉ ማድረግ እስከሚገባን ድረስ ስብከት

በእጅጉ ወሳኝ በሆነ መልኩ ለመንፈሳዊ ብርታታችን ያስፈልገናል። ስብከት ከመስማታችን በፊት፣ ልባችንን ልናዘጋጅ እና ለሰባኪውም ልንጸልይ ይገባናል። በስብከቱ ወቅት ውሸት የሆነውን ልንጥል እና እውነትን ልናምን እንዲሁም ልንወድድ ይገባናል። በሚጠናቀቅ ጊዜ፣ በአእምሯችን ልናሰላስለው ጊዜ ልንወስድና ልንቸገር፣ ከዚያም ያንን ሁሉ ወደ ተግባር እንዴት ልናመጣው እንደምንችል ልናይ ይገባናል። ለመንፈሳዊ እድገት መንገዱ ይህ ነው። ክርስቶስን የሚመስል ባህርይ እግዚአብሔር የሚሰጠን እንዲህ ነው።

(7) የቤተክርስቲያን ሕይወት የቅደም ተከተል አይደለም

ከሌሎች አማኞች ጋር ስብከቶችን ለመስማት ከመሰባሰብ ባለፈ በቤተክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ተጨማሪ የሆነ ነገር አለ። ይህ የቤተክርስቲያን በጣም ጠቃሚ የሆነው ተግባር ነው፣ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ቃል የሚሰበኩ ስብከቶች በማይቀር ሁኔታ ግልጽ እንደሚያደርጉት ብቸኛው ተግባር ግን አይደለም!

አስተምህሮን የተማሩ ክርስቲያኖች ስለ ቤተክርስቲያን ሕይወት ይገነዘባሉ። ሰዎች ንስሃ እንደገቡና በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳመኑ ሲናገሩ፣ ያ ንግግራቸው ሊመረመር እንደሚገባ ያውቃሉ። ያንን ንግግር የተሻለ ለመመርመር የተሻለ ሥፍራቸውን የያዙት ሰዎች ክርስቶስንበመውደድ፣ መጽሐፍ ቅዱስን በማመን መሪነት ላይ ያሉበመንፈሳዊ ሁኔታ የበሰሉ የክርስቲያኖች ስብስብ ናቸው። ንግግሩ በጥሩ ሁኔታ መሠረት የያዘ ከሆነ፣ አዲሱ አማኝ ይጠመቅና ወደዚያ ማኅበረ-ምእመን ኅብረት ይቀላቀላል።

አዲስ ክርስቲያን በተገቢ ሁኔታ እንክብካቤ ሊያገኝ የሚችለው እንዲህ ባለው ዐውድ ውስጥ ብቻ ነው። አጥቢያ ቤተክርስቲያን በእምነት አዲስ ወንድም ወይም እህት እንደሆነ አድርጋ ትቀበለዋለች። አዲሱ አማኝ ሊያስፈልገው የሚችለውን የትኛውንም ፍቅር፣ ግንዛቤ፣ ድጋፍ፣ ተግባራዊ እገዛ፣ ትምህርት፣ የሚያድስ ማቅኛ ትሰጠዋለች። በክርስቶስ አዲስ ሰዎች መሆናችንን እና ሁሉንም አማኞች በሁሉም ቦታዎችና በሁሉም ትውልዶች ያሉትን በሚጨምር እውነተኛ ቤተክርስቲያን ውስጥ አባላት ለመሆናችን ማረጋገጫ የምንሰጠው በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ዐውድ ውስጥ እምነትን በመጠበቅ ነው።

በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ በአግባቡ መደበኛ የሆነው እጅግ ማራኪ የሆነው ነገር የጌታ እራት ነው። መንፈሳዊ ሕይወታችን በቃሉ እና በጸሎት እንዲበረታ ብቻ ሳይሆን፣ በኃይማኖት ሥርዓት ጭምር እንዲሆን የክርስቶስ ፈቃድ ነው። አንዳንድ ሰዎች 'ኃይማኖታዊ ሥርዓት' የሚለውን ቃል አይወድዱም፣ ነገር ግን የተሻለ ቃል ተገኝቶ አያውቅም። ጥምቀት ከኃይማኖት ሥርዓቶች አንደኛው ሲሆን የጌታ እራት ደግሞ ሁለተኛው ነው። ክርስቶስ ራሱ እስካልባረካቸው እና የእርሱ መንፈስ በእነዚህ ውስጥ እስካልሠራ ድረስ ከእነዚህ ማናቸውም ምንም አይጠቅሙንም። ለእኛ ያደረገውን ሙሉ ለሙሉ እንድናደንቅ እና በእርሱ ላይ ያለንን እምነት እንዲሁም በእርሱ መደሰታችንን እንዲያበረታ ስለ ክርስቶስ እና ስለወንጌሉ የሚያስተምሩን ስእላትን እያንቀሳቀሱ ናቸው።

እንደ ክርስቲያኖች በአንድ ጊዜ አንዴ እንጠመቃለን፣ ይህም ደግሞ የሚሆንብን አንዴ ብቻ ነው። ጥምቀት የደቀመዝሙርነት መለያ ምልክት ነው። አሁን ላይ እንደ አዳኝ እና ጌታ ሥሉሥ አምላክ እንዳለን ለማሳየት፣ እና ላገኘነው ድነታችን ለራሳችን ሳይሆን ሙሉ ለሙሉ ለእርሱ ጸጋ ባለእዳዎች መሆናችንን ለማሳየትጥምቀት የሚከናወነው በአብ፣ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም ነው።

የጌታ እራት የተለየ ነው። የጌታ እራት እንደ ቤተክርስቲያን አባላት በጋራ የምንደሰትበት እና በሕይወታችን ውስጥ በመደበኛ ሁኔታ የምናደርገው ነገር ነው። ክርስቶስ በደነገገበት መንገድ በጋራ ኅብስቱን እንቆርሳለን፣ ከዚያም በጋራ ከጽዋው እንጠጣለን። ኅብስቱ የሚወክለው የክርስቶስን አካል ሲሆን ጽዋው የሚወክለው ደግሞ ደሙን ነው። በመብላታችን እና በመጠጣታችን ሞቱን እናስታውሳለን ደግሞም እናውጃለን። ይህንን ስናደርግ (እያደረግን ያለውን ነገር እስከገባን ድረስ)፣ ልቦቻችን ከእርሱ ጋር ይገናኛሉ፣ ደግሞም በመንፈሳዊ ሁኔታ እናድጋለን፣ እንበረታለንም። ልቦቻችን በፍቅር ኅብረት እርስ በርስ ይገናኛል። በእኛ ውስጥ የሚሆነው ነገር በእውነት ከውጫዊው ክብረ-በዓል እና ምልክቶች በላይ የበለጠ ጠቃሚ የሆነው በውስጣችን የሚከናወነው ነገር እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። ምክንያቱም ልባችን በምናደርገው ነገር *ውሳኖ* ካልሆነ፣ መላው ተሞክሮ በመንፈሳዊ ሁኔታ ጥፋት የሚያስከትል መሆኑ የተረጋገጠ ነው።

ይህ ሁሉ ከስብከት ጋር ምን አገናኘው? ስብከት አስተምህሯዊ ፍሬ-ነገር ሊኖረው ይገባል፣ ደግሞም ይህ ፍሬ-ነገር የጎደለው ስብከት ከሰሚዎቹ ላይ ሊቆጠር የማይችሉ ጠቀሜታዎችን የሚያሳጣ ነው በሚለው ነጥብ ላይ

የማጠናከሪያ አሳብ መስጠታችንን እየቀጠልን ነን።የወንጌል-ተኮር ቤተክርስቲያን አባላት ሳይሆኑ የትኛውንም እውነተኛ መንፈሳዊ ሂደት ማድረግ እንደማይችሉ ስላልተረዱ በሚሊዮን የሚቆጠሩ አማኞች በመንፈሳዊ ድካም ውስጥ ይሸመደመዳል። ክርስቲያኖች እንደሆኑ የሚናገሩ ሰዎች በዚያ አሉ፣ ነገር ግን ከራሳቸው በስተቀር ንግግራቸው በማንም ያልተመረመረላቸው ስንቶች ናቸው? ተጠምቀው የማያውቁና መጽሐፍ ቅዱስ ተኮር ለሆኑ ማኅበረ-ምእመናን ባለመሰጠት ለክርስቶስ ግልጽ በሆነ ያለመታዘዝ ሕይወታቸውን የሚመሩ ሰዎች ስንቶች ናቸው?

መንፈሳዊ እድገታችሁን ሳትገድቡ ልትቀሩበት እንደምትችሉበት ዓይነት ነገር በማድረግ በጌታ እራት ላይ መገኘትን ችላ የሚሉ ሰዎች ስንቶች ናቸው?መጽሐፍ ቅዱስን ከሚሰበክላችሁ ይልቅ በራስ ማንበብ የበለጠ ጠቃሚ እንደሆነ የሚያምኑ የክርስቲያኖችን መጠን መቀነጠር የሚችለው ማነው? ለጋ ክርስቲያኖች እንዲያድጉበት *ብቸኛው* አመቺ ሥፍራ አጥቢያ ቤተክርስቲያን እንደሆነች የተቀመጠውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ለማውለብለብ ደፋር የሆኑ አማኞች የት ናቸው? ክርስቶስ የደነገገው ከመሆኑ እውነታ ባሻገር ከሞላ ጎደል ባለማቀፋዊነት የቤተክርስቲያን የሥነ-ሥርዓት እርምጃ የማይወደድ እየሆነ ስለሄደው ምን እንላለን?አንድ ሰው ለአጥቢያ የክርስቲያኖች ማኅበረ-ምእመንምንም መሰጠት በሌለው ጊዜ እንኳን የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል መሆኑን መናገሩ የምር ተደርጎ የሚወሰድበትን የውሸት ማብቂያ እንሰማ ይሆን?

ምን መደረግ ይችላል? ይህንን ብዥታ የትኛውም ነገር አንጥሮ ሊያወጣ ይችላልን? አዎን፣ አንድ ነገር እና አንድ ነገር ብቻ - በአስተምህሯዊ ደረጃ ፍሬ-ነገር ያለው ስብከት ጋር መመለስ!

(8) ጸሎት የማስመሰል ነው

ስለ ጸሎት ተጨማሪ ነገር ሳንናገር ይህንን ምእራፍ ልንዘጋ አንችልም። በዓለም ላይ ያለ እያንዳንዱ ክርስቲያን ጠቃሚ ነገር እንደሆነ ይነግሯችኋል። አብዛኞቹ የክርስትና ሕይወትን በጸሎት እንደምንጀምር፣ እና ከዚያም በኋላ በእያንዳንዱ ቀን ላይ የምንፈልገው ነገር እንደሆነ ይነግሯችኋል። ነገር ግን በእርግጥ ጸሎት

ምንድነው? መልሳቸው ግልጽም የተሟላም ስላልሆነ ብዙዎቹ እንዲያቅማሙ የሚያደርጋቸው ጥያቄ ይሄ ነው።

በአስተምህራዊ ደረጃ የተማሩ ክርስቲያኖች እንዲህ ያለው ችግር የለባቸውም። ምንም እንኳን በቃላት የሚገለጽ ቢሆንም፣ ጸሎት ማለት የቃላት ጉዳይ እንዳልሆነ ያውቃል። ጸሎት የልብ ጉዳይ ነው። ጸሎት የልብ መሻቶቹን ለእግዚአብሔር የሚያሳውቅበት ነው። ዋናው መሻቱ እግዚአብሔር *የሚሻውን* ነገር ብቻ የሚሰጥበት ነገር ነው።

በክርስቶስ ካልሆነ በቀር ወደ እግዚአብሔር ህልውና መግቢያ እንደሌለ የክርስቲያን ልብ ያውቀዋል፣ ይህም በመሆኑ፣ መሻቶቹ ለእግዚአብሔር የሚታወቁ እንዲሆኑ፣ በክርስቶስ ላይ ሙሉ ለሙሉ በክርስቶስ ላይ የሚታመን እንዲሆን አድርጓል። ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረግን የሚያደናቅፍ ብቸኛው ነገር ኃጢአት እንደሆነ፣ ስለዚህም የሚያውቀውን እያንዳንዱን ኃጢአት ለመናዘዝ ፈጣን እንደሆነ ክርስቲያኑ ያውቀዋል። በተጨማሪም፣ ጸሎት ማለት ጥያቄዎችን ማቅረብ እንደሆነ አድርጎ አያየውም፤ ስለ እያንዳንዱ የታየ መልካምነት ለማሰብ ከልብ የሆነ መሻት አለው።

መሻቱ ከሚጸልይ ልብ ውስጥ ወደ እግዚአብሔር ፈሰስ ሲሆን፣ ተቆጣጣሪ እንደሌለው ጎርፍ በመሆን አይፈስስም። ይህም የሚሆነው ሌሎቹን ሁሉ መሻቶች የሚገዛ ሌላ መሻት ስላለና ያም መሻት እግዚአብሔርን ለመታዘዝ የሆነ መሻት ነው።መንፈሳዊ አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች ምስቅልቅል እና ዝብርቅርቅ ባለ መልኩ እንዲጸልዩ አይፈልግም። ይህ የሚሆነው በቃሉ ውስጥ በርካታ የጸሎት ምሳሌዎች ስለሰጠን፣ ነገር ግን በዋናነት ልጁ ለደቀመዛሙርቱ እንዴት እንደሚጸልዩ ስለነገራቸው ነው። 'አባታችን ሆይ' በሚል ጌታ ያስተማረን ጸሎት አርአያችን ሊሆን ይገባል። አርከቴክቶች አርአያዎችን የሚገነቡት በውስጣቸው ሊኖሩባቸው አይደለም፣ ነገር ግን ለግንባታዎቻቸው እንደ መሠረት አድርገው ሊጠቀሙባቸው ነው። በተመሳሳይ መልኩ የሚጸልይ ልብ 'የአባታችን ሆይ' ጸሎትን ደጋግሞ በማለት አይረካም፣ ነገር ግን ከውስጣዊው ማንነቱ የሚፈልቀውን መሻቶች ለማቀናጀት ይጠቀምባቸዋል።

እንግዲያው፣ እውነተኛ ጸሎት ለኢየሱስ ወይም ለመንፈስ ቅዱስ መደረጉ እውነት ነው። የሚመጣው በመታመን፣ በፍቅር እና ለአብ ባለ መደነቅ ነው። ስለ እርሱ ታላላቅ አሳቦችን ያስባል፣ ደግሞም ሌሎች ተመሳሳይ ነገር

እንዲያደርጉ ይመኛል። ክፋት እንዲጣል፣ መንግሥቱ በዓለም እንዲስፋፋ፣ እና የመጨረሻው መንግስቱ በቶሎ እንዲመጣ ይጠይቃል። በምድር ላይ ያለችው ቤተክርስቲያን በሰማይ እንዳሉት የተመረጡት መላእክትታዛዥ እንድትሆን ይናፍቃል። የክርስቶስ ቤተክርስቲያን እያንዳንዱ አባል እለታዊ ፍላጎቶቻቸው እንዲቀርብላቸው ይጠይቃል። ጥልቅ በሆነ ኅሊና ኃጢአቱን በማወቅ ይቅርታን ይጠይቃል፣ ነገር ግን በራሱ ይቅር በሚል መንፈስ እስከተገዛ ድረስ ብቻ ይሆናል። በኃጢአት አሳብ ላይ ይናወጣል፣ ከፈተና እንዲታደገው ይጮኻል እንዲሁም በዲያቢሎስ ኃይል ውስጥ እንዳይወድቅ ይለምናል። እግዚአብሔር ዘላለማዊ ንጉሥ በመሆኑ እና ለእርሱ እንጂ ለሌላ ለማንም የማይናገር በመሆኑ የእፎይታ ትንፋሽን ይተነፍሳል።

በጣም ጥቂት የሆኑ ዘመናዊ ክርስቲያኖች በጸሎት ግዙፋን ናቸው። በስብሰባዎቻችን ላይ የሚጸለዩ ጸሎቶች አብዛኛውን ጊዜ በእጅጉ ስስ፣ ተራ፣ ድግግሞሻዊ እና እንደውም ስህተተኛ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱሳዊውን አካሄድ የሚከተል እንደሆነ፣ ከእግዚአብሔር ጋር እንድንገጣጠም፣ እና ተደንቀን፣ ትሁታን ሆነን እና አክብረነው እንድንቀር የሚያደርግ ጸሎት የምንሰማው አልፎ አልፎ ነው። ምን ተፈጠረ? እውነተኛ ጸሎት ለሁልጊዜ ቀርቶልናል? በጥቅሉ ሁሉም ነገር፣ ሁሉም ነገር ሁኔታውን ለውጦታልን?

እውነተኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስብከት ሁኔታውን ሊለውጠው ይችላል። እንዲህ ያለው ስብከት በሥነ-ፍታቴ ትክክለኛ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በተጨማሪም በአስተምህሯዊ ሁኔታው ተጨባጭ ነው። እግዚአብሔር ከባረከው፣ ሁሉንም ጭንቅ ይፈውሳል፣ ደግሞም በዚህ ምእራፍ ውስጥ የጠቀስናቸውን ስህተቶች በሙሉ ያስተካክላል። አስተምህሯዊ ያልሆነ ስብከት ቤተክርስቲያንን እያጠፋት ነው። ነገሮች እንዳሉት ሆነው እንዲሄዱ ልንፈቅድ አንችልም። ነገሮችን የተገላቢጦሽ ልናደርግ እና በእግዚአብሔር እርዳታ በማያሳፍር፣ ከልብ በሆነ፣ ክርስቶስን ማዕከል ባደረገ፣ አስተምህሯዊ ፍሬ-ነገር ባለው ስብከት እንገለብጠዋለን።

የተግባር ሥራ

1. “ያለ ነገረ-መለኮት ስብከት የለም - ቢያንስ በአዲስ ኪዳን ስሜቱ’ (ዶናልድ ማክሌዎድ)።[3] ይህንን አነጋገር ተወያዩበት።
2. በ1 ሳሙኤል ምእራፍ 3 ላይ ልትሰብኩ የምትችሉትን ስብከት አስተዋጽዖ ስጡ፣ እንዲሁም በውስጡ ልታካትቱት የምትችሉትን አስተምህሯዊ ትምህርት ዘርዝሩ።
3. ሁሉም አበይት የእምነት አስተምህሮዎች ለአማካይ ማኅበረ-ምእምናን በትምህርትነት ሊሰጡ የሚችሉበትን ተግባራዊ ጥቆማዎች ስጡ።

[3] ‘Preaching and Systematic Theology’ by Donald MacLeod (Chapter 19 in *Preaching*. ed, Samuel T. Logan (Welwyn, Evangelical Press, 1986), p. 246.

3

ግልጽ የሆነ መዋቅር

ስብከት ምን እንደሆነ ተምረናል። ስብከታችን በትክክለኛ ሥነ-ፍታቴ እና በአስተምህሯዊ ፍሬ-ነገር ተለይቶ የሚታወቅ መሆን እንዳለበትም ተነጋግረናል። ነገር ግን እኛ በምንናገርበት ጊዜ አድማጮቻችን ሊከተሉን ካልቻሉ እና ያልነውን ነገር ከዚያ በኋላ ሊያስታውሱ ካልቻሉ፣ ተግተን የሠራንበት ስብከት ይባክናል፣ ደግሞም እድሎቻችን በሙሉ ይጠፉብናል። መልካሙ የምሥራች ይህ ሊከሰት የማያስፈልገው መሆኑ ነው። ስብከቶቻችን ሁልጊዜ *ግልጽ የሆነ መዋቅር* ካላቸው ለመከተልና ለማስታወስ ቀላል ይሆናሉ።

ሕዝቦቻቸውን የሚወድዱ ሰባኪዎች የስብከቶቻቸውን መዋቅር በተመለከተ በጣም ጠንቃቆች ናቸው። ስብከታቸው አንድነት፣ ቅደም ተከተላዊ ሥርዓትና መመጣጠን ያለው እስከሆነ ድረስ መስመራቸውን አብዛኛው ተራ ሰው እንኳን እንደማይስተው ያውቃሉ።*አንድነት* ማለት መልእክቱ በሙሉ እርስ በርሱ የተያያዘ ነው ማለት ነው፤ ከበርካታ ያልተያያዙ ትንንሽ ስብከቶች የተውጣጣ አይደለም።*ቅደም-ተከተላዊ ሥርዓት*ማለት ስብከቱ ወደ ጡዘቱ በሚያመራ መልኩ አንዱ ሌላውን በአሳማኝ ሠንሰለት ከሚከተል የተናጠል አሳቦች የተሠራ ነው ማለት ነው። *የተመጣጠነ መሆን* ማለት እያንዳንዱ አሳብ ተገቢው ቦታ የተሰጠው ነው፣ ጠቃሚ ያልሆኑ ነገሮች ጎልተው አይታዩም፣ ደግሞም ጠቃሚ ነገሮች በአነስተኛ መልኩ አይቀርቡም ማለት ነው። በስብከቱ በምድር ላይ እጅግ የከፋ የተባለው ሰባኪ እነዚህን ሦስት ቃላት ካስታወሰ ወዲያውኑ ያሻሽላል።

'ቅደም-ተከተላዊ ሥርዓት የመንግሥተ-ሰማይ የመጀመሪያው ህግ ነው' ተብሎ ብዙ ጊዜ ተነግሮኛል። በእርግጥም እግዚአብሔር የቅደም-ተከተላዊ ሥርዓት አምላክ ነው። በቅዱስ ሥላሴ ላይ የሚያስብ ማንኛውም ሰው ሥርዓት እንዳለ እና በእግዚአብሔር ማንነት ውስጥ በውበቱ የሚያስደነግጥ ተመጣጣኝነት እንዳለ ያውቃሉ። እግዚአብሔርን መፍራት ለሌለበት ሌላኛው ቃል ሥርዓተ-ቢስነት የሚለው ነው።

በነገረ-መለኮት ኮሌጅ ውስጥ ወይም በሰሜን አሜሪካ ውስጥ እንደሚጠራው በሴሚናሪ ውስጥ ስለ ስብከት ለበርካታ ዓመታት አስተምሬያለሁ። ተማሪዎቼ ለመጋቢያዊ አገለግሎት እና ለባህል-ዘለል የወንጌል ተልእኮ ሥራ እየሠለጠኑ የነበሩ ወንዶች ነበሩ። ሁሉም የተነቃቁ ሰባኪዎች መሆን ይፈልጉ ነበር። ነገር ግን አንዳንዶቹ ያንን የሚያሳኩ እንደማይመስሉ ዐውቅ ነበር፤ ደግሞም በዚህ ግምቴ ተሳስቼ የማውቀው ከስንት አንዴ ነበር። ይህ የሆነበት ምክንያት በተማሪዎች ማስተናገጃ ወይም በቤቶቻቸው ጎብኝቼያቸው ስለማውቅ ነበር።

ፍሬው ብዬ ስለምጠራው ተማሪዬ ልንገራችሁ። በተማሪዎች መኖሪያ ቤቱ ሄጀ በነበኘሁት ቀኑጥር፣ ጽድት ያለ ልብስ ለብሶ ንፁህ በሆነች እና በተስተካከለች ክፍል ውስጥ ዝብርቅርቅ ባላለ ጠረጴዛ ላይ ሲሠራ አገኘዋለሁ። ልብሶቹ በንፅህና ታጥፈው በመሳቢያዎቹ ውስጥ ወይም በቀኑምሳጥኑ ውስጥ ተንጠልጥለው ተቀምጠዋል። ለፍሬው ሥርዓት ያለው ነገር በጣም ጠቃሚ ነገር ሲሆን ነገር ግን ንፅህናው ጎብኚዎቹን ምኞት እንደሚነሣ ያለ የወግ-አጥባቂ ዓይነት አይደለም። ሥርዓት ያለው ቅደም-ተከተል *በነፍሱ* ውስጥ ያለ ነገር ነው። ከዚህ የተነሣ ጥሩ ሰባኪ እንደሚወጣው እጠብቅ የነበረ ሲሆን በእርግጥም እንደዚያ መሆኑን አረጋግጧል። ልጆች እንኳን ያለ ችግር ሊከተሉት እስኪችሉ ድረስ አሳቦቹ እርስ በርሳቸው በሚስብ አሳማኝነት የሚያያዙ ሆነው የሚስብ እና ኃይለኛ ስብከቶችን ይሰብካል። ሕዝቦቹ ይወድዱታል ደግሞም ጠቃሚነቱ ከዓመት ዓመት እየጨመረ የሚሄድ ነበር።

ሌላኛውን ተማሪዬን ጀምበሩ ብዬ የምጠራው ሲሆን እርሱ ደግሞ ከፍሬው ሙሉ ለሙሉ ተቃራኒ የሆነ ሰው ነበር። የጀምሩ ክፍል የሚመስለው የምር ቦምብ የመታው ያክል ነበር! መቼም ንፁህ ሆኖ አያውቅም። ወለሉ በልብሶች፣ ኩባያዎች፣ መጽሐፍት እና በወረቀት ቁራጮች የተሞላ ነበር። ጠረጴዛው በተመሰቃቀሉ ወረቀቶች ከምር የተሞላ ከመሆኑ የተነሣ አብዛኛውን ጥናቱን የሚያደርገው የተመሰቃቀለ ጫካ በሚመስለው አልጋው ላይ ተቀምጦ ነበር። ለሥርዓት ዋጋ አይሰጥም ነበር። የሕይወቱ አንድ አካል አልነበረም። በውጤቱም፣ የስብከቱም አንድ አካል አልነበረም። የሚለው ነገር ጥሩ ነበር፣ ነገር ግን አሳቦቹ የተቀናጁ አልነበሩም። የሰዎቹ ጭንቅላት በግራ መጋባት እንዲጋጭ በሚያደርግ መልኩ አንዳቸው በሌላቸው ላይ የሚመሰቃቀሉ ውድ ነገሮች ከአፉ ይወጡ ነበር። ለረጅም ጊዜ በመጥፎ ሁኔታ ከሰበከ በኋላ፣ ጀምበሩ አሁን ላይ

እየተሻሻለ መሆኑን ስነግራችሁ በደስታ ነው - ነገር ግን ይህ የሆነው ግልጽ የሆነ መዋቅርን ጠቀሜታ *በሰተመጨረሻ* ስላየ ነበር።

ግልጽ መዋቅር ማለት እያንዳንዱ የምንሰብከው ስብከት *መግቢያ*፣ አንዳች የሚባል ነገር (በተለምዶ 'አካል' የምንለው) እና *መደምደሚያ* አለው ማለት ነው። አሁን እነዚህን ሦስት ነገሮች በየተራ እንመለከታቸዋለን።

[1] *መግቢያው*

ፍቺው

መግቢያ የሚያካትተው ተከትሎ ለሚመጣው ነገር ሁሉ አድማጩን የሚያዘጋጅ የመክፈቻ ንግግር ነው። ይህ ምእራፍ በመግቢአ ጀምሯል! *መግቢያ* ማለት ወደ ቤቱ የሚቀበላችሁ በረንዳ፣ የጸሐይ መውጣትን የሚቀድም ንጋት፣ የተቀነባበረውን *ሙዚቃ* እንድትሰሙ የሚያዘጋጃችሁ ቀዳሚ *ሙዚቃ*፣ እና ከመግባችሁ በፊት የመብላት ፍላጎታችሁን የሚከፍት ቀዳሚ ምግብ እንደማለት ነው።

ዓላማ

መግቢያ አንድ ዓላማ ብቻ አለው፡- ልትናገሩት ባለው ርእሰ-ጉዳይ ላይ ሰዎች ፍላጎት እንዲያድርባቸው ያዘጋጃል። ለመስበክ ስንቆም፣ ከፊት ለፊታችን ሁሉም ዓይነት ሰዎች እንዲሁም ልናሸንፋቸው የሚገቡን ሁሉም ዓይነት *መሰናክሎች* ይገጥሙናል። አንደኛው *መሰናክል ደንታ-ቢስነት* ነው፤ ሰውዬው እየሆነ ባለው ነገር ምንም ፍላጎት ሳይኖረው ይቀራል። ሌላኛው *መሰናክል መራር የጥላቻ ሰሜት* ነው፤ ሰውዬው በእኛ እና በቆምንለት ነገር ላይ ተቃዋሚ ይሆናል። ይሁን እንጂ ሌላኛው *መሰናክል ተጠራጣሪነት* ነው፤ ሰውዬው ልንሰብ ያለንበትን መጽሐፍ አያምንም። በዚህም ሆነ በዚያ እያንዳንዱ ሰው ልንለው ያለንን ነገር ሊሰማ ዝግጁ በሚሆንበት መልኩ እንዲገኝ ማድረግ አለብን። *መ*ፍዘዛቸውን ማሸነፍና ፍላጎትን ለመቀስቀስ ትኩረትን መሳብ እና መንገዱን ማዘጋጀት አለብን። ሰዎቹን ካሉበት ቦታ አንስተን ሊያደምጡን ወደሚዘጋጁበት ነጥብ ልናመጣቸው ይገባናል።

‘የጉባዔውን ትኩረት ለማግኘት የተሻለ የሆነው መንገድ ምንድነው?’ ሲል አንድ ወጣት ሰባኪ አንድ ጊዜ ጠየቀ። አዛውንቱ አማኝ ‘ሊገኙለት የሚፈልጉትን አንዳች ነገር ስጣቸው’ አሉ።

ከረጅም ጊዜ በፊት የተነገረ ታሪክ ግትር የነበረ አህያ ስለነበረው አንድ ሩሲያዊ ገበሬ ይነግረናል። ጌታውን የሚታዘዘው በመሰለው ጊዜ ብቻ የነበረ ሲሆን ይህም ከስንት ጊዜ አንዴ የሚከሰት ነገር ነበር! ነገር ግን አህዮች ታዛዥ እንዲሆኑ ሳያሳምማቸው የሚያሠለጥንበት ዘዴ እንዳለው አንድ ሐኪም ሲያወራ ገበሬው ሰማና ወደ እርሻው እንዲመጣ ለመነው። አህያውን በተመለከተ ጊዜ፣ ሐኪሙ ትልቅ የእንጨት ዱላ ከቦርሳው ውስጥ አወጣና አህያውን ያለ ምህረት ራስ ራሱን ይደበድበው ጀመር። ‘አቁም! አቁም!’ ሲል ገበሬው ጮኸ። ‘የምታሠለጥንበት መንገድ ህመም የሌለው እንደነበረ ነግረኸኝ ነበር!’ ሲለው ሐኪሙም ‘እንደዛው’ኮ ነው፤ ነገር ግን አስቀድሜ ትኩረቱን ማግኘት አለብኝ!’ ሲል መለሰለት።

ትኩረቱን እየሰጠን ላለ እና ለምንለው ነገር ለተሳበ አድማጭ ስብከት ማቅረብ ቀላል ነገር ነው። ‘ጥሩ ጅማሬ ካለ፣ ግማሹ ተከናውኗል’ ይላል የጥንቱ ተረትና ምሳሌ።

ጥቆማዎች

መግቢያ በቀጥታ ሊወስድ የሚገባው ወደ ዋናው መልእክት ነው። *መግቢያ* የእግረኛ መንገድ አይደለም። ነገር ግን ወደ ዐውራ ጎዳናው ካልሆነ በቀር የትም የማይወስድ *መጋቢ* መንገድ ነው። በ*መግቢያው* ውስጥ ያለው ነገር በሙሉ ይህንን አንድ ዓላማ ሊያገለግል ይገባል።

ስብከቱ ሊሰጥ ከሚችለው በላይ *መግቢያው* ተስፋ ሊሰጥ አይገባም። ተከትሎ የሚመጣው ስብከት የጡዘቱ ተቃራኒ እስኪሆን ድረስ አንዳንድ *መግቢያዎች* በጣም ጥሩ ናቸው። በረንዳው በጣም የሚሰብ ከሆነ፣ ከበስተጀርባው ያለው ቤቱ የበለጠ የሚሰብ እንዲሆን እንጠብቃለን። ውብ በሆነ በረንዳ ውስጥ አልፎ አሮጌ ወደሆነ ቤት *መግባት* ሁልጊዜም ተስፋ የሚያስቆርጥ ነገር ነው!

መግቢያው ነጠላ የሆነ አሳብን ብቻ የያዘ ሊሆን ይገባል። ቀላል እና ያልተብለጨለጨ መሆን ይኖርበታል። ከበረንዳ ወደ ሌላኛው በረንዳ የሚያስገባ ሌላ በረንዳ ጋር መሄድ ማን ይፈልጋል?

መግቢያዎቻችንን የተለያዩ እንዲሆኑ ማድረግ ጠቃሚ ነው። በመሃል ከተማ ውስጥ ባሉ የቀጠባ ቤት ውስጥ በመኖር አብዛኛውን እድሜዬን ፈጅቻለሁ። የቀጠባ ቤቶች ጎዳና ላይ በርካታ ቤቶች እርስ በርሳቸው ተያይዘዋል። ሁሉም ተመሳሳይ ይመስላሉ።ነገር ግን በዚህ ሁኔታ ውስጥ እንኳን አንዳንድ ልዩነቶች መታየት ይችሉ ነበር። ቢያንስ እያንዳንዱ ቤት ለፊት ለፊቱ በር የተለያየ ቀለም የተቀባ ነበር!

መግቢያ በጣም ረጅም መሆን የለበትም። ነጋዴው አቶ ሰመረ ጠቃሚ ለሆነ ስብሰባ ቀደም ብሎ ደረሰ። በመተላለፊያው ላይ ወንበር ሳብ አድርጎ ተቀመጠና እንቅልፉን ተኛ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጸሐፊዋ ክንዱን ነካ አደረገችውና እዛው ትታው ወደሄደችበትና ባልደረቦቹ ሥራቸውን ወደጀመሩበት ወደ ስብሰባው ክፍል ወሰደችው። የጸሐፊዋ ስም ወ/ሮ መግቢያ ነው።

መግቢያ ሰዎችን ለዋናው የእለቱ ሥራ የሚያስተዋውቅ ነው፣ ነገር ግን ዋናው ሥራ ሊይደለም። ዓላማው ሰዎችን ማንቃት እና ተከትሎ ለሚመጣው ነገር እነርሱን ማዘጋጀት ነው። ዓላማው በእርግጥም ሰዎችን አንቅቶ ከዚያም በድጋሚ እንዲተኙ ማድረግ አይደለም፣ ደግሞም ሊብራሩ ካሉት ትልልቅ እውነታዎች ጋር ከመድረሳቸው በፊት እነርሱን ግራ የሚያጋባቸውን ወይም የሚያሳስታቸውን ነገር የሚያስወግድ መሆን ይኖርበታል።

ረጅም የሆነ መግቢያ ሁልጊዜም ጥፋት ነው። አጭር የሆነው ስህተት የሚሆነው አልፎ አልፎ ነው። እራት ያገኙ እንደሆን እና እንዳልሆነ ሰዎች የሚጠይቁኑበትን የገበታ ልባስ ስናነጥፍ ረጅም ጊዜ መውሰድ የለብንም!

እንግዲያው ሊዘጋጅ የሚገባው ምን ያክል ጠንቃቃ በሆነ መልኩ ነው! ሰዎችን በቀጥጥራችን ስር ማድረግ ይኖርብናል! የመክፈቻ ንግግራችን ምን እንደሚሆን ልናስብ ይገባናል፣ ደግሞም ልምድ የሌላቸው ሰባኪዎች ምናልባትም ሊጽፏቸው ይገባል። ስለዚህ ራሳችንን በአድማጮቻችን ሁኔታ ውስጥ አድርገን ትኩረታቸውን እንዴት እንደምንስብ ልናስብ ይገባናል። ሰዎች ተቀምጠው በቀጥታ እኛን ሲመለከቱ ካየን፣ እንደተሳካልን እናውቃለን።

ምንጮች

መግቢያዎቼን ለማሻሻል ስሞክር፣ መልካም የሆኑ አሳቦችን ከየት ላገኝ እችላለሁ? በስብከት ላይ የተጻፉ መጽሐፍት አብዛኛውን ጊዜ ስለዚህ የሚናገር ጥሩ ነገር አላቸው። የእኔ እምነት እኛ ሁላችን አድማጮቻችንን በተቻለ መጠን ልናውቃቸው እንደሚገባን፣ እና ከዚያም እነርሱን ሊቆጣጠራቸው በሚችል መንገድ አንዳንድ የተለዩ ጥበቦችንና አዳዲስ ነገሮችን መጠቀም እንዳለብን ነው። በተቻለ ፍጥነት እና ሳቢነት፣ ስለምናነሣው ርእስ የጋለ ስሜት እንዲኖራቸው እና ቀድሞት ከሚመጣው መግቢያ ተከታዩ እውነታ የበለጠ የከበረ እንደሆነ ሁልጊዜ እንዲያስታውሱ ልናደርጋቸው ይገባናል። ምንም ዓይነት አስማታዊ ቀመር የለኝም። ጥሩ የሆኑ መግቢያዎች የማሰብ፣ የጸሎት እና ለሕዝባችን ያለን ፍቅር ውጤት ነው። እነዚህ ሦስቱ ነገሮች በሚገኙበት ጥሩ ስብከት የማይሆንልን አልፎ አልፎ ነው።

[2] ዋናው አካል

ፍቺ

መግቢያውን የሚከተለው በጥንታዊ መጠሪያው ‘ዋናው አካል’ የሚባለው ነው። ግን ምንድነው እርሱ? *ያ ለእነዚህ* ሰዎች *ለሁን* ላይ ትምህርት ሊሰጥበት ያለው እውነታ ነው። ዋናው አካል የተውጣጣው በዚህ ስብከት ውስጥ ላስተላልፈው ራሴ ካሰባሰብኳቸው ማስተማሪያዎች ነው።

ወሳኝ የሆነ ዕቅድ

ይህንን እውነታ በውጤታማ መልኩ ለማሸጋገር፣ ዕቅድ ሊኖረኝ ይገባል። ያም ሆነ ይህ፣ *እውነትን* ለሰዎች ላስተምር ነው። አሳቦቼ በአንዳች የተቀናጀ ቅደም-ተከተላዊ ሥርዓት አንዳቸው ሌላቸውን ሊከተሉ ይገባል፣ አሊያ የትም አልደርስም። በተወሰነ አቅጣጫ እየመራቸው ያለውን ስብከት ሰዎቹ እንደ አንድ እንቅስቃሴ መኖር ሆኖ ሊሰማቸው ይገባል።

የስብከቱ ዕቅድ እያንዳንዱ አድማጭ ወደየት እየሄዱ እንዳሉ ማየት እንዲችሉ በተቻለ መጠን ቀላል ሊሆን ይገባል። ጨለማ በሆነ መንገድ በሌሊት መንዳት አስቸጋሪ ነው። ነገር ግን በመንገዱ መሃል ላይ አንጸባራቂ ምልክት ካለ፣ ሁሉም ነገር ቀላል ነው። የመኪናው የፊት መብራት ሲያንጸባርቅበት፣ አንጸባራቂዎቹ ምልክቶች አንድ በአንድ መታየት ይችላሉ። ወደየትኛውም አቅጣጫ ከመዞራችን በፊት በርካታ ማስታወቂያዎች ይኖሩናል።

ምንም እንኳን ዕቅዱ ቀላል ሊሆን የሚገባው ቢሆንም፣ ትኩስ እና የሚስብ መሆንም ጭምር ይኖርበታል። እንደዚያ ካልሆነ፣ ጉባዔው መስማት ያቆማል። እያንዳንዱ ልብ ለራሱ 'እየመጣ ያለውን ላየው እችላለሁ' ብሎ ለራሱ ያቃስታል። ደግሞም ዕቅዱ ረቂቅ፣ ወይም ያልተለመደ ወይም ሲበዛ በሳል መሆን የለበትም። ሰዎች እኛን እንዲያደንቁን ወይም እንዲንቁን የማያደርጋቸው፣ ነገር ግን ዐይኖች ሁሉ የምናቀርበው እውነታ ላይ ጸንተው የተጣበቁ እንዲሆኑ የሚታወስ መዋቅር ያስፈልገናል።

አስቸጋሪ፣ ግትር፣ አሰልቺ ወይም የሚደብሩ እንዲሁም ብሩህ እና አስደናቂ የሆኑትን የስብከት ዕቅዶች ለመተውም ጊዜው ነው። የምንሰብከው *የእግዚአብሔርን* እውነት ነው! የሰዎችን ትኩረት ከእርሱ ለመሳብ ወይም ለመቀልበስ ምንም አስቸጋሪ ሊያደርገው አይገባም። ዕቅድ ለማውጣት ምክንያታችን የሚመነጨው እያንዳንዱ ሰው የእግዚአብሔር እውነታ ምን እንደሆነ ለማየት ምንም ችግር እንዳይኖርበት ለማድረግ ካለን የሚቃጠል መሻት ነው።

የክፍልፋዮች መኖር ኢ-ሸነት

በዕቅዳችን ውስጥ እንዳለን እንድንቆይ፣ እና አድማጮቻችን ያ ምን እንደሆነ እንዲያዩ ለማድረግ፣ ስብከት የተናጠል ክፍልፋዮች ወይም ርእሶች ሊኖሩት ይገባል። ይህ በክረምት ወቅት መንገዶች ላይ የሚደረጉ የበረዶ ላይ ምሰሶዎችን ይመስላል። በረዶው የተከመረ ሲሆን፣ መንገዱ የትኛው እንደሆነ ሾፌሩ ሊያይ አይችልም። ከመንገዱ ስቶ ሙሉ ለሙሉ ሊጠፋ ይችላል። የሚያስፈልገው ብቸኛ ነገር በመንገዱ ጠርዝ ላይ ሆነው የሚጠቁሙ በብሩህነት የሚያንጸባርቁ

ባለቀለም ምሰሶዎች ናቸው። እነዚህ በመንገዱ ላይ ካሉ፣ ሙሉ ለሙሉ አስተማማኝ ሁኔታ ላይ ነው።

ክፍልፋዮች ስብከቱ በቀላሉ የሚታወስ እንዲሆን ለማድረግ ቀላል ናቸው። አድማጮቻችን ሊያስታውሱት የማይችሉት ከሆነ ስብከታችን የትኛውን ዘላቂ የሆነ መልካም ነገር ማድረግ የሚችለው እንዴት ነው? እያንዳንዱ አርእስት ሰዎች አዲስ የተማሩትን እውነታ ሊይዙ የሚችሉበት አዲስ መንጠልጠያ የመሆን ያክል ያገለግላል። ሁሉም መንጠልጠያዎች በአእምሮ ውስጥ በሚሆኑበት ጊዜ፣ መላውን ስብከት ማስታወስ አለመቻላቸው ብቻ ሳይሆን፣ አንደኛው እውነት ከሌላኛው ጋር እንዴት እንደሚያያዝ የተሻለ መገንዘብ ይችላሉ።

ክፍልፋዮችን በተመለከተ አንዳንድ ደንቦች

ይሁን እንጂ፣ ክፍልፋዮች ወይም አርእስቶች በጥሩ ሁኔታ የማይደረጉ ከሆኑ ጠቃሚ መሆናቸውን ያቆማሉ። ክፍልፋዮቻችን የሚከተሉትን መግለጫዎች የሚመጥኑ ከሆኑ ስብከቶቻችንን በበቂ ሁኔታ ኣጋጦች እንዲሆኑ አድርገን እናዋቅራለን፦

የተለዩ

እያንዳንዱ አርእስት ከሌሎቹ በሙሉ የተለየ ሊሆን ይገባል ደግሞም የማናቸውም ድግግሞሽ ሊሆን አይገባም። የራሱ የሆነ ግልጽ መለያ ሊኖረው ይገባል። በዚህ መንገድ ስበከታችን የሚያድግ ሂደት ያለው እንደሆነ አድማጮቻችን ይመለከታሉ። እያንዳንዱ ክፍልፋይ የተገነባው ቀደም ባለው ላይ እንደሆነ እና ወደ ቀጣዩ የሚያመራ እንደሆነ ያያሉ። እያንዳንዱ አርእስት በዋናው መልእክት ውስጥ የየራሱ ልዩ ስፍራ ያለው በመሆኑ የተለየ ነው።

ቅደም-ተከተላዊ ሥርዓት ያለው፣ የሚንቀሳቀስ፣ እያደገ የሚሄድ

በመዝናኛ መናፈሻዎች የተገጠመው የሚሽከረከር ክብ መጫወቻ ሥርዓት እና እንቅስቃሴ ያለው ነገር ነው፤ ነገር ግን ምንም እያደገ የሚሄድ ሂደት የለውም። እንደዚያ ያለውን ስብከት መስማት የሚፈልገው ማነው? ለአመጽ የተነሣሣ ወራሪዎች እንቅስቃሴና እድገታዊ ሂደት አላቸው፣ ነገር ግን ሥርዓት የላቸውም። ትክክለኛ አእምሮ ኖሮት እንዲህ ባለው ስብከት ደስተኛ የሚሆን ማነው? ነገር ግን በእንቅስቃሴ ላይ ያለ ጦር ሠራዊት ግን ሦስቱም ባህርያት ያሉት ነው። አንድ ቦታ ይደርሳል ደግሞም አንድ ነገር ያደርጋል። ከዚህ በላይ ተጨማሪ ነገር መናገር ያስፈልጋልን?

የሚደመር

የሚወድቅ እቃ መውደቂያው ሲደርስ የበለጠ እየፈጠነ እና እየፈጠነ ይሄዳል። ታፍኖ ከቆየው ኃይሉ የተነሣ፣ ሌላው ቢቀር የኀልፍ መጫወቻ ኳስ እንኳን ከከፍታ ላይ እንኳን ቢለቀቅ ሰውን መግደል ይችላል። አንድ ስበከት እየተሰበከ በሄደ ጊዜ ብርታቱን ሊጨምር እና ይህም የተሰባሰበ ብርታት በአርእስቶቹ ሊገለጥ ይገባዋል። ዋናው ሞጋች መልእክት በጥሩ ፍስሰት እየተንቀሳቀሰ እና ኃይሉን እያሰባሰበ እንደሆነ ለሁሉም ግልጽ ሊሆንላቸው ይገባል። ክፍልፋዮቹ በተፈጥሯዊ መልኩ አንዳቸው ወደ ሌላቸው ሊመሩ እና የአሳብ ፍስሰቱም የተያያዘ እንጂ ያልተቆራረጠ/ያልጠፋ እንደሆነ በሚያረጋግጡበት መልኩ የሚሄዱ መሆን ይኖርባቸዋል። እያንዳንዱ ክፍልፋይ አድማጮቹን ሊመጣ ስላለው ጉዞት የበለጠ የሚያቀኑጠንጣቸው ሊሆን ይገባል።

ሰፊያዊነት

መናገር ከመጀመሩ በፊት፣ ሰባኪው ሊያስተላልፈው የሚያስበው እውነት ምን ያክል እንደሚሆን ሙሉ ለሙሉ ግልጽ ሊሆንለት ይገባል። በሁሉም የተለመዱ ሁኔታዎች ውስጥ ከዚያ ጋር መጽናት እና በተጨማሪ ማብራሪያ፣ አስረጅ ምሳሌ ወይም ተዛምዶ በስተቀረ ከዚያ ያለፈ ነገር የማይሰጥ መሆን ይኖርበታል። የእርሱ አርእስቶች የሸፈነውን እውነታ የተሟላ እና የተመጠነ ማጠቃለያ ሊሰጡ

ይገባቸዋል። ሊሰጥ ከሚፈልገው የፍራፍሬ ጭማቂ ሁሉ ከብርቱካኑ ወጥተው የተጨመቀኑ መሆን ይኖርባቸዋል እንጂ አንድ ተጨማሪ ጠብታ ብቻ አይደለም።

ተፈጥሯዊነት

አርእስቶቹ ተፈጥሯዊ እንጂ በግፊት የመጡ መሆን የለባቸውም። በዝግጅቱ ውስጥ ሰባኪው የእርሱ ጥቅስ ወይም ምንባብ፣ አሊያም ጭብጥ በተፈጥሯዊ ሁኔታ የሚከፋፈለው እንዴት እንደሆነ ሁልጊዜ ሊጠይቅ ይገባዋል። ቀድሞውኑ በዚያ የሌለ የትኛውም ነገር በላዩ ላይ ሊጫን አይገባም። አርእስቶች ከመሬት ውስጥ ኃብት የሚያወጡ ሽልማቶች ናቸው፤ እነርሱ ከሌላ ቦታ ለማስገባት የሚያመጧቸው መኪኖች አይደሉም።

ጥቂትነት

ስብከት በጣም ብዙ ክፍልፋዮች ሊኖሩት አይገባም። ትንሽ ልጅ በነበርኩኝ ጊዜ፣ ከወፎች ጎጆዎች ውስጥ እንቁላሎችን መውሰድ ህጋዊ ነገር ነበር። በአገሪቱ ውስጥ ይኖሩ ለነበሩ በርካታ ልጆች የወፍ ጎጆ መሥራት ከሚወደዱ ሙያዎች አንዱ ነበር፣ ደግሞም በእኛ ቤተሰብ ውስጥ በርከት ያለ ስብስብ ነበረን። እንቁላልን ወደ ቤት ብናመጣ፣ ወላጆቼ ሁልጊዜም በጎጆው ውስጥ ስንት እንቁላሎች እንዳሉ ማወቅ ይፈልጉ ነበር። ከአራት በላይ ካሉ፣ ይበቃል ብለው ያስቡ ነበር። ልክ እንደ በርካቶቹ ሌሎች ሰዎች፣ አንድ ወፍ እስከ አራት ድረስ ብቻ መቁጠር ይችላሉ! ከዚህ የተነሣ የተሰረቀውን እንቁላል ስለማያስተውሉ በኃዘን አይሰቀዩም የሚለውን አስተሳሰብ የያዙ ነበሩ!

ይህ የጥንት አስተሳሰብ ትክክል ይሁን አይሁን አላውቅም። ነገር ግን ከአራት በላይ ነጥቦች ያሉት ስብከትን መከተል ወይም ጠብቆ ማቆየት ለሰዎች እንደሚከብድ ግን አውቃለሁ። ሁለት ነጥቦች ብቻ ቢኖሩ፣ በስብከት ውስጥ ሂደታዊ እድገት ለመያዝ፣ እና በልዩ ልዩነት መንገድ ብዙውን ለማስተዋወቅየሰዎችን ትኩረት ጠብቆ ማቆየት ከባድ ነገር ነው። በጣም በርካታ

ነጥቦች ካሉ ስብከቱን ለማስታወስ ሲበዛ አስቸጋሪ ይሆናል። ለዚህም ነው ሦስት ነጥቦች ብቻ መያዙ ብልኅነት የሚሆነው (ምንም እንኳን ይህን በተመለከተ የሚነገሩ ፈዞች ቢኖሩም!)፣ ወይም ቢበዛ አራት።

ሦስት ወይም አራት ክፍልፋዮች ያለው ስብከት ከሞላ ጎደል ሁሉንም አደጋ ያስወግዳል። የማሳመኛው ቀላሉ ቅርጽ መደምደሚያዊ ትንተና ሦስት ነጥቦች አሉት የሚለው ነው። የመደምደሚያዊ ትንተና ምሳሌ ይህንን ይመስላል፦

* ሁሉም ፖስተኞች ሰማያዊ ሱሪ ይለብሳሉ።

* ዩሐንስ ፖስተኛ ነው።

* ስለዚህ ዩሐንስ ሰማያዊ ሱሪ ለብሷል።

ከዚህ የተነሣ፣ በሦስቱ ነጥቦች፣ በርከት ያሉ የተለያዩ አሳቦች መያዝ መቻል ብቻ ሳይሆን፣ ወደ ጡዘት ወይም መደምደሚያ የሚያመራ አሳማኝ የሆነ ሞጋች አሳብ መያዝም ይቻላል። ሦስት ክፍሎች ባሏቸው ሰባኪዎች ላይ መሳቃችንን ልናቆም ይገባናል። የባለ ሦስት ነጥብ ስብከቶች በክፍለ-ዘመናት ውስጥ ሁሉ በጣም ጥሩ የሆኑ የማስተማሪያ መሣሪያዎች ናቸው። የእግዚአብሔርን እውነት ግልጽ ለማድረግ አስደናቂ በሆነ መልኩ አሁንም አሁንም ጥቅም ላይ ውለዋል።

ተመጣጣኝነት

ባጠቃላይ ደንብነት፣ በስብከት ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ክፍልፋይ ተመሳሳይ መጠን ያለው ሊሆን ይገባል። መልእክቱ ሦስት ግልጽ ነጥቦች የነበሩት አንድ ወጣት ሰባኪን ሰምቼ ነበር።በመጀመሪያው ነጥብ ላይ ሃያ ሦስት ደቂቃዎችን እና በሁለተኛው ላይ ሰባት፣ ነገር ግን በሦስተኛው ላይ ሦስት ደቂቃዎችን ብቻ ተጠቀመ! የተወልን ስሜት በመጀመሪያው ክፍል ላይ በጣም ብዙ ጊዜ የተጠቀመ መሆኑ እና በሌሎቹ ሁለቱ ላይ በአጭሩ የቀየረብን መሆኑ ነው። ስብከቱ ሚዛኑን ያልጠበቀ፣ ነገር ግን ሚስጢራዊ በሆነ መልኩ የተታለልን እንደሆንን ያክል ተሰምቶን ነበር። የትኛውም ሰባኪ እንዲህ ያለውን ስሜት ትቶ ማለፍ የለበትም፤ ሰዎች ከቤተክርስቲያን መውጣት ያለባቸው ተነክተው፣ ተደንቀው እና

በእግዚአብሔር ቃል ተገዝተው መሆን አለበት። መዋቅሩ በዚያ ያለው ቃሉን ለማገልገል ነው እንጂ ከእርሱ ለማስቀልበስ መሆን የለበትም።

አሳማኝነት

ስለ አርእስቶቻችን በጥንቃቄ ካሰብን፣ የበለጠ አሳማኝ በሚሆኑበት መልኩ ልናናኖራቸው እንችላለን። በማቴዎስ 6፡1-18 ጌታ ደቀመዛሙርቱን ስለ ቸርነትን ስለማድረግ፣ ስለ ጸሎት እና ጾም አስተምሯቸዋል። ማድረግ *የሚኖርባቸውን* ከመንገሩ በፊት ማድረግ *የሌለባቸውን* ነገር ነግሯቸዋል። ይህ ልንከተለው የሚገባን ጥሩ ምሳሌ ነው፤ አሉታዊያኑ አዎንታዊያኑን መቅደም ይኖርባቸዋል። በተመሳሳይ መልኩ፣ ረቂቅ የሆነው ተጨባጭ ከሆነው፣ ከእውነተኛው በፊት ሐሰቱ፣ እንዲሁም ከተማጥኖ ወይም ምክር በፊት መግለጫ መቅደም አለበት። ጥቂት በሆነው አሳብ እና በአዲስ አካሄድ የበለጠ አሳማኝ ልናደርጋቸው ስንችል መልእክቶቻችንን ለምን ኃይል እናሳጣቸዋለን?

ማራኪነት

በተመሳሳይ መልኩ፣ በነገሮች ላይ ለማሰብ ጊዜ በመውሰድ፣ አርእስቶቻችን የበለጠ ማራኪ እንዲሆኑ ማድረግ እንችላለን። ይህም ሆነ ያ፣ ስብከቶቻችን የሚስቡ፣ ለመከተል የሚቀሉ፣ እና እንደውም ለማስታወስ የሚቀልሉ እንዲሆኑ አይደል የምንፈልገው? ቃሎቻችንን በማቅለል ብቻ ቅጽበታዊ እድገትን እንፈጥራለን - 'ለማየት የተቸገሩ በርካታ አይጦች' ከማለት ይልቅ ለሰዎች የበለጠ ስሜት የሚሰጣቸው 'ሦስት የታወሩ አይጦች' ማለት ነው! በአንድ ቃል የተገለጠ አርእስት በረጅሙ ሐረግ ከተገለጠው ይልቅ ሁልጊዜ የበለጠ ክብደት ይኖረዋል - 'ዋው!' የሚለው ቃል 'ሊሰማን እና ልንገልጸው ከሚገባው ፍንደቃ' በላይ የበለጠ የሚታወስ ነው! አርእስቶች በሐሳብ መገለጽ ያለባቸው ለምንድነው? እንደ ጥያቄዎች አድርጎ እነርሱን መግለጹ የበለጠ በቀጥጥር ሥር የሚያደርግ አይሆንምን? ሁላችንም በጸሎትና በጥንቃቄ ክፍልፋዮቻችንን የበለጠ የሚስቡ አድርገን ልናቀርብ አንችልምን?

[3] መደምደሚያ

መልካም የሆኑ ነገሮች በሙሉ ወደ ፍጻሜ ይመጣሉ፣ ጥሩም ሆኑ መጥፎ መላዎቹ ስብከቶችም እንዲሁ።ነገር ግን ወደ መዝጊያቸው ለማምጣት የተሻለው መንገድ ምንድነው? ጠቃሚ የሆነ መደምደሚያ ምንድነው? በስብከት መዋቅር ላይ የተሳቡ ሰዎች እንዲህ ያሉትን ጥያቄዎች እንዲህ አድርገው ኃላፊነታቸውን ለመተው ፈቃደኞች አይደሉም።

ትርጓሜ

መደምደሚያ ስብከትን ከሚዘጉ አስተያየቶች የተውጣጣ ነገር ነው። ዓላማው የተሰበኩትን እውነታዎች በሚመጥን መልኩ መልእክቱን ማጠቃለል ነው። እንዲሁም ደግሞ ጠቃሚ ከሆኑት ነገሮች መካከል አንዳቸውም አለመጥፋታቸውን የሚያረጋግጥ፣ ነገር ግን በእያንዳንዱ የተገኘው ሰው አእምሮዎች እና ጎሊናዎች ውስጥ ታትሞ እንዲቆይ የሚያደርግ ነው።

ከጥቂት ዓመታት በፊት በሰሜናዊ ዌልስ መንደር ውስጥ ተሰውሮ የነበረ አነስተኛ የቼኮሌት ፋብሪካን ስናገኝ እኔና ባለቤቴ ተደምመን ነበር። የፋብሪካው ባለቤት እያንዳንዱን ቼኮሌት በእጅ ያመርት የነበረ የስዊዝ *ቼኮሌት ሥራ ባለሙያ* ነበር። በእርግጥ ይህ ማለት ምርቶቹ ሲበዛ ውድ ነበሩ ማለት ነው። እርሱ ለእኛ ሲበዛ ደግ ከመሆኑ የተነሣና እኛም ፋብሪካውን መጎብኘታችን የሚስብ ሆኖ ከማግኘታችን የተነሣ፣ ስድስት የሚሆኑ ቼኮሌቶቹን ለመግዛት ወሰንን። በኋላ ላይ በክር አስሮ ለእኛ ሊሰጠን ብሩህ ቀለም ባላቸው ከረጢቶች ውስጥ ሲያስቀምጣቸው እያንዳንዳቸውን ቼኮሌቶች የሚይዛቸው ከሞላ ጎደል አባታዊ በሆነ ፍቅር ነበር። ወደ ቤት ይዘናቸው ስንሄድ ማናቸውም እንዳይጠፉ የምንጨነቀውን ያክል ይጨነቅ ነበር። የእርሱ እንክብካቤ እና ያኛው ከረጢት ለጉብኝታችን የሚመጥን መደምደሚያ ነበር።

ጠቀሜታ

መደምደሚያ የስብከቱን ጠቃሚነት ለመጨመር፣ ነገር ግን ያንን ለማስኬድ የሚያስችል ነገር ነው። እውነታውን ወደ ቤት ሊወስድ፣ ነገር ግን እንዲሁ ደግሞ ሊያጠፋው የሚችል ነገር ነው። በእያንዳንዱ አድማጭ ልብ ውስጥ ሊያትመው

ወይም ከእውቅና በላይ ሊያጎድፈው የሚችል ነገር ነው። የስብከት የመጨረሻዎቹ ጥቂት ዐረፍተ-ነገሮች ማንም ሰው ሊያጋንናቸው የማይችላቸው ጠቀሜታዎች አሏቸው።

ስሜት ቀስቃሽ የነበረ ስብከት የመጨረሻዎቹ ጥቂት ደቂቃዎች ላይ አሰልቺ ቢሆን ጥቅሙ ምንድነው? ስብከት ሰዎችን የሚያነቃ ቢሆን፣ ነገር ግን የሚያበቃው እንዲተኙ በማድረግ ቢሆን፣ ምን ጥቅም ሊፈይድ ይችላል? ትምህርቱ መሆን የሚችለውን ያክል ግልጽ ቢሆን፣ ነገር ግን መደምደሚያው ግልጽ ያልሆነ ወይም ግራ አጋቢ ቢሆን፣ ምን ዘላቂ ጠቀሜታ ሊኖረው ይችላል?

ልጅ ሳለሁ የስኳር ከረሜላ *መሥራትን* ተምሬ ነበር። በጣም በርካታ መጠን ያለው ስኳር ወደሚንተከተክ ውሃ ውስጥ ይጨመርና ከዚያ እንዲቀዘቅዝ ይተው ነበር። በሚቀዘቅዝ ጊዜ፣ የተዋሃደው ስኳር በውሃ ውስጥ እንዲንጠለጠል በሚተውበት ክር ላይ እንዲደርቅ ይደረጋል። እነዚያ ጣፋጭ የጣዕም አንኳሮች ልክ እንደ *መልካም መደምደሚያዎች* ናቸው - በስብከት ውስጥ እያንዳንዱ ነገር በቀላሉ ሊወስዱት በሚችሉበት መልኩ ጣዕሙን ጠብቆ ይረጋል።

ይሁን እንጂ፣ በስበከት ውስጥ ያለው ሁሉ ጣፋጭ መሆን አለበት ማለት አይደለም። ምናልባት መደምደሚያውን ከቀስት ጫፍ *ጋር* ማነፃፀሩ የተሻለ ይሆናል። በቀስት መወጠሪያው (*መግቢያ*) አማካኝነት በፍጥነት በአየር ላይ ይወነጨፍና ጎንና ጎኑ ላይ ባሉትና ማብረሪያ ብለን በምንጠራቸው ሦስት ወይም አራት መከነፊያ ላባዎች አማካኝነት አየር ላይ ይቆያል (ክፍልፋዮቹ)፣ ነገር ግን ዒላማውን እስኪመታ ድረስ *ሥራው* አይጠናቀቅም። በዚያ ቅጽበት ላይ መላው ኃይሉ የሚያተኩረው ነጥቡ ላይ ሲሆን ዒላማውን ሰርስሮ የሚገባው ያ ነጥቡ ነው። የዶለዶመ ቀስት ዒላማውን መትቶ መሬት ላይ ይወድቃል። እንዲህ ያለው ቀስት በጭራሽ ምንም ነገር አያሳካም። እንዴት ያለ ብክነት ነው! የቀስት ጫፍ ተስሎ ከሆነ ሁሉም ነገር የተለየ ይሆናል።

ጥቆማዎች

ቀስቱን ሳሉት! የስብከታችሁን መደምደሚያ በጥንቃቄ አዘጋጁ! በሰዎች ጆሮዎች ውስጥ እንዲደውልባቸው *ጸቅጩን* የምትፈልጉትን ነገር ጻፉት አሊያም በቃላችሁ ያዙት ወይም በማስታወሻችሁ ውስጥ (ሙሉ ለሙሉ) ያዙት።

የመልእክታችንን የመጨረሻውን ቅጂ ከማዘጋጀታችን በፊት መደመደሚያችንን ልናዘጋጅ ይገባናል። በእያንዳንዱ ነጥብ ላይ በአእምሯችን ውስጥ መሆን ይኖርበታል። ከትጥቃችን የምናወጣው የትኛውም መሣሪያ መደምደሚያውን የሚያነሳ ሊሆን ይገባዋል። መደምደሚያው ከእይታችን ሊጠፋ አይገባም። ይህ ስብከት የት እንዲያበቃ እንደምንፈልግ በእያንዳንዱ ነጥብ ላይ ፍጹም ግልጽ ሊሆንልን ይገባል።

የቤተክርስቲያን ህንጻዎች ቀላል እና ጌጥ የሌላቸው መሆን እንዳለባቸው የማምን ሰው ነኝ። ጉልላት ያለው የሚማርክ ቤተክርስቲያን ንድፍን በማውጣት ላይ ያለው የሕንጻ ንድፍ ሠራተኛ (አርክቴክት) ነኝ ብለን እናስብ። ያ ጉልላት ገና ከመጀመሪያውም በአእምሮዬ ውስጥ ነበር። ጉልላቱ እያንዳንዱ ሰው እንዲያየው የምፈልገው ገጽታ ነው። በእያንዳንዱ ንድፍ ውስጥ የሚታይ እና ሁሉንም እቅዶቼን የሚገዛ ይሆናል። ነገር ግን በግንባታው ጊዜ ጉልላቱ የሚገነባው በየትኛው ነጥብ ላይ ነው? በተመሳሳይ መልኩ የሰብከት መደምደሚያ ጅማሬ ላይ የሚታሰብ ቢሆንም ፍጻሜ ላይ ይተገበራል።

መደምደሚያ አጭር ሊሆን ይገባል። ዋናው መልእክት ተጠናቅቋል፣ ስለዚህም እንደገና ያንን ደግሞ መናገሩ ትክክል አይሆንም። መልእክቱን ወደ ቤት የምትሸኙበት ጊዜ ነው! መደምደሚያው ቀድሞት የተነገረውን ዋና መልእክት ሊያከብር በሚችልበት ደረጃ ረዘም ያለ መሆኑ እውነትነት ያለው ነገር ነው። ነገር ግን ዓላማው ለማጠናቀቅ መሆኑን ማስታወስ አለብን!

መደምደሚያዎቻችን የተለያየ መሆን ይኖርባቸዋል። ካልሆኑ ግን፣ መደበኛ የሆኑ አድማጮቻችን ምን ልንል እንደሆነ ቀድመው በፍጥነት ያዩና የሚደነቁሩበት አንድም ነገር አይኖራቸውም። ያሉበትን ሁኔታ ይለውጡና እኛ ከመጨረሳችን በፊት የዝማሬ መጽሐፋቸውን ያነሡ ይሆናል። በምሥራቅ ለንደን መቅደስ ውስጥ ከፖል ቱከር ኃይለኛ አገልግሎት በታች ያሳለፍኳቸው የተማሪነት ዓመታቶቼን በተመለከተ በእጅጉ ደስተኛ ነኝ። ስብከቶቹ ረጃጅም አልነበሩም፣

ነገር ግን የሚያበቃው መቼ እንደሆነ መገመት የማይታሰብ ነገር ነበር። በድንገት ያላቸውን ሁሉ ነገሮች ያሰባስብና ፍቅር ባለበት ሥልጣን ለልባችን እና ለሕይወታችን ዐደራ ሰጥቶ ያበቃል። መደምደሚያው ሲመጣ አይተነው አናውቅም። እስከ መጨረሻው ቅጽበት ድረስ አፋችንን እንዳስከፈተን ይቆያል። ነገር ግን መልእክቱን የሚያጠቃልልበትን እና በመልእክቱ የምናደርገውን ነገር ሲነግረን በሚደውሉብን ቃላት ሳንሰማው ከመቅደሱ ወጥተን አናውቅም።

እንደ አቶ ቱከር የሚሰብኩ ሰዎች ዛሬ ላይ ብዙ አይደሉም። ቍጥር ስፍር የሌላቸው ሰባኪዎች ከፍተኛ ፍጥነት ባለው የመስማት አቅም ሊያጠኑ የሚገባቸው ይመስለኛል። ሁሉም ነገር በሙሉ ፍጥነት እየሄደ ነው፣ ነገር ግን ያኔ፣ መጀመሪያ ላይ በማይታወቅ መልኩ ነገሮች መንቀራፈፍ ይጀምራሉ። ከዚያ በኋላ የበለጠ ቀርፋፋ እና ዝቅተኛ፣ እንደሞተ ሆነው እስከሚቆሙ ድረስ ቀርፋፋ እና ዝቅተኛ እየሆኑ ይሄዳሉ። 'ማብቂያው ይሄ ይሆን፣ ወይስ በድጋሚ ይጀምር ይሆን?' በማለት ጉባዔው እርግጠኛ ባለመሆን ይመለከታል። ሊሰማቸው የሚችለው የልብ መንጠልጠል ቅጽበት ያ ብቻ ይሆናል! እንዲህ ያሉ አሰልቺ ማብቂያዎች ሲሰበክ ለነበረው እውነት ምንም ዓይነት አክብሮት እንዲሰጥ አያደርጉም።

መደምደሚያዎቻችን ትኩረት ያላቸው እና ግላዊ መሆን አለባቸው። የእግዚአብሔርን ቃል በመስበክ ውስጥ ያለው መላው ዓላማ ሰዎች በእርሱ እንዲለወጡበት ነው። *መደምደሚያው ከእርሱና ከእርሱ* እንዲሁም *ከእርሷና ከእርሷ* ውሳኔን ይጠይቅ ዘንድ ይገባዋል። እያንዳንዱ ሰው አሁን ላይ የተጋፈጡት ከምርጫ ጋር መሆኑን መገንዘብ አለባቸው - የሰሙትን ነገር ወደ ተግባር መለወጥ አለባቸው፣ ወይም ያንን ለማድረግ መከላከል። መሃከለኛ ሆነው መሄድ አይችሉም። የእግዚአብሔር እውነት ግላዊ ምላሽን የሚጠይቅ ነገር ነው። እውነታዎች ተድላ ሊደረጉ፣ ተስፋ ቃሎች ሊታመኑ፣ መልካም እድሎች ሊገባባቸው፣ መጽናናቶች ተቀባይነት ሊያገኙ፣ ግዴታዎች ሊፈጸሙ፣ ኃጢአቶች ሊተዉ እና ማስጠንቀቂያዎች የምር ሊወሰዱ - አሊያም ሁሉም ሊጣሉ ይገባቸዋል። ነገር ግን ማንም ሰው እንደመጣ ሆኖ ሊመለስ አይችልም። ውሳኔ መወሰድ ያለበት *ለሁኑኑ* ነው። መደምደሚያው ይህንን ሊጎተጉት ይገባዋል። ከዚያም ሊያቆም።

ባለ ሁለት መቀመጫ ያላቸው ክፍሎች ታሪክ

ግልጽ ስለሆነ መዋቅር ሊባል የሚገባውን ሁሉ አሁን ላይ ሸፍነናል፣ ስለዚህም ባለ ሁለት መቀመጫ ስላላቸው ክፍሎች በመናገር እንድጨርስ እባካችሁን ፍቀዱልኝ፡

ባለፈው እሑድ ወ/ሮ ማክግሬገር ወደ ቤተክርስቲያን ሄደው ነበር። ስብከቱ ከፍታቴ አኳያ ትክክለኛና የተሟላ አስተምህሮ የነበረው ነበር፣ ነገር ግን ያም ሆኖ እንኳን ለእርሳቸው አልጠቀማቸውም ነበር። እንዲሁም ደግሞ ወደ ቤታቸው በሄዱ ጊዜ ምንም እንኳን እርሳቸው የሰሙት ምን እንደሆነ ለማወቅ በጣም ፈልገው የነበረ ቢመስልም ቅሉ በጌታ ላልሆኑት ባለቤታቸው ስለ ስብከቱ ብዙም ሊነግሯቸው አልቻሉም ነበር። እና ችግሩ ምን ነበር? ቢያንስ እርሳቸው መናገር እስከሚችሉት ድረስ ችግር የነበረው ነገር መልእክቱ ጥቂት ወይም ምንም መዋቅር በሌላቸው ዐረፍተ-ነገሮች የተዘጋጀ መሆኑ ነበር። ስለዚህም እርሳቸው ሊከተሉት አልቻሉም ነበር፣ ሊያቆዩትም ሆነ ስለ እርሱ ሊናገሩ አልቻሉም ነበር። እግዚአብሔር በዚህ የሚከብረው እንዴት ነው?

ባለፈው እሑድ ጆን ጆንስ ወደ ቤተክርስቲያን ሄዶ ነበር። ስብከቱ በፍታቴ ደረጃ ትክክልና የተሟላ አስተምህሮ የነበረው ነበር። ወደ ቤቱ እስኪሄድ ድረስ አላስቻለውም ነበር። ከደረጃው ሁለት ሁለቱን እየዘለለ ወጥቶ ከቤተክርስቲያን ለራቀችው ባለቤቱ ስለ ስበከቱ ሁሉን ነገር ነገራት። ነጥብ በነጥብ እየነገራት እስኪያደርሳት ድረስ በቀላሉ ሊያስታውሰው ችሎ ነበር። በእርግጥም ከሞላ ጎደል ሰብኮታል ማለት ይቻላል! እርሷ በተራዋ ተደነቀች፣ ተነካች፣ ደግሞም ጠቀማት። በዚያ የፎቀሩ ክፍል ውስጥ ሁለት ልቦች ለጌታ እንደአዲስ ታደሱ።

ስለ እግዚአብሔር እና የዳኑ ቢሆኑም ባይሆኑም፣ ስለሚሰሙን ሰዎች መልካም እንዲሆን ስንል፣ ግልጽ በሆነ መዋቅር ስብከትን የመስበክ ክህሎትን የተካኑ ለመሆን ራሳችንን እንስጥ!

የምታደርጓቸው ነገሮች

1. ማለዳ ላይ የተሰበከውን መዋቅር-የለሽ ስብከት እየተወያያችሁ ክርስቲያን ከሆኑ ቤተሰብ ጋር እሑድ ላይ ምሳ እየበላችሁ ነው። ሰምታችሁት ሊሆን የሚችለውን ነገር ጻፉት።

2. በሮሜ 12፡1-2 ላይ የተሰበከ ሰፋ ያለ የስብከት አስተዋጽዖ/ቢጋር በጥቆማነት አዘጋጁና መዋቅራችሁን ያዘጋጃችሁበትን ምክንያት አቅርቡ።

3. መለኮታዊው አስተማሪ መንፈስ ቅዱስ እንደመሆኑ መጠን የእግዚአብሔርን ነገሮች ግልጽ የሚያደርገው እርሱ ብቻ ነው፣ ደግሞም ስለ ስብከቱ መዋቅር ሊያሳስበን የሚገባ ነገር የለም ብለው አንዳንድ ሰዎች ይከራከራሉ። እንዲህ ያለውን አስተያየት በተመለከተ የምታስቡትን ጻፉት።

4

ግልጽ የሆነ አስረጅ ምሳሌ

ጥሩ የሆነ ስብከት ቀደም ብሎ በርከት ያለ ሥራ የሚጠይቅ መሆኑ አሁን ግልጽ ሊሆንልን ይገባል። ነገር ግን ስብከታችን ሊከተሉት የሚችሉት ወይም የሚታወስ መሆን ካልቻለ ድካማችን ሁሉ መና ሆነ ማለት ነው። ለዚህም ነው ግልጽ የሆነ የስብከት መዋቅር ጥያቄን በተመለከተ አንድ ሙሉ ምእራፍ መድበን የተመለከትነው። ያው ተመሳሳይ ምክንያት አሁን የሚነዳን *ግልጽ የሆኑ አስረጅ ምሳሌዎች* ወደሚባለው ነው።

[1] የአስረጅ ምሳሌዎች ዋጋ

አስረጅ ምሳሌ የሚባለው በአንድ ነገር ላይ ብርሃንን እንደመፈንጠቅ ወይም አጉልቶ እንደማሳየት ነገሩን ግልጽ የሚያደርግ ነው። ብርሃን ወደ ጨለማ ክፍል እንዲገባ የሚያደርግ መስኮት ነው። ዛሬ ላይ በርካታ ሰዎች በቃላት ላይ በጣም ጥሩ የሚባሉ አይደሉም። ረቂቅ የሆነ ማሳመኛ እና ንድፈ-አሳባዊ አመክንዮ አብረው እንዲሄዱ ማድረግን በጣም ከባድ ሆኖ ያገኙታል። ጥልቅ እና ቀጣይ የሆኑ ሙግቶች ግራ እንዲጋቡ ያደርጓቸዋል። ቃላት በእነዚህ መንገዶች ጥቅም ላይ ሲውሉ፣ ሰዎች በሌሊት የጠፉ ያክል ይሰማል። አንድ ሰው እንዲያዩ አይረዳቸውምን? በጨለማ ውስጥ አጥልቆ ለማየት የሚያስችሉ ጥንድ የብርሃን መነጽሮችን እንደውም ከዚያ የሚሻለውን፣ በእጅጉ የሚያበራ ባትሪ እንዲያገኙ የሚረዳቸው ማነው?

በርካታ ሰዎች ነገሩን በገዛ ራሳቸው አእምሮ ሊያዩት ካልቻሉ በቀር የትኛውንም ነገር በጣም በጥሩ ሁኔታ ሊገነዘቡት አይችሉም። ስዕሎችን ለሚፈነጥቁ ቃላት በጥሩ ሁኔታ ምላሽ ይሰጣሉ፣ ነገር ግን ቃላት በራሳቸው ዱልዱሞች፣ አሰልቺ እና የማይስቡ መሆናቸውን አስቡ። ለባለፉት ኃምሳ ዓመታት ከሞላ ጎደል በየቀኑ ሲሠራጭ የነበረ *ዚ ኦርቸርስ* የተሰኘ የእንግሊዝ ራዲዮ ፕሮግራም ነበር። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች አሁን ድረስ ይሰሙታል።

ተዋንያኑ ቃሎቻቸውን ሲናገሩ ይሰሟቸዋል፣ ነገር ግን የሚታይ አንድም ነገር የለም። እና የዚህ ፕሮግራም ማራኪነት ምንድነው? ራሱን እንደ 'የአገር ቤት የባህል ታሪክ' አድርጎ ማስተዋወቁ ነው። አድናቂዎቹ ጣቢያቸውን የሚዘውሩት ረቂቅ ወደሆኑ የቃላት ጋጋታዎች ሳይሆን በአእምሯቸው ውስጥ ሲገለጥ ሊያዩት ወደሚችሉት ታሪክ ነው።

በርካታ ሰባኪዎች ዘመናዊ ባህልን በእጅጉ የሚተቹ ናቸው፣ በተለይ ደግሞ የቃላት ምስል ላይ ያለውን ጥገኝነቱን። እውነታዎቹን እንዲጋፈጡ እየጠየቅኳቸው ነኝ። ነገሮች የሆኑበትን ሁኔታ ሊይወድዱ ይሆናል፣ ነገር ግን እንድንሰብክ ጌታ የጠራን *ለዚህኛው* ትውልድ እንደሆነ፣ እና ይህ ትውልድ ደግሞ ምስላዊ ቃላትን የሚፈልግ እንደሆነ ልናስታውስ ይገባናል። ከዚህ ጎን ለጎን፣ ያንን በተመለከተ አስፈሪ የሆነው ነገር ምንድነው? የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ያሉ ምስሎችን በእያንዳንዱ ገጽ ላይ አካትቷል፣ ደግሞም ጌታችን ሁልጊዜ ተጠቅሞባቸዋል።

አስረጅ ምሳሌን የተመለከተው ጥያቄ አፋጣኝ የሆነ ትኩረታችንን ይጠይቃል። ጉልህ የሆኑት መብራቶች ሲጠፉ በእግር ኳስ ጨዋታዎች ላይ ትንታኔ ማብራሪያ ለመስጠት የሚሞክሩትን ጋዜጠኞች መምሰላችንን ልናቆም ይገባናል። መብራቶቹን አብሯቸው! ቃሉን ባለው ቀለማቶቹ እና እንቅስቃሴዎች አሳዩ። በአስረጅ ምሳሌዎች ላይ ሥሩ ደግሞም ዋጋቸውን ለማየት የሚከተሉትን ሦስት ነጥቦች ከግምት አስገቡ፡-

(1) እውነታውን ያብራሩ

ለዚህም ነው ጌታችን አብዛኛውን ጊዜ 'የእግዚአብሔር *መንግሥት* . . . ትመስላለች' የሚል የነበረው (ምሳሌ ማቴ. 13፡24፣ 31፣ 33፣ 44፣ 45፣ 47)። ምስለ-ቃላት በአንድ ሰው አእምሮ ውስጥ አንዴ ከገቡ፣ ሁሉም ነገር ግልጽ ይሆናል።

በሮሜ ምእራፍ 6 እና 7 ውስጥ ሐዋርያው ጳውሎስ በእምነት ለጸደቁ ሰዎች በኃጢአት መኖራቸውን መቀጠላቸው ግራ አጋቢ የሚሆነው ለምን እንደሆነ ለማብራራት ይሞክራል። ውስብስብ እና በተጠባበቀ የአመክንዮ ሙግቶች የተሞሉ ቢሆኑ ኖሮ እነዚያን ምእራፎች ለመገንዘብ አስቸጋሪ ሆነው አገኛቸው ነበር። ነገር ግን አይደሉም። ጳውሎስ እየተናገረ ያለው ለአንደኛው

ጌታው ሞቶ፣ ነገር ግን ሌላኛውን ለማገልገል ከሞት ስለተነሣ ባርያ ነው። የትኛው ባርያ የየትኛው ጌታ እንደሆነ ልትናገሩ ስለምትችሉበት የባርያ ንግድ እየተናገረ ነው። እየተናገረ ያለው አንደኛው የትዳር ኣጋር ሞቶ/ታ ሌላኛው/ዋ ኣዲስ ኣጋርን ለማግባት ነፃ ሲ/ስትወጣ ያለውን ሁኔታ ነው። ሐዋርያው የሚጠቀመው ሌላ ምንም ሳይሆን ቃላትን በመሆኑ ለእኛ እየተናገረ ያለው በምስሎች ነው። ምስሎቹ እንድንገነዘብ እኛን መርዳታቸው ብቻ ሳይሆን፣ እያለ ያለውን ነገር በተመለከተ ያሳምኑናል። የሐዋርያውን ምሳሌ ልንገለብጥ ኣይገባንምን? እውነትን ለማብራራት ከዚህ የተሻለ መንገድ የሚያውቅ ሰው ኣለን?

(2) እውነቱ የሚሰብ እንዲሆን ያደርጋሉ

ሰባኪ ጉባዔውን ሲያጣ ተመልከታችሁ ታውቃላችሁ? ሰዎች ክፍሉን ትተው ኣይሄዱም፣ ነገር ግን ኣሳባቸው ሌላ ቦታ እንደሆነ ግን ግልጽ ነው። በድንገት ቀጥ ብለው ይቀመጡና ሰባኪውን ተመልክተው ሙሉ ትኩረታቸውን ይሰጡታል። ምን እየሆነ ነው? ልዩነቱን የፈጠረው ምንድነው? ኣስረጅ ምሳሌ እየተጠቀመ ነው!

ሰባኪዎች ነገሮችን ሁልጊዜ ቀላል ማድረግ ኣይችሉም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት ኣንዳንዶቹ ነገሮች ለመገንዘብ ከባድ ናቸው። ነገር ግን ሰዎች ከባድ የሆኑ ነገሮችን መስማት የሚችሉት ውሱን ለሆነ ጊዜ ብቻ ነው። እረፍት ስጧቸው፣ ኣንዳች የሚያነቃቃቸውን ነገር ስጧቸው፣ ያን ጊዜ በጣም በፍጥነት እናንተን በድጋሚ ለመስማት ዝግጁዎች ይሆናሉ።

በስዊዘርላንድ ውስጥ የሚገኙ በርካቶቹ ሰዎች በባለ ኣሞራ ክንፍ ጣሪያ ያላቸው ቤቶች ውስጥ ኣይኖሩም፣ ነገር ግን በሕንጻ መኖሪያ ቤቶች እንጂ። ከሞላ ጎደል እያንዳንዱ ሕንጻ ኣሳንሰር እና ኣስደናቂ የሆኑ ነገሮች ያሉት ነው! እነዚህ ኣሳንሰሮች በጭራሽ የሚበላሹ ኣይነት ኣይደሉም፤ ነገር ግን ከተበላሹ፣ ሁልጊዜ ደረጃዎቹን መጠቀም ትችላላችሁ። ለእያንዳንዱ ወለል ሁለት ዙር የሚያስወጡ ደረጃዎች ያሉ ሲሆን ሁለቱ በሚገናኙበት ጊዜ ከሞላ ጎደል ሁልጊዜ ወንበር ኣለ! ደረጃዎችን መውጣት ኣስቸጋሪ ነው፣ ነገር ግን ጊዜያችሁን ከወሰዳችሁ እና በእያንዳንዱ ወንበር ላይ ካረፋችሁ፣ ደረጃውን መውጣት በጭራሽ ኣስቸጋሪ

አይሆንባችሁም። በስብከት መካከል አስረጅ ምሳሌዎች መጠቀም ልክ እንደ እነዚያ ወንበሮች ነው።

ውሱን በሆነ ጊዜ ውስጥ ወደ ረጅም ጉዞ መሄድ ካለብን፣ ብዙዎቻችን በፈጣን የተሽከርካሪ መንገድ ላይ መንዳትን እንመርጣለን። በገጠራማ መንገዶች የመንዳትን ያክል በሚጠጋጋ መልኩ በእጅጉ የሚስብ ነገር አይደለም። እያንዳንዱ ማይል ቀደም ብሎ ከነበረው በጣም ተመሳሳይ ይመስላል። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ እንደክምና በተሽከርካሪዎች አገልግሎት መስጫው ላይ ለመቆም እንወስናለን። ወደ ሽንት ቤት እንመለሳለን፣ ሻይ ቡና እንልና ጥቂት ደቂቃዎችን በሱቁ ውስጥ እናሳልፋለን። ይሄን ጊዜ በድጋሚ ለመሄድ ዝግጁዎች ሆነን ራሳችንን የምናገኝ መሆን ብቻ ሳይሆን፣ ያንን ለማድረግ ጉጉዎችም ጭምር እንሆናለን! ምንድነው በእኛ ላይ የሆነው? አረፍን ደግሞም ታደስን። በስብከቶች ውስጥ ያሉ አስረጅ ምሳሌዎች ልክ እንደነዚያ የተሽከርካሪዎች ማረፊያዎች ናቸው።

ከጎናችሁ ለተቀመጠ ትንሽ ልጅ ታሪክ አንብባችሁ ታውቃላችሁ? መጀመሪያ ላይ ልጁ ተስቦ እና ተደንቆ ይሰማል፣ ነገር ግን ከጥቂት ጊዜ በኋላ መቀሩነጥነጥ ይጀምራል። ከዚያም ሁሉ ነገር ይለወጥና እንድትቀጥሉ ይለምናችኋል። የሆነው ነገር ገጹን ስትገልጡ ስዕል ማየቱ ነው!

እውነታውን የሚስብ ስለሚያደርጉት ጭምር አስረጅ ምሳሌዎች የሚያስደምም ያደርጉታል። ጌታችን እንዲህ ያለ ነገር ሊል ይችላል፦ “ያደረጋችሁት ነገር ምንም ቢሆን፣ ያደረጋችሁት ለምንም ያክል ጊዜ ቢሆን፣ የሚወስዳችሁ የትም ቢሆን፣ ወደ እግዚአብሔር ብትመለሱ፣ እርሱ ይቀበላችኋል።’ ነገር ግን አልተቀበላቸውም። ከዚህ ይልቅ እርሱ ያለው ‘አንድ ሰው ሁለት ልጆች ነበሩት. . .’ (ሉቃ 15፡11)። የጠፋው ልጅ ታሪክ ምሳሌ የትኛውም ተራ ዐረፍተ-ነገር ሊገልጸው እንደሚችል ተስፋ ከምናደርገው በላይ አባት እኛን የሚቀበልበትን ሁኔታ ያሳያል። እውነትን እናያለን፣ ግልጽ ሆኖ እናየዋለን፣ ደግሞም በደስታ እናለቅሳለን።

ዳዊት በጌታ ላይ እጅግ አይናውጣ በሆነ መልኩ ኃጢአትን ሲያደርግና ዘማዊነቱን ሲከተል እና ለወራት ያክል ጸሎት ባቆመበት ሁኔታ ሰውዬውን ሲገድል፣ እግዚአብሔር ነብዩ ናታንን ወደ እርሱ ላከበት። ናታን ወደ ንጉሡ መገኛ ዘሎ ገብቶ በቅዱስ ቁጣ ጣቱን እየቀሰረበት ነቀፈውን? ያንን እንዳያደርግ ሲበዛ በብልሃት ተሞልቶ ነበር። የእርሱ ዓላማ የወደቀውን ኃጢአተኛ መመለስ

ነበር እንጂ ወደ ክህደት እንዲገፋፋ ማድረግ አልነበረም። በገርነት ገብቶ ታሪክን ነገረው። ብዙም ሳይቆይ በቀኣጣ ላይ ሆኖ የተገኘው ነብዩ ሳይሆን ራሱ ንጉሡ ነበር። ነገር ግን ከሦስት ሺህ ዓመታት በኋላ እንኳን 'ያ ሰው አንተ ነህ' ብሎ ናታን በተናገረበት ሥልጣን እንደነግጣለን (2 ሳሙ 12፡7)።

(3) እውነታው ሊታወስ የሚችል እንዲሆን ያደርጋሉ

ስለ ሰማችሁት የመጨረሻው ስብከት ምን ልታስታውሱ ትችላላችሁ? ጥቂት የሚያስደነግጥ ተናዳፊ ድምጽ ነበረው? የሚያስደምም የንግግር አጋጣሚዎች ነበሩ? አሳማኝ የሆነ ሙግት ብሩኅ ምሳሌዎች ነበሩ? የምታስታውሷቸው ነገሮች እነዚህ ናቸው? ምናልባት አይደሉም። ነገር ግን ልክ እንደ እኔ እናንተም አስረጅ ምሳሌዎችን ልታስታውሱ ትችላላችሁ!

ከበርካታ ዓመታት በፊት፣ ገና አገልግሎት እንደጀመርኩ፣ የአንድ አጫሽ የአሟሟት ሁኔታ ምርመራ ላይ እንድታደም የተለየ ግብዣ ተሰጠኝ። እንዳይ የተፈለገው ነገር ትምባሆ ማጨስ በሰዎች ሳምባዎች ላይ ምን እንደሚያደርግ በመመልከት እንድደነግጥ እና በየትኛውም ቦታ ላይ ማጨስን ተስፋ ለማስቆረጥ እንደ አገልጋይ ያለኝን ተጽዕኖ እንድጠቀም ነበር። እኔ ድንጉጥ ሰው በመሆኔ ተገኝቼ ቢሆን ኖሮ ምናልባትም ራሴን እስት ነበር። ስለዚህም ግብዣውን ሳልቀበል ቀረሁ። ነገር ግን አንድ ነገር እርግጠኛ ነበርኩ፡- ግብዣውን ተቀብዬ ቢሆን ኖሮ፣ በማጨስ ላይ እስከ ዛሬ ሰምቼው ከማውቀው አኃዛዊ መረጃ በላይ በማየው ነገር የበለጠ ተደምሜ እደነቅ ነበር። የምናየውን ነገር እናስታውሳለን። የምናነብባቸውን እና የምንሰማቸውን አብዛኞቹን ነገሮች እንረሳለን።

ሰባኪዎች እንደመሆናችን ሊታዩ የሚችሉ መርጃ ማስተማሪያዎችን አንጠቀምም። ጌታችን የጠራን በቃላት እንድንሠራ ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር ለሰዎች የሰጠውን በምናብ የመሳል ኃይል ለማነቃቃት እነዚያን ቃላት ልንጠቀምባቸው ይገባናል። በሰዎች ጆሮዎች ውስጥ ዓይኖችን ልናኖር ይገባናል። አእምሯቸውን ለመድረስ ከዚህ የተሻለ መንገድ የለም።

ለመስበክ ስንቆም፣ ሁሉም ዓይነት ሰዎች በፊት ለፊታችን አሉ። በጎሳ፣ በእድሜ፣ በዳራ፣ በትምህርት፣ በክህሎት፣ በእውቀት፣ በተፈጥሮ፣ በባህርይ፣

እነዚህን በመሳሰሉ ነገሮች ይለያያሉ። ነገር ግን በደንብ ባሰብንበት አስረጅ ምሳሌ *ሁሉንም* ልንይዛቸው እንችላለን። ጌታችን ምሳሌዎቹን ሲጠቀም ያደረገው ይህንን ነበር፣ ደግሞም በተለይ ወደ ስቅለቱ ሰሞን አካባቢ ያስተማረባቸው ምሳሌዎች። በማርቆስ 12፡1-12 ላይ የሚገኘው ክፉ የወይን ተከራይ ምሳሌ፣ እንዲሁም በማቴዎስ 25 ላይ የሚገኙት ሦስቱ ምሳሌዎች የተዋጣላቸው ምሳሌዎች ናቸው። በዚህ ጊዜ ጌታ የሚናገረው ከተለመደው ይልቅ በስፋት ልዩ ልዩ ለሆኑ ሰዎች ነበር። የእርሱ አድማጮች ከኢየሩሳሌም ውጪ ለነበረው አገልግሎት ተገኝተው የማያውቁ የነበሩ በጣም የተማሩ ጠላቶችን ይጨምር ነበር። የማይመቹ እውነታዎችን መቼም እንዳይረሱት አድርጎ አስተማራቸው!

የሚታወሰ እውነት ስብከቱ ከተሰበከ ከረጅም ጊዜ በኋላ እንኳን ሥራውን ለረጅም ጊዜ ሊሠራ ይችላል። በሃያዎቹ እድሜዬ ሳለሁ በኤፍ. ቢ. ሜየር የተሰበኩ በርካታ ስብከቶችን አንብቤያለሁ። እስከ ዛሬ ድረስ ላለው ክርስቲያናዊ ህይወቴ የረዱኝን አስረጅ ምሳሌዎች የያዙ ነበሩ። በተመሳሳይ መልኩ፣ ነፍሴ የብሪጆንዱን የሂቄል ግሪፊትስ ስብከት መመገቧን ቀጥላለች። እርሳቸውም ከሰማኋቸው ሰባኪዎች ያለጥርጥር ታላቁ የምላቸው ናቸው። በደቡባዊቷ ፔምብሮክሻየር ትንሿ መንደራችን በመጡበት ዓመታዊ ጉብኝታቸው እርሳቸውን መጀመሪያ ስሰማቸው ሃያ አመቴ ነበር። ደግሞም በእነዚያ ወቅቶች ላይ የነበሩት የእርሳቸው ስብከቶች ከሞላ ጎደል በየቀኑ በእጅጉ የሚጠቅሙኝ ነበሩ። ይህን የምለው የትኛውም ቅጂዎች ስለሌሉኝ አይደለም፤ *ስለማስታውሳቸው* ነው። በዓመታት ውስጥ በሺዎች የሚቆጠሩ ስብከቶችን የሰማሁ ሲሆን ከሞላ ጎደል ሁሉም በትውስታዬ ውስጥ ቦታም የላቸውም። ነገር ግን የሂቄል ግሪፊትስ ስብከቶች ግን በውስጤ ይኖራሉ። ይህም የሆነበት ምክንያት መጀመሪያ ነገር ከሰማያዊው ኃይሉ (በሌላኛው ምእራፍ ላይ የምንመለከተው ርእሰ-ጉዳይ)፣ እና በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ስብከቶች ከጀማሪ አንስቶ እስከ ፍጻሜ ድረስ በአስረጅ ምሳሌ የታጀቡ ስለሆኑ ነው።

ሰዎች የሚያዩትን ያስታውሳሉ። ሰዎች በ*ሉ*ም*ሯ*ው የሚያዩትን ነገር ጨምረው ያስታውሳሉ። እኛ የተፈጠርነው በዚህ መልኩ ነው። ለአርባ አመታት ወደ ቤተክርስቲያን አቅራቢያ ያልነበሩ፣ ነገር ግን በልጅነታቸው በእሑድ የሰንበት ትምህርት ቤት ይካፈሉ የነበሩ፣ ከዚህን ያክል ጊዜ በኋላም በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን ያስታውሳሉ። ስለ እንግሊዝ አገር ታሪክ አንድም እንኳን የረባ የሚባል ነገር የማያውቁ ሰዎች፣ ስለ ንጉሥ አልፍሬድ እና ኬኮቹ፣ ስለ ንጉሥ

ሐሮልድ በሃስቲንግስ ትግል መሞት፣ ስለ ሰር ፍራንሲስ ድራኬ የስፔን የጦር መርከብ እየተቃረቡም ቢሆን ቀስት ውርወራ መጫወቱን ስለመቀጠሉ ታሪክ ይነግሯችኋል! እንግዲያውስ እኛ በስብከቶቻችን ተጨማሪ አስረጅ ምሳሌዎችን በመጠቀም *ወንጌልን* እንዲያስታውሱ አንረዳቸውምን?

በስብከት ላይ የገዛ ራሴን እይታዎች ለመቅረጽ ብዙ ያበረከተው መጽሐፍ በኦውን ጆንስ[4] የተጻፈው *ሰም ግሬት ፕሪቸርስ ኡዝ ዌልስ* የተሰኘው መጽሐፍ ነው። ይህ መጽሐፍ ኃይለኛ የሆነው ስብከት በሺዎች የሚቆጠሩትን ወደ ጌታ በማምጣቱ እና በመጨረሻም ሕዝቡን በመለወጡ በርካታ ሰዎች በቅርበት የሚመለከቱት መጽሐፍ ነው። የመጽሐፉ በጣም ኢጋዥ የሆነው ክፍል ሚ/ር ጆንስ ሰባኪዎቹ የነበሯቸውን አምስት የጋራ የሆኑ ባህርያት የለዩባቸው የመግቢያው መጣጥፍ ነው። ከእነዚህ አምስት ነገሮች አንደኛው *ምናባዊነት* መሆኑ የሚስብ ነገር ነው! እነዚህ ሰዎች በተለያየ መለኪያ ኤድማጮቻቸው አንድ ነገር እንዲያዩ አምጥተዋቸዋል። ተመሳሳዩን ነገር ማድረግ እንችላለን?

[2] አስረጅ ምሳሌዎች የሚገኙባቸው ምንጮች

የማውቀው ሰባኪ ሁሉ አስረጅ ምሳሌን በመስጠት ረገድ ደካማ እንደሆኑ እና ማሻሻል እንደሚፈልጉ ይነግሩኛል። ሰባኪዎቹ እንዲሁም አስረጅ ምሳሌዎች የሚገኙባቸውን ምንጮች በመጠቆም ባግዝ እንደሚያመሰግኑ ይነግሩኛል። ሰባኪ አስረጅ ምሳሌዎችን ከየት ሊያገኛቸው ይችላል?

(i) ከእግዚአብሔር ቃል

ሰባኪ አስረጅ ምሳሌዎችን ከእግዚአብሔር ቃል ሊያገኝ ይችላል። ሥነ-ፍጥረታዊ ትክክለኝነትን ስንነጋገር መጽሐፍ ቅዱስ ራሱን በራሱ የሚተረጉም መጽሐፍ መሆኑን ተመልክተን ነበር። መጽሐፉ እንዲሁም ደግሞ ራሱን በራሱ በምሳሌ

[4] አሁን በድጋሚ ታትሞ በቴንትሜኪንግ አሳታሚዎች፣ 121 ሃርተስሂል ሮድ፣ የሚገኝ ነው።

የሚያብራራ ነው። የታሪክ፣ የግለ-ታሪክ፣ ቅኔ፣ እና ምሳሌዎች ሀብት የተከማቸበት እና ሁሉም የትኛውንም አስተምህሮ ወይም ከገጾቹ ውስጥ የምናስተምራቸውን ትምህርቶች በምሳሌ ለማስረዳት ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። ክርስቲያኖች እንኳን ሳይቀሩ መጽሐፍ ቅዱሳቸውን በደንብ እንደማያውቁ ያንን ይመለከታሉ፤ አስረጅ ምሳሌ ስትፈልጉ ራሱን መጽሐፍ ቅዱስን መጀመሪያ የምታስሱት ወደባቸሁ ለምን አታደርጉትም?

ነገር ግን ጠንቃቆች ልንሆን ይገባናል። የዐሥራ-ሰባተኛው ክፍለ-ዘመን የፒዩሪታኑን ስብከቶች ወይም የዐሥራ-ዘጠነኛውን ክፍለ-ዘመን ሰባኪ የሲ.ኤች ስፐርጅንን ስናነብ፣ ሊሉት ያላቸውን ነገር ለማስረዳት እያንዳንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ ተጠቅመው እንደነበረ እናስተውላለን። እነርሱ እንዳደረጉት ልክ እንደዚያ ማድረግ አንችልም። እነርሱ የሰበኩት መጽሐፍ ቅዱሳቸውን በጥሩ ሁኔታ ያውቁ ለነበሩ ጉባዔዎች ነበር። እንግዲያው፣ አንዳንድ ጊዜ ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ ክስተቶቹ የሚሰጧቸው ማጣቀሻዎች ዝም ብለው የሾርኔ ንግግሮች ነበሩ። ስለ ሺቦሌት፣ በግማሽ ስለተላጨው መላጣ፣ ስለ ባካ ሸለቆ፣ ስለ ሸክላ ሠሪው ሱቅ፣ ስለ ልብስ ቅምቅማት እና ስለ ፕብሊየስ *መታመም* ይናገራሉ - ደግሞም እነርሱ ያወሩት የነበረው ነገር ስለምን እንደነበረ ሁሉ ሰው ያውቅ ነበር! ዛሬ ላይ ያንን ማድረግ አንችልም። እነዚህን አስረጅ ሾርኔ ንግግሮች አስረጅ ምሳሌዎች አድርጎ ለመጠቀም ሙሉ የሆነ ማብራሪያን መስጠት ወይም ታሪክን መናገር ያስፈልገናል። ይሁን እንጂ፣ ይህንን ስናደርግ፣ ሁለት ወፎችን በአንድ ድንጋይ የመግደል ያክል ልንለው ያለንን በአስረጅ ምሳሌ እናብራራለን፣ ደግሞም ለአድማጮቻችን ስለ መላው የእግዘአብሔር ምክር የተሻለ እውቀትን እንሰጣቸዋለን።

ልንጠነቀቅበት የሚገባን ሌላ ነገር አለን። ቀደም ባለው ምእራፍ ውስጥ ስለዚያ ተነጋግረናል፣ ነገር ግን በድጋሚ ልንናገረው ይገባናል። *የታለመው* የቃለ እግዚአብሔር ትርጉም በሆነው ነገር እና *ለአስረጅ ምሳሌነት* ጥቅም ላይ የዋለውን ስንለይ ሁልጊዜ ጠንቃቆች ልንሆን ይገባናል። ይህ ልዩነት ለአድማጮቻችንም እንዲሁ ግልጽ ሊሆንላቸው ይገባል። የሚያቅማማ የልጅ መሰል እምነትን ለማስረዳት በሁሉም መንገድ ንእማንን ተጠቀሙ፣ ነገር ግን 2 ነገሥት 5፡1-19 ሙሉ ለሙሉ ስለዚህ እንደሆነ አድርጋችሁ ግን አትስበኩ። የእግዚአብሔርን ቅርብነት በምሳሌ ለማስረዳት በሁሉም መንገድ የሳሙኤልን መጠራት ተጠቀሙ፣ ነገር ግን የነ ሳሙኤል ምእራፍ 3 ዓላማ ያንን እውነት ለማስተላለፍ እንደሆነ

ሰዎች እንዲገምቱ አታድርጓቸው። አዎን፣ ልንሰብክበት ባለው የቃለ እግዚአብሔር ክፍል ላይ ብርሃንን ለመፈንጠቅ በእርግጥ ሌሎች የቃሉን ክፍሎች ልንጠቀም እንችላለን። ነገር ግን ያንን በማድረጋችን ውስጥ ለአስረጅ ምሳሌነት እየተጠቀምንበት ባለው ምንባብ ላይ ያለው የሰዎች መረዳት የተሸፈነ እንዲሆን ማድረግ የለብንም!

(ii) ምልከታ

እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ሰባኪ በገንዘብ የተሞላ ሳይሆን ነገር ግን በስብከት አስረጅ ምሳሌዎች የተሞላ የባንክ ሂሳብ ሰጥቷል። በአንድ ቀን በሺዎች የሚቆጠሩ አስረጅ ምሳሌዎችን ብንመለከት፣ መቼም አናባክንም። ስለዚህ ይህንን ሂሳባችንን ልንጠቀምበት የምንችለው እንዴት ነው? በቼክ ሠነድ ወይም በጥሬ ገንዘብ ካርድም ሳይሆን፣ ነገር ግን በዓይኖቻችን እና በጆሮዎቻችን ነው። አይንና ጆሮዎቻችንን በቀላሉ አንቅተን እናቆያቸዋለን፣ ከዚያም የምናየውን እና የምንሰማውን በአእምሯችን እንመዘግብና ጥቂት አሳብ እንጨምርበታለን።

የእለታዊ ሕይወት የሚታዩ፣ የሚሰሙ እና የሚገጥሙ ነገሮች የማይሟጠጡ የአስረጅ ምሳሌዎች ምንጮች ናቸው። ከዚህ መደርደሪያ ውስጥ የምትችሉትን ሁሉ ውሰዱ፣ ከዚያም ወዲያውኑ መልሶ የሚደረደር ሆኖ ታገኙታላችሁ። ‘ጥቅም ላይ ያልዋለ’ የሚል መለያ ስላልተሸከመ ስብከታችሁን በዚህ መጭመቂያ ሙሉት። ሌላው ቢቀር ዱራሴል ባትሪ ድንጋይ እንኳን በስተመጨረሻ ያልቃል፣ ነገር ግን ይሄኛው መቼም አይጠፋባችሁም። ሁልጊዜ የሚያበራ ፀሐይ፣ ሁልጊዜ የሚነፍስ ነፋስ፣ መቼም የማይደርቅ ምንጭ፣ መቼም ተስፋ የማያስቆርጥ ተስፋ - መቼም የማይጠፋ የአስረጅ ምሳሌዎች አቅርቦት እነኳችሁ!

በዙሪያችን ሁሉ ካሉት ላይ አስረጅ ምሳሌዎችን እንድናገኝ ያስተማረን ራሱ ጌታችን ነው። ስንዴን ስለ መዝራት፣ ወይንን ስለመጥመቅ፣ ቤቶችን ስለመገንባት፣ እርሾ ስላለው ሊጥ፣ እንጀራን ስለመጋገር፣ ከጎረቤት ስለመዋስ፣ መብራትን ስለማብራት፣ ወለልን ስለመጥረግ፣ እና ሃብትን ስለማግኘት ተናግሯል። ስለ አገልጋዮች ግዴታዎች፣ ከገበታ በታች ስላሉ ውሾች፣ ስለ ቆፋሪ ሌባ፣ ልብስ ስለሚያጠፋ ብል፣ በእሥር ስላለ ባለ እዳ፣ በጨዋታ ላይ ስላሉ

ልጆች፣ ስለ ድግሶች፣ ሠርጎች፣ የፍርድ ጉዳዮች እና ወቅታዊ ክስተቶች ተናግሯል። ከሰማይ መጥቷል፣ ነገር ግን በምድር ላይ ኖሯል፣ እርሱ ከምድር ወንዶች እና ሴቶች ጋር የተነጋገረው ሊገነዘቡት በሚችሉበት ምስላዊነት ነው። እውነተኛ ተከታዮቹ ተመሳሳዩን ነገር ያደርጋሉ።

ሲ.ኤች. ስፐርጅን ተማሪዎቹ ሁሉ አስረጅ ምሳሌ የሚጠቀሙ ሰባኪዎች እንዲሆኑ ይፈልግ ነበር። ዓይኖቻቸውን ከፍተው ምሳሌ እንዲያገኙ እና ያዩትን እንዲያገናዝቡ በተደጋጋሚ ይመክራቸው ነበር። በአንደኛው አጋጣሚ ላይ በፊት ለፊታቸው ያለው ሻማ ብቻ ቢሆን ያ አንድ ሻማ ለበርካታ ስብከቶች በቂ የሚሆኑ አስረጅ ምሳሌዎችን እንደሚሰጣቸው ነግሯቸው ነበር! እነርሱም ሳቁ። እንደዚያም ሆኖ ከሻማ ምሳሌ ሊወስዱ የሚችሉ ሁለት ስብከቶችን በመስጠት ንግግሩን አረጋግጦላቸዋል። *ሰርመንስ ኦን ካንድልስ* የተባለው መጽሐፉ የእነዚያ ስብከቶቹ የታተመ ቅጂዎች ናቸው።

ከሻማዎች የሚወሰዱት አስረጅ ምሳሌዎች ዛሬ ላይ ለበርካታ ሰዎች ያን ያክል ውጤት አይኖራቸውም። የእኛ ዘመን የኤሌክትሪክ ብርሃን፣ የቴሌቪዥን፣ የኮምፒዩተር፣ የመኪኖች፣ የሞባይል ስልኮች፣ የሱፐርማርኬቶች፣ የፋሽን ንድፍ ሥራዎች፣ የንግድ ሙዚቃ፣ ሙያዊ ስፖርት፣ የዓለም ዙሪያ ጉዞዎች እና ህዋን ለማሰስ ያሉ ተስፋዎች ዘመን ነው። ጌታችን አስረጅ ምሳሌዎቹን ያወጣው ከመጀመሪያው ክፍለ-ዘመን የፍልስጥኤም ዘመን ሁኔታዎች ነው፤ ካልቪን ምሳሌዎቹን ያወጣው ከዐሥራ ስድስተኛው ክፍለ-ዘመን ጀኔቫ ነው፣ የስፐርጅን ቃሎች ደግሞ ባለማቋረጥ ያንጸባረቁት የዐሥራ ዘጠነኛውን ክፍለ-ዘመን ለንደን ምሳሌዎች ነው። እኛስ? የሃያ አንደኛው ክፍለ-ዘመን አድማጮቻችን የሃያ አንደኛ ክፍለ-ዘመን አስረጅ ምሳሌዎችን ይሰማሉ? ካልሰሙ፣ እኛ ሰባኪዎቹ አጥተናቸዋል።

(iii) ንፁህ ፈጠራ

ጥሩ የሆነ አስረጅ ምሳሌ ተጠቃሚ ሰባኪ የሚያስፈልጉት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያለ እውቀት፣ በሁለት አቅጣጫ የተከፈቱ ዐይኖችና ጆሮዎች እንዲሁም አስተዋይ አእምሮ ናቸው። ነገር ግን ንፁህ ወደሆነው ፈጠራ ዓለም ውስጥ ለመግባት ፈቃደኛ የሚሆን ከሆነ እንደውም ከዚህ የተሻለ ነገር ሊሠራ ይችላል። በቤት

ውስጥ የተሠሩ ምሳሌዎች እና ተለዋጭ ትርጓሜዎች በተለይ ውጤታማ ናቸው። በእርግጥ፣ የጌታችንን ምሳሌዎች መፎካከር መጀመር እንኳን አይችሉም፣ ነገር ግን፣ *ዚ ፕልግሪምስ ፕሮግረስ* እና *ዚ ሆሊ ዎር* የተሰኙትና በጆን በንያን የተጻፉት ለሚሊዮኖች በረከት አልሆኑምን?

በቀላል ታሪክ አማካኝነት ሮሜ ምእራፍ 7 ላይ ያለውን የጳውሎስ ትምህርት በምሳሌ ያስረዳሁት ከሞላ ጎደል ለሠላሳ ዓመታት ገደማ ነው። በጨለማው ሌሊት ወደ ቤቱ የሚጓዝ ሰው ይህ ያሳስበዋል። ጭቃማ ወደሆነ አረንቋ ውስጥ ወደቀ፣ ነገር ግን ወደ ብርሃን እስኪመጣ ድረስ ምን ያክል ጭቃ እንደለበሰ አላስተዋለም ነበር። ከዚያም የተቻለውን ያክል ንፁህ ለመሆን የሚችለውን ያክል ሞከረ። ችግሩ ወደ ብርሃን በቀረበ ቁጥር፣ ቆሻሻውን የበለጠ ማየቱ እና ለማንፃት የሚያደርገው ሙከራ አስቸጋሪ መሆኑ ነበር። በስተመጨረሻ ከብርሃን በታች ቆሞ እስከዚያ ጊዜ ድረስ ተጣብቆበት ባለው የቆሻሻ ክምር ተሸፋ በመቀኑረጥ ጮኸ። 'እኔ ምንኛ ኅስቋላ ሰው ነኝ!' (ሮሜ 7፡24) የሚለው ሊነገር የሚችለው ለጌታ ቅርብ በሆኑ ሰዎች ብቻ ነው።

ይህንን እየጠቀስኩኝ ያለሁት ለምንድነው? መልካም፣ ከጥቂት ወራት በፊት፣ ተማሪ ሳለሁ አንብቤው የነበረውን አንድ መጽሐፍ በድጋሚ ለማንበብ ወሰንኩ። ከአርባ ዓመታት ክፍተት በኋላ አሁን ላይ ስለመጸሐፉ ያሰብኩትን ለማየት ፈለግሁ። መጽሐፉ በዎችማን ኒ የተጻፈና *ዚ ናርማል ክርስቲያን ላይፍ* የተሰኘ ሲሆን እኔ ራሴ በሐቅ የፈጠርኩት ይመስለኝ የነበረውን የጭቃውን አረንቋ ምሳሌ እዚያ ውስጥ ሳገኘው ተደነቅሁኝ! ነጥቤ ይህ ነው፡- የጸሐፊው ኒ በቤታቸው የፈጠሩት ምሳሌ ግልጽ በሆነ መልኩ በጣም ውጤታማ ሆኖ ነበር። ይህም የሆነው ቢያንስ በእኔ ገጠመኝ እርሳቸው እንደተጠቀሙበት እየተጠቀምኩበት ባይሆንም፣ የእኔ እስኪመስለኝ ድረስ በልቤ ውስጥ ጠልቆ ገብቶ ነበርና ነው።

በስብከቴ አሁን ላይ ለበርካታ መቶ ጊዜያት የምጠቀመው በቤቴ የተፈለሰፉ ታሪኮችን፣ ምሳሌዎችን እና ተለዋጭ ትርጓሜዎችን ነው። በእያንዳንዱ አጋጣሚ ውጤቱ ተመሳሳይ ነው፣ ሰዎች ቀጥ ብለው እንዲቀመጡ፣ ወደ ፊት ጠጋ እንዲሉ እና መላውን ትኩረታቸውን እንዲሰጡኝ፣ ከዚያም በኋላ እንዲያመሰግኑኝ አድርገዋል። በተለመደው ማንኛውም ቀን ላይ አድማጮቻችሁ ላይ ምን እንደሆነ አስባችሁ በዙሪያው ላይ ለምን ታሪክ አትፈትሉም? ፈተናን ወይም ጥርጣሬን፣ ወይም ለመመስከር መድፈር ላይ ረቂቅ በሆነ መልኩ ከመናገር

ይልቅ፣ እያንዳንዱ ሰው የሚያስታውሰውን ትእይንት ለምን አትፈጥሩና በእነዚያ ላይ ተገቢ የሆኑትን ትምህርት እንዲሁም ተዛምዶዎች ለምን አትሠሩም? ንፁህ የሆነ ፈጠራ ማታለል ማለት አይደለም። እያደረጋችሁ ያላችሁትን ሰዎች ያውቃሉ። ጌታችሁም እንዲሁ ያለውን ነገር ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት አድርጎት እንደነበረ ያውቃሉ።

(iv) ከሌላ ቦታ

ከመጽሐፍ ቅዱስ እና በስሜቶቻችን እንዲሁም በምናባችን ከሚመጡልን በተጨማሪ፣ መጠን የሌላቸው ሌሎች የአስረጅ ምሳሌዎች ምንጮች አሉ። እንደ ክርስቲያን ሰባኪዎች፣ ሁሉም እውነት የእግዚአብሔር እውነት እንደሆኑ እናምናለን። መላው ዓለም የእርሱ እንደሆነች እናምናለን። ስለ ኃጢአት የምንችለውን አክል ጥቂት ልናውቅ እንደሚገባን እናምናለን፣ ደግሞም ስለ ሌላው ነገር ሁሉ የተቻለንን ያክል በብዙ። ይህም ሲሆን፣ ለእኛ ክፍት በሆነ በእያንዳንዱ ክልል፣ በታሪክ፣ በመልክዓ-ምድር፣ በሂሳብ፣ በሳይንስ፣ በቋንቋ፣ በህክምና፣ በሥነ-ጥበብ፣ በሥነ-ጽሑፍ፣ በቅኔ፣ ሙዚቃ፣ ማኅበራዊ ሳይንሶች፣ ቴክኖሎጂ፣ ወቅታዊ ጉዳዮች፣ ፖለቲካ፣ ህግ፣ ንግድ-ሥራ፣ ስፖርት፣ የመግባባት ክህሎቶች ወይም በማናቸውም ላይ እውቀታችንን ለማሳደግ የምንችለውን ያክል ጥረት እናደርጋለን። የተራበ አእምሮ ያለው መሆን ትክክል መሆኑን እናምናለን። መጽሐፍትን እናነብባለን፣ ቴሌቪዥን፣ ቪዲዮና ፊልሞችን እንመለከታለን፣ ገለጻዎች ላይ እንገኛለን፣ ወደ ቲያትር እና ኮንሰርቶች እንሄዳለን፣ በውሳኔዎች ላይ ድርሻችንን እንወጣለን፣ ደግሞም በሄድንበት ቦታ ሁሉ ጥያቄዎችን እንጠይቃለን!

የሚታወቅ ያለው ምን ያክል ነው! የምናውቀው ትንሹን ክፍል ብቻ ነው። ነገር ግን በዚያች ትንሽ ክፍል ስብከታችንን በምሳሌ ለማስረዳት ልንጠቀም የምንችለው *ብዙ* ነገር አለ። ዕውቀት እንዲኖረን የምንሻው ለገዛ ራሱ ሲል ነው፣ ነገር ግን ዕውቀትን ስናገኝ የእግዚአብሔርን እውነት የበለጠ የሚስብ በሆነ መንገድ የምናውጅበትን ችሎታ እንጨምራለን።

ነገር ግን፣ አሁንም በድጋሚ ጠንቃቆች ልንሆን ይገባናል። አስረጅ ምሳሌዎች ሰዎች ከሚታወቀው ወደማይታወቀው እንዲያልፉ የሚረዳ መሣሪያ ነው። ምንም ከማያውቁት ክልል አስረጅ ምሳሌው የተወሰደ ከሆነ፣ አብዛኛውን

ጊዜ ሊረዳቸው አይችልም። በተጨማሪ፣ የገዛ ራሳችን ልብ አሳች ይሆናል። ምን ያክል እንደማውቅ በኩራት ለማሳየት ምስባኩን እንደ መድረክ መጠቀም ቀላል ነው። ጌታ በሚሰጠን ዐቅም ሁሉ ይህንን ፈተና ልንቋቋም ይገባናል። ከተቋቋምነው፣ ቢያንስ ለአጭር ጊዜም ቢሆን ይሄዳል (ያዕቆብ 4፡7)።

ይሁን እንጂ፣ ሰዎች ጨርሶ ምንም የማያውቁባት ክልል ቢሆንም፣ ከቤተክርስቲያን ታሪክ ብዙ አስረጅ ምሳሌዎችን እንድታወጡ ልለምናችሁ እወድዳለሁ። አሁንም በድጋሚ፣ ታሪክን *እሰከነገርን* ድረስ ዝም ብሎ መናገር ሳይሆን በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ ልንገድል እንችላለን። የእግዚአብሔርን ታላቅ ተግባር ለሰዎች የማስታወስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግዴታችንን በምንፈጽምበት ጊዜ፣ ነፍስን ሊያነቃንቁ የሚችሉ አስረጅ ምሳሌዎችን ልንጠቀም እንችላለን። አድማጮቻችን ስለ እምነት ታላላቅ ጀግኖች እና ስለውለታቸው ሊያውቁ ይገባል። የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ስላለፈችበት መከራ እና እንዴት እንደተጋፈጠቻቸው ሊያውቁ ይገባል። በጉበዝና ታሪኮች፣ ማስተዋሎች እና በሚስዮናዊያን ጥረቶች ሊነኩ ይገባል። የአስረጅ ምሳሌ ምርጫችን ለእነርሱ ታሪክን እና ቅርስን እየተወላቸው እንደሆነ ማየት መቻል አለባቸው።

ደግሞም ሌላ ልመና አለኝ። ይሄኛው ከበይነ-መረብ (ኢንተርኔት) ጋር የተያያዘ ነው፣ የእግዚአብሔር አቅርቦት አስደናቂ የሆኑ ጥሪቶችን ሰጥቶናል፣ ደግሞም እኛ ስለእነዚህ ልናመሰግነው ይገባናል። አዎን፣ ልክ እንማንኛውም የተፈጠሩ እና በሰዎች የሚንቀሳቀሱ ነገሮች፣ በሚያስፈራ ሁኔታ ቴክኖሎጂው በኃጢአት የተበከለ ነው። አዎን፣ የብርቱ ፈተና ምንጭ ነው፣ ደግሞም በአእምሯቸው ውስጥ ለእግዚአብሔር ክብር ለማይጠቀሙበት መቃብር የሆነ አደጋ ነው። ነገር ግን ለሰባኪ እንዴት ያለ ጥሪት ነው! ይህ መጽሐፍ እየተናገረ ባላቸው ክልሎች ሁሉ ላይ ለመርዳት ጉልህ የሆኑ እገዛዎችን ሊሰጥ ይችላል። በዐሥር ሺዎች የሚቆጠሩ የስብከት አስረጅ ምሳሌዎችን የሚሰጡ ድረ-ገጾች አሉ! ለእናንተ ያለኝ ልመና በይነ-መረብን በኃጢአተኛ መንገድ ሳይሆን፣ የታታሪነት ሥራን ማስወገጃ መንገድ በማድረግ ሳይሆን፣ ነገር ግን በጸሎት እና እንስፍስፍ በመሆን እንድትጠቀሙበት ነው። ደግሞም በተለይ በዚህ የስብከት አስረጅ ምሳሌ ክልል ላይ እገዛ ለማግኘት ተጠቀሙበት። እርሱም እያንዳንዳችን ልናሻሽለው እንደሚገባ አምነን የምንቀበለው ነው።

[3] አስረጅ ምሳሌዎችን መምረጥ

ቀደም ያለው ክፍል የጠቆመውን ነገር ሁሉ ካደረግን፣ ልንቋቋም ከምንችለው በላይ ብዙም ሳንቆይ ብዙ አስረጅ ምሳሌዎች ይኖሩናል! በርካቶቹን ልንጥላቸው እና በጣም ምርጥ የሆኑትን ብቻ ልናቆይ እንፈልጋለን። እናስ የጥሩ አስረጅ ምሳሌዎች ባህርያት ምንድናቸው?

(i) የበታች ናቸው

ስለ አስረጅ ምሳሌ በጣም ጠቃሚ የሆነው ነገር የበታች መሆኑ ነው። በሌላ አነጋገር፣ በምሳሌ እያስረዳ ያለውን እውነት ለማሳየት ትኩረትን ይሰብ ዘንድ የተሳካለት ሊሆን ይገባል። አንዳንዶቹ አስረጅ ምሳሌዎች ትኩረት የሚስቡት ወደራሳቸው ነው። ሌሎቹ አእምሮን የሚያኖሩት ሙሉ ለሙሉ በሌላ ነገር ላይ እንዲያስብ እስኪሆን ድረስ በእጅጉ የሚያነቃቁ ናቸው። አሁንም ሌሎች ከእውነታው በላይ ትልቅ ቦታን በመያዝ እውነታውን ይጨቁናሉ። እንዲህ ያሉ አስረጅ ምሳሌዎች ጆንያ ሊሰጣቸው ይገባል። ሥራቸውን አይሠሩም።

በአንድ ወቅት ላይ የትምህርት ቤት ልጆች ቡድንን ሞና ሊዛን እንዲያዩ ወደ ፓሪስ ወደሚገኘው ሎቭሬ እወስድ ነበር። በጭራሽ አላደነቁትም! ከዚያ በኋላ ሲያወሩ የነበረው ታዋቂ ስለነበረው ስዕል አልነበረም፣ ነገር ግን ዙሪያውን ስለሚገኙት ስለ ሁሉም ዓይነት የደንነት መሣሪያዎች ነበር እንጂ። የሚነጋገሩት ስለ ብርሃኖች እና እንቅስቃሴ መከታተያዎች፣ ማንቂያ ደወሎች እና የደንነት በሮች ነበር እንጂ እንደ ቅርስ የሚታየውን ፈገግታ ጨርሶ አልጠቀሱም። አነጋገራቸው አይተውት እንደማያውቁ ያክል ነበር። ያ ኤሌክትሮኒካዊ መሣሪያ የሚያስታውሰኝ በርካቶቹን የስብከት አስረጅ ምሳሌዎቼን ነበር!

አስረጅ ምሳሌዎች እውነታው ላይ ብርሃን ከመፈንጠቅ በስተቀር ሌላ *ምንም* ሊይነት ዓላማ የላቸውም። ምንም አስረጅ ምሳሌ የማይተዉልን ሰባኪዎች በሚጨቀኑን ደብዛዛ ብርሃን ውስጥ ያደናብሩናል። በርካታ አስረጅ ምሳሌዎች ያሏቸው ሰባኪዎች በዘር ማፍያ ውስጥ የምንኖር ያክል ምኞት ይነሱናል። የሚያስፈልገን ነገር ግልጽ አድርጎ ለማየት የሚያስችል በቂ ብርሃን እንጂ ከዚያ ያለፈ ነገር አይደለም።

ነገር ግን እየሰበክነው ያለው እውነት በአስረጅ ምሳሌ ሊገለጥ የማይችል ቢሆንስ? ለምሳሌ ይህ ከሥላሴ አስተምህሮ አኳያ ሊያጋጥም የሚችል ነገር ነው። የእግዚአብሔር በሦስት አካላት አንድ መሆን ከምንም ነገር *ጋር ሊይመሳሰልምእ* ሥላሴን በምሳሌ ለማስረዳት ብንሞክር በጣም በእርግጠኝነት ስህተት እናስተምራለን። በእርግጥ ይህ ቀድሞውኑም ተከናውኖ ያውቃል። አንዳንድ ሰዎች ሥላሴን ከኤች$_2$ኦ ጋር *ያመሳሰሉት* ሲሆን ይህም እንደ በረዶ፣ ውሃ እና ትነት የተሳለበት ነበር። በረዶ ውሃ አይደለም፣ ውሃ ትነት አይደለም፣ ትነት በረዶ አይደለም - ነገር ግን ሁሉም ሦስቱ ኤች$_2$ኦ ናቸው፤ ሦስቱ በአንድ! ሰዎች እንዲገነዘቡ ይህ አይረዳቸውምን?

በፍጹም፣ አይረዳቸውም። አስረጅ ምሳሌው ሞዳሊዝም ተብሎ የሚጠራውን የሳቤሊየሳዊ የስህተት ትምህርት ብቻ የሚያስተምር ነው። ሞዳሊዝም የሚያስተምረው ራሱን ለእኛ በሦስት አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ በመሆን በተለያዩ መንገዶች የገለጠ አንድ አምላክ አለ በማለት ነው። ኤች$_2$ኦ እንዲሁ ራሱን ለእኛ የሚገልጠው በሦስት የተለያዩ መንገዶች ነው። ችግሩ የትኛውም የተናጠል ኤች$_2$ኦ እንደ በረዶ፣ ውሃ እና ትነት ሆኖ በአንድ ጊዜ መከሰት አለመቻሉ ነው። ሞዳሊዝም ስለ እግዚአብሔር የሚያምነው ይህንን ነው። አንዱ እግዚአብሔር እንደ አባት ሲከሰት በዚያ ቅጽበት ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱሳዊው እውነት በጣም የተለየ ነው:- አብ መላው እግዚአብሔር ነው፣ ወልድ መላው እግዚአብሔር ነው፣ መንፈስ ቅዱስም መላው እግዚአብሔር ነው፤ ይሁን እንጂ አብ ወልድ አይደለም፣ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አይደለም፣ መንፈስ ቅዱስም አብ አይደለም! በቀላል ቃላት ልናስቀምጠው እንችላለን፣ ነገር ግን እንዴት እንደዚያ ሊሆን እንደሚችል ልንገነዘብ አንችልም። እንዲሁም በምሳሌ ልናስረዳውም አንችልም። ስለዚህ *የማንቻል* ከሆነ፣ ልናስረዳ መሞከርም የለብንም።

የሥላሴ አስተምህሮ የሁሉም ታላቁ ምስጢር ሲሆን ከእርሱ ቀጥሎ ያለው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በሁለት የተለያዩ ባህርያት አንድ አካል መኖሩ ነው። እነዚህን አስተምህሮዎች በስብከታችን ውስጥ ለማስተማር ራሳችንን ቀላል ለሆኑ *ዐረፍተ-ነገሮች* መገደብ አለብን። አስረጅ ምሳሌዎችን በጠቅላላ ከተጠቀምን፣ ስህተቶችን ለመጠቆም ብቻ መሆን አለበት! ከዚያም የበለጠ ቀላል በሆኑ *ዐረፍተ-ነገሮች* አስተካክለናቸው፣ ከዚያ እውነቱን በማስተላለፍ ስኬታማዎች ልንሆን ይገባናል።

አስረጅ ምሳሌዎች የበታች ሊሆኑ ይገባል። በየትኛውም ነጥብ ላይ ይህንን ፈተና ከወደቀ፣ ሊተዉ ይገባል። እግዚአብሔር የጠራን ዕውነቱን እንድናውጅ እንጂ፣ እንድናቅበው ወይም እንድናዶለዱመው አይደለም።

(ii) ግልጽ

ግልጽ ካልሆኑ አስረጅ ምሳሌዎች ምንም ዋጋ የላቸውም። አንዳንዶች አድማጩን ግራ እስኪያጋቡ ድረስ በእጅጉ የተወሳሰቡ ናቸው። አስረጅ ምሳሌዎቻቸውን ሲያብራሩ፣ እንደውም የበለጠ በምሳሌ ሲያብራሩ ጊዜ የሚፈጁ ሰባኪዎች አሉ! መብራቶቹን ማብራት ሥራችሁ ሆኖ ሳለ ስለምን ታጠፏቸዋላችሁ?

ዛሬ ላይ ታማኝ አገልጋይ የሆነ፣ ነገር ግን በአንድ ወቅት ልምድ የሌለው የነገረ-መለኮት ተማሪ የነበረና ሲሰብክ እንድሰማው የጋበዘኝ ወዳጅ አለኝ። የመልእክቱ ይዘት ጥሩ ነበር። ይሁን እንጂ ጅማሬው አጥፊ ነበር። ለጉባዔው ስለ ታላቁ ፒራሚድ በመንገር ጀመረ። ነገር ግን ስለፒራሚዱ አንድም እንደማያውቁ ብዙም ሳይቆይ ግልጽ ሆነ። ከዚህ የተነሣ ያለው የት እንደሆነ፣ መቼ እና ለምን እንደተገነባ ሲያብራራ ብዙ ሰዓት ወሰደ። ከዚያም ከፒራሚዱ ግንባታ ትምህርት የሚሆነውን ነገር በማውጣት ስብከቱን ሊያስተዋወቅ ሞከረ። ይህም የግንባታ ርእሰ-ጉዳይ ሌላው ጭራሽ የማያውቁት ነገር ነበር። ከዚህ የተነሣ የታሪክ ትምህርቱ ከብዙ የሲቪል ምህንድስና መረጃ ጋር ተቀይጦ ቀጠለ። መላው ስብከት ወደ ሠላሳ አምስት ደቂቃዎች ወሰደ፤ ከዚያ ውስጥ ዐሥር ደቂቃው ያለፈው በታላቁ ፒራሚድ ገለጻ ላይ ነበር! ሰባኪዎች ተጠንቀቁ! አስረጅ ምሳሌዎች ግልጽ ሊሆኑ ይገባል። በእርግጥ ሊተላለፍ የተፈለገውን ዋናውን ነጥብ ሊስቱት የማይቻል እስከሚሆን ድረስ ግልጽ ሊሆን ይገባል።

(iii) አጭር

አስረጅ ምሳሌዎች አጭር ሊሆኑ ይገባል። አስረጅ ምሳሌዎች ተወስደው ጠቃሚ ባልሆኑ እና ቀረቤታ በሌላቸው ዝርዝሮች ጋጋታ የተሞሉ ከሆኑ እስኪያበላሹ ድረስ ጉባዔያችሁን ያሰለቻሉ። ትናንሽ የሆኑትን መንገዶች እርሷቸውና ወደ ዋናው መንገድ ጉበታችሁ ሰዎቻችሁን በተቻለ ቀጥተኝነት ከሀ እስከ ለ

ውሰዷቸው! በአስረጅ ምሳሌዎች ሁኔታ የሚቆጠረው መዳረሻው እንጂ ጉዞው አይደለም።

ይሁን እንጂ፣ ረጅም አስረጅ ምሳሌ የምታቀርቡ ከሆናችሁ፣ እባካችሁን ልትጨርሱት ይሉኝታ ይያዛችሁ። አንድ ወቅት ላይ በአንድ የሣምንት ማብቂያ መጽሔት ላይ አስደናቂ የሆነ መጣጥፍ ማንበብ ጀምሬ ነበር። የማነበው ስለ ሕይወት ዘይቤ እና ስለ ልዑል ቻርለስ ዐቋሞች ነበር። ጽሑፉም ፈጽሞ ስለማላውቃቸው ነገሮች ይነግረኝ ነበር። ወደ ገጹ መጨረሻ ደረስኩና ገለጥኩት። ነገር ግን መጣጥፉ እዚያ አይቀጥልም ነበር! ወይም በመላው መጽሔት ውስጥ የቱጋር እንደሚቀጥል አይገልጽም። ተበሳጨሁ ደግሞም እንደተታለልሁ ተሰማኝ።

ልክ እንደዚያ የሚያምኑ ሰባኪዎች አሉ። አስረጅ ምሳሌዎችን ይጀምሩና ብዙም ሳይቆዩ ጠቀሜታ እንደሌለው ወይም በጣም ረጅም እንደሆነ መገንዘብ ይጀምራሉ። ስለዚህ ይጥሉትና ስብከታቸውን ይቀጥላሉ። ታሪክ፣ ምሳሌዎች ወይም ተለዋጭ ትርጓሜዎች ካልሆኑ በቀር ጉባዔ ረጅም ምሳሌዎችን አለመውደዱ እውነት ነው። ነገር ግን ቀጥሎ የሆነውን ነገር እንዲገምቱ በአውላላ ሜዳ መተዉንም እንዲሁ አይወድዱም። ምንም ቢሆን ምን ስለዚያስ ነገር የሚያስቡት ለምንድነው? መላውን አእምሯቸውን ለቀረው የሰብከቱ ክፍል እንዲተዉ አትፈልጉም?

(iv) የተከበረ

አስረጅ ምሳሌዎቻችን አጭሮች ቢሆኑ ወይም ረጅም፣ ሁሉም የተከበሩ ሊሆኑ ይገባል። እየሰበክን ያለነው *መለኮታዊ* እውነታን አይደለምን? ሻካራ፣ የማያስደስት ወይም እርባና ቢስ ከሆነው ነገር ውስጥ ስእልን በመሳል ቅዱስ የሆኑ ነገሮች ላይ ብርሃን ልንፈነጥቅ እንችላለንን? በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ መጥፎ ጣዕም የለም፣ ስለዚህ በእርግጥ በክርስቲያን ምስባክ ላይም ቦታ አይኖረውም።

ፈረንሳዊ የሆነው የቅርብ ጓደኛዬ አንድ ወቅት ላይ የሌ ፑዬን ጉልህ የሆነ ካቴድራል እንድመለከት ይዞኝ ወጣ። በጣም ውድ ከሆነው ከተማ በላይ ከፍ ያለ እና ወደ ላይ በምትወጡት በእያንዳንዱ ደረጃ ልክ የበለጠ

የሚያስደምም ነበር። ከሃብቶቹ አንደኛው በከፍተኛው መሰዊያ ላይ የተንጠለጠለው የመካከለኛው ዘመን ስእል ነበር። በደመና ላይ የተቀመጠ ባለ ነጭ ፂም ሽማግሌን ያሳያል። እግዚአብሔር መሆኑ ነው!

የእምነት ተጓጉቹ እና ጎብኚዎቹ በዚያ ስእል ተስበው ሌሎችም መጥተው እንዲያዩት ያበረታታሉ። በፊት ለፊቱ ይጸልያሉ ከዚያም በኋላ የስእሉን ፖስት ካርድ ገዝተው ይሄዳሉ። ነገር ግን፣ በመሠረቱ እግዚአብሔርን ያራከሰ ነገር ነው። ስድብ ነበር። መፈጠሩ በራሱ የህጉ ጥሰት የተፈጸመበት ነው። ግርማዊነቱን ይሰርቀውና በየትኛውም የሚያምን ልብ ውስጥ አምልኮን ለመቀስቀስ ምንም አያደርግም። አዎን፣ ስእሉ ታዋቂ የሆነበት ምክንያት እውነተኛ አይደለም ማለት አይደለም። ይህ ምሳሉ ለምስለ-ቃላትም እንዲሁ ነው። የተከበሩ ሊሆኑ ይገባቸዋል። ሊያስረዱ በመሞከር ላይ ላሉት እውነት ፍርሃት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል።

ይህ ማለት አጫዋች የሆነ ነገር በምስባክ ላይ መቼም አንጠቀምም ማለት ነውን? የእኔ ዐቋም በመደበኛ ሁኔታ አስቂኝ ለመሆን ማቀድ የለብንም፣ ነገር ግን ፈጽሞ ተፈጥሯዊ በሆነ መልኩ አስቂኝ ነገር ከመጣ፣ ንፁህ እስከሆነ ድረስ አብዛኛውን ጊዜ መልካም ነገር ይሆናል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በርካታ አጫዋች ነገሮች ይገኛሉ፤ ምሳሌ ኤልያስ ለበዓል ነብያት የተናገራቸው አላጋጭ ቃላት (1 ነገሥት 18፡27)፣ ወይም በእኩለ ሌሊት እንግዳ የመጣበት ባልንጀራ ታሪክን የተናገረበት የጌታችን ምሳሌ (ሉቃ. 11፡5-8)። እንዲህ ያሉ ቀልዶች በበስተቀረ የሚያዝ ቢኖራቸውም አብዛኛውን ጊዜ አስተምህሮን ለማስተማር ጥቅም ላይ አይውሉም። አብዛኛውን ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውለው እውነታውን ወደ ቤት ለመሸኘት ነው፣ በተለይም ግብዝነትን እና እውነተኛ አለመሆንን ለማሳየት ነው። *የበታችነት* መርኾን በአእምሯችን ከጠበቅን፣ በዚህ ክልል ላይ በርከት ያሉ ስህተቶችን ልንፈጽም አይገባንም።

(v) ልዩ ልዩ

እስካሁን ባልናቸው ነገሮች ሁሉ ላይ በተጨማሪ፣ አስረጅ ምሳሌዎች የተለያዩ ሊሆኑ ይገባቸዋል። ሊቆጠሩ የማይችሉ ትምህርቶችን ከአንድ ሻማ ማውጣት ከሚችልበት ከሲ. ኤች. ስፐርጀን ያልተለመደ ብቃት በተለየ፣ ሁሉም አስረጅ

ምሳሌዎች የተወሰዱት ከዚህ ምንጭ በሚሆንበት መልኩ ስብከት አለመስበኩን ማስተዋሌ ደስተኛ ነኝ። እንደዚያ አድርጎ ቢሆን ኖሮ፣ ዘመናዊ ተንታኞች አስገዳጅ በሆነ የመመሰጥ በሽታ እንደሚሰቃይ አድርገው በሽታ እንዳለበት ሊናገሩ ይችሉ ነበር!

አንድ የአረንጓዴ ከለላ ብቻ ቢኖር ገጠሩ ምን ይመስል ነበር? ደግሞስ አስረጅ ምሳሌዎች ሁሉ የተወሰዱት ከሰባኪው የቤተሰብ ሕኢወት ወይም፣ ከትርፍ ጊዜ መዝናኛዎቹ፣ አሊያም (ከሁሉ የከፋው?) ከእግር ኳስ ፍቅሩ ቢሆን ስብከት ምን ይመስል ነበር? 'ሁሌ አንዳይነት የሆነ' ነገር ምን እንደሆነ ሁላችንም እናውቃለን ደግሞም አዝሎናል። በከረሜላ ፋብሪካዎች የሚሠሩ ሰዎች በሥራ ሰዓታቸው ላይ የወደዱትን ያክል ከረሜላዎች መብላት ይችላሉ፣ ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ የትኛውንም በጭራሽ የማይበሉ ይሆናሉ። በእርግጥም ልዩነት የሕይወት ቅመም ናት።

ወቅቶችን የሰጠ፣ እና የቀስተደመና ቀለማትን የቀባ አምላክ እንደራሴዎች ነን። ይህንን ዓለም በብዙ ዓይነት ዝርያዎች ሞልቶ ለእያንዳንዱ ፊት የተለያየ ቅርጽን ሰጥቷል። በገዛ ራሱ ያልተከፋፈለ ማንነት ውስጥ እንኳን ልዩነት አለ። የስብከት አስረጅ ምሳሌዎችን ቀደም ሲል ከገለጽናቸው ምንጮች በሙሉ በማውጣት ልዩ ልዩነታቸውን ከጠበቅን፣ ለእርሱ ክብርን እናመጣለን።

(vi) ትክክለኛ

ሊገለጽ የሚገባው የመጨረሻው ነገር አስረጅ ምሳሌዎቻችን ትክክለኛ ሊሆኑ የሚገባቸው መሆኑ ነው። እውነተኛ *ባለመሆን* እውነትን በምሳሌ ማስረዳት አንችልም። ያልደረሱብን ሆነው ሳሉ እንደደረሱብን አድርገን ልንናገር አይገባንም። ታሪክ፣ ግለ-ታሪክ ወይም የትኛውንም የዕውቀት ዘርፍ ብናጣቅስ፣ እውነታዎቻችንን ትክክለኛ አድርገን ልናገኝ ይገባናል። ሰዎች ስለ ተራ ነገሮች የማይታመኑ የመረጃ ምንጮች አድርገው ካገኙን፣ ስለ እግዚአብሔር ነገሮች ስናናግራቸው ምን ያስባሉ?

በአንድ ወቅት በፀሐይ ብርሃን ስርዓት መዋቅር ላይ መሠረት ያደረገ አስረጅ ምሳሌ ተጠቀምኩ። ሰዎች ተስበው ነበር፣ ነገር ግን በርካቶቹ እንግዳ የሆነ

ፊት ያሳዩ ነበር። አምልኮ እንዳለቀ በሩ ላይ ሠልፍ ሰርተው ጠበቁኝ። እያንዳንዱ ሰው ተመሳሳይ ነገር ነገረኝ፦ ፕላኔቶቹ እኔ በተናገርኩት ቅደም ተከተል አልነበሩም! አፈርኩኝ፣ ተሸማቀቅሁም። እውነታ የሆነ ያክል ስህተትን ሰበክሁ፣ ከዚያም የተነሣ የገዛ ራሴን ተዓማኒነት አንቄ ገደልኩት። የምላስ ወለምታ አንድ ነገር ነው። ሊወገድ የማይችል ስህተት ሌላ ነው።

አስረጅ ምሳሌዎቻችን በእውነታ ደረጃ ትክክለኛ መሆን ይኖርባቸዋል፣ ከነገረ-መለኮት አኳያም ትክክለኛ ሊሆኑ ይገባል። ስለ ኤች$_2$ኦ አስረጅ ምሳሌ የትኛውንም ተጨማሪ ነገር ማለት ያስፈልገናል? ያ ግልጽ የሆነ እውነትን የማጣመም ሁኔታ ነው። ለምሳሌ፣ አንዳንድ ሰዎች ወደ ጌታ ሲመጡ በቀላሉ ስለ አዲስ ሕጻን መወለድ ተነግሯቸው ወደ ተሻለ መረዳት ይመጣሉ። ሕጻን ልጅ ለመወለድ *ብሎ* ያለቅሳል ወይም *ስለተወለደ* ያለቅሳል? በተመሳሳይ መንገድ ወደ ጌታ የምንጮኽበት ጩኸት አዲስ ልደት ያገኘን መሆናችንን በሚያረጋግጥ መልኩ የሚሆን እንጂ ሰበብ ያልሆነ ነው።

አሁንም በተጨማሪ፣ *የበታችነት* መርኾ እዚህ ጋር ሊጋፈጠን ያሉ አደጋዎች ውስጥ ይመሩናል። በነገረ-መለኮት ደረጃ ትክክል ያልሆነ አስረጅ ምሳሌ እውነቱን ሊያገለግል አይችልም፣ ነገር ግን ትክክለኛ የሆነው ለዘላለም ወደ ትውስታ እንዲገባ ሊያደርገው ይችላል።

* * *

ይህንን ምእራፍ ለመዝጋት ጊዜው ነው። የምንሰብከው የትኛውም መልእክት ግልጽ በሆነ አስረጅ ምሳሌ እንዲሰበክ ሁላችንን እየለመንኩኝ ነኝ። ሕዝቦቻችን ልናስረዳቸው እየሞከርን ያለነውን ነገር ቅርጽ ሁልጊዜ ማየት አይችሉም። መብራቱን እናብራ! እንዲጭበረበሩ በሚተዋቸው እና እና እንደዚያም ሆነ እንዳያዩ በሚያደርጋቸው መልኩ ብዙ ብርሃን ልንለቅ አይገባንም። በመደነቅ እንዲያቃትቱ ወደሚያደርጋቸው የባለጌጥ አምፑል መያዣ ሊኖረን አይገባም። የተለመዱ መብራቶች ይህንን ያደርጋሉ። ደግሞም ስብከታችን ‘ለማለት የፈለገውን አሁን አገኘሁት!’ ሲሉ በምንሰማቸው ጊዜ ስብከታችን አንዳች መልካም ነገር እንዳደረገ እናውቃለን።

* * *

መወያያ ጥያቄዎች

1. በቀላሉ እና ነፃ በሆነ መልኩ አስረጅ ምሳሌ የሚጠቀም ጓደኛ አላችሁ፣ ነገር ግን እርሱን የሚሰሙት ሰዎች እርሱ ታሪክ ተናጋሪ ብቻ ነው ይላሉ? ለእርሱ ምን ትሉታላችሁ?

2. የተቀመጣችሁበት ክፍል ውስጥ ልታዩ ከምትችሉት ነገር ውስጥ ሦስት አስተምህሮዎችን በምሳሌ አስረዱ።

3. ኤፌሶን 2፡8-9 ላይ ለሚሰበክ ስብከት እንዲረዳችሁ የምትጠቀሙበት አስረጅ ምሳሌ ምንድነው?

5

በነጥብ የሚቀመጥ ተዛምዶ

ሙሉ ልብሶቼን ሁልጊዜም የምገዛው ከመስቀያ ውጭ በመሆኑ መቼም ሰፊዎች ጋር ሄጄ አላውቅም። ይሁን እንጂ፣ በርካታ ሰዎች ልብስ ለመለካት አሁን ድረስ የሚሄዱ እንዳሉ ሰምቻለሁ። ይህንን ምእራፍ መጀመር የምፈልገው ይህ አሳብ በአእምሮ እንደተያዘ ነው።

የገዛ ራሱን ልብስ የሚሰፋ ልብስ ሰፊን በምናባችሁ ሳሉ። በክሮቹ (ሥነ-ፍታቴያዊ ትክክለኝነት) ውስጥ ምንም እንከን የለም። ብርቱና ከፍተኛ ጥራት ያለው እቃ ነው (አስተምህሯዊ ፍሬ-ነገር)። የሚስብ ወደሆነው ንድፍ ተሸምኗል (ግልጽ የሆነ መዋቅር)። ሌላው ቢቀር ተራ የሆነ ሰው ምን ያክል መልካም እንደሆነ ሊያይ እና ሊሰማው ይችላል (ግልጽ የሆነ አስረጅ ምሳሌ)። ስለዚህ ቅር የምንሰኝበት አንድም ነገር አይኖርም፣ አለ? ደግሞም ሰፊው ሥራውን ገና እንዳልጨረሰ ሁላችንም እናውቃለን።

የሰፊው ሥራ ለሰዎች ልብስ መስፋት ነው። ደንበኞቹ በሁሉም ዓይነት ቅርጾች እና መጠኖች ውስጥ ሆነው፣ እንዲሁም በጣም የተለያዩ ፍላጎቶች ውስጥ ሆነው ይመጣሉ። የልብስ ምርጫን ከማድረግ ያለፈ ነገር ሊያደርግ ይገባዋል፤ እያንዳንዱ ደንበኛ በየቀኑ እንዲለብሱት ልካቸው የሚሆናቸውን እንዲያገኝ ሊቆርጥ ይገባል። ይህንን ማድረግ የማይችል ሰፊ በንግድ ሥራው ውስጥ መግባት የለበትም።

አድማጮቻችን በእያንዳንዱ የሣምንቱ ቀን ላይ ሊለብሱት ካልቻሉ እንደ ሰባኪዎች የምናደርገው ነገር ሁሉ የከሰርንበት ነው። የቃሉ አድራጊዎች እንጂ ሰሚዎች ብቻ መሆን የለባቸውም (ያዕ. 1፡22)። 'አንዱ ልኬት ለሁሉም ይሆናል' የሚባልለት አይነት ስብከት መስበክ ስህተት ነው። እኛን የሚሰሙን ሰዎች ሁሉ ተመሳሳይ ልብስ መልበስ ይኖርባቸዋል፣ ነገር ግን ለእያንዳንዳቸው በሚሆናቸው ልክ አኳያ ልንቆርጠው፣ ከዚህ የተነሣ በተናጠላዊ ሁኔታዎቻቸው ውስጥ በቀላሉ የሚለብሱት ሊሆን ይገባናል። ከመስቀያው የወረደ አገልግሎት ይህንን አያደርግም። የእግዚአብሔር እውነት በዚህ ዓለም ውስጥ በክብር መለበስ ካለበት፣ ስብከቶች ልክ እንደ *ልብስ ሰፌት በልክ የተሠሩ መሆን አለባቸው።*

[ነ] በነጥብ የሚቀመጥ ተዛምዶ ምንድነው

(ነ) ትርጓሜ

ጆን ኤ. ብሮዱስ በዐሥራ ዘጠነኛው ክፍለ-ዘመን ደቡባዊ የአሜሪካ ግዛቶች ውስጥ በኃይል ይሰብኩ ነበር። መጽሐፋቸው *ዚ ፕሪፓሬሽን ኤንድ ዴሊቨሪ ኦቭ ሰርመንስ* የታወቀ ሥራ ነው። ምንም እንኳን መጽሐፉ ለማንበብ በእጅጉ የሚቀልል ባይሆንም፣ እያንዳንዱ ገጽ የተሞላው ግልጽ በሆነ ትምህርት እና ትክክለኛ ምክር ነው። ተዛምዶ የሚኖረው ትርጓሜ ምን እንደሆነ ካስቀመጡት ፍቺ ውስጥ እያንዳንዱን ቃል ለምን አናገናዝብም? እንዲህ ተተርጉሟል፡-

> ተዛምዶ የሚባለው ነገር ጠበቅ ባለው ስሜቱ ሲቀመጥ ርእሰ-ጉዳዩ እየተነገራቸው ላሉት ሰዎች የሚዛመዳቸው እንዴት እንደሆነ የሚያሳይ የመልእክቱ ክፍል ወይም ክፍሎች ሲሆን እርሱም ምን ተግባራዊ መመሪያዎችን እንደሚሰጣቸው፣ ምን ተግባራዊ ጥያቄን እንደሚያኖርባቸው የሚያሳያቸው ነው።[5]

አሜሪካዊው ፈላስፋ እና የትምህርት ባለሙያ ዳንኤል ዌብስተር እንዲሁ የኖሩት እና የጻፉት በዐሥራ ዘጠነኛው ክፍለ-ዘመን ነበር። በአንድ ወቅት ላይ ታዋቂ በሆነ መልኩ የሚከተለውን ተናግረው ነበር፡- 'አንድ ሰው ሲሰብከኝ፣ ግላዊ ጉዳይ እንዲያደርግልኝ እፈልጋለሁ፣ ግላዊ ጉዳይ፣ ግላዊ ጉዳይ።'[6]

ልክ የፀሐይ ጨረሮች በአጉሊ መነጽር ቆዳ ላይ ትኩረት እንደሚሠሩት፣ ተዛምዶም እንዲሁ እየተቃጠለ ያለውን እውነታ በአድማጩ ጎሊና ላይ ያተኩረዋል። የሚሰብከው *ለሰዎቹ* እንጂ እንዲሁ *በፊት ለፊታቸው* አይደለም። እያንዳንዱን ግለሰብ ይለይና መልእክቱ በግል ለእርሱ እንደሆነ እንዲገነዘብ ያደርገዋል። ይጋፈጠዋል። በልቡ በራፍ ላይ እንደሚያንኳኳና የግል መጥሪያ እንደሚሰጥ የፍርድ ቤት መኮንን ሆኖ ይመጣል። ያ ምላሽን ይጠይቃል ደግሞም እዚያው እና ያኔው ሊሰጥ የሚገባው ነገር ሆኖ ይጎተጉታል።

---

[5] ብሮዱስ ጆን ኤ. *ኦን ዚ ፕሪፓሬሽን ኤንድ ዴሊቨሪ ኦቭ ሴርመንስ* (ሎንዶን፣ ሆደር ኤንድ ስቶግተን፣ ቀን የለውም)፣ ገጽ 211

[6] በጆን ኤ. ብሮዱስ የተጠቀሰ፣ ገጽ 210።

(ii) ጠቀሜታ

ተዛምዶ በማይኖር ጊዜ፣ ስብከት ነፍስ፣ ሕይወት እና ሳቢነት የለውም። ለኅሊና የሚያስደነግጥ አሳማኝ አሳብ አይሸከምም፣ ደግሞም ለልብ ፈዋሽ የሆነ መጽናናት የለውም። እያንዳንዱ አድማጭ መቼም ታቅፎ እንደማያውቅ፣ እንዲሁም በጥፊ ተመትቶ እንደማያውቅ ህጻን ልጅ የሆነ ያክል እንዲሰማው ያደርጋል። ምስኪን ልጅ! ምን አይነት ሰው ይወጣው ይሆን? በሕይወት ውስጥ የሚያልፈው ግራ እንደተጋባ እና እንደተረበሸ፣ መንደርደሪያ ሳይኖረው፣ እሴቶች ሳይኖሩት ነው።

ተዛምዶ የሌለው ስብከት መስበክ አንድን ሰው አንድ የሆነ ቦታ ላይ ይመታ ይሆናል በሚል ተስፋ ቀስትን ወደ አየር እንደመተኮስ ነው። ንጉሥ አክዓብ በ1 ነገሥት 22፡34-35 በደስታ ሊቀበለው በማይችለው መልኩ እንደደረሰበት በእግዚአብሔር ቸርነት እንዲያ ሊያደርግ ይችል ይሆናል። ዒላማ የሌላቸው ስብከቶች አንዳንድ ጊዜ አንዳች ነገርን ያሳካሉ! ይሁን እንጂ፣ የእግዚአብሔር የተለመደው የሥራ መንገድ በእጅጉ የተለየ ነው። በአጊንኮርት ጦርነት ላይ የቄልስ ቀስተኞች ወደ አየር ሲተኩሱ፣ እያደረጉት የነበረውን ነገር በትክክል ያውቁ ነበር። ዒላማቸው ትክክለኛ መሆኑን አረጋገጠና ፈረንሳይን ደመሰሷት።

የቀዶ ጥገና ሐኪም ጥሪ ለመፈወስ ነው፣ ደግሞም የሚጠቀምበት መሣሪአ ቢላዋ ነው። ያለ ቢላዋው ሊፈውስ አይችልም፣ ነገር ግን የት ጋር መቁረጥ እንዳለበት ካላወቀ በሽተኛውን ይገድለዋል። ሰባኪም ከዚህ የበለጠ ጠንቃቃ መሆን ይኖርበታል። ተዛምዶ ነፍስን ሊያድን የሚችል ሆኖ ሳለ፣ ያንን ማድረግ አለመቻል ደግሞ ለዘላለም ሊያጠፋው ይችላል። ለአንደኛው ሰው ተስማሚ የሆነው ተዛምዶ ሌላኛውን ፈውስ እንዳይኖረው አድርጎ ሊያበላሸው ይችላል።

በነጥብ የሚቀመጥ ተዛምዶ በሌለበት እውነተኛ ስብከት የለም። ከሐዋርያት የምንማረው ብዙ ነገር አለን። መልእክቶቻቸው በአስተምህሮ የተሞሉ ናቸው፣ ነገር ግን ጸሐፊዎቹ “መልካም እንግዲህ ይኸው ነው፣ አስተምህሮውን አስረድቻለሁ፤ አሁን እነዚህ እውነታዎች በተግባር የሚዛመዱላችሁ እንዴት ሊሆን እንደሚገባ መንፈስ ቅዱስ እንዲያሳያቸሁ እተውለታለሁ' አላሉም። ፈጽሞ! ፈጽሞ! ደግሞም በፍጹም! በጥቁርና በነጭ አስቀምጠውታል። ለተጠሩበት መጠራት እንደሚገባ እንዲመላለሱ አንባቢዎቻቸውን ለምነዋል

(ኤፌ. 4፡1)። ይህ ምን ማለት እንደሆነ ስለ ግላዊ ሕይወታቸው በማነጋገር፣ እና በቤተክርስቲያን ስላለው ባህርያቸው፣ በቤተሰብና ማኅበረሰብ ውስጥ እንዴት እንደሚኖሩ በዝርዝር አሳይተዋቸዋል። እነርሱ ግልጽ የሆኑ ኃጢአቶችን፣ ግልጽ የሆኑ ግዴታዎችን፣ ግልጽ የሆኑ ችግሮችን፣ ግልጽ የሆኑ እድሎችን እና ግልጽ የሆኑ ደስታዎችን ሞግተዋል፣ ደግሞም በዚህ መልኩ ለእኛም የምንከተውን አርአያ ትተውልናል።

የእውነተኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስብከት አንድ አካል እና ጥቅል የሆነው የባለነጥብ ተዛምዶ ባልዳኑት ሰዎች ዓለም ውስጥ ትይዩ የለውም። በጥንታዊት ግሪክ እና ሮም ውስጥ ንግግር ማድረግ በጣም ጠቃሚ የሆነ የሕይወት ክፍል ነው፣ ነገር ግን በሕዝባዊ ቦታ ተዛምዶ መስጠት አይበረታታም ነበር። ተዛምዶን በፕሌቶ፣ ወይም አሪስጣጣሊስ፣ ወይም በተከታዮቻቸው ውስጥ አታገኙትም። ነገር ግን ተዛምዶን የምታገኙት በጳውሎስ፣ በክሪሶስቶም፣ ዊክሊፍ፣ ሉተር፣ ካልቪን፣ ኦውን፣ በንያን፣ ዊትፊልድ፣ ዌስሊ፣ ስፐርጅን፣ ሎይድ-ጆንስ እና ኸግ ሞርጋን ውስጥ ታገኙታላችሁ! የተዛምዶን ጥያቄ ከግምት ሳታስገቡ የክርስቲያን ምስባክ ኃይልን ልታብራሩ አትችሉም። ክርስቶስ ሰውን እንዲሰብክ ሲልክ፣ እውነትን እንዲናገር ብቻ አልላከውም፣ ነገር ግን ለአድማጮቹ ያ እንዴት በተግባር እንደሚውል ጭምር ነበር እንጂ።

ነገር ግን ያልዳኑ ወንዶች እና ሴቶች ተዛምዶን መስማት አይፈልጉም። መንፈሳዊ ያልሆኑ አማኞችም እንዲሁ። አንድ ጊዜ ፈረንሳይን ከስዊዘርላንድ በሚከፍለው በጆራ ተራሮች ባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ኮንቬንሽን እስብክ የነበረበትን አስታውሳለሁ። ከሁለቱም አገራት የመጡ በርካታ ቀኖር ያላቸው ክርስቲአኖች ተሰባስበው ነበር። አንደኛቸው እኔ በምሰብክ ጊዜ እየጨመረ በሚሄድ መልኩ ቅስቀሳ ያደርግ ነበር። ስብሰባው እንዳለቀ ወዲያውኑ ወደ እኔ በቀጣጣ መጣና፣ 'ሞንሲየር ኦልየት፣ ሕዝቦቼ ሕጻናት አይደሉም፣ ሞኞችም አይደሉም። ቃሉን ስትሰብክ እንዴት ተግባራዊ እንደሚያደርጉት ፍጹም ለራሳቸው ማሰብ የሚችሉ ሰዎች ናቸው። በጣም ቀጥተኛ በሆነ መልኩ ልትነግራቸው አያስፈልጋቸውም' አለኝ።

ስብከቴ ፍጹም እንዳልሆነ አምናለሁ፣ ነገር ግን ያ ሰው ተሳስቷል። የሰው ልብ ክፉ ነው፣ መለወጥም አይፈልግም። ቃሉ ጎሊናን እስካልተጫነ ድረስ ይሰበክ ዘንድ በጣም ደስተኛ ነው። የእግዚአብሔር እውነት ለሌሎች የሚተገበረው እንዴት እንደሆነ ሊያይ ይችላል፣ ነገር ግን ለራሱ ሊቀበለው

አይፈልግም። ራስ ወዳድ በሆነ ደግነት በመመላለስ ይጋልባል። በፊት ለፊታችን ላሉት ሰዎች የማናዛምድላቸው ከሆነ ስብከት የትም አይደርስም። በእነርሱ ላይ ልንጭነው እና በስብከቱም ልናሳድዳቸው ይገባል። ምክንያቱም ለእነርሱ በግል ምንም እያላቸው እንዳልሆነ ያስባሉና ነው። ነገር ግን ይህ የሚደረገው እንዴት ነው?

[2] በነጥብ የሚቀመጥ ተዛምዶ እንዴት ይሠራል

(i) ግልጽ ሁኑ

እኛ ሰባኪዎች ነን። ስብከት ስለ ለውጥ ነው፣ ደግሞም ስብከት *ሙሉ ለሙሉ* ስለዚያ ነው። ግልጽ ባልሆነ እና በጥቅል መንገድ እንድንናገር ወይም መርኾዎችን ዝም ብለን እንድናስረዳ አልተጠራንም፣ ነገር ግን ስለ ኃጢአት እንድንናገር፣ ወደ ክርስቶስ እንድንጠቁም፣ እና ስለ ወንጌል ስለሚጠይቀው ግዴታዎች እና ማጽናኛዎች ለሰዎች በደነዘ መልኩ አንንገራቸው። ለሌላ ትውልድ ሲጽፍ ቻርለስ ብሪጅስ ልክ እንዲህ አስቀምጦት ነበር፦ 'ስብከት ውጤታማ እንዲሆን፣ ግልጽ ካልሆነ ጥቅል መልእክትነት፣ ተጨባጭ ወደሆነ የግላዊ ባህርይ - ወደ እያንዳንዱ ሰው ቤት እና ሥራ እንዲሁም ወደ ደረቱ ሳይቀር መውረድ አለበት'[7]

ጌታ በማቴዎስ 19፡21 ላይ እንዴት እንደፈጸመው ተመልከቱ። ባለጠጋ የሆነው ወጣት ገዢ በቤቱ ሳይሆን በልቡ ውስጥ ጣዖት እንዳለው ማየት ችሎ ነበር። ፈጣሪውን ከሚወድድበት ፍቅር በላይ ገንዘቡን የበለጠ የሚወድድበት ኃይማኖተኛ ቀሳዊ ሰው ነበር። በስር ያለውን ጣዖት አምልኮ ጋር የተያያዙ መርኾዎችን በተመለከተ ጌታችን ገለጻ ሰጥቶት ከዚያ በውጤቱ ምን ሊያደርግ እንደሚችል እንዲያስብ አልተወውም። ወደ ቤት እንዲሄድ፣ ጣዖቱን እንዲያደቅቅ፣ ዘላለማዊ ብድራቱን እንዲያስብ እና ጌታውን እንዲከተል ነገረው፦ 'ፍጹም ልትሆን ብትወድ፥ ሂድና ያለህን ሽጠህ ለድሆች ስጥ፥ መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ፥ መጥተህም ተከተለኝ አለው።'

ጌታችን በዩሐንስ 4፡15-16 ያደረገውን ተመልከቱ። ግብረ-ገብ እንደሌላት የምትቆጠረውን ሳምራዊት ሴት በሕይወት ውሃ ላይ ግላዊ ፍላጎቷን

---

[7] ብሪጅስ፣ ቻርለስ፣ *ዘ ክርስቲያን ሚኒስትሪ* (ለንደን፣ ዘ ባነር ኦቭ ትሩዝ ትረስት፣ 1958)፣ ገጽ 271።

እስከምታሳይበት ነጥብ ድረስ ያነጋግራት ነበር። ቀጣዩ እንቅስቃሴው የኋላ ጊዜ ሕይወቷ ላይ ንስሃ ልትገባ የሚገባት መሆኑን ጠቅለል ባለ መልኩ መናገር አልነበረም። እንድትጋፈጠው ነው ያደረጋት። 'ሂጂና፣ ባልሽን ጠርተሽ ነይ' አላት። ከዚያ በኋላ ተከትሎ የሆነውን ነገር እናውቃለን።

ጌታችን በማርቆስ 7፡20-23 ላይ ያደረገውን ነገር ተመልከቱ። ስለ ልብ መበከል ምንም ያልገባቸውን ሰዎች እያነጋገረ ነበረ። ስለዚህም ስህተታቸውን አሳያቸውና ጥቅል የሆነውን መርኸ አስተማራቸው፡- 'ሰውን የሚያረክሰው ከሰው የሚወጣው ነው።' በርካታ ዘመንኛ ሰባኪዎች የሚያቆሙት እዚያ ጋር ነው። ከዚያ አልፈው አይናገሩም፣ ነገር ግን ይህ በእርግጥ ምን ማለት እንደሆነ እንዲያስቡ ሰዎቹን ይተዉአቸዋል። ጌታችን እንደዚያ አልነበረም። የትኛውም ሰው በዐይነ-ኅሊናው ሊስለው እንደሚችለው አድርጎ በጥቂርና ነጭ ያስቀምጥላቸዋል።

> ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣ ክፉ አሳብ፥ ዝሙት፥ መስረቅ፥ መግደል፥ ምንዝርነት፥ መጐምጀት፥ ክፋት፥ ተንኰል፥ መዳራት፥ ምቀኝነት፥ ስድብ፥ ትዕቢት፥ ስንፍና ናቸውና፤ ይህ ክፉው ሁሉ ከውስጥ ይወጣል ሰውን ያረክሰዋል።

ሐዋርያው ጳውሎስ የጌታውን ዘዴ በጣም በቅርበት የተከተለው እንዴት እንደሆነ ተመልከቱ። በገላትያ 5፡16-18 ላይ በዚህ ዓለም ውስጥ ሁለት ዓይነት ባህርያት እንዳሉ ለአንባቢዎቹ ነገራቸው። አንደኛው ዓይነት በመንፈስ የተመራ እና ሌላኛው ደግሞ 'የስጋ ፍትወት' ነው። በመንፈስ መንገድ ከሄዳችሁ የሚያባብል ቢሆን እንኳን በሌላኛው መንገድ አትሄዱም። ደንቦች በተሳሳተው መንገድ ከመሄድ አይመልሷችሁም፣ ነገር ግን በመንፈስ መንገድ መሄድ ግን ይመልሷችኋል!

ጳውሎስ የጻፈው ነገር ግልጽ ነው፣ ነገር ግን ጥያቄን ያስነሳል፣ ገላቲያውያኑ *በእውነት* የትኛው መንገድ የትኛው እንደሆነ አውቀዋልን? ጳውሎስ ሰባኪ ነበር፣ ስለዚህም በየትኛውም ጥርጣሬ ውስጥ አልተዋቸውም፡-

> የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው እርሱም ዝሙት፥ ርኵሰት፥ መዳራት፥ ጣዖትን ማምለክ፥ ምዋርት፥ ጥል፥ ክርክር፥ ቅንዓት፥ ቁጣ፥ አድመኛነት፥ መለያየት፥ መናፍቅነት፥ ምቀኝነት፥

> መግደል፥ ስካር፥ ዘፋኝነት፥ ይህንም የሚመስል ነው። አስቀድሜም እንዳልሁ፥ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም። የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው። እንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም።
>
> (ገላ. 5፡19-23)

እንዲህ ካለው አንቀጽ በኋላ እያንዳንዱ ገላትያዊ አንባቢ ክርስቲያናዊ ባልሆነው እና ክርስቲያናዊ በሆነው ባህርይ መካከል ያለውን ልዩነት በዝርዝር ያውቃል። በተመሳሳይ መንገድ ሐዋርያው ለጢሞቴዎስ ሁለት ዓይነት ሰዎች በምድር ላይ እንዳሉ ግልጽ አደረገለት፣ ጻድቅ እና ህግ-የለሽ። ነገር ግን ህግ የለሽ ሲባል በተጨባጭ ምን ይመስላል? በድጋሚ፣ ሐዋርያው የጌታን የማስተማር ዘዴ ተከትሏል፦

> ይኸውም፥ ለበደለኞችና ለማይታዘዙ፥ ለዓመጸኞችና ለኃጢአተኞች፥ ቅድስና ለሌላቸውና ለርኵሳን፥ አባትና እናትን ለሚገድሉ፥ ለነፍሰ ገዳዮችና ለሴሰኞች፥ ከወንድ ጋርም ለሚተኙ፥ በሰዎችም ለሚነግዱ፥ ለውሸተኞችም በውሸትም ለሚምሉ፥ የብሩክ እግዚአብሔርንም ክብር እንደሚገልጥ ለእኔ አደራ እንደ ተሰጠኝ ወንጌል የሆነውን ደኅና ትምህርት ለሚቃወም ለሌላ ነገር ሁሉ ሕግ እንደ ተሰራ እንጂ ለጻድቅ እንዳልተሰራ ሲያውቅ ነው።
>
> (1 ጢሞ. 1፡9-11)

ጌታችንም ሆነ ሐዋርያው ጥቅል በሆኑ ንግግሮች ላይ እርካታ አልነበራቸውም። በላያቸው ላይ ስጋን ያኖሩባቸው ነበር። እየተናገሩ ለነበሩት ነገር የምሳሌዎች ዝርዝሮችን ይሰጡ ነበር። ተዛምዶ ሲበዛ ጥቅል ከሆነ ተዛምዶ መሆኑን ይተዋል። የሰባኪ ትልም ሁልጊዜ ጎሊና ነው። ወደ ጎሊና የሚደርሰው በአእምሮ በኩል ነው፣ ደግሞም ጎሊና ሕይወትን እንዲያነቃቃ ይጠብቃል።

ያነቃንቀዋል፣ ጥያቄን ይጠይቀዋል፣ እና በተሰበከው እውነት ብርሃን እንዲያስብ እና እንዲተገብር ይጎተጉታል።

ከዐሥራ ዘጠነኛው ክፍለ-ዘመን የቄልስ ታላላቅ ሰባኪዎች አንደኛው የሆነው የታልሳርኑ ጆን ጆንስ አንዳንድ ጊዜ በአስባበከ ዘዴው ላይ አስተያየት ይሰጣል። ሁልጊዜ ወደ ምስባኩ የሚሄደው በርካታ ቦምቦችን በመሸከም እንደሆነ ይናገራል። በስብከቱ ጅማሬ አካባቢ አንደኛውን ቦምብ ወደ ጉባዔው በአግባቡ ይወረውርና ጥቂት ሰዎችን ሲገድል ይመለከታል። ከዚያም እያንዳንዳቸው አድማጮቹ 'እስኪታረዱ' ድረስ ቦምቦቹን መወርወሩን ይቀጥላል!

ምን ማለቱ ነው? ጆን ጆንስ በተዛምዶ ያምናል ደግሞም ቃሉ በእያንዳንዱ በተገኘው ሰው ላይ ውጤት እስኪያመጣ ድረስ ቃሉን በተለያዩ መንገዶች ማዛመዱን ይቀጥላል። በጣም ኃይለኛ የሆኑ ሰባኪዎች በታሪክ ውስጥ ሁልጊዜ ተመሳሳዩን ነገር አደርጉ ነበር። በህትመት ደረጃ ያላ ስብከት ከእውነተኛው ነገር ጋር ተመሳሳይ አይደለም፣ ነገር ግን ይህንን ገጽታ እንዲህ ባሉ ሰዎች እንዲሁም በእነ ጆን ዌስሊ፣ ጆርጅ ዊትፊልድ እና ጆናታን ኤድዋርድ ያሉ ሰዎች ውስጥ ልናይ እንችላለን። ፒዩሪታውያኑ ከእነርሱ ቀድመው አድርገውት ነበር፣ ደግሞም የሚገልጡት እና የሚያስተምሩት 'የሚጠቅም' ብለው ከሚጠሩት ጋር ሁልጊዜ የታጀበ ነበር። እነዚህ 'ጥቅሞች' ወይም ተዛምዶዎች፣ አብዛኛውን ጊዜ በጣም በቀኑጥር የበረከቱ እና ዋናው ባህርያቸው ለጉባዔው ስለ ኃጢአት፣ ግዴታዎች፣ ችግሮች፣ እና እድሎች በጣም *በግልጽ* የሚናገሩ መሆናቸው ነበር። እነርሱ የተናገሩትን ያክል ግልጽ አድርጎ መናገር አለመቻላችን ዛሬ ላይ የስብከት ውስጥ ኃይል በከፊል የጎደለን መሆኑን ያስረዳ ይሆንን?

(ii) ለይቶ የሚያውቁ ሁኑ

ልንሰብክ ስንቆም እና ወደ ጉባዔው ስንመለከት፣ በርካታ የተለያዩ ዓይነት ሰዎች እንደሚገኙ እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን። ምናልባትም ወንጌልን በጥቂቱ ያወቀ ወይም ቀድሞም የማያውቅ እንግዳ ሰው ሊኖር ይችላል። ወደ ቤተክርስቲያን በመደበኛ ሁኔታ የሚመጣ ነገር ግን የተለወጠ ሕይወት የሌለው ሰው ሊኖር ይችላል። 'ለክርስቶስ ውሳኔ ያደረገ' ነገር ግን ገና በመንፈሳዊ ሕይወቱ የእውነት ሕያው መሆኑን ያላሳየ ሰው ሊኖር ይችላል። ገና ያልዳኑ ነገር ግን የምራቸውን

ሆነው ጌታን የሚፈልጉ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ። በጌታ አዲስ የሆኑ ሰዎች አሉ። የበሰሉ ቅዱሳን አሉ። ብርቱ በሆነ ፈተና፣ ጥርጣሬ፣ ወይም ችግር ውስጥ የሚያልፉ ይኖራሉ። እየጨመረ በሚሄድ መልኩ ራስ-ተኮር እየሆኑ የሚሄዱ እና መንፈሳዊ ጉዟቸው የደከመ እና ሁሉን ዓይተው የሰለቻቸው አሉ። እዚያ መሆን ደስ የሚላቸው ህጻናት አሉ፣ ችለው ለመቀመጥ የወሰኑም አሉ። ጭንቅላቱን በእጆቹ የደገፈ የተሰላቸ ታዳጊም አለ። እንዲህ እንዲህ እየቆጠርን ልንቀጥል እንችላለን። በዝርዝሩ ላይ ልናኖራቸው የምንችላቸው የተለያዩ የሰዎች ዓይነት ምን ያክል ናቸው?

እነዚህን ሁሉ ሰዎች ምን ልናደርጋቸው ነው? መድሃኒቱን በማስተናገጃው ላይ አስቀምጠን ‘ይኸውላችሁ ቤተሰቦቼ! መልካም ይሆንላችኋል። የሚመጥናችሁ የሚመስላችሁን እንክብል መጠን ውሰዱ!’ ትሏቸዋላችሁ? ወይም ልክ ኃላፊነት እንደሚሰማው ፋርማሲስት ለእያንዳንዳቸው *በተናጠል* ትክክል የሚሆንላቸውን እንሰጣቸዋለን?

በእርግጥ በሕዝባዊ ስብከት ውስጥ የምናተኩረው ግለሰቦች ላይ አይደለም፣ ወይም ማንንም ሰው በስም አንጠራም። ነገር ግን እውነት በሚሰበክበት ጊዜ፣ እያንዳንዱ የሰዎች ቡድን ያ እውነት እንዴት ከእነርሱ ጋር እንደሚዛመድ ማወቅና እያንዳንዱ የተገኘ ግለሰብ ለራሱ የሚከተለውን ማለት መቻል አለበት ‘በዚያ መልእክት ውስጥ *ለእኔ* የሚሆን ነገር አለ’።

ግብረ-ገቧን ጥላ ወደነበረችው ወደ መጀመሪያዋ ክፍለ-ዘመን ቆሮንቶስ እንሂድና በዚያ ከነበረችው የክርስቲያን ቤተክርስቲያን ጋር ጥቂት ጊዜ እንውሰድ። ከሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ደረሳቸው! አንድ ሰው በሚያነብበው ጊዜ ሁሉም ሰው ተረጋግቶ ተቀመጠ። አንድ ቦታ ላይ ሲደርስ የተለየ ፀጥታ ሆነ፡-

> ወይስ ዓመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳይወርሱ አታውቁምን? አትሳቱ፤ ሴሰኞች ቢሆን ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀላጮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩ ወይም ሌቦች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካሮች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም። ከእናንተም አንዳንዶቹ እንደ እነዚህ ነበራችሁ፤ ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ

ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል፥ ተቀድሳችኋል፥ ጸድቃችኋል።

የየራሳቸው ኃጢአት በሚነበብበት ጊዜ እያንዳንዱ ሰው ምን ሊሰማው እንደሚችል ልትገምቱ ትችላላችሁ? የመጨረሻዎቹ ሁለት ዐረፍተ-ነገሮች በሚነበቡበት ጊዜ በጉባዔው ላይ ሊንሰራፋ የሚችለውን የእፎይታ ስሜት ልትገምቱ ትችላላችሁ? ሐዋርያው እንዲሁ ዝም ብሎ 'የአንዳንዶቻችሁ ኃጢአት አስቸጋሪ ነው፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ሁላችሁንም ይቅር ብሏችኋል' ብሏቸው ቢሆን ኖሮ እንዲህ ያለው ጥልቅ የእፎይታ ስሜት እና መደነቅ ይኖርባቸው ነበርን? ግልጽ በሆነ ብቻ ሳይሆን ለተለያዩ የሰዎች ቡድኖች የሚናገር ተዛምዶ ውስጥ ኃይል አለ።

በዐሥር ሺዎች ለሚቆጠሩ ሰዎች መንፈሳዊ ሕይወትን ለማምጣት እግዚአብሔር የተጠቀመበት በእንግሊዝኛ የተጻፈ መጽሐፍ አለ። የተጻፈው በፒዩሪታውያኑ ጆሴፍ አሌይን ሲሆን *ለና ለላርም ቱ ዚ ለንኮንቨርትድ* ተብሎ ይጠራል። አሌይን ግልጽ እና የማያሻማ በሆነ መልኩ ያልዳኑ የሆኑ ዐሥር ዓይነት ሰዎችን ዝርዝረዋል። ከዚያም ያልዳነ የመሆን ዐሥራ ሁለቱ የሚስጢር ምልክቶች አመልክተዋል። በሌላ ቋንቋ፣ ሃያ ሁለት ዓይነት ያልዳኑ ሰዎች እንዳሉ አሳይተዋል፣ ከዚያም ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የትኛውንም ነጠላ ጥቅስ ሳይቦጭቀሩ እያንዳንዱን ዓይነት ሰው በየተራ ሞግተዋል።[8] እግዚአብሔር ያልዳኑ ወንዶችን እና ሴቶችን በተለየ ሁኔታ የሚገልጽ ቢሆን፣ እንዲህ ያሉት እንዳሉ እኛም ለይተን ልናውቅ፣ እና በዚያው መሠረት ልናናግራቸው አይገባንምን?

ይህ ሁሉ በተግባር ምን ማለት ነው? ለመስበክ ከመቆሜ በፊት፣ ለማን ልሰብክ እንደሆነ አስቀድሜ ላስብ ይገባኛል። እንዲኖረኝ *ሰለምፈልገው* ጉባዔ ሳይሆን ስለሚኖረኝ ጉባዔ ላስብ ይገባኛል! በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላለው ለዚያ ወጣት ልጅ ምንባቤ ምን ይላል? ለዚያኛው ታዳጊ ተዛምዷዊ የሚሆንለት እንዴት ነው፣ ከወላጆቿ ጋር ለእረፍት የመጣችውን ያቺን ሴትስ? ለወጣቶቹ ባለትዳር ጥንዶች የሚናገራቸው እንዴት ባለ ተናጠላዊ መንገድ ነው፣ ሚስዮናዊ ሊሆን ላለው፣ ወደ አርባዎቹ እድሜዋ እየገባ ላለው ለዚያ ወንደላጤ፣

[8] ምእራፍ 4ን ተመልከቱ፣ 'ዚ ማርክስ ኡቭ ዚ አንኮንቨርትድ' በአሌይን ጆሴፍ፣ *ለን ለላርም ቱ ዚ ለንኮንቨርትድ* (ሎንደን፣ ዚ ባነር ኡቭ ትሩዝ ትረስት፣ 1959)፣ ገጽ 44-53።

ላልተቀጠረው፣ ለመበለቲቱ፣ ላዘነው፣ ብቸኝነት ለሚሰማው፣ ለሸመገሉት፣ ለታመሙት እና ለተረበሹት?

ቆንጆ ጥራት ያለው ልብስ ማዘጋጀት በቂ አይደለም። ለመቍረጥ ጊዜው መጥቷል። እያንዳንዱ የተገኘ ሰው ለእያንዳንዳቸው በትክክል የሚሆናቸውን በምስባኩ ላይ የተንጠለጠለ ልብስ ሊያዩ ይገባቸዋል። ነገር ግን ነገሩ ያ ብቻ አይደለም፤ እንዲለብሷቸው ልትለምኗቸውም ይገባችኋል። ይህ ወደ መጨረሻው ነጥባችን ያመጣናል።

(iii) አሳማኝ ሁኑ

አድማጮቻችን ልብሶቹ ሊለበሱ *የሚገባቸው* መሆናቸው ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን ሊለበሱ *እንደሚችሉም* እንዲሁም ያንን ማድረጉም ፈጽሞ በእነርሱ ፍላጎት የሚሆን ነገር መሆኑን ሊያውቁ ይገባቸዋል። ሰዎች ማድረግ ያለባቸውን ብቻ ሰባኪ ከተናገረ *ሥራውን አልሠራም*፣ *እንዴት* እንደሚሠሩት እና *ለምን* ሊሠሩት የተገባ እንደሆነ ሊነግሯቸውም ይገባል። *መጽሐፍ ቅዱስ ሁልጊዜ ምን* በሚለው ላይ ግልጽ ነው። *ለምን* የሚለው ጠቅላላ በሆነው የመታዘዝ በረከቶች ትምህርት ላይ የተሸፈነ ነው - በዚህ ምድር እና በሚመጣውም ዓለም የምናጣጥማቸው በረከቶች። *እንዴት* የሚለው ጥበብ ላይ በተሰጠው ትምህርት ተሸፍኗል፣ ደግሞም እዚህ ሰባኪው አንዳንድ ብልህ የሆኑ ተግባራዊ ጥቆማዎችን ሊያደርግ ይገባዋል። እነዚህም ጥቆማዎች ቀጥተኛ በሆነ የቃሉ ሥልጣን ከመናገር ይልቅ ሕዝቦቹን የሚጠቅም ሊሆን ይገባል። ነገር ግን ችላ ሊለው የሚችለው ክልል አይደለም። ያንን ካደረገ አድማጮቹን የሚወድድ አይሆንም።

አብዛኛውን ጊዜ መሳደብ ተገቢ የሆነውን እንዲያደርጉ ሰዎችን ለማሳመን የተሻለው መንገድ አይደለም። ጨቅጫቃ ሴትን በተመለከተ የእግዚአብሔር ቃል የሚናገረው ብዙ ነገር ያለው ሲሆን ከእነዚያ ውስጥ አንዳቸውም አዎንታዊ አይደሉም! ታማኝ የሆኑ ሰባኪዎች ስለ ኃጢአት እንዲሁም ንስሃ የሚያስፈልግ ስለመሆኑ የደነዙ አይደሉም። ነገር ግን ለሰዎች ግድ እንደሚላቸው ሰዎች፣ እንደዚያም ሆኖ ካሮቱ በእንጨቱ ላይ እንዲሆን ይፈልጋሉ። ልጆቻቸውን የሚወድዱ ወላጆች አስፈላጊ ሲሆን ልጆቻቸውን ይቀጣሉ፣ ነገር ግን ብዙ የሆነውን ጊዜያቸውን ማበረታቻ እና እንክብካቤ

በመስጠት ያሳልፋሉ። ትንሽ ውሻ ታዛዥነትን የበለጠ ፈጥኖ የሚማረው ጥብቅ በሆኑ ቃላት እና ምት ከሚሆነው ይልቅ በቼኮሌት ጠብታዎች በኩል ነው።

ወጣት ሰባኪ ሳለሁ አንድ ጊዜ በደቡባዊ ዌልስ ትንሽዬ መንደር ውስጥ ባሉ የተለዩ ስብሰባዎች ላይ እንድሰብክ ተጋብዝኩኝ። ከጠበቅሁት ይልቅ ፈጥኖ መቅደሱን ቶሎ ስላገኘሁት ከመከፈቱ በፊት ደረስኩ። ሁለት በእድሜ የገፉ ሴቶች በውጪ እየጠበቁ ነበር። 'ወደ ስብሰባው መጥታችሁ ነው?' ስል ጠየቅኳቸው። 'አዎን፣ ጅራፉን ለመስማት መጥተናል!' አሉ።

ጅራፍ? እንዳላወቁኝ እርግጠኛ የሆንኩባቸው ሴቶች ከጥቂት ወራት በፊት አንድ ተጋባዥ ሰባኪ ሰምተው እንደነበረ ነገሩኝ። ምን አይነት ግርፊያ ሰጥቷቸው ይሆን! ዛሬ ላይ ከእርሱ ጋር የሚሆኑት እንዴት እንደሚሆን እርግጠኞች አልነበሩም፣ ነገር ግን የጥርጣሬ ጠቀሜታንእየሰጡት በድጋሚ ሊሰሙት በመምጣት ላይ ነበሩ።

እያነጋገሩት የነበረውን 'ጅራፍ' በድንገት ሲያውቁት ምን ያክል እንደሚያፍሩ ልነግራችሁ አይገባኝም! እንዲህ ያለ ቅጽል ስም ስለተሰጠኝ እኔ ያፈርኩትን ያክል እነርሱ አላፈሩም። ከእነዚህ ሁለት ቅዱሳን ብዙ ተማርኩኝ። ቀጥተኛ እና ግልጽ ለመሆን ያለኝን መሻት ለማሳነስ ምንም አላደረጉም፣ ነገር ግን ሰዎችን መለየት እና ማሳመን ሁለት የተለያዩ ነገሮች መሆናቸውን አሳይተውኛል።

ማሳመኛዎች የሰፋችሁት ሙሉ ልብስ ሊለበስ የተገባው መሆኑን ለሰዎች የሚያሳዩ ይሆናሉ። የእግዚአብሔርን እውነት ወደ ተግባር የሚያውሉ ከሆኑ ወደ ሕይወታቸው የሚመጣውን ደስተኝነት እና በረከት ይነግራቸዋል። የሚያስወግዱት አደጋዎች ምን እንደሚሆን፣ ምን ዓይነት መንፈሳዊ እድገት እንደሚያደርጉ፣ ምን ዓይነት ተሞክሮ እንደሚኖራቸው እና ታዛዥነት የተቤዣቸውን እንዴት እንደሚያስደስተው ያብራራላቸዋል። ሰዎች በእግዚአብሔር መንገድ እንዲጓዙ ፈቃደኞች ይሆኑ ዘንድ ብቻ ሳይሆን ጸንፈፈለጉ ያደርጋቸዋል።

በአመታት ውስጥ ወጣት ሰዎች የሰሜን ዌልስን ኮረብቶች እና ተራሮች እንዲወጡ በመውሰድ በርካታ ሰዓታትን አሳልፌያለሁ። እነርሱ ሁልጊዜ እንዲሸከሙ በማደርጋቸው መገልገያ ብዛት ሁልጊዜ ይነጫነጫሉ! ጥቂት ሳንድዊቾችን እና የሚጠጣ ለምን መውሰድ አይችሉም? አንዳች አይነት አለባበስ፣

ባርኔጣ፣ ውሃ የማያስገቡ ጃኬቶች እና እግርን የሚሸፍኑ ልብሶች፣ የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ሣጥን፣ ፊሽካ፣ ባትሪ፣ የድንገተኛ ምግቦች፣ አንድ ሊትር ውሃ፣ ቦርሳ እና የተወሰኑ ሌሎች እቃዎች - ይህን ሁዩ በበጋ ቀን? ከዚያ በኋላ በሌሎች ተጓዦች ላይ ምን እንደደረሰ እና እያንዳንዱ እቃ ለምን እንዳስፈለገ አብራራላቸዋለሁ። መነጫነጩ ይቆማል፣ በጀርባ የሚያዘው ቦርሳ ይታዘላል፣ ከዚያም ቀኑን ተድላ እናደርገዋለን! 'የነገርኳችሁን ዝምብላችሁ አምጡ፣ አሊያ መምጣት አትችሉም' ማለት ተመሳሳይ ውጤት የለውም።

ማሳመን የሕይወት አንድ ክፍል ነው፣ ገር ግን በጣም በተደጋጋሚ የስብከት አንድ አካል እየሆነ አይደለም። እግር ኳስ የሚወድዱ ነገር ግን በሣምንት ሁለት ጊዜ የሚደረገውን የሥልጠና ክፍለ-ጊዜ የማይፈልጉ ምን ያክል ወጣቶችን ታውቃላችሁ? ከዚያም ከሌላኛው ቡድን ይልቅ የበለጠ የሚመጥኑ ከሆኑ፣ በፍጥነት እና ለረጅም ጊዜ መሮጥ ይችላሉ፣ ደግሞም ባዳበሩት ክህሎት በዙሪያቸው መደነስ ይችላሉ፣ ከሞላ ጎደል በየጊዜው ያሸንፋሉ! መደበኛ የሆኑ የማሸነፍ አሳቦች አትሌቶች ከአሠልጣኛቸው ውጪ መሆን የሚፈልጉ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። በመቶ ኪሎዎች ከሚቆጠሩ ግሣጼዎች ይልቅ አንድ ኪሎ ማሳመኛ ተገቢ ነው።

ነገር ግን እውነተኛ የሆነ ማሳመኛ የጋለ መሻት ሊኖረው ይገባል። በኋለኛው ምእራፍ ላይ ይህንን አስመልክቶ ጥቂት ተጨማሪ ነገር ማለት ይኖርብኛል፣ ነገር ግን አሁን ላይ አንድ ነገር መባል አለበት። አንዳንድ ሰባኪዎች የትኛውም ዓይነት ስሜት እንዲታይ አይወዱም፣ የሰባኪዎች አንዳንድ አስተማሪዎች ሆነ ብለው ይህንን አያበረታቱም። ነፍሳችሁ በዚያ ውስጥ ካልሆነች በቀር የትኛውንም ነገር በተመለከተ ለየትኛውም ሰው ልታሳምኑ እንደማትችሉ ሊያስታውሱ ይገባቸዋል። አሳማኝ ንግግር ከስሜት ጋር የተሞላ ነው። አሳማኝ ሰባኪዎች ስለ ክፉት የሚያወሩት በጥላቻ ነው፣ ስለ ክርስቶስ የሚያወሩት በሞቅታ ነው፣ ስለ ክርስቲያኖች የሚያወሩት በፍቅር ነው፣ ስለ ሰማይ የሚያወሩት በፍንደቃ ነው! በውስጣቸው የሚንቀሳቀሱት በማንነታቸው ከፍተኛ ጥልቀት ሲሆን በፊት ለፊታቸው ያለው እያንዳንዱ ጎልማሳ እና ልጅ ያንን ያውቀዋል። እንደ ሐውልት የሚቆሙና ስሜቱ ሳይኖራቸው የሚናገሩ ሰባኪዎች ሰዎችን ለማሳመን ምንም አያደርጉም። ሰብዓዊውን መንካት አጥተውታል። ያንኑ መረጃ በበይነ-መረብ ላይ በቀለማት ልታገኙ ስትችሉ ገላጭ ያልሆነውን የእውነታዎችን ጋጋታ ስለምን ታደምጣላችሁ?

ወደ ታላቁ የ1914-18 ጦርነት እንመለስ። ጭቃማ በሆነ ቦይ ውስጥ ከምሽጉ በስተጀርባ የፈሩ ወታደሮች ቡድን ቆመዋል። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ፊሽካ ይነፋና በመሰላሉ ፈትለክ ብለው፣ በምሽጉ ላይ ከዘለሉ በኋለ ወደ ጠላት በሚተኮሰው የጦር መሣሪያ ጋጋታ ውስጥ ይሮጣሉ። በርካቶቹ በአንድ ጊዜ ይሞታሉ፣ ሌሎች በማንም ሰው መሬት ላይ ሳይሆኑ እስኪሞቱ ድረስ ይደማሉ፣ እናም ጥቂቶች ብቻ ይመለሳሉ። እንደዚያ ያሉ ሰዎችን የምታነሣሣቸው እንዴት ነው? በእነዚያ መሰላሎች ተነሥተው ከሞላ ጎደል እርግጠኛ ወደሆነ ጥፋት እንዲገሠግሡ የምታሳምኗቸው እንዴት ነው?

ኃምሳ አለቃው በድምጹ ጥልቅ የሆነ ስሜት ኖሮት ይናገራቸዋል። በዚህ ጦርነት ውስጥ የሚያሰጋው ነገር ምን እንደሆነ ያብራራላቸዋል። ከተሸነፉ፣ ነፃነት ይጠፋል። ወላጆቻቸው ይታረዳሉ፣ ሚስቶቻቸው ይደፈራሉ፣ ደግሞም ልጆቻቸው ባርያ ይሆናሉ። ዋጋ የሚሰጧቸው ነገሮች በሙሉ ለዘላለም ይጠፋሉ። ይህ ጦርነት ጠቃሚ ነው። በእርግጥ፣ ወሳኝ በሆነ መልኩ ጠቃሚ ነው። ካሸነፉ፣ ጦርነቱ የሚያሸንፉት አይሆንም፣ ነገር ግን ቢያንስ ድል አንድ እርምጃ የሚቀርብ ይሆናል። በዚህ ነጥብ ላይ ኃምሳ አለቃው መሣሪያዎቹን ፈተሸ፣ ፊሽካውንም ነፋ፣ ድል አድራጊ በሆነ መሻት 'ቀጥሉ! ወደፊት!' ሲል ጮኸ።

ጥልቅ ስሜት በሌለበት ውስጥ ማሳመን የለም። ራሱ ጄኔራሉ ቢመጣና ተመሳሳይ የሆኑትን እውነታዎች ሰጥቶ ቢሆን፣ በተነካ ስሜት፣ ወይም ኃይል አሊያም የሚጨምር ግለት ውስጥ ሳይሆን እንደ በረዶ ቀዝቅዞ ቢናገረው፣ ውጊያው ሊሸነፉት ይችሉ ነበር። ሰዎቹ ተስፋ ይቆርጡና በጥርጣሬ ይሞሉ ነበር። ግዴታ በመሰላሉ እንዲወጡ ያደርጋቸዋል፣ ነገር ግን ወደ ድል አያወጣቸውም። ምንም ያክል እውነተኛ ቢሆኑ፣ ወደ ልብ የሚደርሱት ብቸኞቹ ቃሎች ከልብ የሚወጡት ናቸው። ሰባኪዎች ራሳቸው ካልተነኩ የትኛውንም ሰው አይነኩም።

* * *

ይሁን እንጂ የመጨረሻው የስብከት ፈተና በሚሰበክ ጊዜ ሰዎች የሚሰማቸው ነገር አይደለም። የቅጽበቱ 'ደስታ' ጠቃሚ እንደሆነና ስብከትም ያለ እርሱ ዓላማውን ሊያሳካ እንደማይችል አይተናል። የሆነ ሆኖ፣ አሁንም ትልቁ ጥያቄ ይሄ ነው፡- *የተሰበው ሰብከት በተግባር የተፈተነ* እውነት ሆኗልን?

አንድ ሰኞ ማለዳ በምናብ የሳልነው ልብስ ሰፊ በእያንዳንዱ እሑድ ለባለፉት ጥቂት ወራት ወደሚሰብከበት ወደ ትንሿ ከተማ መጣ። አሁን ላይ በደንብ ስላወቃቸው የሚችል ከሆነ ወደ እያንዳንዳቸው ጎራ ለማለት ወሰነ። ያዕቆብ እና ማርያም ወደ ትምህርት ቤት የሚወስዳቸውን አውቶቡስ ሲጠብቁ ተመለከተ። ባንክ ውስጥ ከምትሠራው ሙኒት ጋር ጥቂት አወራ። እስከሚቀጥለው ሣምንት ደረስ ወደ ዩኒቨርስቲ ከማይመለሰው ስጢፋኖስ ጋር ሻይ ቡና ተባባሉ። ሱፐርማርኬት፣ ክሊኒክ፣ ነዳጅ ማደያ፣ ቤተመጽሐፍት፣ ጠበቆቹ ጋር፣ አበባ መሸጫው ሱቅ፣ ወደ ማዘጋጃ ቤቱ፣ እንዲሁም ወደ ታክሲ ቢሮ ሄደ። በዝርዝሩ ከያዛቸው ዐሥራ ዘጠነኙ ላይ የተሠርቷል ምልክት ካደረገ በኋላ ከሃያኛዋ ሚስቱ ጋር ምሳ ለመብላት ወደ ቤቱ ተመለሰ። እንደ ቀሩት ሁሉ እርሷም እርሱ ያዘጋጀውን በሰፊ የተሠራ ልብሶች ለብሳ እንደነበረ አስተዋለ። ስለዚህ ከመብላቱ በፊት ወደ ላይኛው ክፍል ሄዶ እጆቹን ታጠብ፣ ወደ መኝታ ቤቱ እየዳኸ ሄዶ፣ ተንበረከከና እግዚአብሔርን አመሰገነ።

* * *

የምታደርጉት ነገር

1. ቀደም ሲል ሄዳችሁበት በማታውቁት እና ማንንም ሰው ጨርሶ በማታውቁበት ቤተክርስቲያን ውስጥ ልትሰብኩ እየሄዳችሁ ነው። ስብከታችሁ ትርጉም ባለው ተዛምዶ የተሞላ እንዲሆን ምን ልታደርጉ ትችላላችሁ?

2. አዲሱ አገልጋይ በነጥብ የሆነ በከፍተኛ ሁኔታ ተቺ ስብከት ለማቅረብ ያስባል። አንዳንድ ምክር ስጡት።

3. በሕዝቅኤል 37፡1014 ላይ አንድን ስብከት አስተዋጽዖ አውጥታችሁ ተዛምዶዎቻችሁን ዘርዝሩ።

6

ጠቃሚ የሆነ የስብከት አቀራረብ

መጽሐፍ መጽሐፍ *የማይሆነው* መቼ ነው? ይህንን ጥያቄ መመለስ ለእኔ ቀላል ነው። እስከ አሁን ድረስ ያነበባችሁትን የጻፍኩበት ኮምፕዩተር ፊት ለፊት ተቀምጫለሁ። መጽሐፍ ሊሆን ነው፣ አሁን ግን አልሆነም። መጽሐፍ እስካልታተመ እና እስካልተጠረዘ ድረስ ሕልውናውን አላገኘም።

ስብከት ስብከት *የማይሆነው* መቼ ነው? ሥነ-ፍታቴው በሚጠናቀቅበት ጊዜ፣ አስተምህሮው ሲሰባሰብ፣ መዋቅሩ በአንድነት ሲዋቀር፣ አስረጅ ምሳሌዎቹ ቦታቸውን ሲይዙ፣ ተዛምዶዎች ሲዘጋጁ እና የመጨረሻው ቅጽ ማስታወሻዎች ሲጻፉ፣ አሁንም ድረስ ስብከት የለም - በጭራሽ ስብከት የለም! ስብከት እስካልተሰበከ ድረስ ሕልውና የለውም።

ለዚህም ነው የስብከት መሰበክ ወሳኝ የሆነ ጠቀሜታ ያለው። በዓለም ላይ በቆንጆ ሁኔታ የተዘጋጀ ስብከት በደካማ ሁኔታ ከተሰበከ ያለው ዋጋ የወረደ/ትንሽ ነው። የሰዓታት እና የቀናት ብርቱ ሥራ በቅጽበት ውስጥ ይጠፋል። ሕጻን እስከሚወለድበት ጊዜ ድረስ በማኅጸን ውስጥ ተጸንሶ ፍጹም በሆነ ሁኔታ በዚያ ያድጋል፣ ከዚያም ሕይወት አልባ ሆኖ ወደዚህ ዓለም ሲመጣ የወላጆቹን ልቦች ይሰብራል።

ቀደም ብዬ እንደነገርኳችሁ እንደሚመስለኝ፣ በሕይወቴ በርካታ ስብከቶችን ወደምሰማበት እርከን መጥቻለሁ። ከምዞርባቸው ዙሮች የተነሣ፣ ይዘታቸውን በተመለከተ ያለኝ ቅሬታ በጣም ጥቂት ነው። ነገር ግን ከሞላ ጎደል ሁሉም የሚተላለፉት መጥፎ በሆነ ሁኔታ ነው። ይህ ሊሆን የቻለው ሰባኪዎች ለዝግጅታቸው የሚሰጡትን ብዙ ትኩረት ያክል ለአሰባበካቸው ስለማይሰጡ ነው። ወደ ምስባካቸው የሚሄዱት ዝግ በሆነ ስሜት ነው። ሕልውና ያለው ብቸኛው ስብከት ሰዎች ይዘውት የሚሄዱት እንደሆነ ባለማስተዋል ለራሳቸው 'እኔ ስብከት አለኝ' ይላሉ። ስብከቶቻቸው ዝግጁ የሚሆኑበት መንገድ ላይ ጠንቃቆች ናቸው፣ ደግሞም ስብከታቸውን በሚያስተላልፉበት መንገድ ላይ ግን ቸልተኞች እንደውም መናኞች ናቸው።

ይህ አይሠራም። በደካማ ሁኔታ የሚሰበኩ ስብከቶች እግዚአብሔርን አያከብሩትም። ሕዝቡን ተስፋ ያስቆርጣል፣ የወንጌልን መሠራጨት ያዘገያል፣ ደግሞም ከፍተኛ የሆነ ንቀትን ያነሣሣል። እያንዳንዱ ሰባኪ በተናገረ ቍጥር አሰባበኩን መገምገም ይኖርበታል። ወዲያውኑ አያሻሽልም። እንደውም መጥፎ ልማዶቹ ሊያራግፋቸው እስከማይችል ድረስ በውስጡ የተቀረጹበት ከሆነ እየባሰም ሊሄድ ይችላል። የአሰባበክ አቀራረብን ችላ የምንል ከሆንን፣ ብዙም ሳይቆይ ልናስተካከለው የዘገየንበት እንሆንበታለን። እንግዲያው የሚከተሉትን ሰባት ሁኔታዎች እንድታስቡ ልጠይቃቸሁ?[9]

[ነ] *መንፈሳችሁ*

እናንተ የምትሰብኩት ስብከት ስብከቱን ከሚያደርጉት *ከእናንተ* የተፋታ ሊሆን አይችልም! ለወንዶች እና ሴቶች በምትሰብኩበት ጊዜ *ከመንፈሳችሁ* አንዳች ነገር ወደ እነርሱ ይተላለፋል፣ ደግሞም ድብቅ ሊሆን አይችልም። በሰባኪው እና በስብከቱ መካከል ያለውን የማይበጠስ መያያዣ የሚገልጸው በእጅጉ ታዋቂ የሆነ ንግግር የሚገኘው ፊሊፕስ ብሩክ 'ዚ ቱ ኢለመንትስ ኡቭ ፕሪቺንግ' በሚል ርእስ በ1877ቱ የሊማን ቢቸር ገለጻዎች ላይ በሰጡት ገለጻ ውስጥ ነው፡-

> ስብከት አንድ ሰው ለብዙ ሰዎች እውነትን የሚያስተላልፍበት ነው። በውስጡ ሁለት መሠረታዊ ባህርያት አሉት፣ እውነት እና ስብእና። ከሁለቱ የትኛቸውም ሊተዉ እና እንደዚያም ሆኖ ስብከት ሊሆኑ አይችሉም. . . ስብከት በስብእና በኩል እውነትን ማምጣት ነው. . . እውነት በራሱ ቋሚ እና ጽኑ የሆነ ባህርይ ነው፤ ስብእና የሚለያይ እና የሚያድግ ባህርይ ነው።[10]

---

[9] መጀመሪያ እነዚህ ሰባት ነጥቦች ትኩረቴን የሳቡት የጊብስ አልፍሬድ ፒ. ፓሪሽ *ዚ ሥርድ* (ኦክ ፓርክ፣ ኢሊኖይስ፣ ኤማሁስ፣ 1958)ን በማንበቤ ነበር። ተከትሎ የመጣው በከፍተኛ ሁኔታ የተሻሻለ እና የተለወጠ ቢሆንም የእርሱን ቢጋር አንብቤ ነው። ይሁን እንጂ ለዚያ መጽሐፍ ያለኝን ጥልቅ ምስጋና እና ለመስበክ መጀመሪያ የነበረኝን የሚያደናቅፍ ሙከራ እንድወጣው የረዳኝ ምን ያክል እንደሆነ መከተብ እፈልጋለሁ።

[10] ፊሊፕስ ብሩክስ፣ *ሌክቸርስ ኦን ፓሪቺንግ፣ 1877 ዩል ሌክቸርስ፣ ግራንድ ራፒድስ፣ ቤክር፣ 1969*)፣ ገጽ 5፣ 28

እኛ ሁላችን የተለያዩ ባህርያት እና ስብእናዎች አሉን። ይሁን እንጂ፣ ለእያንዳንዱ ሰባኪ እውነት የሆነ አንዳንድ ጥራቶች አሉ። ከሁሉ አስቀድሞ፣ *ብርቱዎች* ልንሆን ይገባናል። ወንዶች እና ሴቶች ያላቸው አስተያየት ምንም ቢሆን ምን የተጠራነው ለእግዚአብሔር እውነተኛ የሆኑ ሰዎች ተሰልፈውበት በነበረበት መስመር ላይ እንድንቆም ነው - ይህ መስመር ሙሴ፣ ኤልያስ፣ ኤርምያስ፣ መጥምቁ ዩሐንስ፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ሐዋርያት፣ ሰማእታት፣ እንደ ማርቲን ሉተር እና ጆን ኖክስ ያሉ ተሐድሷውያን፣ የዐሥራ ስምንተኛው ክፍለ-ዘመን የመነቃቃት አራማጆች፣ እና በርካታ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሌሎች ቆመውበት የነበረበት መስመር ነው። እኛ የእግዚአብሔርን ቃል የምንሸከም ነን! የተናቀውን መስቀልን እንሰብካለን። መልእክታችን በማጽናናት የተሞላ ነው፣ ነገር ግን ንስሃ ለማይገቡት እንደ ስኳር የሚጣፍጡ ቃሎች የሉንም፣ ደግሞም ከዘመኑ እግዚአብሔርን መፍራት የሌለበት መንፈስ ጋር የምናመቻምችበት አሳብ የለንም።

ትሑታን ልንሆን ይገባናል። ኩራት የሥራችን ዋናው አደገኛ ነገር እንደሆነ፣ አገልግሎቶቻችንን ሊያጠፋ እንደሚችል እና ኃይላችንን እንደሚሠርቀን እናውቃለን። ለምናመጣው መልእክት ዐቅቦተ-እምነት እንደማናደርግ እርግጥ ነው፡- ‘ማንም ሰው የሚናገር ቢሆን፥ እንደ እግዚአብሔር ቃል ይናገር፤’ (1 ጴጥ. 4፡11)። ይሁን እንጂ፣ ራሳችንን ጠቃሚዎች በምናደርግበት ድባብ ከሰበክን፣ ራሱን ላዋረደው የክርስቶስ ወንጌል ታማኞች አንሆንም። ኃጢአታችንን፣ የአዳኛችንን መስቀል፣ እና የትኛውንም ነገር ያለ እርሱ በረከት ልናሳካ የማንችል የመሆኑን እውነታ ከዘነጋን በየእለቱ ኩራት ላይ እንወድቃለን።

እውነተኞች ልንሆን ይገባናል። ሰዎች፣ እና ወጣት ሰዎች በተለይ፣ እውነት የሚመስል ያልሆነ ነገርን ይጠላሉ። በሰባኪዎች ውስጥ እንዲህ ያለውን ነገር በግማሽም ቢሆን መጠበቃቸው የሚያሳዝን ነገር ነው። እኛ ፍጹማን እንደሆንን እንዲያስቡ እንዳናደርጋቸው እውነተኞች ልንሆን እና የምንሰብከውን ሁሉ የምናደርግ ቅዱሳን እንዳልሆንን እንዲያውቁ ማድረግ አለብን። ወጥ ባልሆነ መልኩ በመኖር መላው አገልግሎታችንን መቀልበስ እንችላለን። እውነተኞች የሆኑት በቃላት ለማስቀመጥ ከባድ የሆነ አስደናቂ ኃይል በእኛ ላይ እንደሚኖራቸው እኛ ሁላችን እናውቃለን። እንደ እውነተኛ ሰው ለመናገር ብቸኛው መንገድ እውነተኛ ሆኖ መገኘት ነው!

ቅኖች ልንሆን ይገባናል። ወደ መላው የስሜት ጥያቄ ተመልሰናል፣ ይህም ዛሬ ላይ በጣም በትንሹ ብቻ ትኩረት የተደረገበት ነገር ነው።

የምንናገረውን ነገር ልናምን ይገባናል፣ የምንለውን ነገር ከምራችን ልንለው ይገባል፣ ደግሞም የምንለው ነገር *በሰሚታችን የሚሰማን* ነገር ሊሆን ይገባል። ከፊት ለፊታችን ስላሉት ሰዎች ግድ ይለናል ወይስ አይለንም? ዘላለማዊ መዳረሻቸው እኛ ለምንለው ነገር በሚሰጡት አጸፋ ላይ ጥገኛ ነው፤ የተነካን ልንሆን የማንችለው እንዴት ነው? ዘላለማዊ ጉዳዮች በአደጋ ላይ ሆነው የሚያስተኛ የስብከት አቀራረብ ያላቸው መሆን ይቅር የማይባል ነገር ነው፣ ነገር ግን እንዲህ ያለው አቀራረብ ሊመረት የሚችል ነገር አይደለም። በነፍሳችን ጥልቀት ውስጥ የእውነት ፍጹም ኃይል ሊሰማን ይገባል፣ ከዚያም በበቂ ሁኔታ አሳማኞች ሆነን እንናገራለን።

ራሳችንን የምንቆጣጠር ልንሆን ይገባናል። የምናስተምረውን በጥሩ ሁኔታ የምናውቅ ከሆንን፣ በልባችን የምናምነው ከሆነ እና ስብከታችንን በጥልቀት የምናዘጋጅ ከሆነ፣ አቀራረባችንም ልበ-ሙሉነት ያለበት እና የተጠናቀረ ይሆናል። እውነተኝነት እና ቅንነት እንግዲያው አሳማኝ በሆነ መልኩ እንድንገልጸው ያንቀሳቅሱናል። ራስን መቆጣጠር በሌለበት፣ ሰባኪዎች እንደሚደነፉ ወግ አጥባቂዎች ይሆናሉ። ራስን መካድ በሌለበት፣ ስሜት የሌላቸው ሐውልቶች በመሆን ይመጣሉ። ነዳጁም እሳቱም አንድ ላይ መኖር አለባቸው። ነዳጅ የሌለው እሳት በፍጥነት ይጠፋል፣ እሳት የሌለው ነዳጅ ደግሞ ቀዝቃዛ እና መከረኛ ሊሆን ይችላል። የምር ሁለቱንም ልንሆን ይገባናል፣ ደግሞም ከዚህ በሚያንሰው ልንረካ አይገባም! ከተነሣው ጌታ *ጋር ጊዜ የሚወሰድ፣* በቃለ እግዚአብሔር ውስጥ ድምጹን የሚሰማ ደቀመዝሙር መኖሩን ሳውቅ ደስ ይለኛል። ይህ ደቀመዝሙር ልቡ በውስጡ *ወደሚቃጠልበት* የኤማሆስ መንገድ ልምምድ ውስጥ ይገባል (ሉቃ. 24፡32)።

ሩሀሩሆች ልንሆን ይገባናል። ቸ ጠኖች በመሆን እና ባለጌ በመሆን መካከል ያለውን ልዩነት ካላወቀ በስተቀር ማንም ሰው ሊሰብክ አይገባውም። ሰዎችን ካስቀየምን፣ ነገሮችን በምንናገርበት መንገድ *መቹም* ሊሆን አይገባም። ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል በሚለው ነገር *ብቻ* መሆን አለበት። ሻካራ የሆኑ አስረጅ ምሳሌዎች፣ መጥፎ ጠባያት፣ ስድ የሆኑ ቃላት እና የተጠሉ አኳኋኖች በክርስቲያን ምስባክ ውስጥ ቦታ የላቸውም። እንዲሁም ደግሞ ሰባኪው ባልተገኙት ሰዎች ኃጢአት የተገኙትን ሰዎች መሳደብ የለበትም!

ጥሩ ቀልደኞች ልንሆን ይገባናል። ‘ለማልቀስ ጊዜ አለው፣ ለመሳቅም ጊዜ አለው’ (መክ. 3፡4)። በምስባክ ላይ ስለሚቀርብ ጥቂት ቀልደኝነት ቀደም

ሲል ትንሽ ብለናል፣ ነገር ግን አሁን ጥቂት ተጨማሪ ነገር እንበል። ኮስታሮች መሆንን ከጨለምተኝነት ጋር መቀላቀል ገዳይ ነገር ነው። በእርግጥ፣ ሊሳቅባቸው የማይገቡ እንደ እግዚአብሔር፣ ሥርየት፣ ሞት፣ ፍርድ፣ መንግሥተ ሰማይና ሲዖል ያሉ ነገሮች አሉ። ነገር ግን ቀልደኝነቱ የእውነት አገልጋይ ሊሆን በሚችልበት ጊዜ ላይ (ደግሞም በእርግጥም ይህ ትልቅ መርኾ ነው)፣ ልንጠቀምበት አንፍራ። የስሜት ጫናዎችን ሊያስታግሥ ይችላል፣ ትኩረት እንዲደረግ ይረዳል፣ ለእኛ እምብዛም የሆኑ ሰዎችን ይይዛቸዋል፣ ግብዝነትን ይወቅሳል፣ አንዳንድ አሳቦች ምን ያክል አስቂኝ እንደሆኑ ያሳያል፣ ደግሞም ለሰሚዎቻችን እኛ ሰዎች መሆናችንን ያረጋግጥላቸዋል። እግዚአብሔር እንዲህ ያሉ መገልገያዎችን በእጃችን ካኖረ፣ ያንን መጣሉ ትክክለኛ ነገር ይሆናልን?

[2] ቋንቋችሁ

ፊት ለፊታችን ላሉት ሰዎች መልእክታችንን የምናስተላልፈው እንዴት ነው? በቃላት! እነዚያ ቃላት ግልጽና አስገዳጅ ከሆኑ፣ መልእክቱ ግልጽ እና አስገዳጅ ይሆናል። ቃላት በአእምሯችን ውስጥ ያለው ነገር ወደ እነርሱ አእምሮዎች የሚተላለፍባቸው መኪኖች ናቸው፡፤ በዚህ ምእራፍ ውስጥ የተጠቀሱት ሌሎቹ እውነታዎች በሙሉ መልእክቱን ሊረዱ ወይም ሊያደናቅፉ የሚችሉ ናቸው፣ ነገር ግን መልእክቱ በራሱ የሚቀርበው *በቃላት* ነው።

ለሚጠቀሙባቸው ቃላት የትኛውንም ቀጣይነት ያለው ማገናዘብ የሚሰጡት ሰባኪዎች ቍጥር እንዴት ጥቂት ነው! ይህ ወጣት እና ልምድ የሌላቸው በሆኑት ውስጥ ብቻ ያለ ትልቅ ጥፋት አይደለም፣ ነገር ግን እንዲሁም ለዐሥርት ዓመታት በዚህ ላይ ያሉት ሰዎች ጭምር ጥፋት ነው።

የእግዚአብሔር ቃል ስለ ቃላት ምን ያክል እንደሚናገር አስባችሁ ታውቃላችሁ? ያንን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጥቂት ሰዓታት ታገኙት ይሆናል። ደግሞም ቃላት ማውጫ መጽሐፍ ይህንን እንድታደርጉ እውነተኛ ዓይን ከፋቾች ናቸው። ምንም እንኳን እንዲህ ያለውን ጥናት ያደረግሁ ቢሆንም፣ ስለዚያ ሁሉ እዚህ ላይ ልነግራችሁ ቦታ አይኖረኝም። ልነግራችሁ የምችለው መጽሐፍ ቅዱስ የቃላት ምርጫዎቻችን *በእርግጥም* በጣም ጠቃሚ የሆኑ መሆናቸውን

እንደሚናገር ነው። ራሱ መጽሐፍ ቅዱስ ለእኛ የተሰጠን በመንፈስ እንደተመረጡ ቃላት ሆኖ አይደለምን?

ስለ ታላፊ እና ወቅታዊ ስብከቶች እናስብ። በደካማ ሁኔታ ከተመረጡ፣ ሰዋሰዋዊ ካልሆኑ፣ በመጥፎ ሁኔታ ከተነገሩ ሰባኪ ከተጠቀመባቸው ቃላት የተነሣ በርካታ ሰዎች መልእክቶቹን የሚያቃቂል ሆነው አላገኟቸውምን? በሺዎች እና በሺዎች የሚቆጠሩ የተዋጣላቸው መልእክቶች ሰዎች ለመረዳት ቀላል ሆነው ካላገኟቸው ቃላት የተነሣ ምንም ምላሽ ያላስገኙ ሆነው አያውቁምን?

ቃላትን ጠንቃቃ በሆነ መልኩ ሳንጠቀምበት መልካም የሆነ የስብከት አቀራረብ ሊኖር አይችልም። ስለዚህ ቋንቋችን ምን ሊመስል ይገባዋል? ሁልጊዜ ልናስታውሳቸው የሚገቡን አራት ነጥቦች እነኋችሁ፡-

ቀላል

የንግግር አማርኛ ቀላል የሚሆነው የሚከተሉት ሲሆኑ ነው፡-

- በአንድ ዐረፍተ-ነገር ውስጥ አንድ ነጥብን ብቻ ስናስጨብጥ።
- አብዛኞቹ ዐረፍተ-ነገሮቻችን ወደ ዐሥር ቃላት ርዝመት ብቻ ያላቸው ሲሆኑ።
- 90 በመቶ የሚሆኑት ቃሎቻቸውን አንድ ወይም ሁለት ቦታ የሚከፈሉ ሲሆኑ።
- ሰሚዎቻችን *በቀላሉ* የማይረዷቸው *የትኛውንም* ቃላት የማንጠቀም ስንሆን።

ዐረፍተ-ነገሮች ልክ እንደ ብሎኬት ናቸው፤ ስብከታችንን በሰዎች አእምሮዎች ውስጥ የምንገነባው በአንድ ጊዜ አንድ አሳብን በመናገር ነው። *በንግግር የሚቀርብ ዘይቤ* ማለት *በጽሑፍ እንደሚቀርብ ዘይቤ* ማለት እንዳልሆነ ለሰባኪዎች ለማስረዳት የሞከርኩበት በርካታ የሕይወት ዘመን ተሞክሮ አለኝ። ደግሞም እዚህ ጋር በድጋሚ ይህንኑ እየተናገርኩኝ ነኝ። ጥልቅ የሆኑ ሳቦች ሊኖሩን ይገባል፣ ነገር ግን እነዚያን በቀላሉ መግለጽ ይኖርብናል። ልጆች ሊረዱ

ካልቻሉ፣ ሲበዛ ውስብስብ እየሆንን ነን ማለት ነው፤ ስለዚህም ሁልጊዜ በአእምሯችን ልንይዛቸው ይገባናል።

በተለየ ዐውድ ውስጥ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ ‘እንዲሁ እናንተ ደግሞ የተገለጠውን ቃል በአንደበት ባትናገሩ ሰዎች የምትናገሩትን እንዴት አድርገው ያስተውሉታል? ለነፋስ የምትናገሩ ትሆናላችሁና።’ ሲል ጽፏል (1 ቆሮ. 14፡9)። ‘ብዙ ሕዝብም በደስታ ይሰሙት ነበር’ ተብሎ የተነገረለት ጌታችን ነው (ማር. 12፡37)።

ሰዋሰዋዊ

ትኩረትን *ከመልእክቱ* ወደ *መልእክተኛው* ለምን ታዞራላችሁ? ትክክለኛ ያልሆነ አማርኛ ስንጠቀም የሚሆነው ነገር ይህ ነው። የሚያፍን እና ተፈጥሯዊ ያልሆነ በሆነ መንገድ እስከንናገር ድረስ ለእያንዳንዱ ነገር በእጅጉ መጠንቀቅ የለብንም። በእውነት ጠቃሚ የሆነው ነገር *ግልጽ* መሆን እንጂ ትክክል አለመሆን አይደለም። ነገር ግን በሰዎች ጆሮዎች ውስጥ የሚንሳጠጥ ስህተቶችን የምንሠራ ከሆንን ግልጽ እየሆንን አይደለንም።

ጥሩ አማርኛ መናገር ከባድ ነገር አይደለም። በጥሩ ሁኔታ የተጻፉ በርካታ መጽሐፍትን ካነበብን፣ ማሰብ ሳይኖርብን መልእክቱን እንቀስማለን። በተጨማሪም፣ ነገሮች በደንብ እንዲገቡን ለማድረግ ራሳችንን በአንድ ወይም ሁለት ገጾች እየገደብን በአማርኛ ሰዋሰው ላይ የተጻፉ ጥቂት መጽሐፍትን ማንበቡም ጠቃሚ ነው። ጥሩ የሆነ ጓደኛችሁ ስህተታችሁን እንዲታዘብላችሁ እና ስለ እነዚያም እንዲነግራችሁ ለምን አትጠይቁትም? ጉባዔያችሁ በቋንቋ አጠቃቀማችሁ ከሚረበሽ ይልቅ የእርሱን ትችት ብትከናነቡ የበለጠ የሚሻላችሁ ነገር ነው።

ኃይለኛ

ልንለው የፈለግነውን ነገር *በትክክል* የሚገልጹልንን ትክክለኛ ቃላት ልንመርጥ ይገባናል። ካልመረጥን፣ ሰዎች እንዲገባቸው *የምንፈልገው* ነገር እና በእርግጥም *የሚገባቸው* ነገር ተመሳሳይ ነገር አይሆንም።

ተናጋሪው ቃላት ያልሆኑትን በሚጠቀም ጊዜ ቋንቋ ኃይለኛ ሊሆን አይችልም። ዛሬ ላይ በርካታ የሆኑ ቃላት የሌላቸው ንግግሮች ያሉ ሲሆን ወጣት ሰዎች በተለይ እነዚያን በዐረፍተ-ነገሮቻቸው ውስጥ መጠቀም ይወድዳሉ። ነገር ግን አብዛኛውን ጊዜ ጅማሬ ላይ ይጠቀሙባቸዋል። እነዚህ አያስፈልጉም። ሰባኪው የሚያቅማማ፣ እርግጠኛ ያልሆነ እና ደደብ እንደሆነ እንዲመስልበት ያደርገዋል። ሥልጣኑን ይሰርቀኑታል። ይሁን እንጂ፣ እንዲህ ያሉ የሚሰቀጥጥ ልማድ እንዳላችሁ የምትወቀሱ ከሆነ፣ ከእንግዲህ ወዲህ አትጠቀሙባቸው። ቃል አልባዎቹን የምትጠቀሙባቸውን ጊዜያት እንዲያው በቀላሉ *ልብ በሏቸው* ከዚያም እነርሱ በራሳቸው የሚጠፉ ይሆናሉ።

የቃላት አልባዎቹን ያክል መጥፎ የሆነው እንደመጡ የሚነገሩ ዋልጌ ቃላት ናቸው። እነዚህኞቹ ለዐረፍተ-ነገሩ ትርጉም ምንም የማይጨምሩ፣ ነገር ግን ውጤታቸው ጠቃሚ እንዳልሆነ እንዲመስል የሚያደርጉት እውነተኛ ቃላት ናቸው። ጥሪያችሁን የምር ከወሰዳችሁት፣ ዋልጌ ቃላትን ለዘላለም ትተዉአቸዋላችሁ። መደበኛ የሆኑት 'ታውቃለህ?' ደግሞም 'ማለት የፈለግሁትን ታውቃለህ?' ከሁሉ የከፋው 'እስኪ' 'እስኪ እንጻልይ' 'እስኪ ጥቂት ክፍሎችን ከማርቆስ ላንብብላችሁ'፣ 'እስኪ ልነግራችሁ የፈለግሁትን ስሙ' - ይህም የሚሆንበት ምክንያት እያላችሁ ላላችሁት ነገር ከሞላ ጎደል ይቅርታ እየጠየቃችሁ እንዲመስል ማድረጉ ነው። ይህ ተራ ቃል ሲተው ሁሉም 'እስኪ' ያለባቸው ዐረፍተ-ነገሮች ደመቅ ብለው እና በብርቱ ይነገራሉ።

በትክክለኛ ቅላጼ መናገር

በድጋሚ፣ በመልእክቱ ጉባዔን ለምን እንረብሻለን? *ምንም ነገር* በመንገዱ ውስጥ መሰንቀር የለበትም። ሁላችንም የትኛውንም እርግጠኛ ያልሆንንበትን ቃል በትክክለኛው ቅላጼው ልንናገረው መዝገበ ቃላትን መጠቀም አለብን። የእያንዳንዱ ተውላጠ ስም ቅላጼ በምንባቡ ውስጥ የተሰጠ ሲሆን ይህንን የሚያሳዩን የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎችን (ማለትም ቅላጼን የሚያሳይ መጽሐፍ

ቅዱስ) ልንጠቀም ጭምር ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስ ወደ አማርኛ ከተተረጎመ አሁን ረጅም ጊዜ ሆኖታል። የእያንዳንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ሰው እና ቦታ ስም ቅላጼ የምናይበት መደበኛ የሆነ የአማርኛ መንገድ ስላለ በምትሳሳቱበት ውስጥ የራሳችሁን ቅላጼ ለምን ትፈጥራላችሁ?

በሌሎቹ ቃላት ሁኔታ መሠረት፣ ቅላጼው እንዴት እንደሆነ *በእርግጠኝነት* የማናውቀውን ቃል *መቼም* ልንጠቀምበት አይገባም። በገዛ ቋንቋችሁ ሥሩ! በምትሰብኩ ጊዜ ከምትናገሩበት ሁኔታ የተነሣ ወንጌል ማላገጫ እንዲሆን ሰበብ አትሁኑ። በስብከት ውስጥ የምትጠቀሟቸው ቃላት ልብሶቹ ናቸው - ስለምን ብጭቅጫቂ እንዲለብስ ታደርጉታላችሁ?

[3] ድምጻችሁ

የሚሰብ ድምጽ ለማዳበር እንዲረዳቸው እናም ተወጥሮ የሚጎዳ እንዳይሆን ለመጠበቅ የሚረዳቸው ቀላል የሆኑ ጥቂት ደንቦች ይኖር እንደሆነ ወጣት ሰባኪዎች ደጋግመው ይጠይቃሉ። የትኛውም እንዲህ ያለውን ደንብ ልሰጣቸው እንደምችል መቼም ተሰምቶኝ አያውቅም፣ ነገር ግን ጥቂት ፍንጮችን ለመስጠት ግን እመርጣለሁ። ከእነዚህም መካከል በጣም ጠቃሚ የሆነው 'የስብከት ፍጹምነት ስንናገረው ነው' (ሲ. ኤች. ስፐርጅን) የሚለው ነው። መደበኛ በሆነ ውይይት ውስጥ ስለ ድምጻችን ብዙም አናስብም። አእምሯችን የሚያዘው ልንለው በምንፈልገው ነገር እና ቀጥሎ እንዲሆን በምንፈልገው ነገር ነው። በስብከት ላይም እንዲሁ ዓይነት ነገር ቢከሰት፣ በጥሩ ሁኔታ እንናገራለን። ስብከት አቀራረባችን ፍስሰት አለው፣ ቀላል እና ከሞላ ጎደል የውይይት ያክል ይሆናል - 'ከሞላ ጎደል' ያልኩት *ልክ* እንደ ውይይት ስለማይሆን ነው። የምንናገረው ከመድረክ ወይም ምስባክ እንደሆነ እንጂ ከባለመደገፊያው ወንበር እንዳልሆነ እያየን እንዴት ሊሆን ይችላል?

ሀብለ-ድምጽ (ቮካል) የሚሠራው እንዴት እንደሆነ በመረዳት ውስጥ በቀላሉ ድምጻችን ይሻሻላል። ድምጽ የነፋስ *መሣሪያ* ነው። በሣምባችን ውስጥ ያለ አየር፣ በሣምባችን ጠርዝ የምንገፋው አየር በሃብለ-ድምጽ እጥፋቶች ውስጥ አልፍና እንዲርገበገቡ ያደርጋቸዋል። እነዚህ ሃብለ-ድምጻዊ እጥፋቶች በማንቀሩታችን ውስጥ አድርገው ወደ አየር ማስገቢያችን ጫፍ ይመጣሉ።

እርግብግቢቶቹ በማንቀሥርታችን፣ ሳይነስ እና አፋችን ባዶ ቦታዎች ውስጥ የሚኖሉ የድምጽ ሞገዶች ይሆናሉ። ላንቃ፣ *መንጋጋ*፣ ጥርስ፣ ከናፍርት እና ምላሽ የእነዚህን ተስተጋቢ ክፍተቶች ቅርጽ የለውጡትና የተለያዩ ድምጾችን ይፈጥራሉ። ስለዚህ ጮክ ብሎ፣ በግልጽ እና በምቾት ለመናገር ትንፋሻችንን መቆጣጠርን መማር ይኖርብናል እንጂ የሃብለ-ድምጽ እጥፋቶችን መወጠር፣ ማስተጋቢያዎችን ማስገደድ፣ እና ድምጽን የሚለውጠውን ማንቀሳቀስ የለብንም። ይህንን በቀላሉ *መገንዘቡ* አብዛኛውን ጊዜ መስተዋል ወደሚችል መሻሻል ያመራል።

ድምጻችን ሊሰሙት የበለጠ የሚስብ እንዲሆን ለማድረግ፣ ፈጣሪያችን ማድረግ እንዲችል ያደረገውን የሚከተሉትን አምስት ነገሮች *መገንዘብ* ጭምር አለብን፦

1. የድምጽ እንቅስቃሴ (ፒች)፦ ከፍ ወይም ዝቅ ሊል ይችላል።
2. ፍጥነት፦ ሊፈጥን ወይም ሊዘገይ ይችላል።
3. መጠን፦ ሊጮኽ ወይም ሊበርድ ይችላል።
4. ቅላጼ፦ ሻካራ ወይም ለስላሳ ሊሆን ይችላል።
5. አጽንዖት፦ በዐረፍተ-ነገሩ ውስጥ ያሉ የተለዩ ቃላት ላይ በጥብቅ ጫን ሊል ይችላል።

ገታ የማድረግን አስደናቂ ኃይል እንዲሁ አስታውሱ። ሩድያርድ ኪፕሊንግ 'በዝምታችሁ ውስጥ ትናገራላችሁ' ሲል ምን ማለቱ ነው? ታላቁ ሕዝባዊ ተናጋሪ ሲሴሮ 'የአሳማኝ ንግግር ሚስጢር ገታ ማድረግ ነው' ብሎ የተናገረው ለምንድነው? እውነታው እንዲህ ያሉ የታሰበባቸው ዝምታዎች *ሁልጊዜ* ትኩረትን ይቀሰቅሱና ለቃላት እና አሳቦች የተለዩ አጽንዖቶችን ለማምጣት ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። ማብቂያ የለሽ የቃላት ጋጋታን አንድ ሰባኪ ሲያፈስስ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? ያ በሚሆንበት ጊዜ ምን ተሰማችሁ? በርካቶቹ ሰዎች እንዲህ ያለ ንግግር አድጋሚ እና ሰቅጣጭ ሆኖ ያገኙታል። አእምሯቸውን ይዘጋሉ። የማስታገሻ መግቻ የሌለው ፍሰት ጋር ከሆነ የመጡት ነገሮችን ማስተናገድ አይችሉም። ነገር ግን አስታውሱ፦ 'መግቻው ትኩረትን ወደ

አሳብ ለማምጣት ረዘም ያለ ሊሆን ይገባል፣ ነገር ዝምታው ለመግቻው ትኩረትን እስኪያመጣ ድረስ ረጅም መሆን የለበትም።'[11]

[4] በቃል የማይቀርቡ መግባቢያዎቻችሁ

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በቃላት የማይቀርቡ መግባቢያዎችን በተመለከተ በርካታ ምርምሮች ተደርገዋል። ሁልጊዜ (ደግሞም መኖሩን አላስተዋልንም!) መልእክቶችን የምናሠራጨው በተቀመጥንባቸው ወይም በቆምንባቸው ሁኔታዎች፣ በፊታችን እና የሠውነት እንቅስቃሴ አገላለጽ እና በእኛ ዙሪያ እንዲኖር በምንፈልገው የቦታ መጠን ነው። ከባህላችን ልዩ ልዩነት የተነሣ፣ እነዚህ ምልክቶች ማለት በተለያዩ ቦታዎች ላይ የተለያዩ ነገሮች ማለት ናቸው።

ይህንን አስደናቂ ነገር ችላ ልንል መድፈር የለብንም! አትቀልዱበት፤ የሃብለ-ድምጽ ቅላጼ፣ ፈገግታዎች፣ የግንባር መቋጠር፣ አተያየቶች፣ ጠቀሳዎች እና ጨረፍታ መመልከቶች የእግዚአብሔር ቃል እውቅና እንደሚሰጠው መልእክቶችን ያስተላልፋሉ (ምሳሌ 6፡12-14)። ስብከት ዝም ብሎ የሚሰማ ነገር ብቻ አይደለም፣ የሚታይ ነገርም ጭምር ነው። ስትሰብኩ ሰዎች በሚመለከቱበት ጊዜ፣ አይኖቻችሁ፣ እጆቻችሁ፣ ፊታችሁ እና እግራችሁ ለእነርሱ የሆነ ነገር እያሏቸው ናቸው። እነዚህ ለእናንተ ወይም በእናንተ ላይ ተግባር ያላቸው ነገሮች ናቸው።

ይህ ከልክ በላይ ራሳችንን የምናውቅ ሊያደርገን አይገባም። ሁላችንም ልንጨብጠው የሚገባን ነጥብ በቃላት ያልሆኑት መልእክቶቻችን በቃላት የሚተላለፉትን መልእክቶች ሊፃረሩ አይገባቸውም የሚለው ነው። 'እናንተ ሽክም የከበደባችሁ ሁሉ ወደ እኔ ኑ፣ እኔም አሳርፋችኋለሁ' (ማቴ. ፲፡28) በሚለው ክፍል ላይ እየሰበክ ሁለት ቡጢዎችን በሰዎቹ ላይ የሚያወዛውዝ ሰባኪን በተመለከተ ምን ትላላችሁ? ሁለት እጆቹን ኪሱ ከትቶ ስለ ሲያል የሚሰብክ ሰውን በተመለከተ ምን ታስባላችሁ? 'ወርቅና ብር የለኝም' (ሐዋ. ሥራ 3፡6)

[11] ሮቢንሰን፣ ሃደን ደብልዩ. *ኤክሰፖዚተሪ ፓሪቺንግ፣ ፓሪንሲፕልስ ኤንድ ፓራክቲስ* (ሌክስተር፣ ኢንተር ቫርስቲ ማተሚያ፣ 1986)፣ ገጽ 207።

አዲስ እና የተሻሻለ የሆነው የዚህ ቆንጆ መጽሐፍ ቅጂ አሁን ገበያ ላይ ይገኛል

በሚለው ላይ እየሰበከ በጋብቻ ቀለበቱ ያለማቋረጥ የሚጫወት ሰባኪ ብታዩ ምን ትላላችሁ? ይህንን ጉዳይ ልናስተውል ይገባናል። የምናስተውል ከሆንን፣ ጠቃሚ ያልሆኑት ምልክቶቻችን በሰፊው ራሳቸውን የሚፈውሱ ይሆናሉ።

የዓይን መገናኘት ጥያቄ ጋር አብሮ ይሄዳል ብለን የምናስበው ጋር እንቆላለፍ። ይህም በርካታ ልምድ ያላቸው ሰባኪዎች እንኳን ሳይቀሩ በሚያስከፋ ሁኔታ የሚስቱበት ክልል ነው። ሰዎቻችሁን ተመልከቱ! *ተመልከታቸው*! በምትሰብኩበት ጊዜ መላውን ዓለም ፊታቸውን እዩ!

ከዚህኛው በተለየ የሚበልጥ ጠቃሚ የሆነ የቃል አልባ መግባቢያ የለም። የዓይን መገናኘት ትኩረትን ይጠይቃል - ወደ ማንም ሰው ተመልከቶ የማያውቅ ሰው መልእክት ላይ ትኩረት የሚያደርገው ማነው? ዓይኖቻቸውን ስትመለከቱ መልእክቱ *በግል* ለእነርሱ እንደሆነ ይሰማቸዋል። አዎን፣ በመልእክቱ ወቅት፣ *በእውነት እየተናገራችሁ* ሳለ በቦታው ላይ ወዳሉት እያንዳንዳቸው ሰዎች ተገናኙ። እንደ ሕዝብ አትቀኑጠሯቸው፣ ነገር ግን እንደ ግለሰቦች እንጂ።

ሰባኪው ጥሩ የዓይን መገናኘት ሲኖረው፣ ሰዎች የበለጠ ኮስተር ብለው ይከታተሉታል። ዓይኖቻችንን የማይመለከቱንን ሰዎች ሁላችንም አናምናቸውም። የማይታመኑ እና አታላዮች አድርገን፣ እንዲሁም አንድን ነገር ከእኛ ሊደብቁ እንደሚሞክሩ አድርገን እናስባቸዋለን። የትኛውም የወንጌል ሰባኪ እንዲህ ያለውን መልእክት ሳያውቀው ካልሆነ በቀር ሊሰጥ አይገባውም። ስለዚህ ሰዎቻችሁ ፊታችሁን እንዲያዩ አድርጉ፣ እና እናንተም እነርሱን እንደምታዩ እንዲያውቁ አድርጉ።

ከዚህ ባለፈ፣ የዓይን መገናኘት ሌላ ጠቀሜታ አለው። ሰዎች ለመልእክታችሁ አፀፋ እየሰጡ ያለው እንዴት እንደሆነ ማየት ያስችላችኋል። የተሳቡ ይመስላሉ? ግራ የገባቸው? የሰለቹ? የፈነደቁ? የተቸገሩ? የጠሉት? የተደሰቱ? መድከም ጀምረዋል? ትኩረታቸውን ለመሳብ አስረጅ ምሳሌ የምትጠቀሙበት ጊዜ ነውን? ጉባዔያችሁን *የምትመለከቱ* ካልሆናችሁ፣ ከእነዚህ ጥያቄዎች አንዱንም አትመልሱም።

ሕዝቦቻቸውን የሚወድዱ ሰባኪዎች ሁሉ በዓይን መገናኘት ላይ ደግ ናቸው። አጋዥ የሆነ የግል ማበረታቻን ከዚያ በኋላ ለመናገር የሚችሉለት የተቸገረ ሰው ለይተው ማየት የሚችሉት አለበለዚያ እንዴት ነው? ጉባዔያቸው

ተመችቶት ይሁን አይሁን፣ -በጣም ሞቆት ይሁን፣ በጣም ቀዝቅዞት ይሆን፣ በፀሐዩ ደንዝዞ ይሁን፣ በቂ ካልሆነ ብርሃን ጋር እየታገለ ይሁን ወይም ምንም ነገር ሊያዩ የሚችሉት እንዴት ነው? በፊት ለፊት ያለው ሰው እርምጃ ካልወሰደ በቀር በትክክለኛ ሁኔታ እነዚህ ነገሮች ሊስተካከሉ አይችሉም። ስለዚህም ጋሼ ሰባኪ በፊት ለፊት ያለው ያ ሰው *እርሰዎ* ነዎ!

ራሳቸውን አልፎ ለመመልከት፣ ወደ ማስታወሻዎ አቀርቅሮ ለመመለከት፣ በመስኮት ወደ ውጭ ለማየት ወይም ዓይኖቻችሁን ለመጨፈን ጊዜው አይደለም፣ ነገር ግን ሰዎችን በዓይኖቻቸው ለማየት እና በማያፍር መልኩ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስጠት እንጂ።

[5] ገጽታችሁ

ስለ ስብከት አቀራረብ በምናስብ ጊዜ ስለ ግላዊ ገጽታችንና ልብሶቻችንም ጭምር ትኩረት ልንሰጥ ይገባናል። ይህ መነጋገሪያ ያለው ጠቀሜታ ጥቂት ወይም ምንም ነው ብላችሁ ለማሰብ ትፈተኑ ይሆናል። ነገር ግን ተሳስተናል። ይህ የሚሆንበት ምክንያት የምቀርብበት ገጽታ አድማጮቼ ለእኔ ምላሽ የሚሰጡበትን መንገድ የተለየ ስለሚያደርገው ነው። እንግዲያው መነጋገሪያው አንገብጋቢ ነው ማለት ነው።

ይሁን እንጂ፣ በዚህ ክልል ላይ ከባድ እና ፈጣን ደንቦችን እንዳናኖር መጠንቀቅ ይኖርብናል። ለዚህ ምንም ደንቦች የሉም። የሚለበሱ ፋሽን ልብሶች እና የአለባበስ ዘይቤዎች ባለማቋረጥ እየተቀየሩ ናቸው። ይህ ከተባለ፣ በዓለም ላይ ያለ እያንዳንዱ ሰባኪ የሚከተለውን መርኽ ማስታወስ አለበት፡- *ምንም ነገር የሰዎችን ትኩረት ከመልእክቱ ወደ መልእክተኛው ሊቀይረው አይገባም፤ እንዲሁም የትኛውም ነገር መልእክቱን እንዲያቃልል ወይም እንዲያሳፍር ሊፈቀድለት አይገባም።*

በሃያ አንደኛዋ ክፍለ-ዘመን ቃሉን እንደሚሰብክ እንግሊዛዊ፣ በእኔ ሁኔታ ውስጥ የሚከተሉትን በጣም አስፈላጊ አድርጌ እቆጥራቸዋለሁ፡-

- በጥሩ ሁኔታ የተበጠረ ጸጉር።

- ከልኩ የሚያልፍ ክብደት እንዳይኖረኝ።

- ላብ መከላከያ የተደረገበት ሰውነት፣ ንጹህ ጥርስ እና ጣፋጭ ትንፋሽ።

- ጠቃሚ የሆነ የሚናገረው ነገር እንዳለው ሰው ሆኖ መልበስ። በእኔ ባህል ያ ማለት ሙሉ ልብስ፣ ሸሚዝ እና ከረቫት ማለት ነው። ተወካዮቻችን በፓርላማ የሚለብሱት እንደዚህ ነው። የአማካሪ ሐኪሞች፣ ስኬታማ ነጋዴዎች እና በጣም የታወቁ የእግር ኳስ ጨዋታ ሥራ አስኪያጆች አለባበስም እንዲሁ ነው!

- ንጹህ ጫማዎች፣ ከፍ ብለው የሚታጠቁ ሱሪዎች፣ ያላበጡ ኪሶች፣ ንፁህ ሸሚዝ እና በጥሩ ሁኔታ የታሠረ ከረቫት።

አለባበሳቸው ጥሩ ባልሆኑ ሰዎች ቃል አሁንም አሁንም ራሴን ስረበሽ አገኘዋለሁ። ከሰውዬው አገጭ ትንሽ ወረድ ብሎ ጠብ ባለ ትልቅ የቡና ጉድፍ ላይ ወይም በሰባኪው ቲሸርት ላይ የሚስቅ በረዶ ተንሸራታች ከነመነተቻው መመልከት ወይም በጣም ታዋቂ የሆነ የካርቱን ገጸ ባህርይን ለአንድ ሰዓት መመልከት አያስደስትም! ከአንድ ጊዜ በላይ፣ በእጅጉ የታመሙ ሰዎች ተጋባዥ አገልጋዮቻቸውን የምር ሊከታተሉ እንደማይችሉ ይነግሩኛል። ይህም የሚሆንበት ምክንያት ምንም እንኳን የእግዚአብሔርን ቃል ያነበቡና የጸለዩ ቢሆኑም፣ የሚመጡት የእግር ኳስ ማሊያዎችን ለብሰው ነው። የሚፈቀድ በሆነው እና ባልሆነው ነገር ላይ ሁላችንም አንስማማም። ነገር ግን ይህ የበለጠ አጥልቀን ልናስብ የሚገባን ክልል እንደሆነ ሁላችንም ልንስማማበት ይገባል።

[6] እንቅስቃሴዎቻችሁ እና የሰውነት እንቅስቃሴ መግለጫዎቻችሁ

ስብከት *ፖሚታይ* እንዲሁም የሚሰማ ነገር እንደሆነ ማስታወሳችን ጠቃሚ ነገር ነው። እኛ ሰባኪዎች ወደ ምስባኩ መንቀሳቀስን ከመማራችን በፊት ከሁሉ በፊት አስቀድመን *መቆም* ልንማር ይገባናል። እንደ አዋጅ ነጋሪዎች ቀጥ ብለን ልንቆም እንጂ ተጨብጠን ልንቆም አይገባንም። ይህ ማለት ክብደታችን በሁለቱም እግሮቻችን ላይ ተመጣጥነው ለመላው የመልእክት ቆይታ ጊዜ መቆም አለብን ማለት ነው። በመስበኪያ ጠረጴዛው ላይ ልንጣበቅ አይገባንም፣ ነገር ግን በቀላሉ ክንዶቻችን ጥቅም ላይ በማይሆኑበት ጊዜ ወርደው ልንቆም ይገባናል። ይህ መጀመሪያ ላይ አስቸጋሪ ሊመስለን ይችላል። ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ

ትለምዱትና በእርግጥም አተነፋፈስን ቀላል ያደርገዋል። ይህ ማለት ድንገተኛ የመሆንን ስሜት የምንሰጥ በምንሆን ጊዜ *መቼም* እጅን ወደ ኪስ አለመስደድ ማለት ነው። ይህ ማለት ማከክን፣ ቀኑጥንጥነትን፣ ጣቶቻችንን ያለምክንያት ማንቀሳቀስን፣ ወይም ኣይኖችን፣ ጸጉርን ወይም መነጽሮችን መነካካት ለሕይወት ዘመን ሙሉ ማቆም ማለት ነው። ይህ ማለት አንዳንድ ጊዜ ወዳጃዊ ወይም የቅርበት የሆነ ነጥብን ለማስቀመጥ ወደ ምስባኩ መቅረብ፣ ነገር ግን ከዚያ በኋላ ወደ መደበኛ አቋም መመለስ ማለት ነው።

የተለመደ በሆነ ውይይታችን ውስጥ፣ በተለይ ቆመን ሳለን በሰውነቶቻችን፣ ራሳችን እና እጆቻችን ምን እናደርጋለን? የጭንቀት ጉልበትን ለማስወገድ በተለመደ መልኩ እንጠቀምባቸውም፣ ነገር ግን እያልነው ያለነውን ነገር ለማስተላለፍ እና አስፈላጊ ከሆነም በበለጠ ሙልዓት ለመግለጽ እንጠቀምበታለን። በስብከትም ላይ ልክ እንዲሁ ልናደርግ ይገባናል። ስብከት በሕዝብ ፊት የሚደረግ ውይይት እንደሚመስል ካስታወስን፣ አብዛኞቹን ዋና ስህተቶቻችንን እናስወግዳለን።

ለመታየት እና ለመንቀሳቀስ ልንፈራ አይገባንም! በጉዳዩ ላይ የትኛውም ምርጫ ካለን፣ ሰዎች ከራስ እስከ እግር ድረስ ሊያዩን ከሚችሉበት ቦታ ሆነን ልንናገር ይገባናል። በጣም ለረጅም ጊዜ ከበስተጀርባችን ይንጨት አጥሮችን ደብቀናል፣ ደግሞም ያ እንድንግባባ አላገዙንም። መልእክት ያለው ሰው በመላው አካሉ ይናገራል እንጂ በራሱ እና በትከሻው ብቻ አይደለም። ትውፊታዊ ለሆነው ምስባክ የክብር መቀበሪያውን ልንሰጠው፣ እና እኛም በቀላሉ ልንታይ ከምንችልበት መድረክ ልንናገር ጊዜው መጥቷል።

የምንጠቀመው ምስባኮችን ቢሆን ወይም መድረኮችን፣ የሰውነት እንቅስቃሴ መግባቢያዎቻችን ሰዎች እንዲገባቸው ሊረዷቸው ይችላሉ ወይም ሊያደናቅፏቸው። በአግባቡ ስንጠቀምባቸው የሰውነት እንቅስቃሴዎች ነጥባችንን በኃይል ለማስረጽ ይረዳሉ። አድማጮቻችን ወደ እኛ ለመመልከት፣ እኛን መመልከታቸውን እንዲቀጥሉ፣ እና መላውን ትኩረታቸውን እንዲሰጡን ይነሣሣሉ። እየነዳን ያለነውን ያዩና የበለጠ በተሟላ መልኩ ወደዚያ ይገባሉ። ደግሞም አንድ ነገር በእኛ ላይ ይሆናል፣ በሚጨምር መልኩ እየቀለለን ይሄዳል።

ጠቃሚ የሆኑ የሰውነት እንቅስቃሴ *መ*ግባቢያ ባህርያት ምንድናቸው? ሃድሰን ደብልዩ. ሮቢንሰን የሚከተሉት ነገሮች መሆናቸውን ይነግሩናል፡–[12]

- *ድንገተኛ፣* ያልታቀደባቸው። እያልን ላለነው ነገር ከሚኖረን ስሜታችን የተነሣ በተፈጥሯዊ መልኩ ይወጣሉ።

- *ቀሩርጠኛ፣* በተከፈለ ልብ ወይም በአስቸጋሪ አይደለም። ሰውነታችን ወደ እነርሱ እናኖራለን።

- *ዮተለያየ፣* የትኛውም የሚደጋገም የሰውነት እንቅስቃሴ ብዙም ሳይቆይ የሚኮሰኩስ እና መልእክቱን የሚረብሽ ስለሚሆን።

- *ተገቢ ጊዜውን የጠበቀ፣* እያስቀመጥነው ያለውን ነጥብ የሚቀድም ወይም የሚያጅብ። የሚከተሉት ከሆነ አስቂኝ ይሆናል።

በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የሰውነት እንቅስቃሴ መግባቢያዎቻቸውን በመስታወት ፊት ቆመው የሚለማመዱ ሰባኪዎችን የተመለከቱ በርካታ ታሪኮች አሉ! በግሌ ይህ ጥሩ አሳብ እንደሆነ አላስብም። ሰባኪው እያደረገው ላለው ነገር ራሱን በእርግጠኝነት የሚያውቅ እንደሚያደርገው እርግጠኛ ነኝ፣ ደግሞም ከዚህ የተነሣ የሮቢንሰንን የመጀመሪያውን ደንብ የሚጥስ ይሆናል። ይሁን እንጂ፣ ጠቃሚ ያልነበሩትን የሰውነት እንቅስቃሴዎች ለይቶ ለማወቅ የስብከታችንን በቪዲዮ የተቀረጸ ቅጂ አልፎ አልፎ መመልከት ትርጉም እንደሚሰጥ አስባለሁ። ይህንን በዓመት ከሁለት ጊዜ በላይ ልናደርግ እንደሚገባ አላስብም፣ አለዚያ በእጅጉ ተስፋ እንቆርጣለን! ነገር ግን ዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንደ ሰባኪ እንድናሻሽል ሊረዳን የሚችል ከሆነ፣ ጥቅሞቹን የማናጭደው ለምንድነው?

[12] ሮቢንስን፣ ሃደን፣ ደብልዩ. *ሌክስፖዚተሪ ፓሪሺንግ፣* ገጽ 200-1

[7] ጊዜያችሁ

ይህንን ምእራፍ የምንዘጋው አብዛኛውን ጊዜ የሚቀለድበትን፣ ነገር ግን ታላቅ ጠቀሜታ ያለውን የአቀራረብ ገጽታ በመመልከት ነው። እርሱም የጊዜ ጉዳይ ነው።

በታላቅ መንፈሳዊ መነቃቃት ውስጥ እየኖርን እንዳልሆነ በቀጥታ ላስታውስ እፈልጋለሁ። በዓለም ዙሪያ መሠራጨቱን እየቀጠለ ያለውን የወንጌል መልእክት ማየቱ አበረታች ነገር ነው፣ ነገር ግን እንደ ዐሥራ ስምንተኛው ክፍለ-ዘመን ያለ የወንጌላዊያን መነቃቃት ያለ ነገር ማናችንም እየተለማመድን እንደሆነ አናስመስልም። በዚያ ጊዜ ለምሳሌ፣ ጆን ዌስሊ አብዛኛውን ጊዜ ለሁለት ሰዓታት ይሰብክ ነበር፣ ጆናታን ኤድዋርድስ ደግሞ ለሦስት ሰዓታት! ሰዎች ተከታታይ የሆኑ በርካታ ስብከቶችን መስበካቸው ያልተለመደ ነገር አልነበረም። ጉባዔያቸው በቃሉ እንደተሳቡ ቆይተው፣ ዘላቂ የሆነ መንፈሳዊ ሥራ ይሠራ ነበር።

ክርስቶስ የላከው እያንዳንዱ ሰባኪ ማንንም ሰው መለወጥም ሆነ የትኛውንም የሚዘልቅ መልካም ነገር ሊያደርጉላቸው እንደማይችሉ እርግጠኞች ነበሩ። ቃሉን አጉልቶ ለማሳየት ስለሚረዳው መንፈስ ቅዱስ በሚያውቀው ነገር ሁሉ አመስጋኝ ነው። ደግሞም መንፈስ በአንዳች ያልተለመደ መንገድ በእርሱ ላይ እንዲመጣበት ይናፍቃል። እንዲህ ያለው ተሞክሮ ደግሞ እያንዳንዱ ሰባኪ ከጊዜ ወደጊዜ ከሚሰማው የአድሬናሊን ሆርሞን ወይም የፍንደቃ ስሜት በጣም የተለየ እንደሆነ ያውቃል። በስተመጨረሻ ለሰዓታት የሚሰብክ የሚችል ሆኖ ራሱን እንደሚያገኘው ያውቀዋል። በዚያው ጊዜ ላይ የተለመዱ ደንቦች ተግባራዊ ሊደረጉ እንደሚገባቸውም ጨምሮ ያውቃል!

የተለመዱት ደንቦች እነዚህ ናቸው፡-

- ልትጠቀሙበት የተሰጣችሁ ጊዜ ምን ያክል እንደሆነ እወቁ።
- በጊዜ ጀምሩ - ደጋግመው እየዘገዩ ለሚመጡት ብላችሁ አትዘግዩ!
- በጊዜ አብቁ። ሰዎች የሚመጡት ሰብሰባው ለተወሰነ ጊዜ እንደሚቆይ ባላቸው መረዳት ውስጥ ሆነው ነው። ከዚህ

የተነሣ በጊዜ መጨረስ ማለት የኃቀኝነት ጉዳይ ነው። እንድትከበሩ እና ጠቃሚነታችሁ እንዲጨምር የሚአደርግም ነገር ነው።

- ስብሰባውን ከእናንተ ጋር የሚካፈለውን የሌላውን ሰው ሰዓት ለራሳችሁ አትውሰዱ። ይህ በትክክል የወጣለት ስያሜ 'የመድረክ ሌብነት' የሚል ነው። ምክንያቱ ደግሞ ሊመለስላቸው የማይችለውን ነገር ከሌሎች ላይ መውሰድ ስለሆነ ነው።

እየጠላው እንዲሄድ ከማድረግ ይልቅ ጉባዔውን ሁልጊዜ እንዲናፍቀው አድርጎ መሸኘት የተሻለ ነው። የምንኖረው በአጠቃላይ አነጋገር ረጃጅም ስብከቶችን የሚያደንቅ ትውልድ መካከል አይደለም። ብዙ ፍሬ-ነገር ያለው ነገርን በዐሥር ደቂቃዎች ውስጥ ልትናገሩ አትችሉም፣ ደግሞም አብዛኞቹ ሰዎች ዛሬ ላይ አርባ ደቂቃዎችን አድካሚ አድርገው ይቆጥሯቸዋል።

ይሁን እንጂ፣ አንዳንድ ጉባዔዎች ይህንን በትእግስት ተምረዋል፣ ደግሞም ከሌሎች ይልቅ ለረጅም ጊዜ መስማት ይችላሉ። ምን ያክል ትምህርት እንደምናቀርብ ስንወስን በአእምሯችን ልናኖር ከሚገቡን ጉዳዮች አንዱ ይህ ነው። ምናልባት ጥሩ የሆነው ደንብ ወደ ሦላሳ ደቂቃዎች ገደማ ያክል ወይም ጥቂት አለፍ ብሎ ድረስ መስበክ፣ ነገር ግን ልክ ለሃያ ደቂቃዎች የተሰበከ ያክል እንዲመስል ማድረግ ነው።[13] ይህም መሆን ያለበት 'ስብከትን የማሳጠሪያው እውነተኛ መንገድ የበለጠ እንዲስብ ማድረግ ስለሆነ ነው' (ኤች. ደብልዩ. ቢቸር)።

ስብከታችንን ስንጨርስ፣ *ልናቆም* ይገባናል! የተመደበውን ጊዜ እንዲሞላልን ብለን ስብከትን መደጋገም ስህተት ነው። ሰባኪ እንዲህ ያለውን ነገር ለምን ያደርጋል? ምናልባት በጣም ቀደም ብሎ መጨረሱን እንዳይተችበት ፈልጎ ሊሆን ይችላል። ጉዳዩ ይህ ከሆነ የውስጥ መነሻ አሳቡ ራስ ወዳድ ነው፣ ደግሞም እንኳን ለቃሉ አዋጅ ነጋሪ ይቅርና ለክርስቲያን የማይገባ ነገር ነው። ወይም ምናልባት ጉባዔውን ተስፋ ማስቆረጥ አልፈለገም፤ ነገር ግን ያሳጠረ

[13] ይኼኛው ምክር በስቶት ጆን አር.ደብልዩ፣ *ሉይ ቢሊቭ ኢን ፕሪቺንግ* (ሎንዶን፣ ሆደር ኤንድ ስቶግተን፣ 1982) ገጽ 294 ላይ የተመሠረተ ነው።

ከመሆን ይልቅ አላስፈላጊ የሆነ ትርኪ ምርኪ ነገርን ሳይፈልጉ እንዲቀበሉ በማድረግ ሕዝቡን ተስፋ የሚያስቆርጥ ይመስላል።

ይሁን እንጂ አብዛኞቹ ሰባኪዎች ተቃራኒ የሆነው ችግር አለባቸው፤ በጊዜ መጨረስ ከባድ ሆኖ ያገኙታል! ለሌሎች በርከት አድርገው ካላሰቡ በስተቀር ምንም ነገር አይፈውሳቸውም። ጊዜ እያለቀባቸው ከሆኑ፣ የቀራቸውን ነገር አርመው፣ በሚጠበቀውበት ቅጽበት ላይ መጨረስ፣ እና ከዚያም ወደ ቤት ሄደው በቂ ላልሆነው ዝግጅታቸው ንስሃ መግባት አለባቸው። በተገቢ ሁኔታ የተዘጋጁ ሰባኪዎች ከጊዜያቸው በላይ አይወስዱም።

አንዳንድ ሰዎች ጊዜ እንዳለቀባቸው እያወቁ ሕዝባዊ የሆነውን ኃቀኛ ያለመሆን ኃጢአት ይፈጽማሉ። ለሰሚዎቻቸው በቶሎ እንደሚጨርሱ ይናገራሉ፣ ከዚያ ግን ዝም ብለው ይቀጥላሉ። እርስዎ ልከ እንዲህ ያሉ ሰባኪ ከሆኑ፣ አንድ ሰው ልቅ የሆነ ጥያቄ ሊጠይቃችሁ ይገባል፦ በገዛ ራሳችን ጆሮዎች እርስዎ *ውሸታም* መሆንዎን እየሰማን አሁን ላይ መልእክትዎን ወደ ልባችን መውሰድ የሚኖርብን ለምንድነው?

* * *

ጠቃሚ የሆነ የስብከት አቀራረብ ምን ያክል ጠቃሚ ነው! በአንድ ቀን የምንማረው የክህሎት አይነት አይደለም። እንደ ሰባኪዎች *መጎልመስ* ካለብን፣ በዚህ ክልል ላይ ማሳየት ያለብን እድገት ምን ያክል እንደሚሆን የበለጠ ልናስተውል ይገባናል። በስብከት ላይ የተጻፉ መጽሐፍትን ማንበባችንን፣ ገለጻዎችንና ኮንፈራንሶችን መካፈል መቀጠል ይኖርብናል። እንዲሁም ልናገኝ ከምንችልበት ቦታ ሁሉ እገዛ ማፈላለግ አለብን። ልንወስደው የምንችለው የትኛውም ፍንጭ ይኖር እንደሆን ሌሎች እንዴት እንደሚያቀርቡ ልብ ብለን መመልከት አለብን። ጓደኞችን እና ባልደረቦችን በአቀራረባችን ላይ አስተያየት እንዲሰጡ መጠየቅ ማፈራችንን እናቆማለት።

ነገር ግን ከዚህ ሁሉ በላይ ጠቃሚ የሆነ አንድ ነገር አለ፤ ከቆዳችን መውጣት የምንችልበት እና ራሳችን ስንሰብክ ማየትና መስማት የምንችልበት ብቃት ነው። ራሳችንን በሚሰሙን ሰዎች ስሜት ውስጥ ማኖርን እና የገዛ

ራሳችንን ገሃዳዊ የአቀራረብ ግምገማ ማውጣትን በቀላሉ መማር አለብን። በሕይወት እስካለን ድረስ፣ *በሰበክን ቍጥር* ይህንን ልናደርግ ይገባል!

* * *

የምታደርጉት ነገር

1. የገዛ ራሳችሁን አቀራረብ ገምግሙና ያንን ለማሻሻል እቅድ ንደፉ።

2. በእናንተ አስተያየት የስብከት አቀራረባቸው ጠቃሚ ባልሆኑ ሰዎች የሚሠሩት ‘ዐሥሩ ቀንጮ ኃጢአቶች’ ምንድናቸው? መልሶቻችሁን ጻፉት።

3. ሁሉም ስብከት *ድራማ* የሆኑት በምን መልኩ ነው፣ ደግሞስ ሊተወን የሚገባበትን ይህ ሊነካው የሚገባው እንዴት ነው? ይህንን ከሌሎች ሰባኪዎች ጋር ተወያዩበት።

7

ልዕለ-ተፈጥሯዊ ሥልጣን

በ1973 ዓ.ም አሜሪካንን ለመጀመሪያ ጊዜ ጎበኘሁ። በዚያ ጊዜ የትሪኒቲ ባፕቲስት ቤተክርስቲያን መጋቢ ከሆኑት መጋቢ ኤ. ኤን ማርቲን ጋር በሞንትቫይል፣ ኒው ጀርሲ ውስጥ በርካታ ቀናትን አብሬ አሳለፍኩ። በጉባዔው ካሉት ሰዎች መካከል አንድ ሰው የስብከታቸውን ዝርዝር የያዘ መጠነኛ መጽሐፍ ሰጠኝና፣ በውስጡ ሕይወቴን ለዘላለም የለወጠ አንድ አስተያየት ነበር። መጠነኛዋ መጽሐፍ የመጋቢ ማርቲን ስብከቶች የሚለዩት 'ሥነ-ፍታቴያዊ ትክክለኝነት፣ አስተምህሯዊ ፍሬ-ነገር፣ ግልጽ መዋቅር፣ ጉልህ የሆነ አስረጅ ምሳሌ፣ በነጥብ የሚቀመጥ ተዛምዶ እና መንፈሳዊ አጣዳፊነት' በመያዛቸው እንደሆነ ትገልጻለች። በመጨረሻ ላይ ግሩም የሚባል ስብከትን የሚሠሩ አስፈላጊ ነገሮችን የያዘ ዝርዝር አገኘሁ!

ልታዩ እንደምትችሉት፣ 'ጠቃሚ የሆነ የስብከት አቀራረብ' ላይ አንድ ምእራፍ የጨመርኩኝ ብሆንም፣ ይህንን መጽሐፍ በምጽፍበት ጊዜ ያንን ዝርዝር በነፃነት ተጠቅሜያለሁ። እንግዲያው ይህ የመጨረሻ ምእራፍ 'መንፈሳዊ አጣዳፊነት' ተብሎ እንዲጠራ ትጠብቁ ይሆናል። ነገር ግን አይደለም፣ ለዚህ ማብራሪያው ደግሞ ይኸውላችሁ።

ከጥቂት ምእራፎች በፊት ስለ ጥልቅ ስሜት ርእሰ-ጉዳይ ወደ ኋላ ላይ እንደምመለስ ተናግሬ ነበር። ያ ጊዜ አሁን ደርሷል። በስብከት ወቅት ስሜታዊ መስተጋብር የሚያስፈልግ ስለመሆኑ ብዙ ሊነገር ይገባል። ይህንን መጽሐፍ እየጻፍኩኝ ያለሁት በሃያ አንደኛው ምእተ ዓመት መግቢያ ላይ ነው። እዚህ በመኖር ላይ ያለሁት ስለ ስብከት ብዙ ነገር እየተባለ እና እየተጻፈ ባለበት ጊዜ ላይ ነው። ሰዎች የተሻለ እንዲሰብኩ ለመርዳት የማይቆጠሩ የትምህርት ኮርሶች በመዘጋጀት ላይ ናቸው። እየሆነ ያለው አብዛኛው ነገር ስብከትን ወደበታው ከመመለስ ይልቅ የሚያጠፋ የሚመስል እንደሆነ ያለኝን እምነት መደበቅ አልችልም።

ሰባኪ የሚሰብከውን የቃል ምንባብ በግልጽ ካብራራ እና በፊት ለፊቱ ላሉት ሰዎች ካዛመደላቸው ጥሩ ሥራ እንደሠራ በሰፊው የሚነገር አስተያየት አለ። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንታኔውን ግልጽ እና ተዛማጅ እስካደረገ ድረስ ኃላፊነቱን ሙሉ ለሙሉ ተወጥቷል። ሌላ ምንም ነገር ሊያደርግ አይገባውም። የእግዚአብሔር ቃል አሁን የራሱን ልዩ የሆነ ሥራ እንዲፈጽም ለራሱ ሊተው ይችላል።

ይህ አሳብ መሬት ረግጦ ከቆመና ገዢ አሳብ ከሆነ፣ ብዙም ሳይቆይ የእውነተኛ ስብከት ቀብር ላይ እንገኛለን። አካሉ ይቆያል (ምንም እንኳን ፈጥኖ የሚበሰብስ ቢሆንም)፣ ነገር ግን ነፍሱ ትሄዳለች። ያች ነፍስ ሊለያዩ እስከማይቻል ድረስ እርስ በርሳቸው የተጠላለፉ ሁለት ባህርያት አሏቸው። ‘መንፈሳዊ አጣዳፊነት’ አንደኛው ባህርይ ሲሆን፣ የእግዚአብሔርን ቃል በመስጠት ውስጥ ሰባኪው ራሱን የሚሰጥ መሆኑን ያመላክታል - መልእክቱ በብዙ የተደበቁ የማንነቱ ጥልቀቶች ውስጥ የሚገኙ ጥልቅ ስሜት፣ ቅንነት፣ ቀጥ እና ስሜት ይሸፈናል። ሌላኛው ባህርይ ‘ልዕለ-ተፈጥሯዊ ሥልጣን’ ነው። እግዚአብሔርን ሊገልጥ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው፣ ደግሞም መንፈስ ቅዱስ መልእክቱን ለእነዚያ የትኛውም ሰብአዊ ድምጽ ሊደርስባቸው የማይችላቸው የሚስጢር ማረፊያዎች አይወስዳቸውም፣ ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊው መልእክት የትኛውንም ያክል በጥሩ ሁኔታ ቢቀርብ በጭራሽ ጥሩ ነገር አይሠራም።

እያልኳችሁ ያለሁት ነገር ለእናንተ እንግዳ ከመሰላችሁ፣ በምድር ቤት ውስጥ እሳት የተነሣባቸውን የአፓርታማ ቤቶች እንድታስቡ ልጠይቃችሁ እፈልጋለሁ። ገና ጥቂት ጊዜ ስላለ፣ በዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ለማስጠንቀቅ ወደ ላይኛው ወለል ተጣድፋችሁ ትሄዳላችሁ። ለእነርሱ የምትሏቸው ነገር ትክክል ነው፤ ሕንጻው በእውነት በእሳት ተያይዟል (ሥነ-ፍታቴያዊ ትክክለኝነት)። ወዲያውኑ ካላመለጡ፣ በወላፈኑ እንደሚጠፉ ትነግሯቸዋላችሁ (አስተምህሮዊ ፍሬ-ነገር)። ራሳችሁን ግልጽ አድርጋችሁ ትገልጻላችሁ (ግልጽ መዋቅር፣ ጉልህ አስረጅ ምሳሌ)። ዓይኖቻቸውን እያያችሁ እንደ ግለሰቦች ታነጋግሯቸዋላችሁ (በነጥብ የሚቀመጥ ተዛምዶ፣ ጠቃሚ የሆነ አቀራረብ)። ነገር ግን ይህንን ሁሉ ያደረጋችሁት የትኛውንም አጣዳፊነት በድምጽ ቅላጼያችሁ ወይም በሁኔታችሁ ሳታሳዩ ቢሆንስ? ይህንን ሁሉ የተናገራችሁት ‘አለዚያ ግድ የለኝም’ በሚል መልኩ

ቢሆንስ? በተግባር እየቀለደ ያለ ሰው አትመስሏቸውምን? ደግሞስ ሄዳችሁ መናገራችሁ ምን ያክል ስኬት ይኖረዋል?

ስሜት በሌለበት፣ አሳማኝነት የለም። በዚህ ዓለም ውስጥ ይህ እውነት የሆነ ነገር ነው፣ ደግሞም በመንፈሳዊ ገጽታዎችም ከእውነትም በላይ የሆነ ነገር ነው። ጥልቅ ስሜት የሌለው ስብከት በጭራሽ ስብከት አይደለም። ያም ብቻ አይደለም፣ በእግዚአብሔር ላይ ስድብም ጭምር ነው፤ ሪቻርድ ባክስተር አብዛኛውን ጊዜ እንደሚከተለው በአጽንዖት እንደተናገሩት፡-

> ምን! ለእግዚአብሔር እና ለሰዎች ድነት ተቀዛቅዞ መናገር? ሕዝቦቻችን ወደ ጌታ ሊመጡ ወይም ሊኮነኑ የሚገባቸው ሆነው ሳለ እንቅልፋም በሆነ ድምጽ መናገር? ወንድሞች ወደ ምስባክ ከመሄዳችሁ በፊት የኃጢአተኞችን ልቦች ለማንቃት የምትመጥኑ እንድትሆኑ በእግዚአብሔር ስም የገዛ ራሳችሁን ልቦች ለማንቃት ሥሩ። ሊነቁ ወይም ሊጠፉ እንደሚገባቸው እና እንቅልፋም የሆነ ሰባኪ የተጫጫናቸው ኃጢአተኞችን ሊያነቃቸው እንደማይችል አስታውሱ። ምንም እንኳን የእግዚአብሔርን ቅዱስ ነገሮች በቃላት ከፍተኛ ውዳሴ ብትሰጧቸውም፣ ይህዩን እንጂ በተቀዛቀዘ ሁኔታ እያደረጋችኋቸው ናቸሁ፣ በሁኔታውም ያላችሁትን ነገር እንደላላችሁት ያክል ትመስላላችሁ። ለታላላቅ ነገሮች እንዲህ ያለው የእርካታ ስሜት በተለይም የእጅግ ታላላቅ ነገሮችን ያለ ብዙ ፍቅር እና ንዳድ መናገር ትክክለኛ እርካታ አይደለም። አኳኋኑ እንዲሁም ቃሎቹ ሊያስወነጭፏቸው ይገባል።[14]

[14] ባክስተር፣ ሪቻርድ *ዘ ሪፎርምድ ፓስተር* (ኤዲንበርግ፣ ዘ ባነር ኦቭ ትሩዝ ትረስት፣ 1974)፣ ገጽ 148።

መንፈስ ቅዱስ የሚያስፈልገን መሆኑ

ነገር ግን ጥልቅ ስሜት በራሱ መንፈሳዊውን *ሥራ መሥራት* አይችልም። ይህ እግዚአብሔርን ከሚፈራ ሰው ልብ ውስጥ ስለሚፈስስ ቅዱስ ስሜት በምንነጋገርበት ጊዜ እንኳን እውነት የሆነ ነገር ነው። ምንም ያክል የተቀደሰ ቢሆን፣ እንደዚያም ሆኖ ሰብአዊ ጣእም አለበት ደግሞም መለኮታዊውን *ሥራ* ሊሠራ አይችልም። መንፈሳዊ የሆነ *ሥር* ነቀል ለውጥ ሊያመጣ የሚችለው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው። ያለ መንፈስ ቅዱስ ነኪነት በዓለም ላይ ምርጥ የሆነው ስብከት ምንም ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በራሱ፣ እንደውም ፍጹም በሆነ መልኩ ቢገለጥ፣ ለየትኛውም ሰው የትኛውንም ነገር ሊያደርግ አይችልም፤ የውስጡ እውነት በሰብአዊያን ልብ ላይ የሚያስደምም የሚሆነው በመለኮታዊው ጸሐፊ ነው። ሰባኪው በልእለ-ተፈጥሯዊ *ሥልጣን* መናገር ካለበት አንዳች የሰማይ የሆነ ነገር መፈጠር አለበት። ይህ ካልሆነ፣ ወንዶች እና ሴቶች ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል የሚቀበሉት *የሰዎች* ቃል እንደሆነ ያክል አድርገው ነው (1 ተሰ. 1፡5፣ 2፡13 ተመልከቱ)።

ስለዚህ በመንፈሳዊ አጣዳፊነት ልናገር የምችለው እንዴት ነው? ደግሞስ በመንፈሳዊ *ሥልጣን* የምናገርበት የትኛውም ዓይነት መንገድ ይኖራልን? አሁን ልንመጣባቸው የሚገቡን ጥያቄዎች እነዚህ ናቸው።

መንፈሳዊ አጣዳፊነት

መንፈሳዊ አጣዳፊነት የአንድ ነጠላ የምናምንበት ነገር ፍሬ ነው። ይህ ሰውን በሚይዘው እና በሚቆጣጠረው ጊዜ፣ በዚህ ክልል ላይ የሚከሰር አይሆንም። ስለዚህ የምናምንበት ነገር ምንድነው? የምናምንበት ነገር *ወንዶች እና ሴቶች ሊሰሙት የሚገባው እውነት አለኝ* ማለት ነው።

ያንን ታምናላችሁ? ያንን የእውነት እና በጥልቀት ታምናላችሁ? በወንጌላዊ ሁኔታ ስትሰብኩ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ስመ-ጥር የሆነውን 'የትምህርት መልእክቶች' በምትሰጡ ጊዜስ ታምኑበታላችሁ? ካመናችሁበት፣ ይህ የምታምኑበት ነገር የመላው እውነተኛ አንደበተ-ርቱእነቶች እናት በመሆኑ በጥሩ ሁኔታ ትናገራላችሁ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ሰባኪዎች በመንፈሳዊ አጣዳፊነት ይናገራሉ። በየቦታው አሉ ሰዎች ከእነርሱ ጋር ሊወስዱት እንደሚገባ የሚያምኑበት እውነት እንዳላቸው በማወቅ ይቆሙና መልእክታቸውን ይሰጣሉ። ‘አመንሁ ስለዚህም ተናገርሁ’ እንዳለው ዘማሪ (መዝሙር 116፡10)፣ ጳውሎስ እና ጢሞቴዎስ በጽሑፋቸው የሚያስተጋቡትን ተናግረውታል ‘ነገር ግን፡- አመንሁ ስለዚህም ተናገርሁ ተብሎ እንደ ተጻፈ ያው አንዱ የእምነት መንፈስ ስላለን፥ እኛ ደግሞ እናምናለን ስለዚህም እንናገራለን፤’ (2 ቆሮ. 4፡13)። ጴጥሮስ እና ዩሐንስ የሐዋርያትን ሁሉ ልብ በመግለጥ፣ ከዓመታት በፊት እንዲህ ብለው ነበር ‘እኛስ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር ዝም ማለት አንችልም አሉአቸው።’ (ሐዋ. 4፡20)። እንዲህ ባለው ስሜት መናገራቸው ምንም አያስደንቅም! ስብከታቸው በእጅጉ አሳማኝ መሆኑ አያስደንቅም! የነገረ-መለኮት ተማሪ በነበርኩ ጊዜ እንደተነገረኝ፣ ‘መናገር እንጂ ሌላ ማድረግ የማይችል ሰው፣ መስማት እንጂ ሌላ ማድረግ ለማይችሉ ሰዎች ይናገራል!’

ገና ከመነሻው ሁሉም ሰው ሊሰማው የሚገባው እውነት እንዳላችሁ አምናችሁበታልና በቅንነት እንደ አንድ ሰው ትናገሩታላችሁ። ሒዌል ግሪፊትስ ‘ከልብ የሚመነጭ ብቻ ልብን ይደርሳል’ ብለው እንደሚናገሩት ንግግራችሁ አሳማኝ ይሆናል። የድምጻችሁ ቅላጼ፣ የፊታችሁ መግለጫ እና የአኳኋናችሁ እያንዳንዱ ነገር በጋራ የሚጣመረው ትኩረትን በቀኑጥጥር ሥር ለማዋል ነው። የሰሚዎቻችሁ ጎሊናዎች እየሰሙ ያሉት እየተናገረ ባለው ነገር የሚያምን ሰውን እንደሆነ ይነግራቸዋል።

በየትኛውም ቦታ ያሉ ሰዎች የዘላለም ሲያል አደጋ ላይ ናቸው። ንስሃ የማይገባው ወደዚያ ይሄዳል፣ ደግሞም እያንዳንዱ ማመኑን የሚናገር ክርስቲያን ነገር ግን በእምነት የማይጸናውም እንዲሁ። እውነት ብቻ እንጂ ሌላ ምንም ነገር ሊታደጋቸው አይችልም። በጸጋ እና በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ዕውቀት እንዲያድጉ የሚያደርጋቸው ሌላ ምንም ነገር ሳይሆን እውነት ነው! እንዲህ ያለው እምነታችሁ ከያዛችሁ፣ የይዘት እና አቀራረብ እንከን ቢኖርባችሁም የሚሰሟችሁን ወንዶች እና ሴቶች፣ ታዳጊዎች እና ልጆች ማነሣሣት አያቅታችሁም። አጣዳፊነታችሁ ዘልቆ ይመጣል። የተለያዩ ሰባኪዎች ይህንን አጣዳፊነት በተለያዩ መንገዶች ይገልጹታል፣ ደግሞም ሌላው ቢቀር ያው ሰባኪ በተለያዩ መንገዶች እና በተለያዩ አጋጣሚዎች ይገልጸዋል። ነገር ግን አጣዳፊነታችሁ ዘልቆ የሚመጣ ይሆናል። የሰው መንፈስ ሕልውናውን ለይቶ

ያውቃል፣ ደግሞም ጆሮዎቹ ይቀልቡታል። ነገር ግን ይስተዋል፣ የሰው መንፈስ እንዲሁም አለመኖሩንም ለይቶ ያውቃል፣ ደግሞም በዚያ ነጥብ ላይ በግዴየለሽነት እንቅልፍ ውስጥ ሰጥሞ ይገባል።

ታላቁ የዐሥራ ስምንተኛው ክፍለ-ዘመን ወንጌላዊ፣ ጆርጅ ዊትፊልድ ስለ መንፈሳዊ አጣዳፊነት ያውቅ ነበር። ትሑታን የሆኑ ጉባዔዎች ቦታ ሲቀይሩ እና በስብከቱ ወቅት ሲንሾካሾኩ፣ እጅሮቹን ረገጥ አድርጎ በቀጥታ ለእነርሱ ይናገራል፣ ከዚያም እንዲሰሙት ይጎተጉታቸዋል። ያልተለመዱ ሕዝቦች እርሱን ለማስመጥ ሊገመት በሚችለው ዘዴ ሁሉ ሲከማቹ፣ ድምጹን ከፍ ያደርግና ያሸንፋቸዋል። ሊድኑበት የሚገባበት እውነት ነበረው! ዝም ሊያሰኙት የማይቻል ነበር! በዚህም ይሁን በዚያ መልእክቱን ወደ ጆሮዎቹ ያደርስ ነበር! አዎን፣ ግልጽ በሆኑ ቃላት፣ ሊገነዘቡት የሚችሉትን የቃላት ምስሎችን በመጠቀም ይናገራቸዋል። አዎን ለሰሚዎቹ ተስማሚ የሆኑ ተዛምዶዎችን ያደርጋል። ነገር ግን እርሱን የሚነዳው ሁሉን ድል የሚያደርግ ጥልቅ ስሜት እያንዳንዱን ነገር ከመንፈስ ቅዱስ በረከት ሥር ማኖሩ እና ያም በዐሥር ሺዎች የሚቆጠሩትን ወደ ጌታ መምራቱ ነበር።

ስሜት

ስሜትን በጣም የምንፈራው ለምንድነው? በእውነት የሚንቀሳቀስ እስከ ሆነ ድረስ እና በእውነት *ብቻ* የሚንቀሳቀስ እስከሆነ ድረስ፣ አደገኛ ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው? ምናልባት ችግሩ ያለው በውስጣችን ይሆን? ‘እብዶች እንደሆንን’ (2 ቆሮ. 5፡13) ተደርገን እንዳንቆጠር ፈርተናልን? ዘማሪው ‘የቤትህ ቅናት ይበላኛል’ (ዩሐ. 2፡17፤ መዝ. 69፡9 ተመልከቱ) በማለት የገለጸበትን የጌታን መንፈስ እየተቋቋምን ነን? ራሳችንን ‘በከተማው ጣዖት መሙላቱን እየተመለከተ መንፈሱ ከተበሳጨበት’ (ሐዋ. 17፡16) ከሐዋርያው ጳውሎስ እያራቅን ነን? እንደ ዳንኤል ሮውላንድ ያሉ ሰዎችን እስከናከብር ድረስ በእጅጉ ግብዞች እየሆንን፣ ነገር ግን እርሳቸው ግን በሰበኩ ቍጥር ‘በእሳት ላይ እንዳሉ’ ሆነው መስበካቸውን ተመችቶን ዘንግተነዋልን?

ከሃያ አንደኛው ክፍለ-ዘመን የለንደን ሰባኪዎች ስመ-ጥር የሆነው አንደኛውን በተመለከተ እንዲህ ተብሏል። እርሳቸው ሁልጊዜ እያንዳንዳቸውን

ሰሚዎቻቸውን አስታግሰው፣ አጽናንተው እና በሰላም አድርገው ይተዉአቸዋል። ለዚህም ነበር ሰዎች በእጅጉ ይወድዷቸው የነበረው። እንዲህ ባለው ስብከት ላይ የእግዚአብሔር ቃል ጀርባችንን እንድናዞር ይጠራናል። ሰዎችን ወደ ሐሰተኛ የዋስትና ስሜት የሚያባብል ወይም ጥልቅ ወደሆነ ግላዊ ደስታ ውስጥ እንዲዘፈቁ ከሚያደርጉ ልዝብ ስብከቶች እንድንሸሽ ይጠራናል። የምናምንበት፣ የሚያነሣሣ፣ ጉልበት ያለው እና ቅን የሆነውን እንድንሰብክ ይጠራናል። የተሸላለሙትን፣ ለታይታ እና የማስመሰል የሆኑትን ስሜቶች ይንቃል፣ ደግሞም የእግዚአብሔርን እውነት ጥልቅ በሆነ ስሜት፣ ጭንቀት፣ ሞቅታ፣ ሕይወት እና ፍቅር እንድናውጅ ያዝዘናል። ጥሪያችን ጎትጉን እንድናወርድ፣ እንድንነነባ፣ እንድናቆስልና እንድንፈውስ፣ እንድናስጨንቅ እና እንድናጽናና፣ እንድናስለቅስ፣ እንድናጓጓ፣ እንድንለምን እና እንድንመክር ነው። መልእክቱ ትክክል መሆኑ ብቻ በቂ አይደለም፤ በዚያ መልእክት *ውስጥ* በእወጀው ውስጥ መላውን ማንነታችንን በማዋል ልንገኝ ይገባናል።

ዛሬ ላይ በርካቶቹ ስብከቶች እንደ ቀብር ደወሎች አሰልቺዎች ናቸው። ይዘቱ አጥጋቢ ነው፣ ነገር ግን የሰባኪው ልብ መቼም አይታይም። እንዲህ ያሉ ሰባኪዎች ሐሰተኛ ስለሆነ እሳት ወይም ስለ አከራሪነት የሚከሰሱበት ምንም ዓይነት ስጋት የለባቸውም። ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ የትኛውም ዓይነት ወላፈን በውስጣቸው እየተቃጠለ ለመሆኑ ምንም ማስረጃ አለመኖሩ ነው። የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ስብከት ቅናት እና ጥልቅ ስሜት የታለ? የነብያት እና ሐዋርያት ለቅሶ የታለ? ምን ያክሎቹ ዘመናዊ ሰባኪዎች የምራቸውን ‘ሦስት ዓመት ሌሊትና ቀን በእንባ እያንዳንዳችሁን ከመገሠጽ እንዳላቋረጥሁ እያሰባችሁ ትጉ’ ማለት ይችላሉ (ሐዋ. 20፡31)?

በዚህ የሃያ አንደኛው ክፍለ-ዘመን ላይ አቶ አማካኝ ወንጌላውያን ሲሰብኩ ለመስማት እንሂድ። የሚነዳው የሚመስለው ነገር ሕያው የሆነው እግዚአብሔር በመለወጣቸው እና በመንፈሳዊ እድገታቸው ውስጥ ሲከብር ለማየት ከመፈለግ ይልቅ ሰሚዎቹ እንደተሳቡበት እንዲቆዩ የማድረግ መሻቱ ነው። ለግማሽ ሰዓት ያክል ይሰሙት ዘንድ በጣም የሚያስደስት በሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልእክት ላይ ይወራጫል። ነገር ግን የዛምንቱ በጣም የማይረሳ ክስተት በመሆን ሊገለጽ አይችልም! የትኛውንም ሰው አያናውጥም፣ ወይም አያስፈነድቃቸውም። ስለ ስብከቱ ልትሉት የምትችሉት ጠቅላላ ነገር ቢኖር ‘ጥሩ ነው’ የሚለውን ብቻ ነው። የማንም ሰው ጎሊና አልተናወጠም፣ ማንም ሰው

በደስታ ሊያለቅስ አልፈለገም። ከዚህኛው የእግዚብሔር እውነት ማብራሪያ ይልቅ በርካቶቹ የዚህ ሳምንት የቴሌቪዥን ዝግጅቶች በማይቆጠር ሁኔታ የበለጠ የሚታወሱ ሆነዋል!

እንዴት የሚያሳፍር ነገር ነው! የምንሰብክ ሰዎች እግዚአብሔርን ልንፈልግ እና የነነነ ህገወጥነታችንን ለእርሱ ልንናዘዝ ይገባናል። ታላላቅ አሳቦች አእምሯችንን ሙሉ ለሙሉ አያሳትፉም። *ጸውነትን* አሁንም አሁንም መስበክ የምንችለው ቀዝቃዛ እና ደካማ በሆነ መንገድ ነው። የጠፉ ሰዎችን ዓይኖቻቸውን እያየን ሳንለምናቸው ወይም ራሳችንን ዘላቂ ለሆነ ማሳመኛ ሳንሰጥ እንተዋቸዋለን። መላው ልባችን ሁልጊዜ በምንለው ነገር ሁሉ ላይ አይደለም። ኮስታሮች ሳንሆን፣ አንዳንድ ጊዜ እንደውም ቀላል ሆነን እንመጣለን። ሰሚዎቻችን ተቸግረዋል። የጥንቱ ሰባኪ ትክክለኛውን ነገር እንደሚያደርግ ልናምን ይገባናል፡ 'አሁን ድረስ በአግዳሚ ወንበሩ ላይ ብዙዎች መኖራቸው በምስባኩ ላይ ብዙ ጠጣር ልብ ያላቸው ስለበዙ ነው።' ልክ እንደ እኛ ላሉ ሰዎች በክርስቶስ ይቅርታ መኖሩ እግዚአብሔር ይመስገን!

ልዕለ-ተፈጥሯዊ ሥልጣን

ልዕለ-ተፈጥሯዊ ሥልጣን የሚለማመዱት ሰባኪዎች በአንድ ነጠላ የሚያምኑበት ነገር ላይ የተካኑ ሰዎች ናቸው። አንድን ሰው ይህ በሚይዘው እና እና መላውን አገልግሎቱን በሚገዛ ጊዜ፣ የዚህን ክብር የሞላበት በረከት ማወቅ አያቅተውም። እና ያ የሚያምንበት ነገር ምንድነው? *እየሰበክሁ ያለሁት መልእክት በእግዚአብሔር መንፈስ የታጀበ እሰካልሆነ ድረስ ለየትኛውም ሰው ምንም ኣይጠቅምም* የሚለው ነው።

እግዚአብሔር እስካልባረከው ድረስ የትኛውም መልእክት የትኛውንም ነገር ሊያሳካ አይችልም። ዘሩን ልንዘራ እንችላለን፣ ውሃ ልናጠጣውም እንችላለን፣ ነገር ግን ሕይወት ሊሰጠው የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው (1 ቆሮ. 3፡6)። በታማኝነት ከሰበክን፣ ነገር ግን የትኛውንም የዳነ ሰው ካላየን፣ ማብራሪያው ምንድነው? ቃሉን ብንከፍት፣ ነገር ግን አማኞች በመልእክታችን ሥር-ነቀል ለውጥ ሲያገኙ ካላየን፣ እንዴት እንመሰክርለታለን? መልሱ

እግዚአብሔር ሁልጊዜ ኃይሉን መልሷል። እርሱ ብቻ ሊያደርግ የሚችለውን ነገር አላደረገም።

የእግዚአብሔር መንፈስ በሥራ ላይ ባልሆነበት የትኛውም መንፈሳዊ ሥራ ሊሠራ አይችልም። ራሱ እግዚአብሔር በዚያ ውስጥ አልፎ ካልሠራ በቀር ስብከት ሁልጊዜም አይሳካም። ኢሳይያስ ይህንን ተገንዝቧል፦ 'የሰማነውን ነገር ማን አምኖአል? የእግዚአብሔርስ ክንድ ለማን ተገልጦአል?' (ኢሳ.53፡1)። የእርሱ ሁለቱ ጥያቄዎች በመሠረቱ አንድ ናቸው፣ ደግሞም ሁለተኛው ለመጀመሪያው መልሱን የያዘ ነው - የትኛውም ሰው የሚያምን ከሆነ፣ የጌታ ክንድ ለእርሱ ተገልጣለች፤ ነገር ግን አንድ ሰው *ካላመነ*፣ የጌታ ክንድ *ሰላልተገለጠችለት* ነው። እግዚአብሔር በኃያል ጉልበቱ ልባቸውን ካልነካ በስተቀር ማንም ሰው ሊያምን አይችልም። የተዓምራት መታየት እንኳን ወደዚያ ነጥብ ሊያመጣቸው አይችልም (ዩሐ. 12፡37-38 ተመልከቱ)። *በውሰጣቸው* አንድ ነገር ሊገባ ይገባል፣ ያ ደግሞ እግዚአብሔር ብቻ ሊያደርገው የሚችለው ነገር ነው።

ጌታችን ራሱ ይህንን ትምህርት በተቻለ መጠን ግልጽ አድርጎ አስተምሮታል። በርካታ የሚሆኑት ደቀመዛሙርቱ ሊቀበሉት ያልወደዱት ትምህርት ነበር፣ ደግሞም ከሰሙበት ቅጽበት ጀምሮ ጀርባቸውን አዙረውበታል (ዩሐ. 6፡66)። ትምህርቱን የተቀበሉት ሰዎች ከእርሱ ጋር ቀጠሉ። የክርስቲያን አገልግሎትን በጣም መሠረታዊ የሆነ ሚስጢር ተማሩ። የጌታችንን ትክክለኛ ቃሎች 'የላከኝ አብ ከሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ። ደግሞ። ስለዚህ አልኋችሁ፥ ከአብ የተሰጠው ካልሆነ ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም አለ።' (ዮሐ.6፡44፣ 65)። ራሱ እግዚአብሔር በሥራ ላይ ካልሆነ፣ አንድን ሰው እንኳን ወደ ክርስቶስ ሊያመጣ የሚችል እኛ ማድረግ የምንችለው አንድም ነገር አይኖርም። በምንሰብክ ጊዜ የእርሱን በረከት ልናገኝ ይገባናል!

ሪቻርድ ሲሲል ይህንን ትምህርት የተማረው በአገልግሎቱ ጅማሬ ላይ የነበረ ሲሆን እንግሊዝ ውስጥ የዐሥራ ስምንተኛው ክፍለ-ዘመን በጣም ኃይለኛ ከሆኑ ወንጌላዊያን አንቂ ሰባኪዎች አንዱ ሆኖ ነበር። የእርሱ ምስክርነት ይኸውላችሁ፦

በአንድ ወቅት በልቤ ጅልነት ለራሴ እንዲህ አልኩኝ ‘ሦስት ሺህ ነፍሳት በአንድ ጊዜ ወደ ጌታ የመጡበት የቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት ምን ዓይነት ስብከት ቢሆን ነው!’ ምን ዓይነት ስብከት ነው! እንደ ሌሎች ዓይነት ስብከቶች። በውስጡ ያልተለመደ የሆነ ነገር አይገኝም። ውጤቱ የተገኘው ከአንደበተ-ርቱእነቱ አይደለም፣ ነገር ግን በቃሉ ውስጥ ከነበረው የእግዚአብሔር ኃይል መገኘት የተነሣ ነው። መንፈስ ቅዱስ ቃሉን እንዲያጅብ ካልጸለይን በስተቀር አንድ አገልጋይ ከሌላው ቀጥሎ መምጣቱ እና ስብከት በስብከት ላይ መደራረቡ በከንቱ ነው።[15]

እግዚአብሔር ጉዳዩን ለማስኬድ ሰዎችን ይጠቀማል፣ ስለዚህም ሁሉም ግስጋሴ ሊሰጥ የሚገባው ለእግዚአብሔር ነው። በሥሪያ አንጾዮክያ መጀመሪያ የመሰከሩት ሰዎች ስኬት የነበራቸው እንዴት ነበር? ‘የጌታም እጅ ከእነርሱ ጋር ነበረ፤ ቍጥራቸውም እጅግ የሚሆን ሰዎች አምነው ወደ ጌታ ዘወር አሉ’ (ሐዋ.11:21)። በፊሊጵስዩስ የወንዝ ዳር የጸሎት ስብሰባ ላይ ብቸኛዋ ወደ ጌታ የመጣች ሴት ሊድያ ብቻ የሆነችው ለምን ነበር? ‘ጳውሎስ ይናገረው የነበረውን ነገር ታስተውል ዘንድ ጌታ ልቧን ስለከፈተላት’ ነው (ሐዋ. 16:14)። በተሰሎንቄ ያሉ አይሁድ እና በብዙ የሚቆጠሩ አረማዊያን በፍጥነት ወደ ጌታ መምጣታቸውን ልናስረዳ የምንችለው እንዴት ነው?

> ወንጌላችን በኃይልና በመንፈስ ቅዱስ በብዙ መረዳትም እንጂ በቃል ብቻ ወደ እናንተ አልመጣምና፤ በእናንተ ዘንድ ስለ እናንተ እንዴት እንደ ነበርን ታውቃላችሁ። ስለዚህም የመልእክትን ቃል እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ከእኛ በተቀበላችሁ ጊዜ፥ በእውነት እንዳለ በእናንተ በምታምኑ ደግሞ እንደሚሠራ እንደ እግዚአብሔር ቃል እንጂ እንደ ሰው ቃል አድርጋችሁ ስላልተቀበላችሁት፥ እኛ ደግሞ እግዚአብሔርን ሳናቋርጥ እናመሰግናለን።
>
> (1 ተሰሎንቄ 1:5፣ 2:13)

[15] በብሪጅ ቻርለስ *ዚ ክርስቲያን ሚኒስትሪ* (ለንደን፣ ዚ ባነር ኦቭ ትሩዝ ትረስት፣ 1958) ገጽ 79 ውስጥ የተጠቀ

ለእግዚአብሔር ሁሉ ይቻለዋል። ያለ እርሱ ምንም ነገር አይቻልም። የሁለት ሺህ ዓመታት የቤተክርስቲያን ታሪክ የሚገልጠው ነገር በከፍተኛ ሁኔታ ተሰጥዖው ያለው ወይም በዘዴ ደረጃ የተዋጣለት ሰባኪ መሆን ብቻውን በቂ እንዳልሆነ፣ ይሁን እንጂ ተሰጥዖም ሆነ ብርቱ ሥራ ሊናቀኑ እንደማይገባ ነው። መልካም ተሰጥዖ ያላቸው በርካቶቹ ሰዎች መላውን ማኅበረሰብ እንዲሁም አንዳንድ ጊዜ ሕዝቦችን ለመለወጥ እግዚአብሔር ተጠቅሞባቸዋል።

አንዳንድ ጊዜ ብዙ ሙግቶች ሳይሳካላቸው ቀርቶ አንድ ነጠላ ዐረፍተ-ነገር የወንጌል ጠላቶችን የሚያሸንፍበት ጊዜ አለ። አንዳንድ ጊዜ ቃሉ የሚመጣው ከኃይል ጋር ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አይደለም። እንግዲያው በስብከት ውስጥ በዝግጅታችን እና አቀራረባችን ጥራት ላይ ልንታመን አይገባንም። ይሁን እንጂ፣ እንዚህ ነገሮች ጠቃሚዎች ናቸው። ልንታመን የሚገባን በእግዚአብሔር ላይ ብቻ ነው፣ ደግሞም በእርሱ ላይ መታመናችንን የሚቀንስ የትኛውንም አካሄድ ልንከተል አይገባንም።

ጳውሎስ በቆሮንቶስ የነበረውን አገልግሎቱን ሲያስረዳ ትክክለኛውን አካሄድ እንደሚከተለው ሰጥቶናል፡-

> እኔም፥ ወንድሞች ሆይ፥ ወደ እናንተ በመጣሁ ጊዜ በቃልና በጥበብ ብልጫ ለእግዚአብሔር ምስክርነቴን ለእናንተ እየነገርሁ አልመጣሁም። በመካከላችሁ ሳለሁ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር እርሱም እንደተሰቀለ ሌላ ነገር እንዳላውቅ ቆርጬ ነበርና። እኔም በድካምና በፍርሃት በብዙ መንቀጥቀጥም በእናንተ ዘንድ ነበርሁ፤ እምነታችሁም በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ጥበብ እንዳይሆን፥ ቃሌም ስብከቴም መንፈስንና ኃይልን በመግለጥ ነበረ እንጂ፥ በሚያባብል በጥበብ ቃል አልነበረም።
>
> (1 ቆሮንቶስ 2፡1-5)

ቅብአ-ቅዱስ

በ1961 ዓ.ም. ጀምሮ በዓመት ቢያንስ አንድ ጊዜ የማነብባትን ትንሽ መጽሐፍ አገኘሁ። መጽሐፏ *ፓወር ሰሩ ፕሬየር* የምትባል በኢ. ኤም ባውንድስ የተጻፈች ነበረች።[16] ከመጽሐፍ ቅዱስ እና ከዌስትሚኒስተር አጭሩ የእምነት መግለጫ ቀጥሎ፣ ይህ መጽሐፍ ከሌሎች ካነበብኳቸው መጽሐፍት በላይ በእኔ ላይ ብዙ ተጽዕኖ አለው ማለት እችላለሁ። መጽሐፉን በማነብበት ጊዜ 'ከሰማያት ጠል በታች' የሚል ምእራፍ ወዳለው ምእራፍ ደረስኩ። በዚያ የተወሳሰበብኝን ሚስጢራዊ ነገር አነበብኩኝ። ከተሞክሮዬ በላይ የሆኑ ነገሮች ነበሩ። ጸሐፊው እየተናገረ የነበረውን ነገር መረዳት አልቻልኩም። ጥቂት ምሳሌዎች እነኋችሁ፡-

> ቅብአ-ቅዱስ ፍቺ ሊቀመጥለት የማይችል፣ ማስረዳት የማይቻል፣ ነገር ግን የታወቀ አዛውንት የስኮትላንድ ሰባኪ እንዲህ ብሎ ያስረዳው ነገር ነው፡- 'አንዳንድ ጊዜ በስብከት ውስጥ በሁኔታ ወይም በመግለጫ ማስረዳት የማይቻል ነገር አለ፣ ደግሞም ምን እንደሆነ ማስረዳት የሚከብድ፣ ወይም ከየት እንደመጣ የማይገለጽ፣ ነገር ግን ጣፋጭ በሆነ አመጽ ልብን ሰርጾ የሚገባ እና ፍቅር የሚያስይዝ፣ ደግሞም ወዲያውኑ ከጌታ የሚመጣ ነገር ነው፣ ነገር ግን እንዲህ ያለውን ነገር ለማግኘት የትኛውም ዓይነት መንገድ ቢኖር ሰባኪው ለሰማያት ባለው ተጋላጭነት የሚሆን ነገር ነው' . . .
>
> ይህ መለኮታዊ ቅብአ-ቅዱስ እውነተኛውን የወንጌል ስብከት ከሌሎቹ ሁሉ እውነት ከሚሰበክባቸው ዘዴዎች የሚለይ እና የሚነጥል ገጽታ ሲሆን ሰፊ የሆነ መንፈሳዊ የሃሳብ ልዩነትን በሰበከው ሰባኪ እና ባልሰበከው መካከል የሚፈጥር ነገር ነው። የተገለጠው እውነት በእግዚአብሔር ኃይል የሚፀንስ እንዲሆን ይደግፋል። ቅብአ-ቅዱስ እግዚአብሔርን በገዛ ራሱ ቃል እና በሰባኪው . . . መያዝ ነው። ማተለቅ፣ ነፃነት፣ የአሳብ ሙልአት፣

[16] ባውንድስ፣ ኢ. ኤም. *ፓወር ሰሩ ፕሬየር*፣ ዎርልድ-ዋይድ ሰርኩሌሽን ኤድሽን (ለንደን ማርሻል፣ ሞርጋን ኤንድ ስኮት፣ ቀን የሌለው) የተጠቀሱት በሙሉ ከምእራፍ 10 ገጽ 43 ጀምሮ ነው

የንግግር ቀጥተኝነት እና ቀላልነት የዚህ ቅብአ-ቅዱስ ፍሬዎች ናቸው. . .

ይህ ቅብአ-ቅዱስ ሰባኪው የስብከትን ቋንቋ እና የማዳን ጫፎችን የሚያሳካበት መለኮታዊ ማስቻያ ነው። ያለዚህ ቅብአ-ቅዱስ ምንም የሚሳካ መንፈሳዊ ውጤቶች የሉም፤ ውጤቶቹ እና በስብከት ውስጥ ያሉት ኃይላት አጥጋቢ ካልሆነ ንግግር ውጤቶች በላይ ሊነሡ አይችሉም። ያለ ቅብአ-ቅዱስ የቀደመው የምስባኩን ያክል የበቃ ነው. . .

የዚህ ቅብአ-ቅዱስ በሰባኪው ላይ *መገኘት* ንቅናቄውን እና በበርካታ ጉባዔ ላይ ሰበቃውን ይፈጥራል። በፊደላቱ ጥብቅነትም ላይ ተመሳሳይ እውነታዎች ተነግረዋል፣ ነገር ግን የትኛውም መበታተን አልታየም፣ ምንም ህመም የለም ወይም የሚሰማ ርግብግቦሽ የለም። የመቃብር ያክል ሁሉም ጸጥ ብለዋል። ሌላኛው ሰባኪ *መጣ*፣ ደግሞም ይኼኛው ሚስጢራዊ ተጽዕኖ በእርሱ ላይ ነበር፡ የቃሉ ፊደል በመንፈስ ቅዱስ የተቀጣጠለ ሆኗል፣ የኃይለኛ እንቅስቃሴ ስቃይ ይሰማል፣ የሚስፋፋው ቅብአ-ቅዱሱ ሲሆን ኅሊናን ያናውጣል፣ ልብንም ይሰብራል። ቅብአ-ቅዱስ የሌለው ስብከት ሁሉንም ነገር ከባድ፣ ደረቅ፣ ጠጣር፣ እና ሙት ያደርገዋል።

ቅብአ-ቅዱስ? ዶ/ር ባውንድስ እየተናገሩበት የነበረውን ነገር ለመግለጽ ትክክለኛ ቃል ስለመሆኑ ዛሬ ላይም ቢሆን እኔ አላመንኩበትም። ነገር ግን እየተናገሩ የነበረው *ምን ነበር*? የእኔ ጥያቄ ያ ነበር። በሕይወቴ በዚያኛው እርከን ላይ በገዛ ሕይወቴ ወይም በሌላ ሰው ሕይወት ውስጥ የዚህ ነገር ምንም ተሞክሮ አልነበረኝም። ደራሲው በአእምሯቸው የነበረውን በተመለከተ ምንም ነገር መገመት አልቻልኩም።

በቀጣዩ አመት የጸደይ ወቀት ላይ ነገሮች በፍጥነት እየተቀየሩ እንደሆነ ሲሰማኝ አወቅሁ። በጊዜው ተማሪ ነበርኩኝና እናቴ ስልክ ደውላ ወደ አገሬ መመለስ እችል እንደሆነ ጠየቀችኝ። እንድተዋወቀው የምትፈልገው ሰው ነበሩ። እርሳቸው በስድሳዎቹ እድሜ አጋማሽ ያሉ እና በአንድ ወቅት የድንጋይ ከሰል ማእድን አውጪ የነበሩ፣ አሁን ግን ከሃያ አምስት ዓመታት በላይ አገልግሎት ላይ

ያሉ ሰው ነበሩ። በመንደራችን ውስጥ በሣምንቱ ስብሰባዎች ይሰብኩ ነበር፤ ደግሞም እናቴ በቃላት ልትገልጸው ያልቻለችው አንድ ነገር ነበር። ለራሴ ብሰማቸው ልገነዘበው እችል ነበር። ልትነግረኝ የቻለችው ነገር ቢኖር አስደናቂ እንደሆነ ብቻ ነበር።

ወደ አገሬ መመለስ ለእኔ ከባድ ነበረና ሒዌል ግሪፊትስ ሲሰብኩ ከመስማቴ በፊት ሌላ አንድ ዓመት መጠበቅ ነበረብኝ። በኮሼስተን ሚሽን ቤተክርስቲያን አግዳሚ ላይ እንደተቀመጥኩ፣ በመጨረሻ 'ቅብአ-ቅዱስ' ምን እንደሆነ ተገነዘብኩ። የሰባኪው ስብከት በጣም ረጅም ነበር፣ በምስለ-ቃላት የተሞላ እና ግልጽ በሆነ ፍቅር እና ጥልቅ ስሜት የተላለፈ ነበር። ነገር ግን ሌላም ነገር ነበረው። ሊነገር በማይችል ተጽዕኖ የታጀበ ነበር። ሒዌል ግሪፍትስ ሲሰብኩ፣ ሰማያት ወደ ምድር ይመጣሉ። የማይታየው ዓለም ከሚታየው ይልቅ የበለጠ እውነተኛ ሆኖ ነበር። የክብር ንክኪ ነበረ። ክርስቶስ በአጥናፈ-አለሙ ውስጥ ከየትኛውም ነገር ወይም ከየትኛውም ሰው በላይ ውድ ነበር። ቃሉ የመጣው ራሱን እውነተኛ በሚያደርግ ሊቋቋሙት በማይችል ኃይል ነበር። ማስረዳት በማይቻል መልኩ ሞኝነት ስለሚሆን አለማመን ምርጫ አልነበረም። ብቸኛው ብልኅ የሆነው ነገር ጌታን ሙሉ ለሙሉ መታመን፣ እና እርሱንም በሙሉ ልብ፣ ነፍስ፣ አሳብ እና ኃይል መውደድ ነው።

እነዚህን አስደናቂ አሳቦች ስቀበል ብቸኛው አልነበርኩም። ከእያንዳንዱ ስብከት በኋላ ጉባዔው አስደናቂ በሆነ ጸጥታ ይቀመጥና፣ በቃሉ ፍጹም ኃይል ይሸነፍ ነበር። አንዳንድ ጊዜ ድንገተኛ ከሆነው ጸሎት የሚከተለው ነገር ጸጥታ ነበር። አንዳንዶች ወደ ክርስቶስ መጥተዋል። በርካታ ሌሎች ልክ እንደኔ አማኝ የነበሩ፣ ለዘላለም ተለውጠዋል። በመነቃቃቱ የሆነውን ነገር በትንሽ ጣዕም ተለማምደነዋል፣ ደግሞም 'ቅብአ-ቅዱስ' ምን እንደሆነ ሁላችንም አውቀናል። ኢ. ኤም. ባውንድን እየጻፉለት የነበረውን ነገር ለመገንዘብ የትኛውም ችግር የለብኝም!

> ቅብአ-ቅዱስ፣ መለኮታዊ ቅብአ-ቅዱስ ይህ ሰማያዊ ቅባት ምስባክ የሚያስፈልገው እና ሊኖረው የሚገባው ነገር ነው። ይህ መለኮታዊ እና ሰማያዊ ዘይት በእግዚአብሔር እጅ መቄን መላውን ሰው - ልቡን፣ ራሱን፣ መንፈሱን ከመላው ምድራዊ፣ ዓለማዊ፣ ሥጋዊ፣ ራስ ወዳድ ተነሣሥቶቶች እና ዓላማዎ ወደ

መላው ንፁህ እና እግዚአብሔርን መምሰል ወዳለበት እስኪለየው ድረስ ሊያለሰልሰው እና በቅባት ሊያርሰው ይገባል።

ቅብአ-ቅዱስን ማግኘት

እሺ ቅብአ-ቅዱስ የሚገኘው እንዴት ነው? መልሱን ከንባቤ ብቻ ሳይሆን ከገዛ ራሴ ተሞክሮ ጭምር የማውቀው መሆኔን ስነግራችሁ ደስ እያለኝ ነው። የእግዚአብሔርን መንፈስ ልናዝዘው አንችልም። የሰማዩ ነፋስ ወደ ወደደው ይነፍሳል (ዩሐ. 3፡8)። የት እንደነበረ ወይም ቀጥሎ የት እንደሚሄድ ልናውቅ እንኳን አንችልም። ምንም ቢሆን ምን በእርሱ ላይ የመቆጣጠር ብቃት የለንም። እግዚአብሔር እግዚአብሔር ነው ደግሞም ያስደሰተውን ያደርጋል (መዝ. 115፡3፣ 135፡6)። የሰውን ፈቃድ ለማድረግ ራሱን አያስርም።

ደግሞም እግዚአብሔር ጸሎትን ይመልሳል። በእርግጥ ይመልሳል! ይህንን የሚአደርገው ያንን ለማድረግ ቃል ስለገባ ነው። 'አምናችሁም በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ ትቀበላላችሁ' (ማቴ. 21፡22) ያለው ላመኑ ኃጢአተኞች ነው። በጸሎት ውስጥ ብርቱ የሆኑ መሞገቻዎችን ያኖረው በዳኑ ኃጢአተኞች እጆች ውስጥ ነው፡- 'እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠትን ካወቃችሁ፥ በሰማያት ያለው አባታችሁ ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መልካም ነገርን ይሰጣቸው?' (ማቴ. 7፡11)። ልጁ ያልተለመደ የሆነውን ግብጣ የሰጠው ለዳኑ ኃጢአተኞች ነው 'እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና፤ አብም ስለ ወልድ እንዲከበር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ። ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ።' (ዩሐ. 14፡13-14)። ደግሞም እነዚህ ጥቅሶች ናሙናዎች ብቻ ናቸው። ተመሳሳይ የሆኑ በመላው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ተስፋ ቃሎች በብዛት እንደሚገኙ ሁላችንም እናውቃለን።

መንፈስ ቅዱስን ከሚያሳዝነው የትኛውም የሕይወቱ ነገር እያንዳንዱ አማኝ፣ እንዲሁም የትኛውም ሰባኪ እንዲወጣ ግዴታው ነው (ኤፌ. 4፡30)። ክርስቶስን እንድናውጅ፣ መንፈስ እርሱን ሊያከብረው እንደሚወድድ በማወቅ እና ከዚያም የተነሣ እንዲያ ያለውን ስብከት እንደሚባርክ ማወጅ የክርስቲያን ሰባኪዎች ጥሪ ነው (ዩሐ. 16፡14)። ነገር ግን ሰባኪው ቅድሚያ የሚሰጠው ነገር እንዲሆን ሐዋርያት በክርስቲያኗ ቤተክርስቲያን የጨቅላነት ወቅት ያወጡት ነገር የሚከተለውን ነው፡- 'እኛ ግን ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን።' (ሐዋ. 6፡4) በዚያ ቅደም ተከተል!

እግዚአብሔርን ድል መንሣት የሚባል እንዲህ ያለ ነገር አለ። በጸሎት ከመድከም እና ከዚያም የተነሣ በምትሰብኩበት ጊዜ በልእለ-ተፈጥሯዊ ሁኔታ የሚያጅባችሁን ግላዊ ማረጋገጫ ከእርሱ እስክትቀበሉ ድረስ እግዚአብሔርን በሚስጢራዊው ቦታ መያዝ ይቻላል። በልባችሁ ጌታ ራሱ ቀጣዩን መልእክታችሁን እንደሚባርክ እና በምትሰብኩም ጊዜ በአስደናቂ ሁኔታ እንደሚያጅባችሁ እርግጠኛ ሆናችሁ በሰላም እና ድክም ብሏችሁ የጸሎት ቦታችሁን እስክትሰናበቱ ድረስ መታገል እና መጥመልመል ይቻላል። ይህ ማለት የእግዚአብሔርን በረከት *ማግኘት* ይቻላል ማለት አይደለም። ብድራታችንን እንዲመልስ የሚገደድበት ለእርሱ ልንሰጠው የምንችለው የትኛውም ዓይነት *ሥራዎች* አሉ ማለት አይደለም። ያ ማለት በእርሱ ጸጋ በሚወተውት ጸሎት ድል እንድንነሣው ለራሱ ፈቅዷል ማለት ነው።

ያንን ታምናላችሁ? አንድ ሰው ለእግዚአብሔር ‘ሊነጋ አቀላልቶአልና ልቀቀኝ። እርሱም። ካልባረከኸኝ አልለቅህም አለው።’ ማለት እንደሚችል ታምናላችሁ (ዘፍ. 32:26)። እንዲህ ላለው ሰው ጌታ ‘በዚያ ባረከው’ ሊባልለት እንደሚችል ታምናላችሁ (ዘፍ. 32፡29)? ካላመናችሁ፣ እንደ ጆን ክሪሶስቶም፣ ማርቲን ሉተር፣ ጆን ዌስሊ፣ ጆናታን ኤድዋርድስ፣ ዳንኤል ሮውላንድ፣ ጆን ኤሊያስ፣ ሲ. ኤች. ስፐርጅን፣ ሒዌል ግሪፊትስ፣ ዲ. ማርቲን ሎይድ-ጆንስ እና ኸግ ሞርጋን ያሉ ሰዎችን አገልግሎት እንዴት ትረዳላችሁ? እነዚህ ሰዎች አንዳቸው ከሌላቸው በጣም የተለዩ ነበሩ ደግሞም በእያንዳንዱ የተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ሰብከዋል፣ እናስ የጋራ የሚሆናቸው ነገር ምን አለ? በእግዚአብሔር የታመኑ እና ሙሉ ለሙሉ በእርሱ የታመኑ ናቸው። ስለዚህ እርሱን ለመፈለግ ራሳቸውን አኑረዋል፣ እርሱን ለመግኘት፣ እርሱን ለማወቅ፣ እርሱን ድል ለመንሣት፣ እና በረከቶቹን ለመለማመድ። እነርሱ በግንባር-ቀደምትነት ሰባኪዎች አይደሉም፤ እነርሱ የጸሎት ሰዎች ነበሩ። ደግሞም እንደተለመደው በጸለዩባቸው አጋጣሚዎች፣ እግዚአብሔር በረከቱን የሸሸገ ሲመስል ‘አዎን፥ አባት ሆይ፥ ፈቃድህ በፊትህ እንዲህ ሆኖአልና’ (ማቴ. ፲፩:26) ብለው ለማንሾካሾክ የበቁ ደስተኞች ነበሩ።

ኢ.ኤም. ባውንድስ የሚከተለው ገብቷቸዋል፡-

ይህ ቅብአ-ቅዱስ እንዴት እና ከየት መጣ? የጸሎት መልስ በመሆን በቀጥታ ከእግዚአብሔር መጣ። የሚጸልዩ ልቦች ብቻ በዚህ ቅዱስ ቅባት ይሞላሉ፤ የሚጸልዩ ከናፍርት ብቻ በዚህ መለኮታዊ ቅብአ-ቅዱስ ይቀባሉ።

ጸሎት፣ ብዙ ጸሎት የስብከት ቅብአ-ቅዱስ ዋጋ ነው፤ ጸሎት፣ ብዙ ጸሎት ይህንን ቅብአ-ቅዱስ የምንጠብቅበት ብቸኛውና አንዱ ሁኔታ ነው። የማያቋርጥ ጸሎት ሳይኖር ቅብአ-ቅዱስ ወደ ሰባኪው አይመጣም። በጸሎት ሳይጸኑ እንደ መና የሚያቆዩት ቅብአ-ቅዱስ ትል ያፈራል።

* * *

የዚህ መጠነኛ መጽሐፍ ዋናው ክፍል አሁን ወደ ማብቂያው መጥቷል። ስብከት ምን እንደሆነ እና መሠረታዊ ንጥረ-ነገሮቹ ምን እንደሆነ ላሳያችሁ ሞክሬያለሁ። እስካሁን ድረስ ስላነበባችሁ ላመሰግናችሁ እወዳለሁ። የቀረውንም እንድታነብቡ ላበረታታችሁ ጭምር እፈልጋለሁ።

ያልኩት ነገር ሁሉ ጠቃሚ እንደሆነ አምናለሁ። ከምእራፎቹ የትኛቸውም ተጥለው እንደሆን፣ ይህ መጽሐፍ ጉድለት ያለበት እና ሚዛናዊ ያልሆነ እንደሚሆን አምናለሁ። ነገር ግን በዚህ ሰዓት የትኞቹ ምእራፎች የተለየ ጠቀሜታ እንዳላቸው እንደማስብ እንድነግራችሁ ከተጫናችሁኝ፣ ያለ ጥርጥር የምጠቀሥማችሁ ምእራፎች ሥነ-ፍታቴያዊ ትክክለኝነት እና መለኮታዊ ሥልጣን ላይ የተጻፉት ምእራፎችን ነው። ይህ የሚሆንበት ምክንያት ሁለቱም ቃል እና መንፈስ የሚያስፈልጉ ከመሆናቸው የተነሣ ነው።

እኔ 62 ዓመቴ ነው፣ ደግሞም ገና ጥቂት የአገልግሎት አመታትን እንደሚሰጠኝ አምናለሁ። ይህ ሊሆን እንደሚችለው ቢሆንም፣ ከጅማሬው ይልቅ ወደ ሕይወቴ ፍጻሜ እንደቀረብኩ አስተውላለሁ። እንግዲያው የእኔ የተለየ ጸሎት በቡድን ያሉ ወጣቶች በሙሉከዘህ መጽሐፍ የተለየ እገዛ እንዲአገኙ እና እያለ ላለው ነገር ራሳቸውን ቢያንስ እንደ ቃሉ እያለ ላለው ነገር እንዲሰጡ ነው። ደግሞም አገልግሎታቸው ለመላው ዓለም በረከት ይሁን!

ተሰጥዖዎቼ፣ ሥጦታዎቼ እና
ጸጋዎች፣ ጌታዬ

ከአንተ እጅ
እንደተቀበልኳቸው፤

የአንተኑ ቃል እየሰበክሁ
እንድኖረው

ደግሞም ለአንተ ክብር
እንድኖረው

እያንዳንዱ የምኖርበት
የተቀደሰ ቅጽበት

የኃጢአተኞችን ወዳጅ
አጉልቼ ላሳይበት።

ቻርለስ ዌስሊ፣ 17-7-88

* * *

የምታደርጓቸው ነገሮች

1. የሚጮኽ ሰባኪ እንደሆናችሁ በጥልቀት ተሰማችሁ። እድለኞች ሆናችሁ ሚስታችሁ ሰለጉዳዩ ነገረቻችሁ። ምን ታደርጋላችሁ?

2. ወንጌላዊያን በታሪክ ውስጥ ‘ቅብአ-ቅዱስ’ ሲሉ ምን ማለታቸው እንደሆነ ለመስማት ፍላጎት ላደረበት ወጣት ክርስቲያን አብራሩለት።

3. በጸሎት እና ‘በቅብአ-ቅዱስ’ መካከል ያለውን ግንኙነት አስሱ።

ክፍል ሦስት

1.

ጥቆማ የተሰጠበት የስብከት አዘገጃጀት ዘዴ

2.

በፍቅር የሚታወስ፦
ኸግ ዴቪድ ሞርጋን
(1928-1992)

1

ጥቆማ የተሰጠበት
የስብከት አዘገጃጀት ዘዴ

ብከቶች ሲሰበኩ ይገባል። ‘ወደ ምስባክ በተለመደ መልኩ ሳይዘጋጁ መምጣት ይቅርታ የማይደረግለት ድፍረት ነው’ ሲሉ ሲ.ኤች. ስፐርጀን (ስፐርጀን ሲ.ኤች. *ሌክቸርስ ቱ ማይ ስቱደንትስ፤* ሁለተኛው ቅጽ (ለንደን፣ ፓስሞር ኤንድ አላባስተር፣ 1882) ገጽ 4። ተናግረዋል። ጆን ስቶት ሌላ ነጥብን ያስታውሱናል ‘ትውልዳቸው ላይ ተጽዕኖ ያሳደሩ ታላላቅ ሰባኪዎች ሁሉ በንቀኑ ኅሊና ሊደረግ ስለሚገባው ዝግጅት ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል።’ (ስቶት፣ ጆን አር. ደብልዩ፣ *ኣይ ቢሊቭ ኢን ፕሪቺንግ* (ሎንዶን፣ ሖደር ኤንድ ስቶግተን፣ 1982)፣ ገጽ 212።)

ስብከት የሞቱትን ለማንቃት እና ሕይወትን ለመገንባት እግዚአብሔር የሚጠቀምበት መንገድ ነው። ያንን የምናምን ከሆንን፣ በጸሎት፣ የምር በመሆን እና በአጥኚነት ካልሆነ በቀር በሌላ በማንኛውም መንገድ ልንቀርበው አንደፍርም። የስብከት *ሥጦታችን* የሚመጣው ከእግዚአብሔር ነው፤ የዚያ ስጦታ *መዳበር* የእኛ ኃላፊነት ነው።

የህግ ባለሙያው የሚከራከርለትን የህግ ጉዳይ በጥንቃቄ ያዘጋጃል፤ የሥነ-ሕንጻ ዲዛይን ባለሙያው እቅዶቹን ይነድፋል፤ ሐኪሙ የሕክምና ጉዳዩን እና ሕመምተኛውን ያጠናል። እንዲሁም እኔም የወንጌል ሰባኪው *በዓለም ላይ በእጅጉ ጠቃሚ የሆነውን ሥራ* ግዴየለሽ በሆነ መልኩ እሠራዋለሁን?

በመክብብ 12፡9-12 የተሰጠን ግሩም የሆነ ምሳሌ ቢኖርም፣ ለስብከት አዘገጃጀት የሚሆኑ ከባድ እና ፈጣን ደንቦች የሉም። ተከትሎ የሚመጣው ለእናንተ አደራ ልሰጥ የምፈልገው የግሌ የሆነ ዘዴ ነው፤ በተለይ ደግሞ በቅርቡ መስበክ የጀመራችሁ እንደሆነ። ተከታዩ መሠረታዊ የሆኑትን ሁሉ የሚያካትት ሲሆን የስብከት አዘገጃጀትን ከጸሎት ጋር ያዋሃደ ነው። ደንብ እንዲሆን የታሰበ ሳይሆን እንደ መምሪያ እንዲሆን የተፈለገ ነው። ምናልባትም በሚሞች መንገድ ልትቀይሩት ወይም የሆነ ነጥብ ላይ ከዚያ ልትለዩ ትፈልጉ ይሆናል። የሆነ ሆኖ አንዳንድ ሰዎች ጠቃሚ ሆኖ እንደሚያገኙት በጣም እርግጠኛ ነኝ።

ውጤታማ ለሆነ ስብከት ዐሥሩ እርከኖች

- ዝግጅታችሁን በተቻለ መጠን ቀደም ብላችሁ ጀምሩ። በጥድፊያ የሚደረግ ዝግጅት መጥፎ ዝግጅት ነው።

- ዝግጅታችሁን ማዘግየት/ማስተላለፍ ውድቀትን መጋበዝ ነው - የሰባኪውን ስንፍና ለመሸፈን ብሎ እግዚአብሔር አላስፈላጊ ተዓምራትን አይሠራም።

- *መሠረታዊ* የሆነው ነገር *መጀመሩ* ነው - ስለ እርሱ *ሊታሰቡበት* - *ሊድርጉት*!

- በርከት ካለ ብርሃን ጋር፣ መጽሐፍ ቅዱስ አዘጋጅታችሁ፣ እርሳስ እና በርካታ ወረቀት ይዛችሁ በትልቅ ጠረጴዛ፣ በጠንካራ ወንበር ተቀመጡ።

- ከዚያም ይህንን የእርከን-በእርከን መምሪያ ተከተሉ፣ ቀደም ያለውን ሙሉ ለሙሉ ሳታጠናቅቁ በፊት ወደሚቀጥለው እርከን *በጭራሽ* አትሂዱ።

1. *ሥራችሁን አሰላስሉ*

- ቁሙ!

- በጌታ ፊት ፍጹም ዝም በሉ።

- *ሥራችሁ* ምን እንደሆነ ለአእምሯችሁ ለማስታወስ ጊዜ ውሰዱ። ያላመኑትን ወደማመን እንዲመጡ፣ እንዲሁም ደካማ ክርስቲያኖችን ብርቱዎች አድርጋችሁ በመለወጥ እግዚአብሔርን ልታከብሩት ናችሁ።

- ይህ የሚደረገው የእግዚአብሔርን ቃል በመግለጥ እና በማዛመድ መሆኑ እውነት ነው። ይሁን እንጂ፣ እናንተ *የስብከት ሠሪዎች* አይደላችሁም፣ ነገር ግን *የቅዱሳን አናጺዎች* እንጂ።

- በዝግጅታችሁ ጊዜ ሁሉ እይታችሁን አለማጣታችሁ መሠረታዊ ነገር ነው።

2. ምንባባችሁን አሰላስሉ

- 'ምንባብ' ስንል አንድ ጥቅስ ቢሆን፣ በርካታ ጥቅሶች ቢሆኑ፣ አንቀጽ፣ ምእራፍ፣ መጽሐፍ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጭብጥ. . . ቢሆን ልትሰብኩበት ያለው የእግዚአብሔር ቃል ክፍል ማለታችን ነው።

- ምንባባችሁን እንዴት እንደምትመርጡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አልተወያየንበትም፣ ነገር ግን በስብከት ላይ በተዘጋጁ ሌሎች መጽሐፎች ውስጥ ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ ጠቃሚ የሆነ ምክር በቀላሉ ልታገኙ ትችላላችሁ።

- **ተንበርከኩ** (*በተግባር!*)። አሁን ምንባባችሁን አንብቡ።

- እያንዳንዱን ክፍል ለጸሎት እንደሚያቀጣጥል ነዳጅ በማድረግ *ዐረፍተ-ነገር በዐረፍተ-ነገር፣ ቃል በቃል* አንብቡት።

- አዎን - ሌላውን ነገር ሁሉ እስኪታስወግዱ ድረስ ምንባቡ ላይ ትኩረት አድርጉ፤ ጣልቃ የሚገቡ ረባሾችን ሁሉ (*ሁሉንም!*) አስወግዱ፤ በጌታ ጎልዎት ውስጥ በምንባቡ ላይ አፍጥጡ።

- ስለምታዩት ስለ እያንዳንዱ እውነት እና ትምህርት አምልኩት።

- ያልገባችሁ የትኛውም የምንባባችሁ ክፍል ቢኖር፣ ጸልዩ፣ አፍጥጡበት እና እስከሚገባችሁ ድረስ አሰላስሉት። እንደዚያም ሆኖ የሚገባችሁ ነገር ከሌለ፣ ማብራሪያ መጽሐፍቶቻችሁን እና ሌሎች አጋዦችን

አማከሩ - ነገር ግን ይህ ሐረግ፣ ወይም ዐረፍተ-ነገር ምን ማለት እንደሆነ ለማጣራት ብቻ እንጂ ከዚያ ላለፈ ለየትኛውም ነገር አይደለም።

- እግዚአብሔርን በምትጠብቁበት ጊዜ፣ አሳቦች መምጣት ይጀምራሉ፣ ምናልባትም መጀመሪያ ላይ ቀስ ብለው። ነገር ግን አንደኛው አሳብ ሌላኛውን እየጠቆመ ያመጣል፣ ይህም በተራው

- ምንባቡ ነፍሳችሁን እስኪያቀጣጥለው ድረስ በጉልበታችሁ ቆዩ - እሳቱ እስኪያቃጥላችሁ፣ አሁን ላይ የገዛ ራሳችሁ ያደረጋችሁትን እውነቶች እስክትሰብኩ አላስችል እስኪላችሁ ድረስ፣ እንዲሁም በተለየ ሁኔታ 'ትልቁ አሳብ'፣ ማለትም ምንባቡ ለማለት የፈለገውን ጠቅለል የሚያደርገው ገዢ አሳብ።

- ምንባቡን አልጠየቃችሁም። ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል አሁን እያስደነቃችሁ ነው፣ ደግሞም የመልእክታችሁ አቅጣጫ ግልጽ ነው።

3. *መጻፍ ጀምሩ*

- **ወደ ጠረጴዛችሁ ሂዱና** ለምንባባችሁ ጥያቄ ጠይቁት። መልሶቹን ጻፏቸው። በዚህ እርከን ላይ የትኛውንም ነገር አሳማኝ በሆነ ቅደም ተከተል ለማቀናጀት አትሞክሩ - ይህ ኋላ ላይ ሊደረግ ይችላል። ይህንን *ሥራ በጥልቀት ለመሥራት ጊዜ ውሰዱ* - ወረቀት ሊያልቅባችሁ አይገባም፣ ደግሞም አሰፈላጊ ከሆነ በርከት ያሉትን ልትጠቀሙ ትችላላችሁ።

- ከሁሉ አስቀድማችሁ፣ እነዚህን መሠረታዊ ጥያቄዎች ጠይቁ፡-

    - የቅርብ፣ ሰፊ እና ታሪካዊ የሆኑት ዐውዶች ምንድናቸው?

- ይህ ምንባብ ለጸሐፊው እና ለመጀመሪያዎቹ አድማጮች ምን ማለት ነበር? ዛሬስ ምን ይላል?
- ስለ እግዚአብሔር አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ ምን ያስተምራል?
- ስለ ሰዎች፣ እግዚአብሔርን በተመለከተ እና አንዳቸው ሌላቸውን በተመለከተ ስላላቸው አመለካከት ምን ያስተምራል?
- መከተል የሚገባ ጥሩ ምሳሌ፣ ወይም ማስወገድ የሚገባ መጥፎ ምሳሌ አለ?
- መታዘዝ የሚኖርብን ትእዛዝ አለ?
- ልንቀበለው የሚገባን ማስጠንቀቂያ አለ?
- ልናምነው እና ልናውጀው የሚገባን ተስፋ ቃል አለ?
- መጽሐፍ ቅዱሳዊ ወይም ግላዊ የሆነ ልንመልሰው የሚገባ ጥያቄ አለ?
- በተለይ ወደ ልብ መውሰድ የሚኖርብን አንዳች ትምህርት አለ?
- በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሚረጋገጥ ትምህርት አለ?

- አሁን ለአንዳንድ ሌሎች ጥያቄዎችን ጠይቁ፣ ለምሳሌ በሐዲን ደብልዩ. ሮቢንሰን፣ ምእራፍ 4 (*ኤክስፖዚተሪ ፕሪቺንግ*፣ ሌከስተር፣ ኣይቪፒ፣ 1986)፣ *ሰርች ዚ ስክሪፕቸርስ* (ሌከስተር፣ ኣይቪፒ፣ 1967) እና *ዚስ ምርኒንግ ዊዝ ጋድ* (ዶውነርስ ግሩቭ፣ ኢንተርቫርስቲ ፕሬስ፣ 1968)።

4. የምታስተምሩትን አቀናጁ

- አሁንም በጸሎት መንፈስ ውስጥ እንዳላችሁ፣ የስብከት ማስታወሻችሁን *በግርድፍ* የምትጽፉበት ጊዜ ነው። ይህ ማለት ቀደም ሲል ሞልታችኋቸው ከነበሩት በርካታ ቍርጥራጭ ወረቀቶች ውስጥ

መሥራት፣ እዚያ ያለውን ማሻሻል፣ እና ራሳቸው ብቅ የሚሉትን አዳዲስ አሳቦች መጨመር ማለት ነው።

- አዲስ ወረቀት በማግኘት ጀምሩና ይህንን መልእክት *ለምን* እየሰበካችሁ እንደሆነ ጻፉ። *ዓላማው* ምንድነው? ይህንን በአንድ ሐረግ ግለጹ።

- አሁን ለዚህ ዓላማ መሳካት ስብከቱ ሊኖረው የሚገባው *ቅርጽ* ምን ዓይነት እንደሚሆን ወስኑ። ለምሳሌ፣ ልታብራሩት የሚገባ አሳብ አለ? ልታሻሽሉት የሚገባ ጥቆማ? ልትተገብሩት የሚገባ መርኾ? የምትናገሩት ታሪክ? የምታጠናቅቁት ርእሰ-ጉዳይ? ወይስ ምን?

- ኋላ ላይ ለምታስገቡት *መግቢያ* ክፍት ቦታ ተዉለት።

- ወረቀታችሁን ለሦስት አምድ/ረድፍ ከፈሉትና፣ *ገለጻ*፣ *አስረጅ ምሳሌ*፣ *ተዛምዶ* ብላችሁ ጻፉበት።

- *ገለጻ* ባላችሁበት አምድ ላይ ከምንባቡ ልታመጡት አለውን መልእክት ጻፉት። መዋቅሩ ግልጽ፣ ቀላል፣ ተፈጥሯዊ እስኪሆንላችሁ ድረስ - በምንባቡ በራሱ ሊሰጥ ያለ መዋቅር እስክታገኙ ድረስ ምንም አታድርጉ። ከዚያም ሙሉት።

- ሙሉውን ረቂቅ አትጻፉት። በአንድ መስመር አንድ አሳብ ጻፉ።

- ነጥቡን ጠብቁ። 'ትልቁን አሳብ' የማያገለግለውን የትኛውንም አሳብ አስቀሩት።

- ለተጻፈው ለእያንዳንዱ አብይ እውነት፣ አስረጅ ምሳሌ አግኙለት ወይም ፍጠሩ። ከዚያ እውነት በትይዩ ባለው *አስረጅ ምሳሌ* በሚለው አምድ ትክክል ጻፉት።

- የምትሰብኳቸውን ሰዎች በምናብ በመሳል፣ *ተዛምዶ* በሚለው አምድ ውስጥ የተዛምዶ አሳብን በምታስተምሩትና በምሳሌ በምታስረዱት

በእያንዳንዱ አብይ እውነት ትይዩ ጻፉ። ይህንን አምድ *ማድረግ ያለብኝ እንዴት እንደምናደርገው፣ ለምን ልናደርገው እንደሚገባ* በሚናገሩ ንዑሳን ክፍሎች ከፈሉት።

- ረቂቅ ማስታወሻችሁን ስትጨርሱ፣ እያንዳንዳቸው ሦስት አምዶች ከሞላ ጎደል እኩል ለኩል ይሞላሉ።

- ይህ ካለቀ በኋላ፣ አሁን በተዋችሁት ቦታ ላይ *መግቢያ* አስገቡ። የመስማት ፍላጎታቸውን የሚቀሰቅስ እና አድማጮቻችሁን ወደ ስብከቱ ርእሰ-ጉዳይ የሚመራ መሆን ይኖርበታል።

- በመጨረሻ፣ ለመልእክቱ *መደምደሚያ* አዘጋጁለት። አድማጮቻችሁ የምንባቡን 'ትልቅ አሳብ' በተለመከተ እርምጃ እንዲወስዱ ልታሳምኗቸው ወደ ልባቸው ልታቀጣጥሉት የምትችሉትን ነገር በእጅጌያችሁ አቆዩ። ቅዱስ ለሆነ አመጽ አሁን ጊዜው ነው!

5. የያዛችሁትን የማጣሪያ ዝርዝር ተከተሉ

   - ረቂቅ ማስታወሻችሁ ላይ መልሳችሁ *ሥሩ*፣ አስፈላጊ እንደሚሆን በሚከተሉት ዝርዝሮች አኳያ የምታስተምሩት በመጣል ወይም በመጨመር *ሥሩ*። የዝግጅታችሁን ወሳኝ የሆነ ጠቃሚ ክፍል አታሳንሱ። *ጊዜ ውሰዱ።*

      1. **ሥነ-ፍታቴያዊ ትክክለኝነት**። ይህ መልእክት ገዢ በሆነ አሳብ ላይ ('ትልቁ አሳብ') በማተኮር የእውነት የምንባቡን *የታሰበውን ትርጉም* የያዘ እና የሚያስተላልፍ እና ወደ ቤት የሚወስደው ነውን? ሥነ-ፍታቴው ትክክለኛ ከሆነ፣ መልእክቱ ሁልጊዜ ወደ ጌታ ኢሱስ ክርስቶስ እና ወደ መስቀሉ ትኩረትን የሚስብ ይሆናል (ሉቃ. 24፡27፤ ሐዋ. 3፡24)። ይህንን ነጥብ ለማጣራት

ማብራሪያ ሰጪ መጽሐፍትን እና የቃላት መተርጎሚያ አጋዦችን ተጠቀሙ።

2. **አስተምህሯዊ ፍሬ-ነገር።** ይህ መልእክት መጽሐፍ ቅዱስ ሊያስተምር ያለውን የአስተምህሮ ሥርዓት ሰዎች እንዲገነዘቡ የሚያደርገው በምን ዓይነት ግልጽ መንገዶች ነው? አስተምህሯዊ ስህተት ወይም አለመመጣጠን እንዳይኖር የትኛውንም አስተምህሯዊ ነጥቦች ከታሪካዊ የክርስቲያን ቤተክርስቲያን የእምነት መግለጫዎች አኳያ አጣሩ (ለምሳሌ፣ የዌስትሚኒስቴር ወይም የለንደን እምነት መግለጫዎች)።

3. **ግልጽ የሆነ መዋቅር።** ለተወሰነ ጊዜ ከዚህ ማስተማሪያ ጋር ኖራችኋል፣ ነገር ግን ጉባዔው የሚሰማው አንዴ ብቻ ነው። የመልእክቱ መዋቅር የማያሻማ፣ በደንብ ግልጽ የሆነ እና ለመከተል ቀላል ነውን? እንደ ጥቅል ደንብ፣ ሦስት ወይም አራት አርእስቶች ብቻ እና ምንም ንዑስ-አርእስት ይኑራችሁ። ሁሉም ነገር ገቢውን አሳብ የሚያገለግል ነው? መግቢያው አጭር፣ የሚስብ፣ የሚቆጣጠር፣ እና ተከትሎ የሚመጣው ነገር አገልጋይ ነውን? መደምደሚያው መልእክቱን የሚያጠቃልል እና ውሳኔ እንዲደረግ የሚነተጉት ነውን?

4. **ጉልህ የሆነ አስረጅ ምሳሌ።** አስረጅ ምሳሌዎች የመልእክቱን አንድ ሦስተኛ የያዙ ናቸውን? ሊብራሩ ያላቸውን እውነታዎች ወይም ሊቀመጡ ያሉትን ተዛምዶዎች የምር ያገለግላሉን? ትኩረትን ወደራሳቸሁ የሚስቡትን አስረጅ ምሳሌዎች ሁሉ ጣሉ።

5. **በነጥብ የሚቀመጥ ተዛምዶ።** ለእያንዳንዱ ሊብራራ ያለ እውነት ተዛምዶዎች አሉን? የመልእክቱን አንድ ሦስተኛ የያዙ ናቸውን? ልትሰብኩላቸው ላሉት ሰዎች የእውነት ቀረቤታ ያላቸው ናቸውን? በደግነት የተገለጹ ናቸውን?

6. ማስታወሻችሁን ጻፉ

- የስብከታችሁን ማስታወሻ ቆንጆ አድርጋችሁ ጻፉ።
- ቋንቋችሁ *ትክክለኛ* እንዲሆን ለማድረግ ጊዜውንና አስቸጋሪ ሁኔታውን ውሰዱ። ቋንቋችሁ ተጨባጭና ግልጽ፣ ትክክለኛና ጉልህ እንዲሆን አድርጉት። ቀላል እና ግልጽ የሆኑትን ቃላት ምረጡ - አብዛኞቹ አንድ ወይም ሁለት መከፈያዎች ይኑራቸው። ዐረፍተ-ነገሮቻችሁ አጭር ይሁኑ፣ እያንዳንዳቸውም ነጠላ አሳብ ብቻ የያዙ ይሁኑ። የሚቻል በሚሆንበት ጊዜ ሁሉ 'እናንተ' የሚለውን ተጠቀሙ።

- *በርካታ* የሆኑ *በርካታ* አሳማኝ ጥያቄዎችን ማካተታችሁን እርግጠኞች ሁኑ።

- በመደጋገም ማስረዳት ጠቃሚ የሚሆነው የቱጋር እንደሆነ አስቡ።

- ማስታወሻችሁን ስታዘጋጁ፣ ከምንም በላይ ለግልጽነት ቦታ ስጡ። ለማንበብ *ቀላል* ሊሆኑ ይገባል።

- ትልልቅ ጻፉ - ወይም በኮምፕዩተር ጻፉ፡፤

- በወረቀቱ አንድ ጎን ብቻ ጻፉ።

- ለገጾቹ ቁጥሮችን ስጡ።

- ዋና አርእስቶችን በቀይ አስምሩባቸው፣ እና ንዑሳን አርእስቶች የሚኖሩ ከሆነ በሰማያዊ ወይም በአረንጓዴ አስምሩባቸው።

7. ከአምላካችሁ ጋር ተደራደሩ

- በተጠናቀቀ*ት* ማስታወሻዎች ላይ ለመጸለይ በድጋሚ ተንበርከኩ። ይህ መልእክታችሁን ከመለማመድ ሚሊዮን ጊዜ ይልቅ የሚሻል ነገር ነው!

- *ለመጀመሪያው* ጊዜ የሰዎችን ትኩረት ወደ ሥላሴው አምላክ እንዲስብ እና ስለ እርሱ ትልልቅ አሳቦችን እንዲያስቡ እንዲያደርጋቸው በእያንዳንዱ መስመር ላይ ጸልዩ።

- *ለሁለተኛው* ጊዜ ያልዳኑትን ወደ ክርስቶስ እንዲያመጣ እና የዳኑትም በሁለቱም በጸጋ እና እውቀት እንዲያድጉ በመጠየቅ በእያንዳንዱ መስመር ላይ ጸልዩ።

- ይህኛው የጸሎት ጊዜ በተጠናቀቀው ማስታወሻችሁ ላይ አንዳንድ ለውጦችን እንድታደርጉ ሊያንቀሳቅሳችሁ ይችላል። ይህንን ለማድረግ አታቅማሙ። ማስታወሻዎቻችሁ የተቀደሱ ወይም የማይጣሉ አይደሉም።

- እንደተንበረከካችሁ ቆዩ፡- መዝሙር ምረጡና ሌሎቹንም የአምልኮ ቆይታውን ቅደም-ተከተል ዝርዝሮች አቀናጁ።

- አምልኮ አገልግሎቱ የተሟላ መሆን ይኖርበታል። በውስጡ ያለው ሁሉ በመልእክቱ ውስጥ ሊታወጅ ያለውን ገዢ የሆነውን አሳብ (ወይም 'ትልቁን አሳብ') የሚያንላ መሆን ይኖርበታል።

8. የመጨረሻውን ዝግጅቶች አድርጉ

- ወደ ቤተክርስቲያን ቀደም ብላችሁ ድረሱ።

- ወደ ምስባኩ ወይም ወደ መድረኩ ሂዱና ራሳችሁን ከምስባኩ፣ ከድምጽ መሳሪያው፣ ከመቀመጫው፣ እና ከስብከታችሁ ጋር ከተያያዙት አካላዊ ሁኔታዎች ሁሉ ጋር አላምዱ።

- መጽሐፍ ቅዱሳችሁን፣ ማስታወሻችሁን የአምልኮ ቅደም-ተከተሉን እና የዝማሬ መጽሐፉን አምልኮ ከመጀመሩ በፊት ቀድማችሁ አቀናጁ።

- የምትችሉትን እና የምታገኙትን ያክል ሰው ሰላም በሉና አምልኮ ከመጀመሩ በፊት ከቤተክርስቲያኒቱ አገልጋዮች ጋር ለመጸለይ ጊዜ ውሰዱ።

9. ወደ ሥራችሁ ሂዱ

- ዛሬ እንድትመሩና እንድትሰብኩ የእግዚአብሔር መግቦት ሾሟችኋል - ስለዚህ በጸሎት፣ በሥልጣን እና በፍቅር አድርጉት።

- የጉባዔያችሁን ዓይን እያያችሁ ተናገሩ።

- ሁለት ነገሮች ላይ ብቻ ትኩረት አድርጉ - ጌታን ከፍ ማድረግ እና እነዚህን ሰዎች ቅዱሳን ማድረግ። አምልኮው እና ስብከቱ እነዚህን ትልልቅ ውጤቶች የምታስገኙባቸው ምክንያቶች ናቸው። በራሳቸው ውጤት አይሆኑም፡፤

10. በሚስጢር ወጥታችሁ ተደበቁ

- ከስብከት በኋላ የሆነ ጊዜ ላይ ለግል ጸሎት በቂ የሆነ ጊዜ ለመውስ ጸጥታማ ቦታ አግኙ።

- የአምልኮ ቅደም ተከተሉን እና የስብከት ማስታወሻውን በድጋሚ አውጡና በእነዚያ ላይ ጸልዩ።

- በተሻለ መልኩ ልትናገሩበት ትችሉ ለነበረው ለእያንዳንዱ ነጥብ ይቅርታን ጠይቁ።

- ላስታወቃችሁት ለእያንዳንዱ እውነት ጸልዩ - ሰዎቹ እንዲያስታውሷቸው፣ ስለ እግዚአብሔር ታላላቅ አሳቦችን እንዲያስቡ እንዲያደርጓቸው፣ ያልዳኑት ወደ ጌታ እንዲመጡበት፣ የዳኑትም

በሁለቱም በመንፈሳዊ ግንዛቤ እና ኑሮ ፋይዳ ያለው እድገት እንዲያደርጉበት ጸልዩ።

- ልታስታውሱ የምትችሏቸውን ያክል ግለሰቦች እየጠቀሳችሁ ጸልዩላቸው።

- ከዚያም ሁሉን ነገር በጌታ እጆች ላይ ተዉና የሚቀጥለውን መልእክት መዘጋጀት ጀምሩ!

* * *

በኑሮ ሁኔታ ውስጥ ስብከት ለማዘጋጀት በተለመደ መልኩ የሚወስደው ምን ያክል ጊዜ ነው? *መልሱ የሚወሰደውን ያክል!* የሚል ነው። ሁሉም ወደ አንድነት የሚመጣው በምን ያክል ፍጥነት እንደሆነ፣ ደግሞስ ይህንን የተለየ ስብከት በዚህ የተለየ ጊዜ ላይ እንደሚባርክ የግል ማረጋገጫ እስክታገኙ ድረስ ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት ለመታገል ምን ያክል ጊዜ እንደሚወስድ ማን ይነግረኛል?

ይህንን ያክል ልንናገር ችለናል፦ የሥላሳ ደቂቃ ስብከት ለመስበክ ቢያንስ የ*ዐሥራ* ሁለት ሰዓታት የመነሻ ጊዜ ያስፈልጋችኋል። ዓመታት እየጨመሩ በሚሄዱ ጊዜ ይህ ምናልባትም እያነሰ ይሄድ ይሆናል። መቀነስ የምትችሉት ትንሹ ሰዓት ለእያንዳንዱ የአምስት ደቂቃ ስብከት የአንድ ሰዓት ጊዜ ነው።

እኔ የምጠቀሥመው ዘዴ ስብከቶች በራሳቸው ውጤት እንዳልሆኑ ትኩረት የሚያደርግ ነው። አማኞችን በመገንባት ረገድ እና ያልዳኑትን ወደ ጌታ በማምጣት ረገድ እግዚአብሔር የሚከብርበት አንድ መንገድ ነው። ዘዴው የሚያበረታታው ያልተጣደፈ የምንባቡ ማሰላሰል እንዲደረግ፣ ለአስተምህሯዊ ንፅህና የማያፍር መሰጠት እንዲኖር፣ ግልጽ የሆነ መዋቅር ለመሥራት ዘላቂ ጥረት እንዲደረግ፣ ትጉ የሆነ አስረጅ ምሳሌዎች እና ተዛምዶዎች እንዲደረጉ፣ በተገለጸው መስፈርት ብርሃን ዘላቂ ቅኝት እንዲደረግ፣ ማስታወሻ ለመጻፍ የቅርብ የሆነ ትኩረት እንዲደረግ፣ የጽናት ጸሎት እንዲኖር፣ ደፋር እወጃ እንዲደረግ እና የግል ንስሃ እንዲደረግበት ነው።

ይህንን ዘዴ የምትከተሉ ከሆናችሁ፣ የስብከት አዘገጃጀታችሁ የቸኮላ አይሆንም፣ ደግሞም ግሩም ለሆነ ስብከት እያንዳንዱን የሚፈለግ ባህርይ ያካተተ ይሆናል። ደግሞስ እንዲህ አለው ስብከት ግልጽ የሆነ የሰዓቱ ተፈላጊ ነገር አይደለምን?

2

በፍቅር የሚታወስ፡-

ኸግ ዴቪድ ሞርጋን (1928-1992)

ይህ በስብከት ላይ የሚያተኩር መጽሐፍ ነው፤ ስለዚህ በእጅጉ የሚናፈቅ የወንጌል አገልጋይን መታሰቢያ በመዝጊያው ላይ የምናነሣው ለምንድነው? መልሱ ቀላል ነው፡- ቀደም ባሉት ገጾች ውስጥ የተቀመጡትን መርኾዎች በምሳሌነት ያሳዩ በርካታ ዘመናዊ ሰባኪዎች ስለሌሉ ነው። ነገር ግን ጥቂቶች የነበሩ ሲሆን ኸግ ሞርጋን አንዱ ናቸው። ምንም እንኳን እርሳቸው በክብር ውስጥ ከሆኑ አሁን በርካታ አመታት ያስቆጠሩ ቢሆኑም፣ ተጽዕኗቸው እንደዘለቀ ነው። እስከ አሁን ድረስ ያነበባችሁት በተግባር ይፈጸም ዘንድ እንደሚቻል፣ እንዲሁም ደግሞ ንቀኑ እና ተንከባካቢ ከሆነ መጋቢያዊ አገልግሎት ጋር ሊጣመር የሚችል እንደሆነ ሕያው ማረጋገጫ የሰጡ የእግዚአብሔር ሰው ናቸው። በዚያ መልኩ እኛን ሁላችንን ያበረታቱናል።

ሕይወታቸው

ኸግ ዴቪድ ሞርጋን የተወለዱት በላኔሊ ውስጥ በ1928 ዓ.ም. ሲሆን በዚያው ከተማ ውስጥ አስደናቂ በሆነው የወንጌላዊያን ስብሰባ ወቅት ጎብኚ ተማሪዎች በመጡበት የተባረከ ሣምንት ውስጥ አስደናቂ በሆነ ሁኔታ በ1945 ዓ.ም. በድጋሚ ተወለዱ። በዚህ ወቅት ከመቶ በላይ የሚሆኑ ወጣት ሰዎች ወደ ጌታ መጥተው ነበር። ኋላ ላይ ያገቧትን ሜሪ ዊሊያምስን የተዋቀሩት በዚያው ሣምንት ውስጥ ነበር። ቀደም ሲል ካልቪኒስቲክ ሜቶዲስት ኮኔክሽን ይባል በነበረው በፕሬስቢተራንያን ቸርች ኡቨ ዌልስ የአገልግሎት ሥልጠና ለማግኘት ወደ አቤሪስቲዝ፣ ከዚያም ወደ ባላ ከመሄዳቸው በፊት ከትምህርት ቤት እንደተመረቁ ለንጉሣዊው አየር ኃይል ሁለት ዓመታት በብሔራዊ አገልግሎት ሰጥተዋል።

የኸግ የመጀመሪያው መጋቢያዊ አገልግሎት ሮንዳ ሸለቆ በሚባለው ሥፍራ ላይ ሲሆን ይህም ሜሪን ካገቡ ካጭር ጊዜ በኋላ በ1953 የሄዱበት ነበር። እርሳቸው በዚህ ሥፍራ ለዘጠኝ አመታት ቆዩ። መጋቢነታቸው ለሁለት ቤተክርስቲያናት ሲሆን አንደኛው ተን ፔንትሬ ውስጥ ላለችው ለቤተኒ (ወጣቶቹ ጥንዶች ይኖሩበት በነበረበት) እና ጌሊ ውስጥ ላለው ደፍሪን ነበር። ኸግ ራሳቸውን በጣም አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ውስጥ አገኙት። ቤተክርስቲያናቱ ለዘብተኛ በሆነ ነገረ-መለኮት ተውጠው ነበር፣ ደግሞም የቤተክርስቲያኑ ሕይወት የተሞላው ገንዘብ ለማሰባሰብ ተብለው ይካሄዱ በነበሩት የሙዚቃ ድግሶች እና የሥራዎች ሽያጮች ነበር። ነገር ግን ጌታ በዚህ ወጣት አገልጋዩ ላይ እጁን አኖረ። መጽሐፍ ቅዱስን ከፍተው ወንጌልን በድፍረት ሰበኩ፣ ይህንን በየዋህነት እና በሚፍለቀለቅ ፍቅር አደረጉት። ቀስ በቀስ ቅሬታዎች መምጣታቸውን አቆሙ፣ ጠላቶች ድል ተነሡ፣ ልቦች ቀለጡ፣ ደግሞም በርካታ ሰዎች ነቁ፣ ደግሞም ዳኑ። ኸግ እና ሜሪ እንዲሁም ሴቶች ልጆቻቸው ቤታን እና ሲያን ሊዘዋወሩ ጊዜው ሲመጣ፣ በሕዝቦቻቸው ፍቅር እንደ ቤተሰብ ታጅበው ተዘዋወሩ።

በ1962 ዓ.ም. ኸግ በማልፓስ ሮድ ፕሬስቢተራንያን ቤተክርስቲያን፣ ኒውፖርት ውስጥ አገልግሎታቸውን ጀመሩ። ከመጀመሪያው ይልቅ ትልቅ ቤተክርስቲያን ስትሆን፣ ነገር ግን በቅርብ ዓመታት ውስጥ ስለ ወንጌል የምታውቀው በጣም ጥቂት ነበር። ኸግ ከምስባካቸው ሆነው በሥልታዊ ሁኔታ የእግዚአብሔርን ቃል ይገልጡ ጀመር። ይሁን እንጂ፣ ራሳቸውን በአመዛኙ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ ሳይሆን እንደ ወንጌላዊ በማየት አደረጉት። ከምስባክ አገልግሎታቸው በስተጀርባ በሚስጢር የሚደረግ ጸሎት ነበር፣ ደግሞም ከዚህ ጋር ተዋህዶ የነበረው እርሳቸው እና ሜሪ በሣምንቱ ውስጥ በሕዝባቸው መካከል ይለማመዱት የነበረ ተግባራዊ የሆነ የእንክብካቤ አገልግሎት ነበረ። የመጀመሪያዎቹ ዓመታት በጣም አስቸጋሪዎች የነበሩ ሲሆን የተወሰኑ ሰዎችም ቤተክርስቲያኒቱን ትተው ሄደዋል። ይሁን እንጂ፣ ከ1970-1980 ያሉት ዓመታት የተለየ በረከት የሚታጨድባቸው ነበሩ። ኸግ በስብከታቸው ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ ዝም ብለው የሚቆሙ እና መንፈስ ቅዱስ ሲሠራ የሚያዩ ያክል ይሰማቸው ነበር። ቤተክርስቲያኒቱ የኢቫንጀሊካል ሪፎርምድ እምነት ስትቀበል፣ እና የወንጌል ብርሃን ስትሆን በርካታ ሰዎች ወደ ጌታ ይመጡ ነበር። ይህ ለወንጌል ያለው መሰጠት ነበር ጉባዔው በ1976 ከነበረው አገዛዝ በስተመጨረሻ ላይ እንዲገነጠል እና የማልፓስ ሮድ ኢቫንጀሊካል ቤተክርስቲያን እንዲሆን አድርጎት የነበረው።

ይሁን እንጂ፣ የኸግ የሠላሳ ዘጠኝ ዓመታት አገልግሎት በሁለቱ መጋቢያዊ አገልግሎቶች ብቻ የተገደበ አልነበረም። የክርስቶስ ጉዳይ በአጥቢያ ከተያዙበት ሁኔታ በላይ ትልቅ እንደሆነ በጥልቀት አውቀው ነበር። ገና ከጅማሬ የክፍት አየር ሰባኪ እና በበርካታ የተማሪዎች የወንጌል ተልእኮዎች ውስጥ ተደጋጋሚ ተሳታፊ ነበሩ። በ1962 ዓ.ም. የኢቫንጀሊካል ሙቭመንት ኡቭ ዌልስ ጠቅላላ ኮሚቴ አባል ከሆኑ በኋላ እስከሞቱበት ጊዜ ድረስ በዚያ ቆዩ! እንቅስቃሴው በአገልጋዮች መካከል ባለው ሥራ ውስጥ የመሪነት ሚና ነበራቸው፣ የገንዘብ ኮሚቴውን መርተዋል፣ ጠቅላላ ኮሚቴውን ብሪንትሪየን ውስጥ ባለው የእንቅስቃሴው ዋና ጽ/ቤት ውስጥ እሳት መነሳቱን ተከትሎ በነበሩት አስቸጋሪ ቀናት ውስጥ በሰብሳቢነት አገልግለዋል። በዌልስ ዙሪያና ከዚያም ባለፈ እንደ ወንጌል ሰባኪ እና የኮንፈራንስ ተናጋሪ ታዋቂ አገልጋይ ሆኑ። ቤሪ በሚገኘው የሳውዘርን ዌልስ ባይብል ኮሌጅ ውስጥ ያስተምሩ ነበር፣ ደግሞም ያንን ማድረጋቸውን የቀጠሉት ኮሌጁ ኢቫንጀሊካል ቲዎሎጂካል ኮሌጅ ኡቭ ዌልስ ተብሎ በብሪጀንድ ውስጥ እስከተደራጀበት ጊዜ ድረስ ነበር። ለዩኒቨርስቲዎች እና ኮሌጆች የክርስቲያን ጎብረቶች ሥራ የተሰጡ ነበር፣ ወንጌላዊያን ዛሬ ላይ ለተባለው ወርሃዊ ጸሎት እና ከሌሎች ጋር በመሆን ምሥረታ ላይ ዋና ሰው በነበሩበት የዌልስ ወንጌላዊያን ቤተክርስቲያናት ማኅበር ላይ ተሳትፈዋል። ደግሞም በተለያዩ በርካታ መንገዶች የመከሯቸው እና ያበረታቷቸው ወንዶች እና ሴቶች ግለሰቦች አይቆጠሬ ሰዎች አልጠቀስነውም። ኸግ ሞርጋን በጣም በቀላሉ በወንጌል ሥራ ውስጥ ደከመኝ የማያውቁ ነበሩ።

የኸግ ሞርጋን አንደኛው የሚወድዱት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ፊሊጵስዩስ 1፡21 ‘ለእኔ መኖር ክርስቶስ፣ ሞትም ጥቅም ነው’ የሚለው ነበር። ሐሙስ ጃኑዋሪ 30፣ 1992 ዓ.ም. አመዛኙን ቀን አቤሪስትዊዝ ውስጥ በኢቫንጀሊካል ሙቭመንት ኡቭ ዌልስ ጠቅላላ ኮሚቴ ውስጥ ሲሳተፉ ዋሉ። አርብ ጃኑዋሪ 31 ላይ ለስብከታቸው ተዘጋጁ፣ በመጋቢያዊ ሥራቸው ላይ ውሰለው ምሽቱን ከማልፓስ ሮድ ኢቫንጀሊካል ቤተክርስቲያን ጋር በዚያ ተተኪ ሰውን ለማስቀለመጥ ጥሪ ስለማድረግ እንዲዘጋጁ ሲወያዩ አሳለፉ። ቅዳሜ ፌብሩዋሪ 1 ቀን 1992 ዓ.ም. ላይ 1፡00 ላይ በቤተክርስቲያናቸው ለመነቃቃት በሚደረገው የጸሎት ስብሰባ ላይ ሲሳተፉ ቆይተው 3፡00 ላይ ወደ ቤት ከተመለሱ በኋላ ባጭር ጊዜ ውስጥ በክብር ወደ ጌታቸው ተሰበሰቡ።

ባህርያቸው

ይህ እርግጥ የሆነ ክብር ነበር፣ ነገር ግን ስለ ኸግ ሞርጋን የሚነገር ብዙ ነገር የለም። ‘አብዛኛውን ጊዜ “ጌታ ሆይ፣ ይቅር የተባለ ኃጢአተኛ ሊሆን የሚችለውን ያክል ቅዱስ አድርገኝ” ብዬ እጸልያለሁ’ ይሉ ነበር። እውነተኛ ቅደስና ምን እንደሆነ ገብቷቸዋል። በእግዚአብሔር ነገሮች ላይ ኮስታራ መሆን እና በግል ልማዶች ላይ ራስን መግዛት ማለት ነበር። ነገር ግን ደስታ ቢስ ወይም ሰው-ሠራሽ መሆን ማለት አልነበረም። ስለዚህም እርሳቸው ጥሩ ጨዋታ አዋቂ፣ የተግባራዊ ቀልዶች አፍቃሪ፣ የረግቢ ተጫዋች እና ደጋፊ፣ እንዲሁም መጽሐፍትንና ጋዜጦችን በጉጉት የሚያነብቡ ነበሩ። ምንም እንኳን ራሳቸውን የሚያጠሩ ሰው የነበሩ ቢሆኑም፣ ሰዎች ከእርሳቸው አቅራቢያ መሆን ይወድዱ ነበር፤ ደግሞም ይህ በተለይ ለሚስታቸው፣ ልጆቻቸው እና የልጅ ልጆቻቸው እውነት የሆነ ነገር ነበር። እንደ ጎብኚ ሰባኪ ወደ ቤታቸው እንዲመጡ የሚጋብዟቸው ጎልማሶች ቢሆኑ ህጻናት ተመልሰው እስኪመጡ ድረስ ይናፍቋቸው ነበር።

እርሳቸው የጸሎት ሰው ነበሩ። የግል ጸሎትን ቀላል ሆኖ አያገኙትም ነበር፣ ነገር ግን እንደዚያ ቢሆንም ራሳቸውን ለዚያ የሰጡ ነበሩ። አብዛኛውን ጊዜ ከጾም ጋር ይጸልዩ ነበር። ተማሪ ሳሉ ጸልየዋል፣ አገልጋይ ሲሆኑ ጸልየዋል፣ ከቤተሰባቸው ጋር ጸልየዋል፣ ደግሞም ከጓደኞቻቸው ጋር ጸልየዋል። የወንጌል ሥራ በእጃቸው እንዲሰጥ ጸልየዋል፣ ደግሞም ይፈጽሙት ዘንድ ለሁለቱም ለጸጋ እና ብርታት ጸልየዋል። ለሕዝባቸው ጸልየዋል፣ ለቤተክርስቲያን በጥቅሉ ጸልየዋል፣ ጌታ የተሰበከውን ቃል ያጅብ ዘንድ፣ እንዲሁም እርሱ ሕዝቡን በመነቃቃት በረከት በድጋሚ እንዲጎበኝ በተለየ ሸክም ውስጥ ሆነው ጸልየዋል።

እርሳቸው ሰዎችን ይወድዳሉ፣ ደግሞም በተለይ ጌታ መጋቢ እንዲሆኑላቸው የጠራቸውን ሰዎች ይወድዱ ነበር። እነዚህን እርሳቸው ለራሳቸው ጤና ወይም ምቾት ሳያስቡ ቀንና ሌሊት አገልግለዋል። ሰዎችን የሚቀርቡት ከልብ በሆነ ሰላምታ እና በሚማርከው ፈገግታቸው ሲሆን ከጎልማሶች እና የትኛውም እድሜም ሆነ ዳራ ካላቸው ልጆች ጋር ዘላቂ የሆነ ውይይት ለማድረግ ምንም ችግር አልነበረባቸውም። ለእርሳቸው በዓለም ውስጥ ያለው ትልቁ እድለኝነት በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ መካተታቸው ሲሆን ትልቁ መሻታቸው ሌሎች ሰዎች ወደዚያ ቤተሰብ ሲመጡ ማየት ነበር። እንግዲያው እርሳቸው ስለ መንፈሳዊ ሁኔታቸው ጠጣር የሆኑ ጥያቄዎችን ከመጠየቅ

አይቆጠቡም ነበር፣ ነገር ግን ይህንን የሚያደርጉት በየትኛውም የእብሪተኝነት ወይም እንስፍስፍ ያለመሆን ፍንጭ በማሳየት አልነበረም።

ጥቂት ሰዓታት ከእርሳቸው ጋር ለማሳለፍ እድል ያገኘሁት በሰሜናዊቷ የጣልያን አነስተኛ ከተማ ውስጥ ነበር። እርሳቸው እና ሜሪ ስዊዘርላንድ ውስጥ እረፍት ላይ ነበሩና ድንበሩን አብረን በዚያ ቀን እያቋረጥን ተጓዝን። ስለ ተሃድሶ እና በክልሉ ላይ አምጥቶት ስለነበረው ተጽዕኖ በሰፊው አወራን። ከዚያም ኸግ የአካባቢውን የዋልዴንሲያን ጳሎት ቤት እንድንጎበኝ ዘንድ እንደሚገባ በእጅጉ ጎተጎቱ። መጋቢው ከምሳ በኋላ የሚያደርጉት ሽለብታ ላይ ነበሩ፣ ነገር ግን ኸግ ገር በሆነ ሁኔታ ለመከፈት እስኪስማሙ እና እስኪመጡ ድረስ በራቸውን አንኳኩ። መጋቢው በጣም ጥቂት የሆነች እንግሊዝኛ የሚናገሩ፣ ኸግ ደግሞ ምንም ጣልያንኛ የማያውቁ ነበሩ። ነገር ግን በተወሰነ መልኩ በጋራ ረጅም የሆነ ውይይት ማድረግ ቻሉ። ብዙም ሳይቆይ ሰውዬው ወንጌል በትክክል ያልገባቸው እና አዲሱን ልደት ተለማምደው የማያውቁ ሆነው ተገኙ። መጋቢው ከምድር አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ ወደሰማይ እንዲሄዱ ሊያውቋት የሚገባውን ነገር ሁሉ በጸጥታ ለመግለጥ ኸግ ኢጋጣሚውን የተጠቀሙት እንዴት እንደነበረ ማየቱ ያስደንቅ ነበር።

ኸግ ሞርጋን ሁልጊዜም ፈገግተኛ ነበሩ። ኃቀኝነታቸው ነቀፌታ የሌለበት፣ ባህርያቸው ግልጽነት ያለው፣ ሁኔታቸው የደግነት፣ እና በገርነታቸው እና በጥበባቸው የታወቁ ነበሩ። ዋናው የሚያሳስባቸው ነገር ጌታን የሚያስደስተውን ነገር ሁልጊዜ ማድረግ ነበር። ያ ማለት ምን እንደሆነ እርግጠኛ ሲሆኑ፣ ያንን ከማድረግ ምንም ነገር አይመልሳቸውም! ይሁን እንጂ መሰናከሉ ምንም ቢሆን፣ ተቃውሞው ቢበዛ፣ ምንም እንኳን በዝግታ መሄድ ማለት ቢሆንም በጽናት እና በፍቅር ሆነው ትክክለኛ በሆነው ጎዳና ይሄዳሉ። ምንም ነገር መንገዳቸውን አያስቀይራቸውም። እንዴት ተስፋ እንደሚቆረጥ አያውቁም። ለማስደሰት የሚሞክሩት የሰዎች ክበብ የለም፤ እርሳቸው ለማስደሰት የሚሞክሩት ጌታን ብቻ ነው።

ስብከታቸው

ኸግ ሞርጋን ሲሰብኩ ሰምተው የማያውቁ ሰዎች ስብከታቸው ምን እንደሚመስል መገመት አያስፈልጋቸውም። ለዚህ ምክንያቱ በርካታ የሆኑት ስብከታቸው አሁን ድረስ ከማልፓስ ሮድ ኢቫንጀሊካል ቤተክርስቲያን፣ ኒው ፖርት የሚገኙ መሆናቸው ነው። ይሁን እንጂ፣ አንድን ሰው በተቀዳ ካሴት በመስማት እና በሥጋ መስማት መካከል ትልቅ ልዩነት አለ።

መጽሐፍ ቅዱሳቸውን በጥሩ ሁኔታ ያውቃሉ፣ ደግሞም አብዛኛውን አገልግሎት ያሳለፉት በሥልታዊ እና ጭብጥን መሠረት ባደረገ መልኩ እያብራሩት ነበር። ምንባቡ ላይ ጠንቃቃ ነበሩ። የሕያው እግዚአብሔርን ንግርቶች የያዙ ስለመሆናቸው ያውቁ ነበር፣ ደግሞም ኃላፊነታቸው ትርጉሙን እንዳያበላሽ በጥልቀት ጎሊናቸው ያውቀው ነበር። ስብከታቸው አስደናቂ በሆነ መልኩ ክርስቶስን ማዕከል ያደረገ እና ታላቁን የወንጌል የማዳን እውነት በዘላቂነት ወደ ትኩረት የሚያመጣ ነበር። የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን፣ እና ቤተክርስቲያኒቱን ያሟሉት ወንዶች እና ሴቶች ቅዱሳን መሆን እንዳለባቸው ያሳስባቸው ነበር። የልብ እና የሕይወት ቅድስና ከዚህ የተነሣ ዘላቂ የሆነ ጭብጥ በመሆን ከእርሳቸው ይመጣ ነበር።

ለተራ ሰዎች እንደሚሰብኩ ያውቁ ነበር። የእግዚአብሔር ነገሮች ላይ ያላቸው የገዛ ራሳቸው ግንዛቤ የሞላ እና በዓመታት ውስጥ የበለጠ የተጣራ ቢሆንም፣ ስብከታቸው ሊገኝ የሚችል እና የሚታወስ ሆኖ ዘልቋል። የገዛ ራሳቸው ሕይወት እና የእርሳቸው ሕይወት በቅርበት አብሮ የተጠላለፈ ሲሆን ከዚያ የተነሣ እርሳቸው ወደ ሕይወታቸው በቀጥታ ይናገሩ ነበር። ይህ ሁኔታ ስብከታቸውን ከወቅታዊ ማስታወሻ ጋር ለሰዎች ቀረቤታ ያለው፣ ቀጥተኛ፣ እና የሚመረምር እንዲሆን አድርጎታል።

የኸግ ሞርጋንን ስብከቶች *የመጋቢያዊ ሰብከት* አስደናቂ ምሳሌዎች አድርገን በተሻለ ሁኔታ ልንገልጻቸው እንችላለን። የክርስትና ምስባክን የረከሰ ወይም ጥራቱን ያጣ አድርገውት አያውቁም፣ ነገር ግን አኳኋናቸው መደበኛ ወይም የሩቅ አልነበረም። እርሳቸው ሕዝባቸውን ይወድዳሉ፣ እነርሱም ደግሞ ያውቁታል። ግሣጼያቸው ዱልዱምና መርማሪ በሚሆን ጊዜ እነርሱ ያውቁታል፤ ምክንያቱም እርሳቸው ያንን የሚናገሩት ሞቃት በሆነ ልብ እና እንደ ገር መጋቢ በመሆን እንጂ ጥላቻን በሚያሳይ ተቺነት አልነበረም።

መልእክታቸውን በመስጠታቸው ውስጥ ራሳቸውን ጭምር ሰጥተዋል። የእርሳቸው መላው ስብዕና ይናገሩት በነበረው ነገር ውስጥ ነበር። ይህ ደግሞ ሰውነታቸው ይንቀሳቀስ በነበረበት መንገድ፣ በፊታቸው መግለጫ፣ እና በአቀራረባቸው ሕያውነት እና ጥልቅ ስሜት ውስጥ ይታይ ነበር። ነገር ግን የሕይወታቸው መገራት እና ምንባቡን ለማገልገል ያላቸው ጉትጎታ በእርግጥ እንደ ጽንፈኝነት እስኪታይ ድረስ ጎዶሎ ነገር አልነበረም።

እንደ እግዚአብሔር ሰው ባላቸው እለታዊ ሕይወታቸው፣ በመጋቢያው አገልግሎታቸው፣ እና በሕዝባዊ ስብከታቸው መካከል መፋለስ ወይም ውጥረት አልነበረም። በእርሳቸው ውስጥ የነበረውን የእግዚአብሔር ጸጋ እናደንቃለን፣ ደግሞም ለሁሉም ትውልዶች ክርስቲያናዊ አገልግሎት እንደ አርአያ እናያቸዋለን። እንዲህ ያሉ ክርስቶስን ማዕከል ያደረጉ፣ ሁሉን ያካተተ ተስማሚነት የሚያስደምም መሆን ብቻ ሳይሆን የማይረሳም ጭምር ነው።

ትተው የሄዱት ቅርስ

ኸግ ሞርጋን ለእኛ ትተው የሄዱት ግንባር ቀደም ቅርስ ያለ ጥርጥር ለእኛ ትተው በሄዱት ምሳሌነት ውስጥ ሲሆን ከዚህም ውስጥ ዋና ገጽታውን ከላይ ላስቀምጠው ሞክሬያለሁ። ይሁን እንጂ፣ በሃያ አንደኛው ክፍለ-ዘመን መግቢያ ላይ እንዳሉ ክርስቲያኖች፣ ከእርሳቸው ልንማራቸው የምንችላቸው ሌሎች የተወሰኑ ትምህርቶች አሉ።

ለግላዊ ቅድስና የሚያደርጉት ጥሪ ለሁሉም ጊዜያት የሚሠራ እና ጠቃሚ ነው። ቅዱስ ያልሆነ ሕይወት ሁልጊዜ በሚነገረው ወንጌል ላይ እፍረትን ያመጣል። በ1978 ዓ.ም. እንግሊዝኛ ተናጋሪ ለሆኑት የአቤሪስትዌዝ ኮንፈራንስ ያቀረቡት የኸግ አራቱ ንግግሮች ግልጽ የሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርትን፣ እንከን የሌለበት አስተምህሮ እና ተግባራዊ እርዳታን ቀይጦ የሚያንቀሳቅስ ነበር። *ዚ ሆሊነሰ ኡቭ ጋድ ኤንድ ኡቭ ሂስ ፕፕል*[17] በሚል ርእስ የታተመው መጽሐፍ

[17] ብሪያንትሪየን፣ ኢቫንጀሊካል ፕሬስ ኡቭ ዌልስ (አሁን ብሪያንትሪየን ማተሚያ) 1978።

ሁልጊዜም ሊታተም ይገባል። መጽሐፉ ብዙዎች ጌታን በአዲስ መንገድ እንዲፈልጉት አንቀሳቅሷቸዋል።

ከዚህም በተጨማሪ፣ በአገልግሎታቸው ዘመን ወቅት፣ ጊዜያት በጣም በእጅጉ እንደተለወጡ ተገንዝበዋል። መጋቢያዊ አገልግሎታቸውን የጀመሩት ወደ ጸሎት ቤት የሚመጡትን፣ ነገር ግን ያልተለወጡትን በርካታ ሰዎች በወንጌል በመድረስ ነበር። ዓመታት እያለፉ ሲሄዱ አሮጌው የጸሎት ቤት ባህልም እንዲሁ እያለፈ እንደሆነ አስተዋሉ። አብዛኞቹ ሰዎች ከአምልኮ ቦታው ጋር የትኛውም መገናኘት አልነበራቸውም። ከወንጌል ጋር የትኛውም መገናኘት ያለው አዲስ ትውልድ በቅሎ ነበር። እንዚህ ሰዎች እንዲጠፉ መተው አለባቸው? የወንጌል ሥርጭታችን አሁን ላይ ውስጥ ካሉት ጥቂቶች ይልቅ በውጭ ባሉት በአመዛኞቹ ላይ ማተኮር የለበትምን? አዳዲስ ተነሣሽነቶችን ለመውሰድ ጊዜው አይደለምን? ወንጌልን በአገራችን ላሉት ለእያንዳንዱ ሰው ለማድረስ ሁለቱንም ቤተክርስቲያናትን እና ግለሰብ አማኞችን ለማንቀሳቀስ ምን ሊደረግ ይችል ነበር? የትኛውንም ነገር በአስተማማኝ መውሰድ እና በተቻለ መልኩ ቀላል አድርገን መናገር አንችልም? ኸግ ሞርጋን እየጨመረ በሚሄድ መልኩ ይጠይቋቸው ዘንድ የጀመሯቸው፣ እና በግልም ሆነ በሕዝብ በሚጨምር መልኩ የሚናገሩባቸው ጥያቄዎች እነዚህ ነበሩ።

ኸግ እንዲሁም በቤተክርስቲያን ተፈጥሮ፣ ጥሪ እና ፍላጎቶች ላይ ተጨማሪ ማገናዘቦች እንዲደረጉ ለማበረታታት እንደተገፋፉ ተሰምቷቸው ነበር። ለወንጌል የተሰጡ ጉባዔያት ወንጌልን በሚቃወሙ ሰውነት ቤተክርስቲያን ውስጥ መቅረታቸው ትክክል አይደለም። በሌላ መልኩ ደግሞ፣ ወንጌል ተኮር ቤተክርስቲያናት በተመሳሳይ አካል ውስጥ ቢሆኑ ወይም ባይሆኑ አንዳቸው ከሌላቸው ጋር ኅብረታቸውን ለመግለጽ መገታታቸው ልክ አይደለም። የማልፓስ ሮድ ቤተክርስቲያን ከቤተ-እምነቷ ተገንጥላ እንድትወጣ ያሳመኑት ምክንያቶች እነዚህ ነበሩ። የዌልስን ወንጌላዊያን አብያተክርስቲያናት ኅብረት ለመመሥረት፣ እንዲሁም የወንጌል አገልጋዮች እና ቤተክርስቲያናት በዋና ቤተ-እምነታቸው ወይም በሌላ ቦታ መዋደዳቸውን እና መደጋገፋቸውን እንዲቀጥሉ ዋና መሣሪያ ከሆኑ ሰዎች መካከል ኸግ አንዱ እንዲሆኑ ያንቀሳቀሱ እምነቶች እነዚህ ነበሩ። እንዲህ ያሉት ቤተክርስቲያናት እና አገልጋዮች በወንጌል ቤተክርስቲያናት መካከል አንድነትን በማስተዋወቅና በመግለጽ ንቁ ሊሆኑ ይገባቸዋል። ፍዝዘት አይሠራም። ያ የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ታዛዥነት ተፃራሪ ነው።

ቄልስ ውስጥ ባሉት የተለያዩ የወንጌላዊያን ክርስቲያኖች ቡድኖች መካከል የተነሡትን ውጥረቶች ኸግ እንዳላየ አያልፏቸውም ነበር። የጌታ ሕዝቦች አንዳቸው አንዳቸውን እንዲቀበሉ ለማበረታታት የሚቻላቸውን ሁሉ አድርገዋል። *ዮሱንጣጠሉ* ተቋማት እንደሆኑ ራሳቸውን ማየታቸው ስህተት እንደሆነ በሚያምኑበት እምነት ተንቀሳቅሰዋል። እነርሱ አንድ ሕዝቦች ነበሩ። አንዳቸው የሌላቸው አካል ናቸው። አንዳቸው ሌላቸውን ይፈልጋሉ። ከዚህ የተነሣ እርስ በርስ መዋደድ፣ እርስ በርስ መሰባሰብ እና በሚቻለው መንገድ ሁሉ አብረው መሥራት አለባቸው። ይህ ሁሉንም ያበረታታል፣ ደግሞም ለሚመለከተው ዓለም ጥሩ ምስክርነትን ይተዋል። ሊከናወን ይገባዋል! ደግሞም መዘግየት የለበትም!

በብዙነት የሚቆጠሩት የጠፉት እና የቤተክርስቲያን ቅደስናና አንድነት ማጣት፣ በየትኛውም ትውልድ ውስጥ ትልቁ ፍላጎት ጌታ መንፈስ ቅዱስን በሚያፈስበት መልኩ ሕዝቡን መጎብኘቱ እንደሆነ በኸግ አእምሮ ውስጥ በጉልህ ተቀምጦ ነበር። መነቃቃት ያስፈልገናል። አዎን፣ እንዲህ ላለው በረከት በመጠባበቅ ውስጥ ሆነው በመጸለይ ላይ ሳለን ለወንጌል ሥርጭት፣ ወንጌል ተኮር ለሆኑ ቤተክርስቲያናት መገንባት እና የጌታ ሕዝቦችን በየቦታው ለማበረታታት ራሳችንን መስጠት አለብን። ቀኖቹ ተስፋ ቢስ ናቸው። በሚሰበከው ቃል በኩል የጌታ ኃይል ካልታየ፣ ሕዝባችንን ለክርስቶስ ድል የምንነሣው እንዴት ነው? ልንሆን የሚገባንን ዓይነት ሕዝቦች ልንሆን የምንችለው እንዴት ነው? እግዚአብሔር የተለየ በሆነ መልኩ በመካከላችን እንዲሠራ ልንለምን ይገባናል። እርሱን ልንይዘው ይገባናል። እርሱ እስካልባረከን ድረስ እንዲሄድ መፍቀድ የለብንም። ልንጸልይና በጋራ ልንጸልይ ይገባናል። መቼም ተስፋ መቁረጥ የለብንም።

ኸግ ሞርጋን ከእኛ ተለይተዋል፣ ነገር ግን የተዉት ቅርስ ግን ይኖራል። ስለዚህ ቅርስ ምንም ካላወቅን እንዴት አድርገን ልንጠቀምበት እንችላለን? የእኔ ጸሎት ይህች አጭር መታሰቢያ ያንን ቅርስ ወደ ትኩረት መልሳ እንድታመጣ፣ በገዛ ራሳችን ችግር ችላ ያልነው መሆኑን ማሳየት እና ወደ ልባቸው ለሚወስዱት የበረከት በር ክፍት ሆኖ እንደሚቆያቸው ማረጋገጥ ነው።

ከሰማያዊቷ የኢየሩሳሌም ማማዎች
በሚያስሱት የበረሃ ማለፊያ ጎዳናዎች
እንዲሁም የተሰቃዩባቸው እያንዳንዳቸው መከራዎች
ለጸጋው ክብር ዝናቸው መጨመሩ
በዐውሎ ነፋሱ ላይ የጣሉት ምልከታ መኖሩ
በፍርሃት፣ በአሰቃቂው ሞት እና በመቃብሩ
በሰላም አልፈዋቸው አሁን ይፈነጫሉ
ይህም ሁሉ ሊያድናቸው ቻይ በሆነው በኃያሉ

እኛም እንዲሁ፣ ከበረሃው ሃሩር ወጥተን
ወደ መጽናኛዋ ምድር በሸሸት እንገሰግሣለን
የህይወት እንባዎች ወደ ደስታ ይቀየራሉ
የደከሙለትና የታገሉለትም ያርፋሉ
በዚያ መሸሸጊያችንን ለዘላለም እናያለን
ከኃጢአት፣ ከመከራ፣ ከህመም እንወጣለን
ደግሞም ጣፋጭ በሆነው በአዳኙ ፍቅር
ማብቂያ የሌለው ደስታ በውስጣችን ሊቀር

ዴቪድ ቻርለስ፣ 1762-1834፤
በሌዊስ ኤድዋርድስ 1809-87 ተተረጎመ